# የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ
ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

መጀመሪያ እትም 1982

አዘጋጆች

እግቀይሽ መለሰ

ሰሎሞን ወልዱ

መስፍን መሰለ

# ማውጫ


| | ገፅ |
|---|---|
| የጓድ ሚኒስትር መልእክት | 5 |
| የአካዴሚው ጉባኤ ሊቀመንበር መልእክት | 6 |
| ምስጋና | 7 |
| መግቢያ | 9 |
| ሀ — ቤት ምሳሌያዊ ንግግሮች | 21 |
| ለ — » » » | 25 |
| መ — » » » | 38 |
| ረ — » » » | 51 |
| ሰ — » » » | 53 |
| ሸ — » » » | 69 |
| ቀ — » » » | 71 |
| በ — » » » | 75 |
| ተ — » » » | 93 |
| ቸ — » » » | 100 |
| ነ — » » » | 101 |
| አ — » » » | 105 |
| ከ — » » » | 139 |
| ወ — » » » | 158 |
| ዘ — » » » | 168 |
| የ — » » » | 172 |
| ደ — » » » | 225 |
| ጀ — » » » | 233 |
| ገ — » » » | 235 |
| ጠ — » » » | 244 |
| ጨ — » » » | 250 |
| ጸ — » » » | 251 |
| ፀ — » » » | 252 |
| ፈ — » » » | 253 |
| ቃላት መፍቻ | 257 |

ፓርቲያችን ኢሰፓና አብዮታዊው መንግስት ለኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ታሪክ ፣ ባህል ፣ ቋንቋ ፣ ስነፅሁፍና ስነቃል ጥናትና ምርመር አስፈላጊውን መመሪያና ድጋፍ በፓርቲያችን ፕሮግራምና በአስር አመቱ የኢኮኖሚና የሶሻል መሪ እቅድ ውስጥ ተገቢውን ቦታ የሰጡት መሆኑ ይታወቃል ።

ይህንንም ተግባራዊ ከሚያደርጉት ድርጅቶች አንዱ በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ሲሆን ፣ አካዴሚው በህግ የተቋቋመ የቋንቋ ጥናትና ምርምር ማእከል ነው ።

አገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ቋንቋዎችና ስነቃሎች (Oral Literature) ባለቤት በመሆኗ ፣ አካዴሚው በቋንቋና ስነቃል ረገድ የሚያደርገው ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር የኢትዮጵያን ብሄረሰቦች የረጅም ዘመን ታሪክና ባህል ለማጥናት ፣ ለመመዝገብና ምርቱን ከግርዱ በመለየት ለተያያዝነው ሶሻሊስታዊ የባህል ግንባታ እንዲረዳ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ከአብዮታችን መከሰት ወዲህ በተለይም ከ1972 አንስቶ በቋንቋና ስነቃል ጥናትና ምርምር ረገድ በርካታ ጠቃሚ ስራዎችን አከናውኗል ። በዚሁ አኳያ አካዴሚው ካዘጋጃቸው የልዩ ልዩ ብሄረሰቦች ምሳሌያዊ ንግግሮች (Proverbs) መካከል በቅድሚያ ይህን «የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች» መፅሃፍ አሳትሞ ማውጣቱ አካዴሚው የተጣለበትን ከፍተኛ የስራ ሃላፊነት በሚገባ በመወጣት ላይ ለመሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው ።

ስለሆነም የአካዴሚውን የጉባኤ አባላት ፣ የአካዴሚውን ፅ/ቤት የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች በተለይም የዚህን መፅሃፍ አዘጋጆች ከልብ አመሰግናለሁ ።

ግርማ ይልማ

የኢሰፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልና

የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስትር

# የአካዴሚው ጉባኤ ሊቀመንበር መልእክት

የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ስነቃል ማለት ተረት ፣ ምሳሌያዊ ንግግር ፣ እንቆቅልሽ ፣ ህዝባዊ ግጥም ፣ አፈታሪክ . . . ወዘተ ለብዙ ዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አኩሪ የባህል ቅርሳችን መሆኑ ይታወቃል ።

አሮጌው ልማድ በአዲስ እየተተካ ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር የስነቃል ጠቀሜታ እየቀነሰና እየተረሳ ስለሚሄድ ያለፈው ትውልድ ጠቃሚ ቅርስ ከመረሳቱና ከመባከኑ በፊት ባስቸኳይ መመዝገብና ማጥናት ያስፈልጋል ። የየብሄረሰቡ ስነቃል ተሰብስቦ በሳይንሳዊ መንገድ ሲጠናና ሲመረመርም በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች (ታሪክ ፣ ሳይኮሎጂ ፣ አንትሮፖሎጂ . . , ወዘተ) ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከማበርከቱም በላይ በቅርፁ ብሄራዊና በይዘቱ ሶሻሊስታዊ የሆነ አዲስ ስነፅሁፍ እንዲፈጠርና አዲስ ባህል እንዲገነባ ያግዛል ።

በስነቃል ጥናትና ምርምር ረገድ በአገራችን እስካሁን ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው በአንዳንድ ምሁራን የተከናወኑ ስራዎች አሉ ። ሆኖም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ስነቃል ጥናትና ምርምር ገና በጅምር ላይ የሚገኝ ነው ።

ይህ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች መፅሃፍ በስነቃል ስብስብ ረገድ የመጀመሪያው የአካዴሚው የስራ ውጤት ሲሆን በሌሎችም የብሄረሰብ ቋንቋዎች ተመሳሳይ ስራዎች ወደፊት ታትመው ይወጣሉ ።

በዚህ ስራ ላይ የደከሙትን ሁሉ በአካዴሚው ጉባኤና በራሴም ስም ምስጋና አቀርባለሁ ።


አሰፋ ሊበን

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ጉባኤ

ሊቀመንበር

# ም ስ ጋ ና

የዚህ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች (Proverbs) መፅሃፍ አዘጋጆች ለመስከ ስራ በሸዋ፣ በወሎ፣ በጎንደርና በጎጃም በተሰማሩበት ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፓርቲ፣ የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅቶች ሃላፊዎች ላሳዩት የስራ ትብብር ።

መፅሃፉን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት ላደረጉት ለአካዴሚው የስነቃል ጥናትና ምርምር ቡድን ባልደረቦች ለጓድ እማዋይሽ መለሰ፣ ለጓድ ሰሎሞን ወልዱና ለጓድ መስፍን መሰለ ።

የመፅሃፉን ረቂቅ በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት አስተዋፅኦ ላበረከቱ ምሁራን ። በተለይም ለአካዴሚው የስነፅሁፍ አማካሪ ለጓድ በቀለ አበባው ።

መፅሀፉ ጥራት ኖሮት በአጭር ጊዜ ውስጥ ታትሞ እንዲወጣ የአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሃላፊዎችና ሰራተኞች ላሳዩት የስራ ትብብር ።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ስም አብዮታዊ ምስጋና አቀርባለሁ ።

አሰፋ ገብረማርያም ተሰማ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ

ዋና ፀሃፊ

# መ ግ ቢ ያ

የስነቃል ጥናት ጉዳይ ሲነሳ ምንጩና የዘር ግንዱ ስለሆነው ስለ ትውፊት Folklore ሳይንስ ማንሳቱ ተገቢ ነው ። የሰው ልጅ በዚህ አለም መኖር ከጀመረ አንስቶ ትውፊትም ህልውናውን አገኘ ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም ።

ትውፊት እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ ሆኖ ብቅ ያለበትን ጊዜ በውል ለመናገር ባይቻልም በ19ኛው ምእት አመት አጋማሽ ላይ በእንግሊዝና በጀርመን ሀገር የነበሩ ሊቃውንት ለዚህ አቢይ የጥናት መስክ ወጥ ስያሜ ለመስጠት የተለያዩ ሙከራዎች ማድረጋቸውን መዛግብት ይጠቅሳሉ ። ይሁንና Popular Antiquities የሚለውን ጥንታዊ ስያሜ በመተው Folklore በማለት ጥናቱን በትክክል የሚገልጠውን አዲስ ስያሜ የሰጡት እ.ኤ.አ. በ1846 እንግሊዛዊው ዊልያም ጆን ቶምስ ናቸው ።

Folklore ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ኢትዮጵያዊ የሆነ ስያሜ ለመስጠት በተለያዩ ሊቃውንት ሙከራዎች ተደርገው በአሁኑ ወቅት በይበልጥ ተቀባይነት ያገኘው 'ትውፊት' የተሰኘው የግእዝ ቃል ነው ። ትውፊት በግእዝ ቃልነቱ «ስጦታ ፣ ልማድ ፣ ትምህርት ፣ ወግ ፣ ታሪክ ፣ ሃይማኖት ፣ ስርአት ፣ ከጥንት ከአበው ሲወርድ ቃል በቃል ሲነገር የመጣ» የሚል ፍቺ እንዳለው በአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ «መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ» ውስጥ ተገልፆአል ። ይህ እጅግ ሰፊ የሆነ ሀብት ያለው ህዝባዊ ፈጠራ በጥቅሉ ሲታይ ፣

ስነቃል (Oral Literature) ተረት ፣ አፈታሪክ ፣ ምሳሌያዊ ንግግር ፣ እንቆቅልሽ ፤ የተለያዩ አይነት ግጥሞች . . .

ቁሳዊ ባህል (Material Culture) ህብረተሰቡ በልማድ የሚያከናውናቸውን ባህላዊ የቤት አሰራር ፣ የምርት አመራረት ፣ ልብስና አለባበስ ፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና የባህል መድሃኒቶች . . .

ባህላዊ ማህበራዊ ግንኙነት (Social Folk Customs) ሃይማኖታዊ ክንዋኔዎችን ፣ የበአላትን ፣ የሞትንና የመውለድን ፣ የግርዘትን ፣ የሰርግ ስርአትንና አከባበርን . . .

ባህላዊ እንቅስቃሴዎች (Performing Folk Arts) ጭፈራን ፣ ውዝዋዜን ፣ ዘፈንን . . .

በሚይዙ ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል ።

ትውፊት ጥንታዊ እንደመሆኑ የሰው ልጅ ወደ ዘመናዊ ስልጣኔ ከመሸጋገሩ በፊት ያሉትን ቁሳዊና ህሊናዊ ባህሎችን አካቶ ይይዛል ።

ይህ መግቢያ የዚህ ህዝባዊ ቅርስ አካል በሆነውና በዚህ መፅሃፍ የተሰበሰ ቡትን ስራዎች በሚመለከተው በስነቃል (Oral Literature) ላይ ትኩረት ያደ ርጋል ።

ስነቃል ይህን ወጥ ስም ከማግኘቱ በፊት ምሁራን ብዙ አማራጭ ስያሜዎች ሰጥተውት ነበር ። ከነዚህም ውስጥ አፋዊ ስነጽሁፍ ፣ አፋዊ ቅርስ ፣ አፋዊ ድርሰት ፣ ኪነቃል ፣ አፋዊ ኪነተቃል ፣ ቃላዊ ስነፅሁፍ ፣ ስነአንደበት ፣ ትውፊት ፣ አፋዊ ጥበበ ቃል ፣ የመሳሰሉትን ለመጥቀስ ይቻላል ። በእነዚህ የተለያዩ ስያሜዎች የሚጠቀሙ ምሁራን ለየራሳቸው ስያሜ ምክንያት በመስጠት የየግላቸው ስያሜ ተቀባይነት እንዲኖረው ሙከራ ቢያደርጉም በአሁኑ ወቅት በሰፊው የተለመደውና ተቀባይነትም ያገኘው ስነቃል የሚለው ነው ።

በቅድሚያ ስነቃል ምንድነው ? አፈጣጠሩስ እንዴት ነው ? ልዩ ባህሪውስ ምንድነው ? የህልውናውስ መሰረት ? እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማውሳቱ ተገቢ ይመስለናል ።

የሰው ልጅ ታሪክ እጅግ ረጅም ሲሆን ለብዙ ሺህ አመታት ህብረተሰቦች የአኗኗራቸውን ስርአት ፣ ልማዳቸውንና ታሪካቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉ የኖሩት በቃል እንደነበር ታሪክ ያስተምረናል ። ስነቃልም ቀደምት ከሆኑት የሰው ልጅ የመግባቢያ ፣ የመገናኛና የሃሳብ መቀራረቢያ ድልድዮች ውስጥ ዋነኛው እንደመሆኑ ዘመናዊ ስነፅሁፍ ከመዳበሩ በፊትና በይበልጥም በቅ ድመ ካፒታሊስት ስርአቶች ዘመናዊ እውቀት ባልበለፀገበትና ባልዳበረበት ወቅት ፣ የታሪክ ቅርስ በአብዛኛው የተላለፈልን በስነቃል አማካኝነት ነበር ።

ስነቃል ከህብረተሰብ ኑሮ ጋር እጅግ የተሳሰረ ነው ። ሰዎች ሰርግ ሲሰርጉ ፣ ለጦርነት ሲዘምቱ ፣ የተጣላ ሲያስታርቁ ፣ ሙግት ሲሟገቱ ፣ የሞተን ሲቀብሩ ፣ የእለት ኑሯቸውን ለማሸነፍ ሲሰሩ ፣ ሲያድኑ ፣ ከብት ሲጠብቁ ፣ የሚሰማቸውን የደስታ ፣ የሀዘን ፣ የርህራሄና የፍቅር ስሜታቸውን በስነቃል አማካኝነት ይገልፃሉ ።

በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ እንደ አፍሪካ ባሉ አገሮች የስነቃል አይነቶች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ሲሆኑ ፣ በኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ከሚገኙ በርካታ የስነቃል አይነቶች መካከል አፈታሪኮች ፣ ቀልዶች ፣ ተረቶች ፣ እንቆቅልሾች ፣ ምሳ ሌያዊ ንግግሮች ፣ የስራ ፣ የፍቅር ፣ የበአል ፣ የልቅሶ ፣ የልመናና የጀግንነት ግጥሞች ፣ የልጆች ጨዋታዎችና ግጥሞች ፣ ልዩ ልዩ እምነቶች . . . ወዘተ ይገኙባቸዋል ።

ስነቃል የሰው ልጆች ማህበራዊ ቅርስ እንደመሆኑ ፣ ለህልውናው መሰረት ፣ ለእድገቱ ምክንያት ፣ ለስርጭቱ ብቃት እንዲኖረው የሚከተሉት መሰረታዊ ጉዳ ዮች መሟላት ይገባቸዋል ።

ሀ) ምክንያትና አጋጣሚ ፡-

ስነቃል የሚከወንበት ምክንያትና አጋጣሚ እንዲኖር ይገባል ፤ ለም ሳሌ ለፉከራ ግጥሞች መደርደር የጀግንነት ተግባር ፣ ለሰርግ ግጥሞች መነ

ገር ስርዓ እንዲኖር ያስፈልጋል ። ተረት ተረት የሚባለውም ሁኔታው ሲሟላና ምክንያት አስከትሎ ሲገኝ ነው ።

ለ) ከዋኚ ፦

ስነቃል ከዋኚ ያስፈልገዋል ። «እንቆቅልህ» የሚልና «ምንአውቅልህ» የሚሉ ግለሰቦች መኖር የግድ ነው ። ለዘፈን የአውራጅና የተቀባይ መገኘት አጠያያቂ አይደለም ፣ የድምፅ ጥራት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ስነቃልን የሚያወርዱ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንዲኖሩ ያስፈልጋል ።

መ) የወል ትውስታ ፦

ስነቃል በፍቺው ሲታይ ቃል በቃል እየተነገረ የመጣ ከአባቶቻችን የወረስ ነው ቅርስ ነው ። ስለሆነም ከዘመን ዘመን ከልጅ ልጅ እየተላለፈ ሲያስተምረን የሚኖረውና የአባቶቻችንን ወግና የአኗኗር ስርአትም ሊያሳውቀን የሚችለው በሚያስተላልፉት ግለሰቦች የማስታወስ ችሎታ አማካኝነት ነው ። ስለሆነም ጥንታዊው ባህል በስነቃል አማካኝነት ሲተላለፍ የቆየው በየዘመኑ በነበሩ ከዋኚዎች የማስታወስና የስነቃል ማፍለቅ ችሎታ መሆኑ ግልፅ ነው ።

ረ) ተደራስያን ፦

የስነቃል ምንጮች ስነቃሉ የተፈጠረበትና የተነገረለት ህብረተሰብ ፣ ቡድንና ግለሰብ ናቸው ። ለስነቃል ህልውና ማግኘት የተጠቀሱት ክፍሎች መኖር የግድ ነው ። ያለህብረተሰብ ስነቃል ከቶ ሊኖር አይችልም ። በተጨማሪም ስነቃል ሲከወን የአድማጩና የተመልካቹ ትችቶች ፣ አስተያየቶችና ጥቆማዎች የስነቃሉን ጥራትና ምሉእነት ያልቁታል ።

ሰ) ክዋኔ ፦

እንደየስነቃሉ አይነትና ይዘት ስነቃሉ ይወርዳል ። ለምሳሌ ተረት ይነገራል ፣ ዘፈን ይዘፈናል ፣ ዝየራ ይዘየራል ፣ እንደአግባቡም የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ፤ ጭፈራዎችና ውዝዋዜዎች በአንድነት ይከወናሉ ።

ስነቃል ለተለያዩ የጥናት መስኮች ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ግልጋሎት በማበርከት ላይ ይገኛል ። የህብረተሰብ አጥኝዎች ፣ የስነልቦና ተመራማሪዎች ፣ የታሪክ ሊቃውንት . . . ወዘተ. ይጠቀሙበታል ።

ስነቃል በስነፅሁፍ እድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ። የአንዳንድ ታዋቂ ደራስያን ስራዎች መነሻም ስነቃል ሆኖ ተገኝቷል ። ይህንንም የሼክስፒርን ፣ የፑሽኪንን ፣ በአፍሪካም የሶይንካንና የአቸቤን ስራዎች በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል ። በአገራችንም የነከበደ ሚካኤል ስራዎች በስነቃል ላይ የተመሰረቱ ናቸው ። በስነቃል ላይ የተመሰረቱ መፃህፍት ህፃናት የህብረተሰቡን ወግና እሴት ጠንቅቀው እንዲረዱ እገዛ ከማድረጋቸውም በላይ ተነባቢነታቸውና ስሜት የመያዝ ችሎታቸው ከፍተኛ ነው ።

የስነቃል ቅርስ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እየተገናዘበ ለመማሪያ መፃሕፍት ዝግጅት ፣ ለድርሰትና ስነፅሁፍ እድገትና ብልፅግና ፣ ለቲያትርና ሲኒማ መነሻ ጭብጥ ፣ ለስነልሳን ተመራማሪዎች ደግሞ ማመሳከሪያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል ። አሁን በተያያዝነው የመሰረተ ትምህርት ዘመቻ የህብረተሰቡን ፍልስፍናና ስነልቡናዊ አስተሳሰብ ገላጭ የሆነውን የስነቃል ስብስብ በመማሪያ መፃህፍቱ ማካተት ጠቃሚነቱ ከፍተኛ ይሆናል ።

በስነቃል መስክ የሚካተቱ ዘርፎች በርካታ ቢሆኑም የዚህ መፅሀፍ ዋና ትኩረት በአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ብቻ በመሆኑ ሌሎቹን ለመመልከት አይሞክርም ። በዚህም መሰረት ቀጥሎ የምንመለከተው ስለምሳሌያዊ ንግግር ምንነት ፣ አገልግሎት ፣ ቅርፅና ይዘት ይሆናል ።

ምሳሌያዊ ንግግር ለረጅም ዘመናት አንድ ህብረተሰብ የህይወቱን ገጠመኝ የከተበበት በመሆኑ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቱንና አስተሳሰቡን በጉልህ ያንፀባረቀበት መዘክሩ ነው ።

የአማራው ብሄረሰብ ምሳሌያዊ ንግግርን ከተራ የእለት ተእለት ንግግር እስከ ከፍተኛ የሸንጎ ክርክር ሲገለገልበት ለመኖሩ «ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ» የሚለው የአበው አነጋገር ምሳሌያዊ ንግግርና ህብረተሰብ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ስለሚጠቁም በአስረጅነት ሊጠቀስ ይችላል ።

በብሄረሰቡ እምነት መሰረት በምሳሌያዊ ንግግር የተላበሰና የተዋበ ንግግር ማዘውተር ከአዋቂነት በመቆጠሩ ፣ በዚህ የመጠቀም ልምድ ያለው ሰው ከሌላው የላቀ ክብርና ዝና ስለሚኖረው «እገሌ ንግግር አዋቂ ነው» ተብሎ በሸንጎና በአደባባይ ከፍተኛ ስፍራ ይሰጠው ነበር ። ይህም እንደ አሁኑ ዘመናዊ ህግ በስራ ላይ ባልዋለባቸው ዘመናት ህብረተሰቡ የራሱ የሆነ ባህላዊ የፍርድ አሰጣጥ ስነ ስርአት በነበረው ጊዜ ሲያገለግል ቆይቷል ።

ይህ የባህላዊ ፍርድ አሰጣጥ ስነ ስርአት ወይም የእሰጥ አገባ ሙግት በአፍ ብልጠትና በምሳሌያዊ ንግግር የተቋጨ ውርድን በመንዛት ባለጋራን ማንበርከክና መርታትን ስለሚጋብዝ «ከቤት ከዋለ ንብ አደባባይ የዋለ ዝንብ» በማለት ግለሰቦች ተሟግተው ለመርታት ጥረት እንዲያደርጉ ይገፋፋ ነበር ።

በእሰጥ አገባ ሙግት ወቅት አንደኛው ተሟጋች ፦

በላ ! ልበልሃ !
የእጤ ስርአቱን
የአብርሃም እራቱን
አልናገርም ሃሰቱን
ስርክ እውነት እውነቱን ።

በሚሉ ሃረጎች መንደርደሪያነት ይጀምርና አጫጭር ግጥሞችን በምሳሌያዊ ንግግር በማስደገፍ ውርዱን ይነዛል ።

ታገር ከፉ ወጤፈ
ተንጨት ከፉ ጥፊ
ተሀል ከፉ ባቄላ
ተልጅ ከፉ ዲቃላ
ከልብስ ከፉ ነጠላ
ከቤት ከፉ ሰቀላ ።

እያለ ባለጋራው ሳያስበውና ሳይዘጋጅ አፀፋውን እንዲመልስ ይጋብዘዋል ። በተጠየቅ ልጠየቅ ወቅት ለተጠየቀው ጥያቄ ፈጣንና ተገቢ መልስ መመለስ በሙግቱ ከመረታት ስለሚያድን ፤

በላ ! ልበል ሃ!
ምሳር ይሆናል ጥፊ
ችግር ይገፋል ባቄላ
ጥቃት ያወጣል ዲቃላ
ቀን ያሳልፋል ነጠላ
ከደህና ያደርሳል ሰቀላ
ካወቁበት ሁሉም አይጠላ ።

ብሎ የተጠየቀውን ጥያቄ በትና አይበገሬነቱን ያስመሰክራል ። በተጨማሪም ዳኛን ማሞካሸት ፣ ባለጋራን በቃላት አጠቃቀምና በምሳሌያዊ ንግግር መንቀፍና ማዋረድ ፣ የሙግቱ አካል ስለሆነ ሁለቱም ተሟጋቾች አንዱ አንዱን ለመርታትና ተሟጋችነታቸውን ለማስመስከር ይጥራሉ ።

ከዚህም ሌላ ምሳሌያዊ ንግግር በብሄረሰቡ ውስጥ በማህበራዊ ኑሮ ረገድ ሊፈጠሩ የሚችሉ እኩይ ባህርያትን ለመዋጋትና በምትካቸው መልካም ስነምግባር እንዲዳብር ፣ በሰዎች መሃከል ፍቅር ፣ ታማኝነት ፣ ደግነትና ትህትና እንዲሰፍን ትምህርት ሲሰጥበት ኖሯል ።

—ሰው ለወዳጁ ሜጨት ያርዳል ።
—እንኳን ለቤቱ ፣ ይተርፋል ለጎረቤቱ ።
—የተናገሩት ከሚጠፉ ፣ የወለዱት ይጥፉ ።

እነዚህ በሰዎች መሃከል መፈቃቀርና መተዛዘን እንዲኖር የሚያስገነዝቡ ሲሆኑ ፣

—ከስስታም አንድ ያንቀው ፣ አንድ ይወድቀው ።
—አልጠግብ ባይ ፣ ሲተፋ ያድራል ።
—ይሉኝታና ጥቅም ፣ ጎን ለጎን አይሄዱም ።
—አታላይ ለጊዜው ያመልጣል ፣ በሁዋላ ይሰምጣል ።
—እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ ።
—ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል ።

የሚሉትና የመሳሰሉት ደግሞ ስስት ፣ አታላይነት ፣ ግለኝነትና ራስ ወዳድነት በህ ብረተሰቡ ዘንድ አሳፋሪ ምግባሮች መሆናቸውን ያስገነዝባሉ ።

ልጆች በስነ ስርአት ተኮትኩተው ማደግ እንዳለባቸው ወላጆችን የሚመክሩ እንደ ፣

—ለልጅ ከሳቁለት ፣ ለውሻ ከሮጡለት ።
—ልጅን በጡት ፣ እህልን በጥቅምት ።

የመሳሰሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች አሉ ።

የህብረተሰቡን አንድነትና ሰላም ጠብቀው ያኖሩትን አረጋውያንና ባልቴቶች ክብርና እንክብካቤ እንዳይነፈጋቸው የሚያስጠነቅቁ ፤

—የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ ፣ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ ።
—ሽማግሌን ከምክር ከመለየት ፣ ከምግብ መለየት ።
—ሽማግሌ ይገላግላል ፣ የተጠቃ አቤት ይላል ።

የመሳሰሉም አሉ ።

ወጣቱ ትውልድ ለወገኑና ለሃገሩ ተቆርቋሪ እንዲሆን ትምህርት ከሚሰጡት ውስጥ ፣

—ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ፣ ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ ።
—አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ ፣ ማጭድ የሌለው መስከ ሰፋሪ ።

የመሳሰሉትን እናገኛለን ። ይህም አገር ከሌለ ምቾትና ደስታ ሊኖር እንደማይችል ያስተምራል ።

ፍርሃትን በማንኳሰስ ፣ ጉብዝናን ድፍረትን የሚያበረታቱ ፣

—ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም ።
—ፈሪና ንፉግ እያደር ይቆጨዋል ።
—ፈሪ የሚያባርረው ሳይኖር ይሸሻል ።
—በጎዶሎ ቀን የገዛሁት ጋሻ ሳያስገድለኝ አይቀርም አለ ፈሪ ።

የመሳሰሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች በብዛት አሉ ።

የብሄረሰቡ አባላት ከበሽታ እንዲጠነቀቁ ፣ በበሽታም ከተያዙ በጊዜው አስፈላጊውን እርዳታ እንዲጠይቁ ፣

—ታሞ ከመማቀቅ ፣ አስቀድሞ መጠንቀቅ ።
—በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም ።
—ሃኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል ።
—በበሽታው የተጎዳ ፣ በጥንስሱ የተቀዳ ።

በማለት ያስገነዝባሉ ።

ሰው ኑሮውን ለማሸነፍ እላይ እታች ሲል እራሱን ከስህተት ላይ እንዳይጥል ፣ ለስህተቱም አፋጣኝ መፍትሄ መፈለግ እንዳለበት በማስጠንቀቅ ስራን በመስራት ራሱንና ቤተሰቡን ከችግር እንዲያወጣ ትምህርት የሚሰጡ አሉ ።

—በሰኔ ካልዘሩ ፣ በጥቅምት ካለቀሙ ፣ እህል አይገኝም ከድንበር ቢቆሙ ።
—ካልሰሩ ፣ አይገኝም መከሩ ።
—ከመቸገር ፣ ሰርቶ ማደር ።
—ሳይሰሩ ማግኘት ፣ ሳይፀድቁ ገነት ።
—እለፈ በዋዛ ፣ ልብን ሳልገዛ ።
—በሚያዝያ ጎመን የዘራ ፣ ከረምቱን ሁሉ በላ ።

እንዲሁም በጊዜ መጠቀምን ፣ ካልሰሩ መዋረድ ፣ መናቅ እንደሚኖርና በስራ ታታሪ ካልሆኑ ክብር ፣ ዝናና ሞገስ እንደማይገኝ የሚጠቁሙ እንደ ፣

—ሰነፍ ገበሬ በመስከረም ያርማል ።
—በድህነት ላይ ስንፍና ፣ በቂጥኝ ላይ ቁምጥና ።
—ሰነፍ ሰው ያሰንፋል ።
—ሰነፍ ከመውለድ ፣ ይሻላል ማስወረድ ።

የመሳሰሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንፍና ከደዌ ተለይቶ የማይታይ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ፣ ስለሆነ በሰዎች ኑሮ ላይ የሚያስከትለውም ችግር አስከፊ በመሆኑ ይህን ለእድገትና ለብልፅግና እንቅፋት የሆነን ምግባር ይዋጋሉ ።

ህብረተሰቡ እነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች እየታገዘ በመሃከሉ ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ያደርጋል ።

የገዥው መደብ አባላት ምሳሌያዊ ንግግሮችን የግል ጥቅማቸው ማስጠበቂያ ፣ የመበዝበዣና የመጨቆኛ መሳሪያ አድርገው ተጠቅመውባቸዋል ። የራሳቸውን ክብርና ዝና ለማስጠበቅ ሲሉ የስርአቱ ቁንጮ የሆነውን ንጉስ ሃያልነት ፣ ገናናነት ፣ ለጋስነትና መሃሪነት ለማረጋገጥ በርከት ያሉ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመፍጠርና በህዝቡ አእምሮ ሰርፀው እንዲገቡ ያደርጉ ነበር ።

ለምሳሌ ፣

—ንጉስ መንቀፍ ፣ ነብር ማቀፍ ።
—ንጉስን ያገለገለ ፣ ከትልቅ ሃብት የታደለ ።
—ንጉስ አይከሰስ ፣ ሰማይ አይታረስ ።
—ንጉስ የቆረጠው እጅ ፣ ካለ ይቆጠራል ።
—ንጉስ የገደለው ፣ ቀባሪ የሌለው ።

በማለት የንጉስን ፈላጭ ቆራጭነት ለማሳየት ይሞክራሉ ።

ከንጉስ በታች አዛዥ ፣ ገዥ ፣ አለቃ ወዘተ የሚባሉ የፊውዳሉ ስርአት አራማጆች ስለ ነበሩ እነሱም እንደስልጣን ተዋረዳቸው እንዲያስገብሩና እንዲበዘብዙ ስርአቱ ሙሉ ስልጣን ስላስጨበጣቸው አምባገነንነታቸውን የሚዘክሩ ምሳሌዎችን በመፍጠር ሲጠቀሙ ቆይተዋል ።

—ድሃና ሹም ተሟግቶ ፣ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ፣ የማይሆን ነው ከቶ ።
—ከሹም አይጣሉም ፣ ከግንብ አይታገሉም ።
—ተልባ ቢንጫጫ ፣ ባንድ ሙቀጫ ።
በማለት በእነርሱ ስር የሚተዳደረውን ህዝብ አሜን ብሎ እንዲገዛ በመሳሪያነት ተገልግለውበታል ።

ድርብ ጭቆናን የሚያንፀባርቁ ፣ ሴቶች በማጀት ብቻ ተከልለው እንዲኖሩ ተፅእኖ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ ንግግሮችንም ፈጥረዋል ።

—አህያና ሴት ፣ ሲረግጧት አይከፋት ።
—ሴት በማጀት ፣ ወንድ በችሎት ።
—ሴትና ዶሮ ዱር ሲሄዱ ፣ ቤታቸውን ይከዱ ።
—ሴት ያመነ ፣ ጉም የዘገነ ።
—ወንድ ባለ በለት ፣ ሴት ባለች ባመት ።

የመሳሰሉት አባባሎች ወንዱ አጋሩ የሆነችውን ሴት በጥርጣሬ አይን እንዲያያትና እንዲንቃት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል ።

ለእደ ጥበብ ሙያ እንቅፋት የሚሆኑ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመጠቀም ብረታ ብረት አቅላጩን «ቀጥቃጭ» ፣ በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ምርት የተሰማራውን «ፋቂ» . . . ወዘተ በማለት ህብረተሰቡ በዚህ ሙያ የተሰማሩትን ግለሰቦች እንዲንቃቸውና እንዲያጥላላቸው ተፅእኖ አድርገዋል ። ይህንንም ፣

—ለፋቂ ግማት ፣ ለአይጥ ሞት ፣ ብርጉድ አይገኝለት ።
—ከመሆን ፋቂ ፣ ይሻላል ነጣቂ ።
ከሚሉት ለመረዳት ይቻላል ።

የገዥው መደብ አባላት በተሰጣቸው የስራ ሃላፊነት ምክንያት ብዝበዛንና ጉቦን ህጋዊ ለማድረግ ጥረዋል ። በዚህም ለዳኛ ፣ ለሹምና ለአለቃ እጅ መንሻ ጉቦ መስጠት ከመጉላላት እንደሚያድንና ትክክለኛ ነገር መሆኑንም ህዝቡ አምኖ እንዲቀበል አድርገዋል ።

—ተሹሞ የማይበላ ፣ ተጥዶ የማይፈላ ።
—ሲሾም ያልበላ ፣ ሲሻር ይቆጨዋል ።
—ያማከሩት ዳኛ ያግዛል ፣ የመተሩበት እጅ ይወዛል ።
የመሳሰሉትን በመሰንዘር ሰፊው ህዝብ ሞራሉ ላሽቆ በኑሮው ተስፋ እንዲቆርጥና የተባበረ ክንዱን እንዳያነሳባቸው ሲያከላክሉት ኖረዋል ። ሆኖም ሰፊው ህዝብ በሚያገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የራሱን ምሳሌያዊ ንግግሮች በመጠቀም ቅሬታውንና ብሶቱን ከመግለፁም በላይ ፣

—ድር ቢያብር ፣ አንበሳ ያስር ።
—አገር ቢያብር ፣ ለንጉስ ያስቸግር ።
የመሳሰሉትን በመጠቀም አሜን ብሎ እንደማይገዛ ገልፆአል ። ይህንንም በቀጥታ

በማለቱ ተግሳፅና ቅጣት እንዳይደርስበት በሚሰጋበት ጊዜ ደግሞ እንስሳቱን እን ደሰው በማናገር በገዥው መደብ ላይ የነበረውን ምሬት በሚከተለው መልክ ይገ ልፅ ነበር ፡፡

—ትላንትና ልጇን ዛሬ እናቱን ፤ ምን ይበጃል ዘንድሮ ፤ አለ አውራ ዶሮ
—በካብ ላይ ብሰራ እባቡ መከራ ፤ በዛፍ ላይ ብሰራ አሞራው መከራ ፤
የት ወጥቼ የት አድር ብዬ አለች ወፍ ፡፡

ህብረተሰቡ ምሳያሌዊ ንግግሮችን በመጠቀም አመለካከቱንና አስተሳሰቡን አጠርና ቀልጠፍ ባለ አገላለፅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፍ የቆየ ሲሆን ዛሬም ጠቀሜታቸው ከፍተኛ በመሆኑ አገልግሎታቸው በቀላሉ የሚታይ አይ ደለም ፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች ቀደም ሲል በባህላዊ ትምህርት የሰጡት ግልጋሎት ሳይ ረሳ በዘመናዊ ትምህርት ውስጥ ተካተው ተማሪው የቋንቋውን ውስጣዊ ባህርይ እንዲገነዘብ ፤ ምሳሌዎቹ የያዙትን ምስጢር አመዛዝኖና አገናዝቦ እንዲመራመር ፤ የቃላት ፍቺ ለመስጠት በሚያደርገው የሃሳብ ማውጣትና ማውረድ አእምሮውን እንዲያዳብር እገዛ ያደርጉለታል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወጣቱ ትውልድ ከህብረተሰቡ መንፈሳዊና ቁሳዊ ባህል ጋር ራሱን እንዲያዋህድና የቀደምት አባቶቹን ስነ ልቦና ፤ ህግጋት ፤ ታሪክና እሴት ጠንቅቆ እንዲማር ያስችሉታል ፡፡ ይህን ለማስጨበጥ ግን ህብረተሰቡ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ግልፅና ቀጥታ በሆነ አነጋገር አይጠቀምም ፡፡ ዘይቤያዊ ንግግሮችን ያላብሳቸዋል ፡፡ ይህም የታመቀ የውስጥ ስሜቱንና አይታ ውን በምስጢር ለመግለፅ እንዲያመቸው ነው ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከ ተሉት ናቸው ፡፡

ሀ) ተነፃፃሪ፦

ሁለት ተቃራኒ ሃረጎችን በማነፃፀር ወይም በማወዳደር ይገለፃል ፡፡
— የጨዋ ልጅ ሲፋታ ፤ ይጋባ ይመስላል ፡፡
— የጠፋ ፤ ከለማ እኩል ነው ፡፡

ለ) ግነት ፦

ጉዳዩን ከሚገባው በላይ በማጋነን ይበልጥ ስእላዊ ሆኖ ግልፅነት እንዲያገኝ የሚረዳ ነው ፡፡
—ማሩን አምርሮ ፤ ወተቱን አጥቁሮ ፡፡
—ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት ፤ እብቁ አይኔ ገባ አለ ፡፡

መ) ሰውኛ ፦

እንስሳትን በማናገር ወይም እንደሚሰሙና እንደሚናገሩ አድርጎ በመቁጠር «እነሱ አሉ» በማለት ገለልተኛ ሆኖ ብሶትን ፤ ቅሬታንና ትዝብትን ለመግ ለፅ የሚቻልበት ዘዴ ደግሞ የሚከተሉትን ይመስላል ፡፡

—ሺ ቢታለብ ፣ ያው በገሌ አለች ድመት ።
—እኔ ከሞትኩ ፣ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ ።

ሰ) ምፀት ፦

ተቃራኒ ሁኔታዎችን በመጠቀም በአሽሙር መልእክት የሚተላለፍበትና የታሰበው መልእክት ሰወር ባለ መንገድ የሚነገርበት ነው ።

—ሲሉ ሰምታ ፣ ዶሮ ሞተች ከጢስ ገብታ ።
—ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች ።
—ሆድ ሲያውቅ ፣ ዶሮ ማታ ።
የሚሉትን ለመጥቀስ ይቻላል ።

የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች መልእክት ለማስተላለፍ ከዚህ የሚከተሉትን ስልቶችንም በተጨማሪ ይጠቀማሉ ።

ሀ) ጥያቄና መልስ ፦

በጥያቄና መልስ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ራሳቸው ጠይቀው ለጉዳዩ ራሳቸው መልስ የሚሰጡ ናቸው ።
—በቅሎ አባትሽ ማነው ? ቢሏት ፣ ፈረስ አጎቴ ነው አለች ።
—ወጥን ማን ያውቃል ? ቀለዋጭ ።

ለ) ሳቢያና ውጤት ፦

በሳቢያና ውጤት ስልት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጥሩም ሆነ መጥፎ ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት የሚጠቁሙ ናቸው ።

—ካላረፉ ፣ መከራ ነው ትርፉ ።
—እውር እውርን ቢከተል ፣ ተያይዞ ገደል ።

መ) አማራጭ ፦

ሁለት ተፃራሪ ነገሮችን በማወዳደር የሚነገር ነው ።
—ከመልካም ጠላ ፣ ከፉ ጠጅ ።
—ከመልካም ወዳጅ ፣ ከፉ ልጅ ።

ሰ) ማወዳደር ፦

ሁለት የማይገናኙ ነገሮችን በማወዳደር እኩል ውጤት እንዳላቸው ተደርጎ የሚቀርብበት ነው ።

—ንብ ባውራው ፣ ገበሬ ባዝመራው ።
—መሬት ላራሹ ፣ ጥይት ለተኳሹ ።
በነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች መሰረት ንብና ገበሬ ፣ መሬትና ጥይት እኩል ውጤት እንዳላቸው ተደርገው ቀርበዋል ።

ከላይ በአጭሩ የቀረቡት ምሳሌያዊ ንግግሮች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚጫወቱት ሚናና የሚያስተላልፉት መልእክት ምን እንደሚመስልና እነዚህንም መልእክቶች ለማስተላለፍ ምን ምን አይነት ዘዴዎች እንዳሉ በጥቂቱ ለማሳየት ነው ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ የስነቃል ጥናትና ምርምር ቡድን በአሁኑ ወቅት በአማርኛ ፣ ትግርኛ ፣ ኦሮምኛ ፣ ወላይትኛ ፣ ሃዲይኛ ፣ ሲዳምኛ ፣ ከምባትኛ ፣ ጌዴኦኛና ጉራጊኛ ቋንቋዎች የሚነገሩ ስነቃሎችን በመሰብሰብና በማጥናት ላይ ይገኛል ። ስለሆነም የመጀመሪያ የስራ ውጤቱ የሆነውን ይህን የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ስብስብ መፅሃፍ አሳትሞ ለህዝብ አቅርቧል ።

በዚህ መፅሃፍ ውስጥ የሚገኙት ምሳሌያዊ ንግግሮች የተሰበሰቡት በመስክ ስራ አማርኛ በአፍ መፍቻነት በሚነገርባቸው ቦታዎች በጎንደር ፣ በጎጃም ፣ በሸዋና በወሎ እንዲሁም ከመፃህፍትና ከልዩ ልዩ ፅሁፎች ነው ። ይህ የአሰባሰብ ዘዴ ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ምሳሌያዊ ንግግሮች በብዛት እንዲሰበሰቡ አስችሏል ። ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎችና ቦታዎች መሰብሰቡም ፤ በስብስቡ ላይ የሚታየውን አንዳንድ የአነጋገር ልዩነት እንዲኖር ምክንያት ሆኗል ። በአንድ የህብረተሰብ ክፍልና አካባቢ የተነገረው ምሳሌያዊ ንግግር በሌላ አካባቢ ሲነገር የቃልና የሃረግ ለውጥ ተደርጎበት ይነገራል ። እንዲሁም በአንዱ ቦታ መነሻ ሃረግ የነበረው በሌላው መድረሻ ሃረግ ሆኖ ይቀርባል ። ስለሆነም ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ሲተላለፍ የቆየው አባባል ሁሉ በቅርስነቱ ተጠብቆ እንዲኖር ሁሉንም መመዝገብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ።

ከዚህ በፊት አንዳንድ ግለሰቦች (ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወ/መስቀል ፣ ሃጂ ዩሱፍ አብዱራህማን ፣ ሊቀ መዘምራን ሞገስ እቁባጊዮርጊስ . . . ወዘተ) የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመፅሃፍ መልክ አሳትመው አውጥተዋል ።

ይህ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች መፅሀፍ ከዚህ በፊት ከታተሙት የሚለየው በብዛትና በአቀራረቡ ቴክኒክ ነው ። ከዚህ በፊት እንደተገለፀው ምሳሌያዊ ንግግሮች የአንድ ደራሲ ወይም ደራሲዎች የፈጠራ ስራ ሳይሆኑ የህዝብ ቅርስ በመሆናቸው በልዩ ልዩ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ተሰብስበው በመፅሀፍ መልክ ሲወጡ በአቀራረብ ቴክኒክ ፣ በአመራረጥ ስልት ፤ በአይነትና በመጠን ይለያዩ እንጂ ምንጫቸው አንድ በመሆኑ በአመዛኙ ተመሳሳይነት አላቸው ። ይህ ባህርይ ደግሞ የምሳሌያዊ ንግግሮችና የሌሎቹም የስነቃል ዘርፎች (እንቆቅልሽ ፣ ተረት ፣ ህዝባዊ ግጥምና ዘፈን . . . ወዘተ) ብቻ ሳይሆን ምንጩ የህዝብ ቅርስ የሆነው የቋንቋ በተለይም የመዝገበ ቃላትና የሰዋስው ጠባይ ነው ። ከዚህም የተነሳ በአንድ ቋንቋ በተለይም በሰሙ አገሮች ቋንቋዎች (እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ መስኮብኛ—ሩሲያኛ . . . ወዘተ) በተለያየ ወቅትና ምክንያት በርካታ የምሳሌያዊ ንግግሮች ፣ የመዝገበ ቃላትና የሰዋስው መፃህፍት በልዩ ልዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ተፅፈው ይገኛሉ ።

በአማርኛ ስነፅሁፍ ውስጥ አንድ ድምፅ በተለያዩ ሆሄያት (ፊደላት) በመወከል የሚፈጠረውን የአፃፃፍ ችግር ለማስወገድ ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ጉባኤ ሰፊ ጥናትና ምርምር አድርጎ በ1973 ካሳለፈው ውሳኔ መካከል የሞክሼ

ሆሄያትና የፍንፅቅ ፊደላት ቅንሳ ይገኝበታል ። ስለሆነም ይህ መፅሃፍ ሲዘጋጅ ከሞክሼ ሆሄያት መካከል «ሀ—ሰ—አ—ፀ» ሆሄያትን ፣ ከፍንፅቅ ፊደላት መካከል የራብእን ሆሄያትና እንዲሁም ዘመን አመጣሽ ፊደላትን «ኗ ሟ ሯ ቧ . . . ወዘተ» በመጠቀም ነው ።

በዚህ መፅሃፍ 5142 ምሳሌያዊ ንግግሮች በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ተመ ዝግበው ሲገኙ ፣ በመፅሀፉ መጨረሻ ላይ አንዳንድ የቦታ ፣ የቤት ቁሳቁሶችና የእ ርሻ መሳሪያዎች ፣ መጠሪያ ስሞችና ሌሎችም ቃሎች እንደ አገባባቸው ፍቺ ተሰጥቶአቸው አባሪ ሆነው ቀርበዋል ።

አዘጋጆች

— እማዋይሽ መለሰ

— ሰሎሞን ወልዱ

— መስፍን መሰለ

## - ሀ -

ሀ ሳይሉ ጥፈት ፣ ውል ሳይዙ ሙግት ።

ሀ ባሉ ፣ ተዝካር በሉ ።

ሀሜተኛ ያፍራል ፣ ሀሰተኛ ይረታል ።

ሀምሌ ቢያባራ ቢጋ ይመስላል ።

ሀሰተኛ በቃሉ ፣ ስደተኛ በቅሉ ።

ሀሰተኛ ፣ ብርቱ ወንጀለኛ ።

ሀሰተኛን ሲረቱ ፣ በወንድም በእህቱ ።

ሀሰት ስለበዛ ፣ እውነት ሆነ ዋዛ ።

ሀሰት ቢናገሩ ፣ ውቃቢ ይርቃል ።

ሀሰት ነገር ክፉ ፣ ገሀነም እሳት ትርፉ ።

ሀሳቡ ጥልቅ ፣ ነገሩ ጥብቅ ።

ሀሳብ ከውለታ አይቆጠርም ።

ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ፣ ድሀ ለድሀ ይለቃቀሱ ።

ሀብታም ሲወድቅ ከሰገነት ፣ ድሀ ሲወድቅ ከመሬት ።

ሀብታም በመመፅወቱ ፣ ድሀ በፀሎቱ ።

ሀብታም በከብቱ ፣ ድሀ በጉልበቱ ።

ሀብታም በወርቁ ፣ ድሀ በጨርቁ ።

ሀብታም በገንዘቡ ፣ ድሀ በጥበቡ ፣ እርስ በርስ ይቃረቡ ።

ሀብታም በገንዘቡ ይኮራል ፤ ድሀ በጥበቡ ይከብራል ።

ሀብታም ነው መባል ያኮራል ፤ ድሀ ነው መባል ያሳፍራል ።

ሀብታም እንደሚበላለት ፥ ድሀ እንደሚከናወንለት ።

ሀብታም ያለ ድሀ አይኮራም ፤ ድሀ ያለ ሀብታም አይበላም ።

ሀብታም ገንዘቡን ያስባል ፤ ድሀ ቀኑን ይቆጥራል ።

ሀብትና እውቀት ፥ አይገኝም ባንድነት ።

ሀኪም ሲበዛ በሽተኛው ይሞታል ።

ሀኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል ።

ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ፥ ከቤትሽ አልወጣ ።

ሀይለኛ ውሃ አሻቅቦ ይፈሳል ።

ሁለተኛ ግፌ ፥ ጫንቃዬን ተገርፌ ፥ ልብሴን መገፈፌ ።

ሁለተኛ ጥፋት ፥ ቆሞ ማንቀላፋት ።

ሁለተኛ ጥፋት ፥ ከገበያ ማንቀላፋት ።

ሁለቱን የተመኘ ፥ አንዱንም አላገኘ ።

ሁለት ሆነው የተናገሩት ፥ በመሬት የቀበሩት ።

ሁለት ቁና ሰጥቼ ፥ አንድ ጥንቅል ።

ሁለት ነዶ ይዞ ፥ ወደ ክምር ጠጋ ።

ሁለት አይወዱ ፥ ከመነኮሱ አይወልዱ ።

ሁለት አገር አራሽ ፥ ለባልንጀራው አውራሽ ።

ሁለት እግር አለኝ ብሎ ፥ ከሁለት ዛፍ አይወጡም ።

ሁለት ወፎች ባይናከሱ ፥ ይናቀሱ ።

ሁለት የወደደ ፥ አንዱን ሳያገኝ ሄደ ።

ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም ።

ሁለት ጊዜ ተናግረህ ከፋህ ፥ ሁለት ጊዜ በላህ ተፋህ ።

ሁለት ጊዜ ነው የዶሮ ልደት ፥ አንዱ በእንቁላል አንዱ በሚጨፉት ።

ሁለት ጊዜ ይፈርዱ ፥ ጉድ ይወልዱ ።

ሁለት ጥፉ ፥ ካገር ይጥፉ ።

ሁሉ ሄዶ ፥ ተበተነ እህና እኔ ቀረኝ አለ እያዘነ ።

ሁሉ በጁ ፥ ሁሉ በደጁ ።

ሁሉ ቢናገር ፥ ማን ይሰማል ።

ሁሉ አማረኝን ፥ ገበያ አታውጣት ።

ሁሉ አረሰ ፥ ማን ይሸምት ።

ሁሉ ያልፋል ፥ እስኪያልፍ ያለፋል ።

ሁሉ ያልፋል ፥ እውነት ብቻ ይተርፋል ።

ሁሉም ሰው መምሰሉ ፥ ባይታይ አመሉ ።

ሁሉም አካል ነው ፥ ግን እንደ አይን አይሆንም ።

ሁሉን ቢናገሩት ፥ ሆድ ባዶ ይቀራል ።

ሁልጊዜ ከመደንገጥ ፥ አንድ ጊዜ መሸጥ ።

ሂዳ ጉበት የነቧት ፥ ታናሽ ታላቅ ስደዱልኝ አለች ።

ሂድ አትበለው ፥ እንዲሄድ አድርገው ።

ሂድ ካገር ፥ ኑር ካገር ።

ሃይለኛ ዱቄት ከነፋስ ይጣላል ።

ሃይማኖት ከግብር ፥ ፀሎት ከፍቅር ።

ሃጢአት በንስሃ ፥ በደል በካሳ ።

ህመሙ ቀርቶ ሞቱን በተወኝ ።

ህመሙን የሸሸገ መድሃኒት የለውም ።

ሀያዋን ለነገስታት ፥ ሙታን ለካህናት ይገብራሉ ።

ሆደ ሰፊ ፥ ነገር አሳላፊ ።

ሆደ ሰፊ ፥ ይሻላል ካኩራፊ ።

ሆዱ ናረት ፥ ሙያው ከጅረት ።

ሆዱ ፈሪ እግሩ ዳተኛ ፥ አዳም ሲዋጋ እርሱ ይተኛ ።

ሆዱን ያለ ፥ ሆዱን ተወጋ ።

ሆዳም ቢሸከም ፥ የበላ ይመስለዋል ።

ሆዳም ቢፈተፍት ፥ የጠገበ ይመስለዋል ።

ሆዳም ፥ ፍቅር አያውቅም ።

ሆዶ በጀርባዬ ቢሆን ፥ ገፍቶ ገደል በጣለኝ ።

ሆዶ ፥ ኑር በዘዶ ።

ሆዶ ፥ አታጣላኝ ከዘመዶ ።

ሆድ ሆዱን የምትል ወፍ አለች ፥ ምናለች ?

ሆድ ሆዴን የሚለውን ጌታ ያየዋል ፤ አይኔ አይኔ የሚለውን ሰው ያየዋል ።

ሆድ ፥ ለማታ በልቶ ለጧት ።

ሆድ ለባሰው ፥ ማጭድ አታውሰው ።

ሆድ ሲሞላ ፥ ራስ ባዶ ይቀራል ።

ሆድ ሲያር ፥ ጥርስ ይስቃል ።

ሆድ ሲያውቅ ፥ ዶሮ ማታ ።

ሆድ ባዶ ይጠላል ።

ሆድ እንዳሳዩት ነው ።

ሆድ ከሁዳድ ይሰፋል ።

ሆድ ወዶ ፣ አፍ ክዶ ፣ ክፉ ለምዶ ።

ሆድ የኔ ነው ሲሉት ፣ ቁርጠት ሆኖ ይገድላል ።

ሆድ ያበላውን ያመሰግናል ።

ሆድ ያባውን ፣ ብቅል ያወጣዋል ።

ሆድ ዘመድ ሳይወድ ፣ አፍ እህል ሳይለምድ ።

ሆድህና ልጅህ አይጥሉህ ።

ሆድህን ጎመን ሙላው ፣ ጀርባህን ለጠላት አታሳይ ።

ሆድና ግንባር አይሸሽጉም ።

ሆድን በጎመን ቢደልሉት ፣ ይለግማል ጉልበት ።

## - ለ -

ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ ።

ለሃብት መትጋት ሰውነትን ያከሳል ፤ ገንዘብን ማሰብ እንቅልፍ ይነሳል ።

ለሃጥአን የወረደ ፣ ለፃድቃን ይተርፋል ።

ለሂያጅ ፣ የለውም ወዳጅ ።

ለሆዳም በሬ ገለባ ያዝለታል ።

ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል ።

ለሆዴ ጠግቤ ፣ በልብሴ አንግቤ ።

ለሆድ ቁርጠት ብላበት ፤ ለራስ ምታት ጨህበት ።

ለላሙ መንጃ ፣ ለሽማው መቅደጃ ።

ለላሙ መንጃ ፣ ለሽማው መከንጃ ።

ለላም ቀንዷ አይከብዳትም ።

ለላም ከጥጃዋና ካቢላሟ ማን ይቀርባታል ።

ለላም ፣ የሳር ለምለም ።

ለላም ጥጃዋ ፣ ለአህያ ውርንጭላዋ ።

ለሌለው ፣ ምን ትለው ።

ለልጅ ሲሉ ይበሉ ፣ ለወገን ሲሉ ይጠሉ ።

ለልጅ አይስቁለትም ፣ ለውሻ አይሮጡለትም ።

ለልጅ ጥርስህን ፣ ለዝንብ ቁስልህን አታሳይ ።

ለልጅ ጨዋታ ፣ ለባለጌ ቧልታ ።

ለመሄድና ለመላወስ ፣ አዛኸ ራስ ።

ለመሆን ሳይሆን ፣ እንዴት ይሆናል ቢሆን ።

ለመሪህ አሳ ምሰል ።

ለመስራት የሚያፍር ፣ መብላት አይደፍርም ።

ለመስጠት አለመቸኮል ፣ ከሰጡም ወዲያ አለመፀፀት ።

ለመታማት ፣ መፍራት ።

ለመከራ ያለው መነኩሴ ፣ ዳዊቱን ሸጦ አህያ ይገዛል ።

ለሙት ፣ የለው መብት ።

ለሚመለከት ለሚያየው ፣ ሞት ቅርብ ነው ።

ለሚስት ያጎርሷል ፣ ለተመታ ይከሷል ።

ለማን አለው ፣ ፈጣሪ አለው ፤ ጠጅ ለሌለው ፣ ውሃ አለው ።

ለማን ይፈርዱ ? ለወደዱ ፤ አይደለም ለወደዱ ፣ ለወለዱ ።

ለማየት የፈለገ ፣ አይኑን ይገልጣል ።

ለማያውቅ ፎገራ ዱሩ ነው ።

ለማያውቅሽ ታጠኝ ።

ለማይሞት መድሃኒት አለው ።

ለማይሰጥ ሰው ፣ ስጡኝ ማለትን ማን አስተማረው ?

ለምሽት መብራት ፣ ለመከራ ጊዜ ብልሃት ።

ለምን ተክገፎ ፣ አምላክን ይገፎ ።

ለምን ያለው ስልቻውን ፣ ጫን ያለው ኮርቻውን ።

ለምን ጊዜው ነቀዝሽ ።

ለምኖ ለማኝ ፣ ቀቤን ቀማኝ ።

ለሞኝ ሰኔ በጋው ፣ መስከረም ክረምቱ ።

ለሞኝ ንገረው ፤ ምን ይሰማ ብዬ ? ለብልህ ንገረው ፤ ምን ይሳተው ብዬ ?

ለሞኝ ከሳቁለት ፣ ለቅዘን ከሮጡለት ።

ለሞኝ ከሳቁለት ፣ ለውሻ ከሮጡለት ።

ለሞኝ ጉድጓድ አያሳዩትም ፣ ቤት ነው ብሎ ይገባበታል ።

ለሞፈር ቀራጭ ፣ እርፍ አይታየውም በግላጭ ።

ለራሱ አያውቅ ነዳይ ፣ ቅቤ ለመነ ላዋይ ።

ለራሱ ጥላ ፣ ለእግሩ ከለላ ።

ለራስ ምታት ጨህበት ፣ ለሆድ ቁርጠት ብላበት ።

ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ።

ለራበው ሰው ቆሎ ፣ ለቁልቁለት በቅሎ ።

ለራት የማይተርፍ ዳረጎት ።

ለርስት ሴቶች ስንኳ ይሞቱበታል ።

ለስለባ የመጣ ፣ ልብስ ቢጥሉለት አይመለስም ።

ለሰበበኛ ቂጥ ፥ መረቅ አታብዛበት ።

ለሰባቂ ጆሮህን አትስጠው ።

ለሰው ልጅ ሲያበሉ ፥ ለውሻ ልጅ ያብሉ ።

ለሰው ሞት አነሰው ።

ለሰው ቢናገሩ መልሶ ለሰው ፥ ሜር ሜር አድርጌ አፈር ላልብሰው ።

ለሰው ብሎ መሞት ፥ እምላክነት ያሻል ።

ለሰው ብሎ ሲያማ ፥ ለኔ ብለህ ስማ ።

ለሰው ከበሬታው ሰው ፥ ለወጥ ማጣፈጫው ጨው ።

ለሳት ውሃ ፤ ለፀጉር ቡሃ ።

ለሴት ልጅ እስከ አርባ ቀን ሞቷን ፥ ከዚያ ወዲያ ሀብቷን ።

ለሴት ምክር አይገባትም ።

ለሴት ጠላ ፥ ለፈረስ ቆላ ።

ለስሱ ፍትፍት አሳይቶ እበት ያጎርሷል ።

ለስሟ መጠሪየ ቁና ሰፋች ።

ለሽማኔ ማገጃ ፥ ስለት ማረጃ ።

ለሹመት ካልመከሩለት ፥ ለጥርስ ካልከደኑለት ።

ለሺ ፍልጥ ፥ ማሰሪያው ልጥ ።

ለቀላል ምስጢር መንገር ፥ በቀዳዳ ጤፍ መቋጠር ።

ለቀባሪው አረዱት ።

ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው ፤ ቀንዱ ያከልክለው ።

ለቁንጫ ለምዕ ያወጣል ።

ለቂጡ ጨርቅ የለው ፥ ቆንጆ ያባብላል ።

ለቅልብልብ አማት ፣ ሲሶ በትር አላት ።

ለቅሶ ሳለ ከቤት ፣ ለቅሶ ይሄዳል ከጎረቤት ።

ለቅዘን እግር አንስተውለት ።

ለበራ ወለባ ፣ ለውሻ ገለባ ።

ለበጋ ጥጃ ውስ አነሰው ወይ ?

ለበግ ደጋ ፣ ለምኞት አልጋ ።

ለባብ እግር የለው ፣ ለሞኝ መላ የለው ።

ለቤት ሳማ ፣ ለውጭ ቄጤማ ።

ለቤት ሳንቃ ፣ ለሰው አለቃ ።

ለቤት ባላ ፣ ለችግር ነጠላ ።

ለብልህ አይነግሩ ፣ ለድመት አያበሩ ።

ለብልህ አይነግሩ ፣ ላንበሳ አይመትሩ ።

ለብዙ ፀሎት ፣ ማሰሪያው አቡነ ዘበሰማያት ።

ለተማሪ ቆሎ ፣ ለወታደር በቅሎ ።

ለተሚጋች መዘዘኛ ፣ የዳኛ ትእግስተኛ ።

ለተረታው ያበደረ ፣ እሳት ጨመረ ።

ለተራብ በግብር ፣ ለተበደለ በነገር ።

ለተሸሸገ ምግብ ፣ የተሸሸገ ሆድ አይጠፋለትም ።

ለተሾመ ይሚገቱለታል ፣ ለተሻረ ይመሰክሩበታል ።

ለተቀማጭ ፣ ሰማይ ቅርቡ ነው ።

ለተባባሰው ፣ ማጭድ አታውሰው ።

ለትሁዋን ልጓም ማጉረስ ፣ ላፈኛ ሰው መመለስ ።

ለቸኮለ ሰው ፣ ቀንጫ አስጨብጠው ።

ለነገረኛ ሰው ፣ ጀርባህን ስጠው ።

ለነገረኛ ነገር ተውለት ፤ ለሆዳም እህል አቅርብለት ።

ለኔ ፣ ነግ በኔ ።

ለንጉስ ያልረዳ ፣ ከባህር ያልቀዳ ።

ለአበባ ፤ የለው ገለባ ።

ለአምላክ ልንገረው ፣ ለማያስቀረው ።

ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል ።

ለእሳት እንጨት ካልነሱት አይጠፋም ።

ለእሳት ፍላት ፣ ለጮማ ስባት ።

ለእባብ እግር የለው ፣ ለባዳ ውል የለው ።

ለእብለት ስር የለው ፣ ለእባብ እግር የለው ።

ለእበጥ ፍላት ፣ ለእንጨት እሳት ።

ለእውር ዝማሜ ፣ ለመላጣ ጋሜ ።

ለእጅ ርቆ ፣ ለአይን ጠልቆ ።

ለእግሩ የተጠየፈ ፣ ለቂጡ አተረፈ ።

ለእግር የፈሩት ፣ ለቂጥ ይተርፋል ።

ለእግዚአብሔር የቀነቀነ ለዕድቅ ፣ ለጌታ የቀነቀነ ለወርቅ ።

ለከለላ ጥላ ፣ ቢርብህ ብላ ።

ለካህን ጥምቀት ፣ ለገበሬ ግንቦት ።

ለከፋት ያደለው ፣ አሳዳጊ የበደለው ።

ለኩ መሳቢያ ፣ ወፍጮ ማላሚያ ።

ለወሬ ወዳጁ ወሬ ፥ ለመነኩሴ ጥሬ ።

ለወሬ ፥ የለው ፍሬ ።

ለወሬ የለው ፍሬ ፥ ለአበባ የለው ገለባ ።

ለወሬ የቸኮለ እናቱን በመንገድ ላይ ይረዳል ።

ለወታደር ፥ ሰፊ መንደር ።

ለወይዘሮ ፥ መልካም ዶሮ ።

ለወዲላ ፥ መልካም ዱላ ።

ለወዳጅ የማር ወለላ ፥ ለጠላት አሜኬላ ።

ለወዳጅና ለአይን ፥ ትንሽ ይበቃዋል ።

ለወጡም እዘኑለት ፥ አንዳንድ ጊዜ ዶረቅ ጉረሱለት ።

ለወጡም እዘኑለት ፥ ከደረቁም ብሉለት ።

ለዋንጫ ቡሽ ፥ ለውሃ ጉሽ የለውም ።

ለውሻ ፥ ምሳ የለው ራት ብቻ ።

ለውሻ ሞት ፥ ፊት አይነጩለትም ።

ለውሻዬ ያልሁትን ፥ ልጄ ቢበላብኝ አልወድም ።

ለውጡኝ ባይ ፥ የሚሻለውን አውቆ ።

ለዘመዶ ፥ ያዝናል ሆዶ ።

ለዝናም ጌታ ውሃ ነሱ ።

ለይቶ እንደፈፋ ፥ አንጓሎ እንዳረፋ ።

ለይቶት አባ ንጉሷ ።

ለደህና ሰው ፥ ዋጋ አነሰው ።

ለደብተራ ፥ መቋሚያና ጭራ ።

ለደግ ንጉስ ፥ እለት እለት ማልቀስ ።

ለዳርቻው ሲሳሱ ፥ መካከሉን ተነሱ ።

ለዳባ ለባሽ ፥ ነገርህን አታበላሽ ።

ለዳኛ የነገሩት ፥ በርጥብ ያቃጠሉት ።

ለድሃ ፥ ማን ሰጠው ውሃ ።

ለድህነት የፈጠረው ፥ ቢነግድ አያተርፍም ።

ለድሪ ያሉት አንገት ፥ ለአሽክት ።

ለድካም የጣፈኝ ፥ ብነግድ አይተርፈኝ ።

ለዶሮ ሲነግሩ ፥ ምጥማጥ ይሰማል ።

ለጀሮ ጥርስ ፥ ለሆዳም ስስ ።

ለገላጋይ ደም የለውም ።

ለገበሬ ፥ መልካም በሬ ።

ለገቢህ ተንገብገብ ።

ለገዳም የረዳ ፥ አይጎዳ ።

ለጉንዳን ደም የለው ፥ ለዝንብ ቤት የለው ።

ለጉንዳን ደም የለው ፥ ለገንዘብ ቤት የለው ።

ለጋስ ቢለግስ አበደረ እንጂ እንዲያው አልሰጠም ።

ለጠላትህ እንደ ዳቦ እስኪገምጥህ አትመቸው ።

ለጠጪ ሰው ፥ የመጠጥ ወሬ አውራው ።

ለጥቅምት ያልሆነ ቀሚስ ፥ ይበጣጠስ ።

ለጨቅጫቃ ሰው ከማበደር ፥ ይሻላል በጁ ይደር ።

ለያም ግድፈት ፥ ለባል ሽረት ።

ለፈረስህ አንገት ፣ ለጋሻህ እምብርት ።

ለፈሪ ሜዳ አይነሱም ።

ለፍቅር ብትተኛ ፣ ለጠብ አረገዘች ።

ለፍየል ቆላ ፣ ለሙክት ባቄላ ።

ሊሻገር ቢያምረው ይዋኛል ፣ ሊሟገት ቢያምረው ይዳኛል ።

ሊበሉ የፈለጉትን አሞራ ፣ ስሙን ይሉታል ጅግራ ።

ሊወጋ የመጣ ፣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስም ።

ሊያልፍ ውሃ ፣ አደረገኝ ድሃ ።

ሊያስቡት አይገድም ።

ሊጣላ የመጣ ፣ ሰበብ አያጣም ።

ላህያ ማር አይጥማት ።

ላለው ቅንጭብ ያረግዳል ።

ላለፈ አይፀፀቱም ፣ ለሚመጣው አይበለጡም ።

ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራለትም ።

ላሊበላ ሄደሽ ከህንፃው ብትሰፍሪ ፣ አይገኝም ዕድቅ አለ ባህሪ ።

ላሊበላ ፣ አደራውን አይበላ ።

ላሊበላ ፣ የቃሉን አይበላ ።

ላሊበላን ካላጠገቡት ይጮሃል ፣ ሎሌም ካልሰጡት ይከዳል ።

ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው ።

ላመት ልብስ ፣ ለእለት ጉርስ ።

ላም ሲበዘበዝ ፣ ጭራዋን ያዝ ።

ላም በረቱን ፣ የሰው ልጅ አባቱን አይረሳም ።

ላም ባልዋለበት ፥ ኩበት ለቀማ ።

ላም ነጂዋን እንጂ ጌታዋን አታውቅም ።

ላም አለች በደረጣ ፥ ወተቷ ምን ይነጣ ።

ላም አለኝ በሰማይ ፥ ወተቷንም አላይ ።

ላም እሳት ወለደች ፥ እንዳትልሰው ፈጃት ፥ እንዳትተወው ልጅዋ ሆነባት ።

ላም ከወንዝ ፥ ልጅ ከቦዝ ።

ላም የዋለችበትን ትመስላለች ።

ላሳር የጣፈው ፥ ቢነግድ አይተርፈው ።

ላታመልጠኝ ፥ አታሩጠኝ ።

ላታገኝ አትመኝ ፥ ላታጣ አትቆጣ ።

ላትከፍል አትዋስ ፥ ላትደርስ አትገስግስ ።

ላንበሳ አይመትሩ ፥ ላዋቂ አይነግሩ ።

ላንድ ብርቱ ፥ ሁለት መድሃኒቱ ።

ላንድ አራሚ ፥ ዘጠኝ ቋሚ ።

ላንድ ጭቃ አገር ዘጠኝ ምሰሶ ።

ላያቱ እዳ ፥ ላማቱ ፍሪዳ ።

ላያጠግቡ መጋበዝ ፥ ላይገድሉ ካራ መምዘዝ ።

ላያጥብ አይለብስ ፥ ላያርም አያርስ ።

ላይሆን ቤት ፥ በበአል ስፌት ።

ላይሆን ዘመድ ፥ ገንዘቤንም አልሰድ ።

ላይሉኝ ቸር ፥ በየቦታው ስፈነቸር ።

ላይሉኝ ወሰ ፥ ደርሼ ነበር ከረጋ ለቅሶ አለ ጠይብ ።

ላይምረው ፥ አማሰነው ።

ላይሞት ይፈራል ፥ ላይድን ይሸሻል ።

ላይቀር ሞቱ ፥ መንጠራራቱ ።

ላይቀር ሳቁ ፥ ችኩ ።

ላይቀር ጣጁው ፥ አታራፍጅው ።

ላይበላው ፥ አበላሸው ።

ላይተች አይፈርድ ፥ ላያተርፍ አይነግድ ።

ላይችል አይሰጥም ፥ ላይጠግን አይሰብርም ።

ላይን የሚከፋ ፥ ላፍንጫ የሚከረፋ ።

ላይንና ለወዳጅ ፥ ጥቂት ይበቃል ።

ላይኛው ከንፈር ለከርከር ፥ ታችኛው ከንፈር ለምስክር ።

ላይዘሩ አያርሱ ፥ ካላረሱ አያጎርሱ ።

ላይፈሩ ቁጣ ፥ ከእብደት አንድ ነው ።

ላገልጋይ ትእግስት ፥ ለባለቤት መጠቃት ።

ላገሩ እንግዳ ፥ ለሰው ባዳ ።

ላገሬ ሰው እንኳን ነጋሪት አታሞ አይሰጠው ።

ላጠፋ ምህረት ፥ ላጣ ቸርነት ።

ላፈኛ ሰው መመለስ ፥ ለትሁዋን ልጓም ማጉረስ ።

ላፍላ ፥ የለው ጎፍላ ።

ሌሊት ፥ የምክር እናት ።

ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል ።

ሌባ ቢያዩኝ እስቅ ፥ ባያዩኝ እሰርቅ ይላል ።

ሌባ ተይዞ ዱላ ጥየቃ ።

ሌባ እናት ፣ ልጅዋን አታምነውም ።

ሌባ ውሻ ባፏ ሊጥ ፣ በወገቧ ፍልጥ ።

ሌባና ሌባ ፣ ተጣሉ በሰው ገለባ ።

ሌባን ሌባ ቢሰርቀው ፣ ምን ይደንቀው ።

ሌት ከጅብ ፣ ቀን ከህዝብ ።

ልማ በስሉስ ፣ ጥፋ በስሉስ ።

ሊማድ ሲቀር ፣ ምስህ ቅበር ።

ልበ ሰፊ ፣ ነገር አላፊ ።

ልበ ሳንባ ዶሮዬ ።

ልባልባ ቃጥቆ አዛባ ፣ ሱሪ አውልቆ ፈረስ ጋለባ ፣ ራስ ላጭቶ ወለባ ።

ልብ ሲያውቅ ፣ ገንፎ ያንቅ ።

ልብ ሲያውቅ ፣ ጥርስ ከደመኛው ጋር ይስቃል ።

ልብ ሳይገዙ ፣ ነገር አያበዙ ።

ልብ እንቅርትን ለማየት ይመኛል ።

ልብ ከጎንጅ ፣ ትምህርት ከደጅ ።

ልብ ካዘነ ፣ እንባ አይቸግርም ።

ልብ ፣ ካጥባቂ ፈረስ ይስባል ።

ልብ የሌላት ውሻ ፣ ማር ትቀላውጣለች ።

ልብ የሚገኝ በስልሳ ፣ ገንዘብ የሚገኝ በሰላሳ ።

ልብ ያለው ፣ አገሩ ሰማይ ነው ።

ልብ ያሰበውን አፍ ይናገረዋል ፣ አይን ያየውን እጅ ይሰራዋል ።

ልብስ ይፈጃል ሌት መልበስ ፤ ወጥ ይፈጃል መጎራረስ ።

ልብስህን በውሃ ፥ ገንዘብህን በድሃ ።

ልብና ነፋስ ፥ ከሁሉ ያደርሳል ።

ልትደርቅ የደረሰች ምንጭ ፥ ጭልጭል ትላለች ።

ልዩ ስጋ ፥ በመንጋጋ ።

ልጁን በራብ ፥ የእንጀራ ልጁን በጥጋብ ።

ልጅ ለሳቀለት ፥ ውሻ ለሮጠለት ።

ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች ።

ልጅ ለወለደው ፥ ሙቅ ላሞቀው ።

ልጅ ሲያረጅ ፥ አባት ይጦራል ።

ልጅ ቢያስብ ምሳውን ፥ አዝማሪ ቢያስብ ጠላውን ።

ልጅ ቃርጣጣ ፥ እህል ከዘባጣ ።

ልጅ ቃጉል ፥ እህል ከጉራንጉር ።

ልጅ አባቱን ገደለ ቢለው ፥ የኔ ልጅ እንዳይሰማ አለው ።

ልጅ አይወለድ ፥ እውነት አይፈረድ ።

ልጅ እንዳባቱ ፥ ሰው እንደቤቱ ።

ልጅ ከዋለበት ፥ ሽማግሌ አይውልም ።

ልጅ ካባቱ ፥ ሾተል ካፎቱ ።

ልጅ ያለ ፥ ልጅ አከለ ።

ልጅ ያለ እናት ፥ ቤት ያለ ጉልላት ።

ልጅ ያባቱን ፥ ወቄራ ያፎቱን ።

ልጅ ያቦካው ፥ ለራት አይበቃም ።

ልጅ ይወለዳል ከቦዝ ፤ ላም ይገዛል ከወንዝ ።

ልጅ ደረሰ ፤ ቤት ፈረሰ ።

ልጅህንና አትክልትህን ፤ ተጠባበቅ ጎረቤትክን ።

ልጅና ቂስ ፤ በሰው ገንዘብ ያለቅስ ።

ልጅና ጥሬ ፤ አይተጣጡም ።

ልጅና ጠጣ ፤ ውሃ ይጠጣ ።

ልጅን መርገምና ራስጌ መሽናት ፤ ተመልሶ ጉዳት ።

ልጅን በጡት ፤ እህልን በጥቅምት ።

ልግመኛን መምከር ፤ ውሃ በወንፊት ማኖር ።

ልግም እግዜር አይወድም ።

ልጓም ለቆ ቼቼ ።

ልጡ የተራሰ ፤ መቃብሩ የተማሰ ።

ልፉ ያለው ፤ አንድ እንጨት ያስራል ።

ሎሌ ሲከብር ጌታውን ይከሳል ፤ ሙክት ሲሰባ ሾተል ይልሳል ።

ሎሌና አሞሌ ፤ ካዘዙት ይውላል ።

ሎሚ ካልመጠጡት ፤ እንቧይ ነው ።

ሎሚና ትርንጎ ሞልቶ ባገር ፤ እንቧይ ታሸታለህ የድሃ ነገር ።

- መ -

መሄድ መሄድን እያደራጀሁ ፤ እንደ ጉሬዛ ከሬት አረጀሁ ።

መሄድ መመላለስ ፤ ካሰቡት መድረስ ።

መሄድ መነሳት ፤ መከተል መሾኘት ።

መሄድ በጋ ነው ፣ መቀመጥ ክረምት ነው ።

መሄድ የለ ዛቻ ብቻ ፣ መስራት የለ አሳብ ብቻ ።

መሄድ ያማረው እራቱን በጨረቃ ይበላል ።

መለመን የለመደ መላስ ፣ በህልሙ አቁማዳ ይዋስ ።

መላ እንደ ሴት ፣ ግርማ እንደ ሌሊት ።

መላከተኛ ካጤ ቤት ይገባል ።

መልከኛው ኮሶ ቢጠጣ ፣ ጨሰኛው አስቀመጠው ።

መልኩ የኔ ፣ ግብሩ ያረመኔ ።

መልካም ልብ አይነካም ።

መልካም ሰሪ በልጆቹ ፣ የጨረቃ ንጋት በወፎቹ ይታወቃል ።

መልካም ሱሪ ፣ ለተማሪ ።

መልካም ቆንጆ ፣ የላት መቀናጆ ።

መልካም በሬ ለእርሻ ፣ ዶማም አያሻ ።

መልካም ተመኝ ፣ መልካም እንድታገኝ ።

መልካም ወገን ፣ የፀሃይ ውጋገን ።

መልካም ወጥ ፣ እጅ ያስመጥጥ ።

መልካም ጭራ ፣ ለደብተራ ።

መልክ በግምት ይገኛል ፣ ልብ ትልቅ ይመኛል ።

መልኳ ባያምር ፣ አመሏ ይመር ።

መመራመር ፤ ያገባል ከባህር ።

መመሳሰል የጋራ ነው ።

መምሬ ፣ አይበሉም ጥሬ ።

መሪ የሌለው ጠንባሳ ፣ ምርኩዝ የሌለው አንካሳ ።

መራጭ ፣ ይወድቃል ከምራጭ ።

መሬት ሲያረጅ ፣ መጭ ያበቅላል ።

መሬት በድንበር ፣ ውበት በከንፈር ።

መሬት ባቅጣጫ ፣ መልክ ባፍንጫ ።

መሬት እናት ፣ ዘር አባት ።

መርጦ ይገዟል ፣ ዋጋ ያበዟል ።

መርፌ መግቢያዋን እንጂ ፣ መውጫዋን አታይም ።

መርፌ ቢሰበሰብ ማረሻ አይሆንም ።

መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ ለብዙ ሰው ትጠቅማለች ።

መሰረት ነዋሪ ፣ መሪና አስተማሪ ።

መሰስ ሲል ፣ ምን ደስ ይል ።

መሳሳሚያ ከንፈር ፣ መገናኛ ድንበር ።

መስራት እንጂ ፣ ማፍረስ አያቅትም ።

መስተዋት ፊት ያሳያል ፣ መሰንበት ሁሉን ያሳያል ።

መስተዋት ፊት ያሳያል ፣ መሰንበት ይበጃል ።

መስከረም ባበባው ፣ ሰርግ በጭብጨባው ።

መስጠት አያውቅ እራት ፣ መምታት አያውቅ አናት ።

መስጠት የማያውቅ የቁና እኩል ።

መሶብ ሰፍቼ ፣ ለእጤ አበርክቼ ።

መሸሽማ አንበሳም ይሸሻል ፣ መለስ ያለ እንደሆን ሰውን ያበላሻል ።

መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል ።

መቀመጥ ፣ መቆመጥ ።

መቀመጥ በና ነው ፤ መሄድ በልግ ነው ።

መቃ እንዲያ ሲያምር አያፈራ ፣ ወርቅ ቢሞላ አይዘራ ።

መቃን ከመግጨት ፣ ዝቅ ብሎ መግባት ።

መቃዣትና መስከር ፣ ላይመልሱ መበደር ።

መበለት በቄስ ፣ ገበሬ በንጉስ ።

መብሉ እኩል ፣ ስራው ስንኩል ።

መብላት ከሁለት ፣ መፍረድ በውነት ።

መብላት ከባእድ ፣ ምክርን ከዘመድ ።

መብሉ ስንቆ ፣ ምርኩዙ ሽንበቆ ።

መብልን ይዤ ቅልውጤን ረሳሁት ።

መብል ያለመጠጥ ፣ እንጀራ ያለወጥ ።

መብልን ከሰው ቤት ፣ መኝታን ከቤት ።

መብልን ከባእድ ፣ ሃዘንን ከዘመድ ።

መብረቅ የመታውን ወዘት አስተኛው ።

መብራት ለጨለማ ፣ አፍንጫ መያዝ እንዳይገማ ።

መተው ፣ ነገሬን ከተተው ።

መታለል ፣ ገደል መንከባለል ።

መታፈር ፣ በከንፈር ።

መቼ ገባህ ፊት ፣ ምን በላህ ፍትፍት ።

መች መጣሽ ሙሽራ ፣ መች ቆረጠምሽ ሽንብራ ።

መነኩሴ በቆብ ፣ ወንበር በከታብ ።

መነኩሴ ካልሞተ ፥ ስንዴ ካልሸተ አይታወቅም ።

መነዛነዝ ፥ ያመጣል መዘዝ ።

መነገድ ለማትረፍ ፥ መማር ለመፃፍ ።

መናኝ ለነፍሱ ፥ አዳኝ ለጥርሱ ።

መናጆ የሌለው በሬ ፥ ለምድ የሌለው ገበሬ ።

መናገር መልካም ነው ፤ ማዳመጥ ይበልጣል ።

መንደር በልጆች ፥ አገር በገበሬዎች ።

መንደር ከዋለ ንብ ፥ አደባባይ የዋለ ዝንብ ።

መንገደኛ ከስንቁ ፥ ነጋዴ ከወርቁ ።

መንገድ ለቀደመ ፥ ውሃ ለገደበ ።

መንገድ ሳለ በዱር ፥ በቅሎ ሳለ በእግር ።

መንገድ ባሳብ አይደረስም ።

መንገድ ከሸንት ይቀራል ።

መንገድ ካገር ልጅ ፥ ምክር ከጨዋ ልጅ ።

መንገድ ካገር ልጅ ፥ ስደት ከሹም ልጅ ።

መኖር ማለት ፥ ብርሃንና መሰንበት ።

መኖር ማለት ፥ ብርሃንና መስተዋት ።

መኖር በከንቱ ፥ ሰው አለቤቱ ።

መኖር በከንቱ ፥ ያለ ባለቤቱ ።

መከራና እዳ ፥ እንግዳና ሞት ፥ በድንገት ።

መከራና ጉም እያደር ይቀላል ።

መከራው ያላለቀለት በሬ ፥ ከሞተ በሁዋላ ቆዳው ነጋሪት ይጠፈራል ።

መከፈንና መሸፈን ፣ እግዜርን ማመን ።

መካር የሌለው ንጉስ ፣ አላንድ አመት አይነግስ ።

መከዳትና መኩብለል ፣ ወድቆ መንከባለል ።

መከፈልት ሲሹ መቅሰፍት ።

መወለድ ካለ ማዘን አይገድም ።

መውጫህን ሳታይ አትግባ ።

መዝገብ ቢጠፋ ባገር ፣ ቤት ቢላላ በማገር ።

መዝጊያ የሌለው ቤት ፣ ሴሰኛ ሴት ።

መጠጥ ለጨዋታ ፣ ወንድም ለግርግርታ ።

መጠጥ ከጨዋ ልጅ ፣ ምክር ከድሃ ልጅ ።

መጠጥ ከጨዋ ልጅ ፣ ምክር ካገር ልጅ ።

መጣፍና ተማሪ ፣ ቀለበትና ድሪ ።

መጥረቢያው የተውሶ ፣ ጠፋ ተመልሶ ።

መጥፊያው ፣ መልሚያው መስሎ ይታየዋል ለሰው ።

መጥፎ ወሬ ይበራል ፣ መልካሙ ይተኛል ።

መጨነቅ የመጠበብ እናት ።

መጫር ያበዛች ዶሮ የመታረጃዋን ቢላዋ ታወጣለች ።

መጭ ፣ መጭ ከሚሉት በቅሎ መጫሚያ ።

መፍራት ለመታማት ።

መፍታት ሳለ መሞት ።

ሙሽራ በሚዜ ፣ ንስሃ በትካዜ ።

ሙሽራዋስ እኔ ፣ ዶሮዋን ማን በላት ካለኔ ።

ሙቅ ውሃና የሰው ገንዘብ አይጠቅምም ።

ሙታንን ከማመስገን ፣ ህያዋንን ማስተንተን ።

ሙት መውቀስ ፣ ድንጋይ መንከስ ።

ሙት ይዞ ይሞታል ።

ሙዝ ላጥ ፣ ዋጥ ።

ሙግት ላፍለኛ ፣ እብቹ ለጌኛ ።

ሙግት ያውቋል ፣ ይልቋል ።

ሚስቱ ከፉ ባቄላ እራቱ ፣ ብሳና እንጨቱ ፣ ሃዘን ነው እቤቱ ።

ሚስቱ ደግ ስንዴ እራቱ ፣ ወይራ እንጨቱ ፣ ደስታ ነው እቤቱ ።

ሚስቱን ጠልቶ ካግቱ ፣ ልጁን ከሶ ካባቱ ።

ሚስት ባታብል ባሏን ትወዳለች ።

ሚስት ከፈቷት ባዳ ፣ ማሽላ ከተቆረጠ አገዳ ።

ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢለው? ማንን ወንድ ብላ ።

ሚስትህን ስደድ ፣ በሬህን እረድ ፣ ይላል የባለጌ ዘመድ ።

ሚስትና ዳዊት ፣ በብብት ።

ሚዜ ቢከተል አሽከር ይመስላል ።

ሚዳቋ ቀስ ብላ ስትሄድ የተያዘች ትመስላለች ።

ሚዳቋ እንደ አንበሳ እሙህ ብላ ተሰንጥቃ ሞተች ።

ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር ።

ማልደው ቢነሱ ፣ እኩለ ቀን አይደርሱ ።

ማማት የለመደ አፍ ሲያለግ ያድራል ።

ማማው ጥረት ፣ ማሽላው ቅንብቢት ።

ማማው ከጉልበት ፥ ማሽላው ከእንብርት ።

ማምሻም እድሜ ነው ።

ማረገ ቢስ ፥ እራቱ ገሚስ ።

ማረፍና መራገፍ ፥ እየበሉ መንገፍገፍ ።

ማሩን አምሮ ፥ ውተቱን አጥቁሮ ።

ማር ሲሰፍሩ ፥ ማር ይናገሩ ።

ማር ሲበዛ ይመራል ።

ማር ሽጦ ምን ይበሿል ፥ ልጅ ጠልቶ ምን ይወዷል ።

ማር ሽጦ ምን ይገዟል ፥ ልጅ ጠልቶ ምን ይወዷል ።

ማር ነክቶታል ብለህ እጅህን አትላስ ።

ማር አገባ አገባ ፥ ገደል ገባ ።

ማርና ቅቤ ይጣፍጣሉ ፥ ከየት ይገኛሉ ።

ማርና ንብ ፥ ዕህፈትና ንባብ ።

ማርና ውተት ፥ ምን አገናኝቶት ።

ማሽላ ለማሽላ ፥ ተያይዞ ቆላ ።

ማሽላ ሲያር ይስቃል ።

ማሽላና ዘንጋዳ ፥ መከታና ጓዳ ።

ማቅ ይሞቃል ፥ ሻሽ ይደምቃል ፥ ገቢውን ባለቤት ያውቃል ።

ማባበል ፥ መቅለል ።

ማባበልና ማንቆሻበል ፥ ማሞኘትና መደለል ።

ማተብና አንገት ፥ ክታብና ደረት ።

ማን ሲስምሽ ፥ ታሞጠሙጪአለሽ ።

ማን ቢያሮጠኝ ፥ ሱፋጭ ቆረጠኝ ።

ማን አለ መርማሪ ፥ አለ ፈጣሪ ።

ማን ያውራ የነበረ ፥ ማን ያርዳ የቀበረ ።

ማን ያውቃል ባላገር ፥ ማን ያጠብቃል ማገር ።

ማን ያውቅ አገር ፥ ማን ይጠብቅ ማገር ።

ማን ይሙት ጠላት ፥ ማን ይኑር አባት ።

ማንን ታሸንፋለህ፣ ሚስቴን ።

ማወቅ መላቅ ፥ አለማወቅ መናቅ ።

ማወቅ እናውቃለን ፥ ብንናገር እናልቃለን ።

ማውራት ነው ሴትነት ፥ መስራት ነው ወንድነት ።

ማጀት በጎረሰ ፥ ደጃፍ በመለሰ ።

ማግኘት ማውጣትን ያስለምዳል ።

ማግኘት ማውጣትን ይመልሳል ።

ማጣት ከሰማይ ይርቃል ።

ማጣትና ማግኘት ጆሮ ለጆሮ ።

ማፈር ከሌለ ክብር የለም ።

ሜ ባልኩ ፥ ፍየል ከፈልኩ ።

ሜዳ መራመድ ሳታውቅ ፥ መሰላል መውጣት ማን አስተማራት ?

ምለህ በክርስቶስ ፥ ተገዝተህ በቄስ ።

ምላስ ቢጥም ፥ ቀዶ ይጠቅም ።

ምላስ ይቀባል ፥ ጥርስ ይወጋል ።

ምላጭ ለመላጫ ፥ ጠፍር ለመለመጫ ።

ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ ? ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጡ ?

ምርቅና ፍትፍት ።

ምርት ከገለባ ፡ ግዳይ ከሰለባ ።

ምሳሌህ ሁሉ አንካሳ ነው ።

ምስሌ ፡ ሁን እንደኔ ።

ምስር መዝራት ሞያ ማጣት ፡ አተር መዝሩት ወይ ብልሃት ፡ አለች ጠጣ ።

ምስር ፡ ብልት ይቀስር ።

ምስር እራቱ ፡ ምስር ቢያጣ ሞቱ ።

ምስክር ለበለጥ ፡ አውድማ ለመለጥ ።

ምስክር በበለጠ ፡ ባቄላ ባፈጠጠ ።

ምስክር ቢያድር ይለወጣል ፡ ሽንፍላ ቢያድር ይመለጣል ።

ምስክር ከተጠራ ፡ መስዋእት ከተሰራ ።

ምስክር ያለው ሙግት ፡ አያዳግትም ለመርታት ።

ምስጋና አዋቂን ያበረታል ፡ ቂልን ያሳብዳል ።

ምስጢር የባቄላ ወፍጮ አይደለም ።

ምስጥ ፡ ከምድር ውስጥ ።

ምቀኛ ጠላቱን ይተክል ፡ ራሱን ይነቅል ።

ምነው ቢገዙ ፡ መድን ካበዙ ።

ምናልባት ቢሰበር አናት ቅቤ ሻ ፡ ለመተኮሻ ።

ምን በእግሩ ቢመጣ ፡ በእጁ እንዳይመጣ ።

ምን ቢነግሱ ፡ በጅ አይካሱ ።

ምን ቢከፉ ፡ አሳብ ነው ትርፉ ።

ምን ቢወቅሱ ፣ በእጅ አይከሱ ።

ምን ቢዋደዱ ፣ እየቅል ነው መንገዱ ።

ምን ቢያርሱ ፣ እንደ ጎመን አይጎርሱ ።

ምን ቢያርሱ ፣ ድንበር አያፈልሱ ።

ምን ቢያስጠምዱ በዘጠና ፣ ከቤት አይወጣ ቀጠና ።

ምን ቢያውቁ ዳኛ አይሆኑ ፣ ምን ቢያምሩ ሙሽራ አይሆኑ ።

ምን ቢፈሩ ፣ ከሞት አይቀሩ ።

ምን ያመጣ ድሃ ፣ ምን ያገሳ ውሃ ።

ምን ያመጣል ሰኔ ፣ ምን ይሰራል በዘኔ ።

ምን ይሰማ ጆሮ ፣ ምን ይውጥ ጉሮሮ ።

ምን ይበሏል ? ነጭ ፤ ምን ይጠጧል ? ጠጅ ።

ምን ይዞ ጉዞ ።

ምንም በሙቴ ፣ አራድማ ሸምቱ ።

ምንም ቢሆን ስር ነው እንጂ እጢ አይደማም ።

ምንም ቢጠም መንገድ ፣ ምንም ቢከፋ ዘመድ ።

ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ ።

ምንም ብታውቅ ፣ ከዳኛ ጋራ አትሟገት ።

ምንም ብታፈገፍጊ ፣ ከግድግዳ አታልፊ ።

ምንም ብትሞቺ ፣ እንዴት አደርሽ አንቺ ።

ምንም ብጠላው በወንድሜ ግንባር ደም አልይበት ።

ምንሽም ምንሽም አያምረኝ ፣ ከመሄድሽ በቀር ።

ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት ፣ ሸንኮራ ሆኖ እብቁ አይኔ ገባ አለ ።

ምኞትና ጉም ፡ አይጨበጥም ።

ምከረው ምከረው ፡ ባይሰማህ ንከረው ።

ምከረው ምከረው ፡ እንቢ ቢል መከራ ይምከረው ።

ምክር ዝክር በምድር ፡ ልጇ ተመክር ።

ምክር ከሽማግሌ ነው ፡ መሻገር ከጎበዝ ነው ።

ምክር ከድሃ ነበርሽ ፡ ማን ቢሰማሽ ።

ምድር ሲደለደል ፡ ማሳ ሲታደል ።

ምድር በዛፍ ፡ ህግ በመፅሃፍ ።

ምድር በዶሮ ፡ ያውስ ማን ገብሮ ።

ምድር በአለቃ ፡ ሰማይ በጨረቃ ።

ምጡን እርሺው ፡ ልጁን አንሽው ።

ምጥ ለናቷ አስተማረች ።

ምፅዋት ፡ የእለት እራት ።

ሞት ላይቀር ፍርሃት ፡ አመል ላይቀር ቅጣት ።

ሞት ርስት ነው ፡ መፈራቱ ለምንድነው ።

ሞት ሲደርስ ቁስ ፡ ጦር ሲደርስ ፈረስ ።

ሞት በአቤል ፡ ተዝካር በሮቤል ።

ሞት በእንቅልፍ ይለመዳል ።

ሞት በጥር ፡ በነሃሴ መቃብር ።

ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል ።

ሞት ባልቀረለት ፡ ምክንያት ባልሆነበት ።

ሞት አይለመድ ፡ ጎሽ አይጠመድ ።

ሞትን ማሰብ ፣ ከሁሉ መሰብሰብ ።

ሞትን የሰጠ ቀባሪ አይነሳም ።

ሞትን ያሀል እዳ ፣ መቃብርን ያሀል እንግዳ ።

ሞኝ ለራሱ ያውቃል ።

ሞኝ ለጠበቃው ምስጢር ይሸሽጋል ።

ሞኝ ሲናገር ብልሀ ያዳምጣል ።

ሞኝ በብልሀ ይስቃል ።

ሞኝ ቢቆጡት የመቱት ይመስለዋል ።

ሞኝ ቢፈርዱ ፣ ሞኝ ይወልዱ ።

ሞኝ ባያፍር ፣ የሞኝ ዘመድ ያፍር ።

ሞኝ ተላላ አበላል የት ያውቃል ፣ ፈትፍተው ሲያጎርሱት መዋጥ ያቅተዋል ።

ሞኝ ተናጋሪ ፣ ክፉውን በፊት ደጉን በሁዋላ ።

ሞኝ ነጋዴ በራሱ መቀማት ሳያዝን በጓደኛው ማምለጥ ይቆጨዋል ።

ሞኝ አሞራ ያባቱን ዋሻ ይጠየፋል ።

ሞኝ አሳላፊ ወንድሙን ይጎዳል ።

ሞኝ አንዳጅ ፣ ግንዱን በውስጥ ጭራሮውን በላይ ።

ሞኝ አያውቁብኝ ባይ ።

ሞኝ ከመከሩ ቤት እሳት አይሞቅም ።

ሞኝ ከመከረው ፣ እውር ከመራው (ይጣላል) ።

ሞኝ ከመከረው ይጣላል ።

ሞኝ ከመውለድ ፣ ማስወረድ ።

ሞኝ ከጠገበበት አይወጣም ።

ሞኝ ካመረረ ፥ በግ ከበረረ ።

ሞኝ ካገደደ ፥ ልጅ ከለመደ ።

ሞኝ ወርውሮ ቢስት ፥ የወጋ አይመስለውም ።

ሞኝ ወታደር ፥ ሚስቱን ጥሎ መንደር ።

ሞኝ ውሃ ሲወስደው ይስቃል ።

ሞኝ የለቱን ፥ ብልህ ያመቱን ።

ሞኝ የመከሩት እለት ፥ ቁንጫ የጠረጉት እለት ይብሳል ።

ሞኝ የተከለውን ብልህ አይነቅለውም ።

ሞኝ ያገኘው ፈሊጥ ፥ ውሻ ያገኘው ሊጥ ።

ሞያ የለ መልክ ብቻ ፥ አመል የለ ነገር ብቻ ፥ አስቸጋሪ ለጋብቻ ።

ሞፈር ቆራጭ እርፍ አይታየውም ።

## - ረ -

ረባዳ ቤቱ ፥ ገራም ሚስቱ ።

ረኸሙን ባላማ ፥ አጭሩን በጫማ ።

ረኸም ባይፈራ ፥ አጭር ባይኮራ ።

ረኸም ጦር ባይወጉበት ፥ ያስፈራሩበት ።

ረኸም ጭራ ፥ ከጎረቤት ያጣላ ።

ረኸምና ቀፋፋ ፥ ገደልና ፈፋ ።

ሩቅ አሳቢ ፥ ቅርብ አዳሪ ።

ሩቅ አገር ለውሸት ይመቻል ።

ሩዋጭና በራሪ ፥ ንፋግና ፈሪ ።

ራሱን ለተላጨ ፥ ፊቱን ለነጨ ።

ራሱን የማይችል አንገት ፥ ባለቤቱን የማያስገባ ቤት ።

ራስ ሲመለጥ ፥ ነገር ሲያመልጥ ።

ራስ ሳይጠና ፥ ጉተና ።

ራስ ተላጭቶ ወለባ ፥ ልባልባ ታጥቆ አዛባ ።

ራስ ተከናንቦ ፥ ሙርጥ ገልቦ ።

ራስ ከተመለጠ ፥ ነገር ካመለጠ ።

ራስ ከዋለ ለምድ አይገድም ።

ራስ ከዋለበት ፥ እግር ይሰበሰባል ።

ራስ የት ትሄዳለህ ? ካንተ ጋር ፥ ስንቅሳ ? አንተሳ ።

ራስ ያለ አንገት ፥ ዕድቅ ያለ እውነት ።

ራስ ይሸብታል እንጂ ልብ አይሸብትም ።

ራቁቱን የተወለደ ልጅ ለምድ አነሰው ወይ ።

ራብ ይከላከላል ባቄላ ፥ ከጥፍ ያደርሳል ነጠላ ።

ራብ ይከላከላል ባቄላ ፥ ጥቃት ያወጣል ዲቃላ ።

ራብን ባለቤቱ ያውቀዋል ፥ ማን ይጠይቀዋል ።

ራብን ያማርራል ሰው ፥ ቁንጣንን ያልቀመሰው ።

ራት ቢንቁ አንድ እጅ ይለቃለቁ ፥ ዳኛ ቢንቁ ከመከራ ይወድቁ ።

ራት ቢንቁ ፥ አንድ እጅ ይለቃለቁ ፤ ዳኛ ቢንቁ ፥ የተያዘ እህል ይወቁ ።

ራት የለህም ቢሉት ፥ ከወጡ አውጡልኝ አለ ።

ራት የላት ፥ ምሳ አማራት ።

ራት ፥ የሰማይ መብራት ።

ራት የሌለው ቄስ ፥ ከልቡ አይቀድስ ።

ሬሳ በምን ከበደ ? ሃሳቡን በሰው ላይ ጥሎ ።

ሬሳ በዝምታው ይፈራል ።

ሬሳ ባልጋ ፥ ጥሬ በመንጋጋ ።

ርስት በሺ አመቱ ፥ ለባለቤቱ ።

ርስት ያዳግማል ፥ አቀበት ያደክማል ።

ርጎ መስሎሽ እርሾ ጥልቅ ።

ርጥብ ሬሳ ፥ ደረቁን አስነሳ ።

ርጥብ ከደረቅ ይነዳል ።

ሮሮ የማይመረው ፥ ኮሶ የማያሽረው የለም ።

ሮቃ የዝሆን አለቃ ፥ ለምሳር አይበቃ ።

## - ሰ -

ሰላላ መላላ ።

ሰላም ሰላም ለቅኔ ስራቂ ናሁዳ ፥ ዳር ዳሩን ኮርመም መሃሉን ሳይጎዳ ።

ሰላም ሰው በርበሬ አይሰርቅም ።

ሰሚ ልብ ነው ፥ ጆሮማ ቅጠል ነው ።

ሰማሁት ያሻማል ፥ አየሁት ያመሳክራል ።

ሰማህ ? አልሰማሁም ፥ አይህ ? አላየሁም ።

ሰማንያ ለማገኛ ፥ ስለት ለማረጃ ።

ሰማንያ አንድ መፅሀፍ ከተማረው ፥ መከራ የመከረው ይሻላል ።

ሰማይ ምን ይርቅ ፥ መንገደኛ ምን ይጨነቅ ።

ሰማይ ቢያኩ ፣ ጤፍ ቢሰኩ ።

ሰማይ ብልጭ ፣ ወፍ ጭጭ ።

ሰማይ አገሬ ፣ ምድር ወንበሬ ።

ሰማይ ከነግሡ ፣ ምድር ከነልብሱ ።

ሰማይ ይወድቃል ብላ ፣ ምሰሶ ይዛ ቆመች ።

ሰማይን ያህል ዳቦ ባገኘሁ ቢለው ፣ ኮከብን ያህል በላተኛ ያዝብሃል አለው ።

ሰምቶ መቻል ፣ ለእግዚአብሔር ይመቻል ።

ሰምቶ ዝም ፣ አይቶ ዝም ፣ በሆድ ያለ አይነቅዝም ።

ሰምና ወርቅ ፣ እንጀራና መረቅ ።

ሰርቆ ከማሰብ ፣ እጅን መሰብሰብ ።

ሰርቆ የጉም ሌባ ፣ ጉም ሲለቅ የት ሊገባ ።

ሰርገኛ መጣ ፣ በርበሬ ቀንጥሱ ።

ሰርገኛ ሳይመጣ ፣ ሙሽሪት ትመጣ ።

ሰርገኞች መጡ ፣ ብቅል አስጡ ።

ሰባት አመት የታወረ እውር ነገ አይንህ ይበራልሃል ቢሉት፣ዛሬ እንደምን አድሬ አለ።

ሰባት ወልዶ አቃቢትነት ።

ሰባት ጊዜ እንዴት ዋላችሁ አንዱ ለነገር ነው ።

ሰነፍ ሰው ያሰንፋል ።

ሰነፍ ሴት ፣ እድል የላትም ለንብረት ።

ሰነፍ ሴት ያገባ ፣ በሬው በሰኔ ገደል የገባ ።

ሰነፍ በአል ያበዛል ።

ሰነፍ ቢመክሩት ፣ ውሃ ቢወቅጡት ።

ሰነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል ።

ሰነፍ ይፀድቃል ቢለው ፥ ገለባ ይበቅላል ወይ አለው ።

ሰነፍ ገበሬ በመስከረም ያርማል ።

ሰናፍጭ ትቀምሽ ፥ ተልባ መስሎሽ ።

ሰኔ መቃጠሪያ ፥ ሀዳር መገናኛ ።

ሰኔ ፥ ነግ በኔ ።

ሰንበሌጥ ለቤት ፥ ቀሚስ ለባለቤት ።

ሰአሊ በስእሉ ፥ ፈጣሪ በፍጡሩ ።

ሰከሮ ከጌታ መገናኘት ፥ ከሹመት መለየት ።

ሰው ሆኖ አይስት ፥ እንጨት ሆኖ አይጨስ የለም ።

ሰው ሆኖ የማያስብ ፥ እንጨት ሆኖ የማይጨስ ።

ሰው ሆኖ የማይበድል ፥ እንጨት ሆኖ የማይጨስ ።

ሰው ለወደደው ፥ ዘንጋዳ ጤፉ ነው ።

ሰው ለወዳጁ ጫጩት ያርዳል ።

ሰው ላማኙ ፥ እግዚአብሔር ለለማኙ ።

ሰው መሳይ በሸንጎ ።

ሰው መታፈሩ ፥ በከንፈሩ ፤ መሬት መከበሩ ፥ በድንበሩ ።

ሰው መኖሩ ለመከበር ፥ የመሬት ወሰኑ ድንበር ።

ሰው ማመን ቀብሮ ነው ።

ሰው ማመን ገደለኝ ፥ የኔ እየመሰለኝ ።

ሰው ማማት ፥ የሰው ስጋ መብላት ።

ሰው ማን ያህላል ? የተናገረውን ።

ሰው ማጅራቱ አይታየውም ።

ሰው ምን በሰራ ፣ መቅረቱ ይወራ ።

ሰው ምን ቢዋሽ ፣ እግዜርን አያታልልም ።

ሰው ምን ይመስላል ? ቢለው ፣ ኑሮውን ።

ሰው ሲሄድ ላገር ፣ ንብ ሲሄድ ላጥር ።

ሰው ሲያረጅ ከርስቱ ፣ ባል ሲያረጅ ከሚስቱ ።

ሰው ሳይቸግረው ከሰው ቤት ይሄዳል ።

ሰው ቁመቱን አይቶ ደጃፉን ይሰራል ።

ሰው በሰው የተጠጋ ፣ ሰው ወጋ ።

ሰው በእህል እህል በዝርዝር ያምራል ።

ሰው በወሬ ፣ ዱቄት በሙሬ ።

ሰው በወደደው ይደግፋል ።

ሰው በዋለበት ፣ ውሃ በወረደበት ።

ሰው በዘመድ ፣ ከብት በገመድ ።

ሰው በዱር ፣ አይኑ ዝንጉርጉር ።

ሰው ቢሰባ ለመሬት ፣ አያህ ቢሰባ ላራዊት ።

ሰው ቢታጣ ፣ ተመለመለ ጎባጣ ።

ሰው ባላወቀው ይፈርዳል ፣ እግዜር ባወቀው ይቀጣል ።

ሰው ባገሩ ሰው ነው ።

ሰው ባገሩ ፣ ቤት በበሩ ።

ሰው ባገሩ ፣ አንበሳ በዱሩ ፣ አዞ በባህሩ ።

ሰው ባገሩ ወይራ ነው ።

ሰው አለቀ ፡ ምድር ተደባለቀ ።

ሰው አለብልሃቱ ገደል መግባቱ ፡ አለ ጉልበቱ ውሃ መግባቱ ።

ሰው አለወንዙ ፡ ብዙ ነው መዘዙ ።

ሰው አላሳቡ ፡ የሰው በቅሉ መሳቡ ።

ሰው አላገሩ ፡ ምነው መኖሩ ።

ሰው አላገር ፡ መሬት አለዘር ።

ሰው አትመኑ ፡ አብዷል ዘመኑ ።

ሰው አየ ፡ እግዜር አየ ።

ሰው አይወድም በደል ፡ ከብት አይወድም ገደል ።

ሰው እሚበላ ቡዳ ፡ እጉድጓድ ሆኖ ይጠብቃል ።

ሰው እንደቤቱ እንጂ ፡ እንደ ጎረቤቱ አይበላም ።

ሰው እንዳቅሙ ፡ እህል እንደ ቀርሙ ።

ሰው እንዳነጋገሩ ፡ በቅሉ እንዳስጋገሩ ።

ሰው እንግዳ ቢሆን ፡ እግዜር ባላገር ነው ።

ሰው ከመለመን ፡ አምላክን ማመን ።

ሰው ከመከረው ፡ መከራ የመከረው ።

ሰው ከሞተ የለ ንስሃ ፡ ከፈሰሰ አይታፈስ ውሃ ።

ሰው ከራበው የሰይፉን ሰገባ ይበላል ።

ሰው ከተከተተ ፡ ጅብ ካኮተኮተ

ሰው ከቆየ መዛመድ ፡ አህያን በገመድ ።

ሰው ከኖረ ከሚስቱ ይወልዳል ።

ሰው ካለህል ፡ ምን ያህል ።

ሰው ካለቤቱ ፣ ልፋት በከንቱ ።

ሰው ካላማ ፣ ጀንበር አይጠልቅም ።

ሰው ካልሞተና ካልሄደ አይመሰገንም ።

ሰው ወጣኒ ፣ እግዜር ፈፃሚ ።

ሰው የተጠጋ ፣ ሰው ወጋ ።

ሰው ያለበት አገር ፣ ሰው የሌለበት ዱር ።

ሰው ያለቤቱ ፣ ያንሳል ጉልበቱ ።

ሰው ያመነ ፣ ውሃ የዘገነ ።

ሰው ያስገድላል አባይ ፣ ውሃ ያስጮሃል ድንጋይ ።

ሰው ይለፋል ፣ እድል ይሰራል ።

ሰው ይውደድህ ፣ ድንጋይ ይጫንህ ።

ሰው ይጨርሳል እንጂ ሃሳብ አያልቅም ።

ሰው ይጨነቃል ፣ እግዜር ያውቃል ።

ሰው ጠባቂና ፆም ገዳፊ አንድ ነው ።

ሰውነቱን ቢንቁ ፣ ልብሱን ይጠይቁ ።

ሰውና አመሉ ሳይተዋወቁ ይኖራሉ ።

ሰውን ሰው አማው ፣ የራሱን ባይሰማው ።

ሰውን ሰው የሚያደርገው ፣ የራሱ ምግባር ነው ።

ሰውን እጎዳ ባይ ፣ አመድ ተንከባላይ ።

ሰውን ካልናቁ ፣ አጥሩን አይነቀንቁ ።

ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው ።

ሰውዬው ውሃ ሲወስደው ፣ እኔም ወደ ቆላ ወርዳለሁ ብዬ ነበር አለ ።

ሰይጣን ለወዳጁ ድርብ ነው ።

ሰይጣን ቢያረምም ባህታዊ ይመስላል ።

ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ፥ ዶሮህን ለቆቅ ለውጥ ።

ሰዶ ከማሳደድ የያዙትን ማጥበቅ ።

ሰጥቶ በእጅ ፥ መለመን ከሰው ደጅ ።

ሱሪ በአንገት አውልቁ ።

ሲሉ ሰምታ ፥ ዶሮ ሞተች ከጢስ ገብታ ።

ሲል ነበር ፥ ደግሞ ከወግ ይጨመር ።

ሲመሽ ወደ ቤቱ ፥ ሳረጅ ወደርስቱ ።

ሲመትሩለት ይነጭ ።

ሲመች ያማት ተስካር ይወጣል ፥ ሳይመች ያባት ይቀራል ።

ሲመክሩት ለማይሰማ ፥ ሲያበሉት ለሚከሳ ፤ ለዚያም ምክር ፥ ለዚያም እህል ንሳ ።

ሲመክሩት አይመከር ፥ በደም ይነከር ።

ሲመክሩት ያጠፋል ልጅ ፥ ሲያጥቡት ያድፋል እጅ ።

ሲመክሩት ይረሳል ፥ ሲከድኑት ይፈሳል ።

ሲምር ፥ ያስተምር ።

ሲሞላ ይፈሳል ፥ ሲከር ይበጠሳል ።

ሲሞቱ ቢያይ ያንቀላፋል ።

ሲሞቱ ገመድ ፥ ሲገዙ ዘመድ አይታጣም

ሲርበኝ ታነቅሁ ፥ ሲጨንቀኝ ታረቅሁ ።

ሲሮጡ የታጠቁት ፥ ሲሮጡ ይፈታል ።

ሲሮጥ የመጣ እህያን አጥብቀህ ጫነው ።

ሲሰሩ ሎሌ መስሎ ፣ ሲበሉ ጌታ መስሎ ።

ሲሰርቅ ያየሁትን ፣ ቢሰጠኝ አላምነውም ።

ሲሰበር ይሰንጠር ፣ ሲረዝም ይጠር ።

ሲሳይ በርምጃ ይገባል ፣ በሩጫ ይወጣል ።

ሲሳይ ያለቀበት አንበጣ ፣ ከድንጋይ ላይ ያርፋል ።

ሲስሟት ቀርቶ ፣ ሲስቧት ።

ሲሻሩ ከሳሽ ፣ ሲሞቱ ወራሽ አይታጣም ።

ሲሻኝ ፣ ጢስ ወጋኝ ።

ሲቀላወጡ አይን አፍጦ ፣ ሲቆፍሩ አንፈራጦ ።

ሲበሉ መደንደን ፣ ሲያጡ መቅጠን ።

ሲበሉ የላኩት ።

ሲበሉ የላኩት ፣ ሲናገር ያሳስታል ።

ሲበዛ ማር ይመራል ።

ሲበዛ ይገነፍላል ።

ሲበደሉ ማሩኝታ ፣ ቢበድሉ ይቅርታ ።

ሲታጠቡ ከክንድ ፣ ሲታረቁ ከሆድ ።

ሲናገሩት ያልሰማ ፣ ሲመቱት ያልደማ ።

ሲኖሩ ለጠቅ ፣ ሲሄዱ መንጠቅ ።

ሲወለድ ያጠለቀው ፣ ሲሞት አወለቀው ።

ሲወልዱ አየሁ ብላ በጠጧን ማለች ።

ሲወርዱ ፣ ይዋረዱ ።

ሲወጣ ባቱን ፣ ሲገባ ደረቱን ።

ሲዋጥ በመረቅ ።

ሲዞሩ በመኖር ዕድቅ ፣ ሲሙኙ በመኖር ወርቅ አይገኝም

ሲዞር ውሎ ፣ እራቱ ጥሬ ።

ሲያልቅ አያምር ።

ሲያምረኝ ፣ ይቅርብኝ ።

ሲያምኑት የከዳ ፣ አለበት እዳ ።

ሲያረጁ ፣ አንባር ይዋጁ ።

ሲያብል የተኛ ፣ ሲጠሩት አይሰማም ።

ሲያወላውል ፣ ቀረ ባጉል ።

ሲያውቁ በድፍረት ፣ ሳያውቁ በስህተት ።

ሲያውቅ የተኛ ፣ ሲጠሩት አይሰማም ።

ሲያውቅ ያሟገት ዳኛ ።

ሲያውቅ ያጠፋ ሰይጣን ።

ሲያዩት የማያምር ፣ ሲበሉት ያቅር ።

ሲያይ የገባን ፣ ሲሰማ ቅበረው ።

ሲያድጡት ይጥላል ።

ሲያዝሉት ይነክስ ፣ ሲያወርዱት ያለቅስ ።

ሲያጌጡ ፣ ይመላለጡ ።

ሲያጎርሱት የማያጎርስ ከቀማኛ አንድ ነው ።

ሲያጡ እጅ ላፍ ይጠናል ።

ሲገዙ ፣ ይገዙ ።

ሲጠላ ፣ ይጠና ።

ሲጠሩት አቤት ፣ ሲልኩት ወዴት ።

ሲጠሩት የቀረ ፣ ለምኖ ይሄዳል ።

ሲጠባ ያደገ ጥጃ ፣ ቢይዙት ያጓራል ።

ሲፈሩ አይከሱ ፣ በጉጣ አያርሱ ።

ሳለቅስ ሳነባ ፣ ስውል ሳሰማ ፣ የሰጠህኝ ሸማ ፣ ከደጅህ ተቀማ ።

ሳላውቀው እኔ ፣ ስንት ያመጣ ሰኔ ።

ሳል ያለበት ኀልማሳ ፣ ዘንጋዳ ያለበት ዳጉሳ አይጠቅምም ።

ሳል ይዞ ስርቆት ፣ ቂም ይዞ ፀሎት ።

ሳማና አለብላቢት ፣ ውሽማና ሚስት ።

ሳር ማጨድ በማጭድ ፣ ቤት መምረግ በጭቃ በጭድ ።

ሳር ይሸከሟል ለበሬ ፣ ቆንጆ ያገቧል ለወሬ ።

ሳቃዳው ፈሰሰ ።

ሳቢውን ግረፈው ።

ሳብል ብስቀው ፣ የምር መሰለው ።

ሳታት በግርግርታ ፣ ዳዊት በቀስታ ።

ሳታድፊ ፣ አጉራፊ ።

ሳትታመም ተፈወስ ፣ ሳትረክስ ተቀደስ ።

ሳትዋጋ ንገስ ቢሉት ፣ ግድ ተዋግቼ አለ ።

ሳንባ ለድመት ፣ ገለባ ለከብት ።

ሳንባ ፣ ፍየል ሳሰባ ።

ሳያረዱ ፣ አይሰደዱ ።

ሳያርሱ ግርድ ፣ አለዳኛ ፍርድ ።

ሳያስረግጡ ወሬ ፤ ሳይገሉ ጎፈሬ ።

ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ያድራል ።

ሳያሸረው የበላ ኮሰኛ ፤ ሳይፈርድ የበላ ዳኛ ።

ሳያውቅ የተረተ ፤ ሳይዘራ ያመረተ ።

ሳያድጉ ማደግ ፤ ያዳግማል ።

ሳያገቡ ማርገዝ ፤ ሳያረጁ መፍዘዝ ።

ሳይሆን ለጉም ፤ ሳይሰበር ጠግን ።

ሳይለማ በደለማ ፤ ሳይቃጠል በቅጠል ።

ሳይለግሙ ፤ ያግሙ ።

ሳይማሩ መተርጎም ፤ ሳይበጡ ማገም ።

ሳይማሩ ማንበብ ፤ ሳይበሉ መጥገብ ።

ሳይረቱ አይሞቱ ፤ አለዳኛ አይሟገቱ ።

ሳይረቱ ፤ አይበረቱ ።

ሳይርቅ በቅርቡ ፤ ሳይደርቅ በርጥቡ ።

ሳይርበው የሚበላ ፤ ረሃብን አያውቅም ።

ሳይሰሙ ማውራት ፤ መዋረድ አለበት ።

ሳይሰሩ ማግኘት ፤ ሳይፀድቁ ገነት አይገኝም ።

ሳይቀሱ መምሬ ፤ ሳይጠምዱ ገበሬ ።

ሳይቃጠል ፤ በቅጠል ።

ሳይቆጥር የሰጠ ፤ ሰጭውም ሌባ ፤ ተቀባዩም ሌባ ።

ሳይቆጥር ያኖረ ሌባ ፤ ሳይቆጥር የተቀበለም ሌባ ።

ሳይበሉ ማግሳት ፤ ልክበር ብሎ መጓጓት ።

ሳይባርክ ያርዳል ፤ ሳይታየው ይፈርዳል ።

ሳይተርፋት አበደረች ፤ ሳትቀበል ሞተች ።

ሳይታለም የተፈታ ።

ሳይታደሉ አይገዙ ፤ ሳያልቡ አይወዙ ።

ሳይታገል ጣይ ፤ ሳይወጋ ገዳይ ።

ሳይታፈሩ መገላገል ፤ እብድ ያሰኛል ።

ሳይቸግር ፤ ጤፍ ብድር ።

ሳይነገር ይፈርዱታል ፤ ሳይፃፍ ያነቡታል ።

ሳይከካ ፤ ተቦካ ።

ሳይውሉ ያዋዋሉ ፤ ይሰብሩ ላይጠግኑ ።

ሳይውል ሳያድር ፤ የሰው ልጅ ብድር ።

ሳይዘሩ ማጨድ ፤ ሳይራመዱ መሄድ ።

ሳይደወል ቅዱስ ።

ሳይገድሉ ጎፈሬ ፤ ሳያረጋግጡ ወሬ ።

ሳይጠሩት አቤት ፤ ሳይልኩት ወዴት ።

ሳይጠሩት አቤት ባይ ፤ ሳይሰጡት ተቀባይ ።

ሳይጠሩት የመሰከረ ፤ ሳይጠጣ የሰከረ ።

ሳይጠሩት የመጣ ፤ ሳይጠግብ የወጣ ።

ሳይጠሩት ይመጣል ፤ ሳይዘሩት ይበቅላል ።

ሳይጠይቁ አያውቁ ።

ሳይጠጡ መስከር ፤ ሳይሞቱ መቃብር ።

ሳይጣሉት የተጣላ ፤ ሲርብ ያበላ (አይረሳም)

ሳይያሙ ይፀድቃሉ ፤ ሳይታመሙ ይጠየቃሉ ።

ሳይፈታ ሚስቱን ፤ ሳይረታ ከብቱን ።

ሴት ለቤት ፤ ወፍጮ ለዱቄት ።

ሴት ማገዶ ቢቸግራት ፤ ምሰሶ ትነቅላለች ።

ሴት በማጀት ፤ ወንድ በችሎት ።

ሴት በቋጻስ ፤ ኳደሬ በንጉስ ።

ሴት ታውቅ ፤ በወንድ ያልቅ ።

ሴት አማት የመረዘው ፤ ኮሶ ያንዘዘው ።

ሴት ከበዛ ፤ ጎመን ጠነዛ ።

ሴት ከወንድ ፤ እህል ከሆድ ።

ሴት ከጠላች ፤ በቅሎ ከበላች ፤ አመል አወጣች ።

ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም ።

ሴት ካልዋሸች ፤ ባልዋን ትወልዳለች ።

ሴት የላከው ሞት አይፈራም ።

ሴት የወደደ ፤ ገሃነም እሳት ወረደ ።

ሴት ያመነ ፤ ጉም የዘገነ ።

ሴት ያወጣው ጠብ አይበርድም ።

ሴት ይወዷል ፤ ማጀት ያንጎዳጉዷል ።

ሴት ጅብ ትፈራለች ፤ አጥር ትመዛለች ።

ሴትና ቄስ ፤ ቀስ ።

ሴትና ቤት አይታመንም ።

ሴትና አህያ በዱላ ።

ሴትና ዶሮ ሳያብድ አይውልም ።

ሴትና ዶሮ ዱር ሲሄዱ ፣ ቤታቸውን ይከዱ ።

ሴትና ፈረስ ፣ እንደ ኩሬ ውሃ እያደር ማነስ ።

ሴትና ፈረስ ፣ የሰጡትን ይቀምስ ።

ስለ ላቂ ፣ ውል አያውቂ ።

ስለ ከሰሱ ፣ አይፈወሱ ።

ስለ ጨሰ አይነድም ፣ ስለ ዳመነ አይዘንብም ።

ስለ ፍቅር ፣ በስመ አብ ይቅር አለ ሰይጣን ።

ስለት ይቆርጣል ፣ ምላስ ያስቀጣል ።

ስለት ድጉሱን ፣ ደባ ራሱን ።

ስልህ እንዳልልህ ፣ አላገኘሁ ።

ስልቻ ፣ ለስጋ መከተቻ ።

ስልቻ አሳሪ ፣ እርቦ ሰፋሪ ።

ስልቻና አቂማዳ ፣ ቆራጣና ጎማዳ ።

ስልጡን እንግዳ ፣ ይውላል ከጓዳ ።

ስመሰክርልህ ስመሰክርልህ ዋልኩ ቢለው ፣ ስታዘብህ ስታዘብህ ዋልኩ አለው ።

ስሙ ለባለቤት ፣ ቤተሰብ ናኘበት ።

ስሙን ለሰው አወረሰው ።

ስሙን ጠርቶ ፣ ራሱን ቆርቶ ።

ስም እኩል ፣ ስራው ስንኩል ።

ስም ከመቃብር ላይ ፣ ልብስ ያምራል በሰው ላይ ።

ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ።

ስም ይወጣ ከቤት ፤ ይከተላል ጎረቤት ።

ስምንተኛ ሺ ፤ ሰው አበላሺ ።

ስሩን የጠላ ፤ ራሱን የጠላ ።

ስራ ለሰሪው ፤ እሾህ ላጣሪው ።

ስራ ለሰሪው ፤ ወሬ ላውሪው ።

ስራ ከመፍታት ፤ ልጅን ላፋታት ።

ስራ ያጣ ለማኝ ፤ አፍሶ ይለቅማል ።

ስራ ያጣ መነኩሴ ፤ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል ።

ስራ ያጣ ፤ ሚስት ያወጣ ።

ስራ ያጣ ገበሬ በሰኔ ይሞታል ።

ስራ ያጣ ገንፎ ያላምጣል ።

ስራ ያጣ ጢስ ይሞቃል ።

ስሱ ሲበላ ይታነቃል ፤ ሃሰተኛ ባነጋገሩ ይታወቃል ።

ስሱ አንድ ያንቀው ፤ አንድ ይወድቀው ።

ስበላ ቢመሽብኝ ፤ ጭንቅር ይበልብኝ ።

ስብ ያርዱ ፤ ጉፋያ ይነዱ ።

ስታበይው ፤ በልተሽ ታይው ።

ስታበጀው ውላ ፤ ባተላ ።

ስታቦካ ውላ ፤ ባተላ ።

ስትግደረደሪ ፤ ጦምሽን እንዳታድሪ ።

ስንቁን የተቀማ ነጋዴ ፤ ዋግ የመታው ስንዴ ።

ስንቃችን ፣ በልባችን አለ አሞራ ።

ስንቅ ያለው ጦም አያድርም ፣ ዋስ ያለው አይታሰርም ።

ስንቅህን ባህያ ፣ አመልህን በጉያ ።

ስንቅና ማህሌት እንደ ያዥው ነው ።

ስንቅና አባይ እያደር ይቀላል ።

ስንዝርና ጋት ፣ አባትና እናት ።

ስንዴ ምን አልኩ ዘመዴ ፣ ምስር እስኪ ቀስር ፣ አተር እስኪ ተርትር ፣ ባቄላ አንተም እንደሌላ ።

ስንዴ ራቱ ፣ ወይራ እሳቱ ፣ ማለፊያ ሚስቱ ፣ ለምን ሰርግ ይሄዳል ፣ ሰርግ አለ በቤቱ።

ስንዴ በጭንቅ ፣ ባለጌ በጥብቅ ።

ስንፍ የዶባ ፣ ላም የጋለሞታ ።

ስደቡኝ ባይ እመንገድ ላይ ያራል ።

ስደተኛ ሲሰነብት ፣ ይሆናል ባላባት ።

ስደት ለወሬ ያመቻል ።

ስደት ከጨዋ ልጅ ፣ መንገድ ካገር ልጅ ።

ስድብ በልጅ ያምራል ።

ስድብሽና ስድቤ እኩል ነው ፣ ትርፉ ሰው መስማቱ ነው ።

ስጋ ለጥጋብ ፣ አጥንት ለትካዜ ።

ስጋ ሰጥተው ቢላዋ ነሱ ።

ስጋ ቀረ ፣ እዳ ቀረ ።

ስጋ ቀርቦለት አይኑ ወደ ፈረስ ።

ስጋ ቁጠር ቢሉት ፣ ጣፊያ አንድ አለ ።

ስጋ ከመሬት ወድቆ አፈር ሳይዝ አይነሳም ።

ስጋ ከስጋ ነው ።

ስጋ ያንገፈገፈው ፣ ቀይ በሬ ሲያይ ይሸሻል ።

ስጋው ያሳማ ፣ ከበላው የሰማው ገማ ።

ስጋዬን ላራዊት ፣ ነፍሴን ለገነት ።

ስጡኝ አለማለት ፣ ከወዳጅ መስንበት ።

ሶስቱን ቢጠጣቸው ፣ ሁለቱን ጣላቸው ።

ሶስት ጊዜ ለካ ፣ አንድ ጊዜ ቅደድ ።

ሶስት ጊዜ እንዴት አደራችሁ ፣ አንዱ ለነገር ነው ።

## - ሸ -

ሸማ ለብሶ ስልቻ ፣ በቅሎ ጭኖ ለብቻ ።

ሸማ ማዋስ ለባላገር ፣ በቅሎ ማዋስ ለወታደር ።

ሸማ በውሃ ፣ ሰው በንስሃ ።

ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል ።

ሸማኔ በመኑ ፣ ጠይብ በከሰሉ ።

ሸማኔ በድሩ ፣ ጠይብ በመንደሩ ።

ሸማን ጠምዞ ያሰጧል ፣ እህልን አላምጦ ይበሏል ።

ሸምበቆ በመርዘሙ አይሆንም ምሰሶ ።

ሸርሙጣ ስታረጅ ፣ አቃጣሪ ትሆናለች ።

ሸርሙጣን የወደደ ፣ ልብሱን ጥሎ አበደ ።

ሸኝ ቤት አይገባም ።

ሹመት ሲገኝ ዘመድ አይገድም ።

ሹመት ፣ ሺህ ሞት ።

ሹመት በተርታ ፣ ሰጋ በገበታ ።

ሹመትና ቁመት ከልክ አያልፍም ።

ሹም ለመነ ፣ አዘዘ ።

ሹም ለሹም ያወርሳል ፣ ጉም ተራራ ያለብሳል ።

ሹም መክሰስ ፣ ወጅድ ማረስ አይችግርም ።

ሹም ሲቆጣ ማር ይዞ እደጁ ፣ ደስ ሲለው ማር ይዞ እደጁ ።

ሹም ቢሞት ቀባሪው ሃምሳ ፣ የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ሃም ሳ ።

ሹምና ማር እያደር ይከብዳል ።

ሹምና የጋማ ከብት ፣ በጊዜ ይከተት ።

ሹምና ጥጥ እያደር ይከብዳል ።

ሺ በመከረ ፣ አንድ በወረወረ ።

ሺ ዝንብ መሶብ አይከፍትም ።

ሺህ ቢታለብ ፣ ያው በገሌ አለች ድመት ።

ሺህ ያጭሽ ፣ አንድ ያገባሽ ።

ሽያጭ ገዥ ሆኖ ይገምታል ።

ሻው ል ሲሞት ፣ ሺህ ይሙት ።

ሽል እንደሆን ይገፋል ፣ ቂጣም እንደሆን ይጠፋል ።

ሽመልና ዘንግ ፣ ቂልና በግ ።

ሽማግሌ ሳለ ምክር አይጠፋም ፣ ጎልማሳ ሳለ ሳም አይነዳም ።

ሽማግሌ ካለበት ፣ ነገር አይናቅበት ።

ሽማግሌ ካልሞተ ፣ ስንዴ ካልመረተ ።

ሽማግሌ ይገላግላል ፣ የተጠቃ አቤት ይላል ።

ሽማግሌና ስልቻ ሳይሞሉ አይቆሙም ።

ሽማግሌና ጅብ በላላበት ይገባል ።

ሽማግሌን ከምክር ከመለየት ፣ ከምግብ መለየት ።

ሽበት እኖር ብዬ መጥቻለሁ አለ ።

ሽታና ግማት ፣ ሳልሰማ ማውራት ።

ሽንብራ ፣ መኖር በመከራ ።

ሽንኩርት አንድም በሉት ገማ ፣ ደገሙትም ገማ ።

ሽንኩርት የባህሪውን ይሸታል ።

ሾላ በድፍን ።

ሾተልን ወደ አፎት ፣ ቁጣን ወደ ትእግስት ።

## - ቀ -

ቀለም ሲበጠበጥ ፣ ብርእ ቅረፁልኝ ።

ቀሊል አማት ፣ ሲሶ በትር አላት ።

ቀላጅ ፣ የሰይጣን ወዳጅ ።

ቀልብ የሌለው ውሻ ፣ ጠዲቅ አምጡልኝ ይላል ።

ቀሙን ላይቀር ከነጫማቸው ።

ቀማኛና ሽፍታ ፣ ጭለማና ማታ ።

ቀርቀሬ ወርጂ ማር ስልስ ማር ልከፍል ።

ቀስ ፣ እንዳይደፈርስ ።

ቀስ ፣ እንዳይፈስ ።

ቀበሮ የበሬ ቆለጥ ይወድቅልኛል ብላ ስትከተል ዋለች ።

ቀበቶ ለማፈኛ ፣ ሰንሰለት ለማቆራኛ ።

ቀበኛ ማሰሪያውን በልቶ ያሳጥራል ።

ቀበኛ ከብት ፣ ዋጋውን ያደርስ ።

ቀባሪ ፣ በፈጣሪ ።

ቀብረው ሲመለሱ እግዜር ይማርዎ ።

ቀን ሰው መስሎ ፣ ማታ ጅራት አብቅሎ ።

ቀን ሲደርስ ፣ አምባ ይፈርስ ።

ቀን በበቅሎ ፣ ማታ በቆሎ ።

ቀን ቢረዝም ፣ ልብ ያደክም ።

ቀን ቢቆጥሩ ፣ ውሻ ቢጠሩ ፣ ደረሰ በግሩ ።

ቀን እስኪወጣ ያባቴ ገበሬ ያግባኝ ።

ቀን እንደ ተራዳ ፣ ሌት እንደ ግድግዳ ።

ቀን ከሀዝብ ፣ ሌት ከጅብ ።

ቀን ከጣለው ፣ ሁሉ ይጥለው ።

ቀን ካለቀሙ ፣ ሌት አይቅሙ ።

ቀን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል ።

ቀን የጎደለበት ጠገራ አይጥ ይበላዋል ።

ቀንና ጨርቅ ፣ እንደምንም ያልቅ ።

ቀንና ጨርቅ ያልቃል ፣ ብልህ ያውቃል ።

ቀንበር ታርቆ ፣ ጣውንት ታርቆ ምን ይሆናል ።

ቀንዱ ሰማይ ጠቀስ ፣ ጭራው ምድር አበስ ።

ቀንድ ካላት ላም ጎዳ ትከፋለች ።

ቀንድ ገብቶ ጅራት አይቀርም ።

ቀይ መላሱ ፣ ጥቁር እራሱ ።

ቀድሞ ሰኞን አለመሆን ነው ።

ቀጥኜ ቢያዩኝ ፣ ጅማት ለመኑኝ ።

ቁልቢጥ የላት ፣ ቁና አማራት ።

ቁመህ ተከራከር ፣ ዙረህ ተመሳከር ።

ቁም እንዳላማ ፣ ቁርጥ እንደ ጫማ ።

ቁምነገረኛ መምሰል ፣ የተለመደ አመል ።

ቁራ ሲነጣ ፣ አህያ ቀንድ ያወጣ ።

ቁራ ፣ ስሙን ይጠራ ።

ቁርበት ምን ያንጓጓሃል ? ቢሉት ፣ ባያድለኝ ነው እንጂ ፣ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ አለ ።

ቁና ለመስፈሪያ ፣ ብርብራ ለማስከሪያ ።

ቁንጫ መሄድ ሳትማር መዝለል ትማራለች ።

ቁንጫ ሞኝ ናት ፤ ቀን ትበራለች ፤ ተለቃቅማ ታልቃለች ።

ቁጥቋጦም ሲያድግ ዛፍ ይሆናል ።

ቁጭትና መረቅ ለጊዜው ይጣፍጣል ።

ቂል ሲረግሙት ፣ የመረቁት ይመስለዋል ።

ቂል አይሙት ፣ እንዲያጫውት ።

ቂል ከጠገበበት አይወጣም ።

ቂል ያገኘው ፈሊጥ ፣ ውሻ የደፋው ሊጥ ።

ቂልን አንድ ጊዜ ስደበው ፣ ሲሰደብ ይኖራል ።

ቂም ይዞ ፀሎት ፣ ሞድ አዝሎ ወዘት ።

ቂምህን አትርሳ ፣ የወደቀን አንሳ ።

ቂጡ የቆሰለ ውሻ እንደልቡ አይጮህም ።

ቂጡን የተወጋ ውሻ እንደልቡ አይጮህም ።

ቂጥ ገልቦ ክንብንብ ።

ቂጥኛም ከወርዱ ይውላል ።

ቂፍ ቂፍ ያሰኘሽ እንደ ቋብ ዶሮ ፣ ለመከራ ላሳርሽ ኖሮ ።

ቃልህ ሳይዘጋ ፣ እግርህ ሳይዘረጋ ።

ቄሱም ዝም ፣ መፅሀፉም ዝም ።

ቄስ ለኑዛዜ ፣ ፍቅር ለሚዜ ።

ቄስ እበር ፣ አረመኔ ከማህበር ።

ቄስና ንብ እያዩ እሳት ይገባሉ ።

ቅል ባገሩ ድንጋይ ይሰብራል ።

ቅልና ድንጋይ ተማቶ ፣ ሎሌና ጌታ ተሟግቶ ።

ቅልወጥ አሳስቦ ይጥላል ዘመቻ ።

ቅመሙ የበዛበት ወጥ ፣ አይፋጅ አይኮመጥጥ ።

ቅማል በጥፍር ቢድጧት ፣ ራስ ደህና አለች ።

ቅማል ከአካላት ፣ ምስጢር ከቤት ።

ቅማል ውሃ ውረጂ ቢሏት ፣ ስንዳሰስ ለመቼ ልደርስ ፣ ቁንጫ ውሃ ውረጂ ቢሏት ፣ ስፈናጠር የሰው ዶሮ እሰብር አሉ ።

ቅምዝምዝ ወዲያ ፍየል ወዲህ

ቅርንጫፉ ፣ እንደ ዛፉ ።

ቅቤ መዛኝ ድርቅ ያወራል ።

ቅቤ ተነጥሮ ለመብላት ፣ ያባት የናት ።

ቅቤ ይፍሰስ ፣ ከገንፎ አይተርፍ ።

ቅናት ፣ ያደርሳል ከሞት ።

ቅናት ጥናት ፣ አይገኝም ከናት ካባት ።

ቅንቡርስ የት ትሄዳለህ ? መተማ ፤ ትደርሳለህ ? ልብማ ።

ቅንነት ፣ ለነፍስ መድሃኒት ።

ቆሎ ለዘር ፣ እንዶድ ለድግር አይሆንም ።

ቆሎን ቢቆረጥሙት እንጂ ቢያኙት አያልቅም ።

ቆማጣን ቆማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል ።

ቆዳ ሲወደድ ፣ በሬህን እረድ ።

ቋንጣና ባለሟል ሳያር አይቀርም ።

## - በ -

በሁለት በትር አይማቱ ፣ በሁለት ዳኛ አይሟገቱ ።

በሃምሌ ወጨፎ ፣ በሰኔ እርከፍከፎ ።

በሃምሌ ጤፍ ይዘሩ ፣ ቤት ይሰሩ ።

በሁዋላ የመጣ ፣ አይን አወጣ ።

በለምለም መላሴ ኮሸሽላ በላሁ አለች አህያ ።

በሉት አለቀ ፣ ፈጩት ደቀቀ ።

በላይ በላዩ ያጎርሳታል ፣ የበላችው ያገሳታል ።

በል በል ይላሉ ሲፈርዱ ፣ ጣል ጣል ይላሉ ሲያርዱ ።

በልብ አምኖ ፣ ባፍ መንኖ ።

በልተው ከጨረሱ ፣ ከመኻታ ይነሱ ።

በልቶ መጠጥ ያጣ ፣ ተበድሎ ፍርድ ያጣ ።

በልቶ የማይበርደው ፣ የሰው ነገር የማይከብደው አንድ ነው ።

በልቶ የከሳ ፣ የነገሩትን የረሳ ።

በልቼ እንደ እንሰሳ ፣ ተኝቼ እንደሬሳ ።

በልጅ አመካኝቶ ፣ ይበሏል አንጉቶ ።

በልጅነት ወደ ገዳም ፣ በርጅና ወደ አለም ።

በመልካም አንገት እንቅርት ።

በመረጡት ዳኛ ቢረቱ ፣ በቆረጡት በትር ቢመቱ ፣ በማን ያጉመተምቱ ?

በመሰለው ይናገራል ፣ ከበላው ይበላል ።

በመስከረም የሚያብድ ፣ በሰኔ ሱሪውን ከፍ ከፍ ያደርጋል ።

በመስከረም ጤዛ ፣ እንኳን አባቴ ጥጃ አልገዛ ።

በመሸታ የተገዛ ጦር ፣ ቢወረውሩት ከድፍድፍ ።

በመዘንከው ሚዛን ፣ በሰፈርከው ላዳን ።

በሙቅ ውሃ የታጠበ ፣ በሰው ገንዘብ የቸረ ።

በሚያዝያ ጎመን የዘራ ፣ ከረምቱን ሁሉ በላ ።

በማር ላይ ወተት ፣ ሲረባም ሲሰባም ።

በማር አጠገብ ፣ ውሃ ጥገብ ።

በማታየው ፣ እጅህን አታድርሰው ።

በማያድሩበት ቤት ፣ አያምሻሹበት ።

በምን የተነሳ ፣ ይህ ሁሉ ጠባሳ ።

በምንቸት ጠላ ታፈላ ፣ ከጎረቤት ትጣላ ።

በምድር መጠቅጠቅ ፣ በሰማይ መጠየቅ ።

በምድር አለም ፣ አለገንዘብ የለም ።

በምግባሩ ፣ አይታወቅ ማማሩ ።

በምጥ ባጣሽ ፣ በእንግዴ ልጅ አላጣሽ ።

በሞኝ ክንድ ፣ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበት ።

በሞኝ ክምር ፣ ዝንጀሮ ልጅዋን ትድር ።

በረጅም ጦር ባይወጉበት ፤ ያስፈራሩበት ።

በሬ ሆይ ፣ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ ።

በሬ ሲያረጅ ከጥጃ ጋር ይውላል ።

በሬ በመቶ ፣ ያውስ የት ተገኝቶ ፤ ምድር በዶሮ ፣ ያውስ ማን ገብሮ ።

በሬ በጭብጦ ተገዛ ቢለው ፣ ያላቦካ ከወዴት ያገኛል አለው

በሬ ተሾካሽኮ ቀንበር ፣ ገበሬ ተቻካችኮ ከድንበር ።

በሬ አርዶ በስለት ፣ ከብት አርብቶ በበረት ።

በሬ እንኳ ለወገኑ በፈርስ ያጓራል ።

በሬ ከኅለበተ ፣ አሽከር ከሰነበተ ።

በሬ ካራጁ ይውላል ።

በሬ ወደ አገሩ ይስባል ።

በሬ ያርሳል ፣ ምርቱን አህያ ያፍሳል ።

በሬና ሴት ፣ ካገርህ መሬት ።

በሬና በሬ መከሩ ፤ ቀንበር ሰበሩ ።

በርቄ ፤ እሞታለሁ ታንቄ ።

በርበሬ በገዛ እጅ ገብቶ ይፋጃል ።

በርበሬና ሚጥሚጣ ፤ ስጋና ቋንጣ ።

በርቦ ያበድራል ፤ በቁና ይከፈላል ።

በርኖስ ሳይገዙ ካባ ።

በርጥብ አያቃጥሉ ፤ በሰማንያ አይቀጥሉ ።

በሰለ እንብላ ፤ በለገ እንዝራ ።

በሰማንያ የተረታ ፤ መሃል አገዳውን የተመታ ።

በሰማንያ ያለቀ ፤ በፀሃይ የደረቀ ።

በሰማኸው ተማከር ፤ በሳልከው ተመተር ።

በሰማይ የለም ዱር ፤ በቂስ የለም ግብር ።

በሰማይ የለም ፀፀት ፤ ባባት የለም ቅጣት ።

በሰበቡ ፤ መምሬ ተሳቡ ።

በሰባት አመታቸው እንዳይማሩ ፤ ሰባ አመት ይደናቆሩ ።

በሰኔ ዘርን ይዘሩ ፤ ቤትን ይሰሩ ።

በሰንበት ላይ ደብረ ዘይት ፤ በስጋ ላይ አሞት ።

በሰው ምድር ፤ ልጅዋን ትድር ።

በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት ።

በሰው ቂጣ ፤ እጅዋን ትቃጣ ።

በሰው ቡሃቃ እሚጦ አይጋገርም ።

በሰው አገር ፤ አለመናገር ።

በሰው ፊት አያብሉ ፣ ሲታይ አይኮበልሉ ።

በሴት የበከረ ፣ ከእግዜር ተማከረ ።

በሴትና በውሃ የማይርስ የለም ።

በስርቆት ከመክበር ፣ ይሻላል ደሀይቶ መኖር ።

በስተእርጅና ፣ ድቁና ።

በሽማግሌ የታረቀ ፣ በፀሃይ የደረቀ ።

በሽምብራውም ትል አለበት ።

በሽተኛ ፣ ያድርቅህ መጋኛ ።

በሽታውን የደበቀ መድሃኒት የለውም ።

በሽታውን የደበቀ ሬሳው ይዘልቃል ።

በቀን ብዛት እንቁላል በእግሩ ይሄዳል ።

በቀኝ ቁሜ እንደ ክርስቶስ ፣ በግራ ቆመህ እንደ ዲያቢሎስ ።

በቁርበትም ያሰጣ ፣ በደላጎም ያሰጣ ፣ እኩል ቀን ወጣ ።

በቂል ክምር ፣ ዝንጀሮ ይማታበታል ።

በቃል ያለ ይረሳል ፣ በመፅሃፍ ያለ ይወረሳል ።

በቂስ ተናዘዝ ፣ በዘመድ ተገነዝ ።

በቂስ ተናዛዥ ፣ በመነኩሴ ገናዥ ።

በቅሎ ማሰሪያዋን በጠሰች ፣ በራስዋ አሳጠረች ።

በቅሎ ሳይገዙ ኮርቻ ።

በቅሎ ሽንቷን አጠራ ብላ ሃፍረቷን አሳየች ።

በቅሎ በኮርቻ ፣ ስንቅ በስልቻ ።

በቅሎ አባትህ ማን? ቢሉት ፣ ፈረስ አጎቴ አለ ።

በቅሎ እንደ ገሪው ፡ ህዝብ እንደመሪው ።

በቅሎ እንደሰገሩት ፡ እውር እንደመሩት ።

በቅሎ እንዳሰጋገሩ ፡ ሎሌ እንዳስተዳደሩ ።

በቅሎ ከሸጠ ፡ የሸመጠጠ ።

በቅሎ ያለ ኮርቻ ፡ ለማኝ ያለ ስልቻ ።

በቅሎ ግዙ ግዙ ፡ አንድ ጨው ላያግዙ ።

በቅሎ ጭኖ መጭ መጭ ፡ ሚስት አግብቶ ምሳዬን አምጭ ።

በቅጥ የኖረ በቅጥ ያገኛል ።

በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው ።

በቆረጡት ብትር ቢመቱ ፡ ባወጡት ዳኛ ቢረቱ ፤ የእግዜር ግቡ ከብቱ ።

በቆብ ላይ አብርጣም ፡ በመስቀል ላይ ውሾም ፡

በቆፈሩት ጉድጓድ ይገቡበታል ።

በበላህ ገብር ፡ በሰማህ መስክር ።

በበርበሬ የተገዛ ፈረስ መደቆሻ አይዘልም ።

በበሽታው የተጎዳ ፡ በጥንስሱ የተቀዳ ።

በበትሩ እማይማታ ፡ በዘመዱ እማይረታ ።

በበዛብህ ጊዜ የደነቀረ ፡ በበዛብህ አምላክ ሲል ይኖራል ።

በቡጋ ፡ እሞኝ ቤት ተንጋጋ ፤ በክረምት ፡ እቤትህ ተከተት ።

በቡሃ ላይ ቆረቆር ።

በቢላዋ ያርዷል ፡ በውል ይሟገቷል ።

በባዳ ቢቆጡ ፡ በጨለማ ቢያፈጡ ።

በቤተ ዘመድ ገናኝ ፡ በቄስ ተናዛዥ ።

በቤት ይለምዱታል ፤ በአደባባይ ይደግሙታል ።

በብርሃን ካለቀሙ ፤ በጨለማ አይቅሙ ።

በብዙ ከማረስ ፤ ከተቀላቢው ማሳነስ ።

በተለሙ ያርዷል ፤ በጀመሩ ይጨርሷል ።

በተለይ ንጻ ፤ በጠራ ቅጻ ።

በተረገዘ ባመት ፤ በተወለደ በለት ።

በተሳለ ያርዷል ፤ በታየ ይፈርዷል ።

በተሾመ ይከራከሩበታል ፤ በተሻረ ይመሰክሩበታል ።

በተተከለ ግንድ ፤ በተፈተለ ገመድ ።

በተናጋሪ ዘንድ ሰሚ ይደነቃል ።

በተወረሱበት ዘመናት ፤ አይረጠጡበት ።

በተጀመረው ነገር ፤ በተጣበቀው ማገር ።

በትር ለገና ፤ ነገር ለዋና ።

በትር ለገና ፤ ውሃ ለዋና ።

በትር ከጅህ ፤ እባብ ተማርህ ።

በትንሽ መን ገድ ፤ ንጉስም አይሄድ ።

በትንሽ ማረሻ ፤ ትልቅ እርሻ ።

በትንባሆ የገዙት ጦር ፤ ቢወረውሩት ጋያ ይወጋል ።

በትኩስ ስጋ ፤ በርጥብ ፍለጋ ።

በችኮላ ያፈቀሩት ፤ በችኮላ ተጣሉት ።

በናት ላይ ሞግዚት ፤ በራት ላይ ዳረጎት ።

በናትና በልጅ መካከል መርፌ ጠፋ ።

በጎብ ጊዜ ዝንብ ይነክሳል ።

በንጉስ ሞት አይዘበት ፣ በዝሆን ሃሞት አይፈተፈት ።

በንጉስ ሰው አይፈርድ ፣ በውሃ ላይ እሳት አይነድ ።

በንጹህ እቃ ላይ ዝንብ የምትቀምሰው አታገኝም ።

በአጤ ይሙቱ የተከተረ ፣ በስለት የተመተረ ።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ።

በእውር ይጠቃቀሱበታል ፣ በደንቆሮ ይንሾካሾኩበታል ።

በእውር ጎዳና ፣ ብርቅ ነው አንድ አይና ።

በእወ ቀቱ የጎለመሰ ፣ ብቻውን ነገሰ ።

በእድሜህ እወቅበት ፣ ሰርተህ ክበርበት ።

በከብቱ የለገሰ ፣ በፈረሱ የገሰገሰ ።

በካሳ የከበረ ፣ ባጓት የሰከረ ።

በካብ ላይ ብሰራ እባቡ መከራ ፣ በዛፍ ላይ ብሰራ አሞራው መከራ ፣ በምድር ብሰራ እረኛው መከራ ፣ የት ውዬ የት ልደር አድር ብዬ አለች ወፍ ።

በክረምት ፣ በርኖስከን አታውል እቤት ።

በወለዱ የከሰሰ ፣ በከብቱ የለገሰ ።

በወር ልቅ ፣ ባመት ቀሚስ ጥልቅ ።

በወተት ላይ ውሃ መጠጣት ፣ ያበዛዋል ያነጣዋል ።

በወንድሚ ግንባር ደም አልይበት ።

በዋስ ያለ ከብት ፣ በጣት ያለ ቀለበት ።

በዋጋ ፣ ከናትህ ልጅ ተዋጋ ።

በውሌ ፣ ደጃዝማች ነው ባሌ

በውል ከሄደች በቅሎዬ ፣ ያለ ውል የተበላች ቆሎዬ ።

በውርርድ ላይ ውርርድ ፣ ከነብር ላይ ስግርድ ።

በውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም ።

በውሽማ ሞት ፊት አይነጭም ።

በውሽማዋ ዳኘነት ባሏን ሁለት ጊዜ ረታችው ።

በውድ ሽጥልኝ ፣ በሃቅ መዝንልኝ ።

በዘር የላኩ በዝርዝር ፣ በጠዋት የላኩ በቀትር ።

በዘጠና ፣ የለም ጤና ።

በዚህም አዳርህ ፣ ግብር አለብህ ።

በዝሆን አፍ ቅርፊት ።

በዝሆን ጆሮ ትንኝ ።

በዝምታ ፣ ይገኛል ከበሬታ ።

በዝንጋታ ፣ ብዙ ጊዜ ይረታ ።

በየቤቱ ያለ ጥንስስ ጋን ይፈነቅላል ።

በየእለቱ ፣ ይወርዳል መአቱ ።

በየወንዙ ሃሌ ።

በያዘው ብትር አይመታ ፣ በወንድምና ባንቱ አይረታ ።

በደል ዋና አጥታ ትኖራለች ።

በደረቅ አበሳ ርጥብ ይነዳል ።

በደረቅ ይበላ ፣ በእርጥብ ይከላ ።

በደንባሬ በቅሎ ፣ ቃጭል ተጨምሮ ።

በደግነቱ ፣ ተቆረጠ አንገቱ ።

በዳቦ ላይ ሙልሙል ።

በድህነት ላይ ስንፍና ፥ በቂጥኝ ላይ ቁምጥና ።

በድሎ ማሩኝታ ፥ ተበድሎ ይቅርታ ።

በድንገት ፥ አህያ ገባ ከጅብ ቤት ።

በዶሮ ፊንጢጣ ፥ በሽንብራ ቂጣ ።

በጅ አግብቶ ቁንጣን ።

በጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ አንድ ነው ።

በጅ ያገኘሽ አያጣሽ ፥ ያጣሽ አያገኝሽ ።

በጅብ ሆዳምነት ፥ በእህል ጣፋጭነት ሳይተዋወቁ ይኖራሉ ።

በገቡበት ፥ አያወጡበት ።

በገና ጨዋታ ፥ አይቆጡም ጌታ ።

በገዛ ራሱ እባብ ጠመጠመ ።

በገዛ አረሟ ፥ እባብ ይዛ ታስፈራራ ።

በገዛ ዳቦዬ ልብልቡን አጣሁት ።

በጋለሞታ ቤት ፥ ሁሉ ይጣላበት ።

በግ ባልበላሽ ትበይኝ አለ ጅብ ።

በግ ከበረረ ፥ ሞኝ ካመረረ ።

በግ የሌለው ቀበሮን አውሬ አይላትም ።

በጎ አማጭን መጦር ፥ ክፉ አማጭን በጦር ።

በጎዶሎ ቀን የገዛሁት ጋሻ ሳያስገድለኝ አይቀርም አለ ፈሪ ።

በጠላ ላይ ውትት ፥ የግዜር ቸርነት ።

በጠረጠሩ ፥ ጠጠር ይጥሉ ።

በጠራ ተሻገር ፥ በተሳለ ምተር ።

በጠይቆ እውቀት ፥ ይገኛል ክብረት ።

በጠገበሁ ጠብ የለም ።

በጣም ሃብታም ፥ በጣም ድሃም ።

በጣይ ቅቤ አያበሩበትም ።

በጥቂት በጥቂት ፥ ይሞላል ልቃቂት ።

በጥባጭ ካለ ጥሩ ማን ይጠጣል ።

በጦም ቆሎ ፥ በዳገት በቅሎ ፤ ቆሎው ይከካል ፥ በቅሎውም ይነካል ።

በጨለማ እየሄዱ ጅብን ነገረኛ ያደርጋሉ ።

በጨዋታ ያልረታ ፥ ታጥቆ ያልመታ ፥ ይናደዳል ወደ ማታ ።

በጨው ደንደስ ፥ በርበሬ ተወደሰ ።

በጫማ የሚሄድና በቃሪያ የሚበላ ሰውን አይጠብቅም ።

በጭቃ የተመራ ፥ በቅቤ የተሰራ ።

በፈረስ የፈለጉት በእግር ይገኛል ።

በፊት እወቁኝ ፥ በሁዋላ ደብቁኝ ።

በፊት የደረሰን ወፍ ይበላዋል ፥ በፊት የተናገረውን ሰው ይጠላዋል ።

በፋሲካ የተቀጠረች ገረድ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስላታል ።

በፍርድ ከሄደች በቅሎዬ ፥ ያለፍርድ የተበላች ጭብጦዬ ።

ቡሉኮና ጋቢ ፥ አቢላምና አላቢ ።

ቡቃያ አይታጨድ ፥ አንበሳ አይጠመድ ።

ቡቃያው አንድ ማሳ ፥ አራሚው አምሳ ።

ቡናና ፍቅር በትኩሱ ነው ።

ቢርበኝ ሰረቅሁ ፤ ቢጨንቀኝ ታረቅሁ ።

ቢሰናከል መንገዱ ፤ ጣለኝ ከወንበዴ ።

ቢሰጡኝ እንዳ ፤ ቢነሱኝ እረዳ ።

ቢስ የቢስ ለት ፤ ከፉ የከፉ ለት ።

ቢቆጡት የማይፈራ ፤ ቢናገሩትም አይሰማ ።

ቢቆጡት ያልሰማ ፤ ቢመቱትም ያው ነው ።

ቢበላ ገት ፤ ቢኖር አመት ።

ቢበይኑለት ቀጠነኝ ፤ ቢፈርዱለት ይግባኝ ።

ቢተኙ ነገር ፤ ቢሄዱ አገር ፤ ቢቆፍሩ አፈር አይታጣም ።

ቢተኙ ነገር ያገኙ ፤ ቢነሱ ነገር ይረሱ ።

ቢነግሩሽ ትናገሪብኝ ፤ ቢያጥቡሽ ትሰክሪብኝ ።

ቢናገር የማያምር ፤ ቢቀመጥ አይከበር ።

ቢከማች ፤ እዳው ላንቺ ።

ቢከፍቱት ተልባ ።

ቢወዱኝ ብሎ ሞት ፤ ቢጠሉት ምን ሊመጣበት ።

ቢዋደዱ ጠም ገደፉ ፤ ቢጣሉ ተዋረፉ ።

ቢዘል ማጀት ፤ ቢወጋ ምንቸት ።

ቢያብዱም ቢሞቱም ፤ የአንዱን ነገር አያጫውቱም ።

ቢያብዱም ቢጨምቱም ፤ ያንዱን ነገር ላንዱ አያወጡም ።

ቢያንጋልሏት ጡት የላት ፤ ቢደፏት ቂጥ የላት ።

ቢያዝሉት ያለቅስ ፤ ቢስሙት ይነክስ ።

ቢያዩኝ እስቅ ፤ ባያዩኝ እሰርቅ ።

ቢጠረጥሩ ፣ ጠጠር ይጥሉ ።

ቢጠሩት ያልሰማ ቢጠቅሱት አያይም ።

ቢጠሩኝ አቤት ፣ ቢልኩኝ ወዴት ።

ቢጠናባት ጠናች ፣ የልጅዋን ባል ቀማች ።

ቢፈትጉት ይነጣል ፣ ቢመረምሩት ይወጣል ።

ቢፈጀኝ በማንካዬ ፣ ባይፈጀኝ በጄ ።

ባሀር ዛፍ ከተከሉት ይፀድቃል ፣ ገንዘብ ካላኖሩት ያልቃል ።

ባህያ ቆዳ የተሰራ ቤት ፣ ይበታተናል ጅብ የጮኸለት ።

ባለማ ፍረዱኝ ፣ ባጠፉ ስደዱኝ ።

ባለርስት የርስቱን ያህል ይከበራል ።

ባለቁርጥ አትደንግጥ ፣ ባለ አንቀልባ አታግጥ ።

ባለቤቱን እፊቱ ማመስገን ከማማት እኩል ነው ።

ባለቤቱን ካልናቁ ፣ አጥሩን አይነቀንቁ ።

ባለቤቱን ካልናቁ ፣ ውሻውን አይመቱ ።

ባለቤት ሲያፍር እንግዳ ይጋብዛል ።

ባለቤት የወደደው አሞሌ በሬ ይለውጣል ።

ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዳ አይቀበለውም ።

ባለቤት ያከበረው አህያ በቅሎ ይለወጣል ።

ባለነገር ከቤት ፣ ጠበቃ ከችሎት ።

ባለኩል ፣ ያሰናክል ።

ባለካባ ከባለካባ ፣ ባለዳባ ከባለዳባ

ባለጌ ማማቱን ፣ ቆዳ መንጓጓቱን አይተውም ።

ባለጌ ሲሞት ሬሳውን በሽመል ።

ባለጌ ሲቀመጥ ቂጡን ገልቦ ነው ።

ባለጌ ሲወዱት ፥ ከልጅ እኩል አድርጉኝ ይላል ።

ባለጌ ቁም ነገሩን ዒልት ያደርገዋል ።

ባለጌ አፉን እንጂ እግሩን አያድጠውም ።

ባለጌ ከበቅሎ የወጣ እንደሆን ፥ ከሰማይ የደረሰ ይመስለዋል ።

ባለጌ ካወራው ፥ የሰው ልጅ የገመተው ።

ባለጌ የተመከረለት ፥ ቁንጫ የተጠረገለት ይብሳል ።

ባለጌ ያለበት ሸንጎ ፥ ዝንብ ያለበት እርጎ ።

ባለጌ ጃሮ ከለበሰ ፥ አዋሽ ከደፈረሰ ።

ባለጌና ቆቅ በራሱ ያወራ ።

ባለጌን ካሳደገ ፥ የገደለ ፀደቀ ።

ባለጌን ገንዘቡ አያኮራውም ።

ባለጠጋ ሲቀናጣ ፥ የድሃ ልጅ ይሞታል ።

ባለጠጋ በከብቱ ፥ ድሃ በጉልበቱ ።

ባላዋቂ ቤት ፥ እንግዳ ናኘበት ።

ባላደራ ፥ ጩሀ በተራራ ።

ባላገር ሆደ ገር ፥ ከፉ አይናገር ።

ባላገር የሚበላው ቢያጣ ፥ የሚከፍለው አጥቶ አያውቅም ።

ባላጋራ ያለው ፥ እንቅልፍ የለው ።

ባልበላ ጭሬ አላፈሰም ወይ አለ ዶሮ ።

ባልነቃ ሰንጥቆ ፥ ባልዳመነ ባርቆ ።

ባልነበር ፡ ይሻል ነበር ።

ባልና ሚስት ካንድ ባህር ይቀዳል ።

ባልና ሚስት ፡ ፍትህና መንግስት ።

ባልንጀራህ ሲበልጥህ ፡ ቁንጣን ይምለጥህ ።

ባልንጀራህ ሲታማ ፡ የኔ ብለህ ስማ ።

ባልንጀራው ቢያጠቃው ወደ ሚስቱ ሮጠ ።

ባልንጀራዬ ሲበልጠኝ ፡ ቁንጣን ይፍለጠኝ ።

ባልወልድልሽ ፡ ታከትሁልሽ ።

ባልዋጁት ጣት ፡ የዘንዶ ጉድጓድ ይለካበት ።

ባልጋ የሚለያይ ፡ በፍቅር ይራራቃል ።

ባልፈሱበት ቂጥ ፡ አያፍሩበት ።

ባልፈጨሽ በኖብሽ ፡ ባልነበርሽ በርቆብሽ ።

ባመጣኸው ዳኛ ፡ ትሆን እስረኛ ።

ባምሌ በነሃሴ ፡ ቀረችልኝ ነፍሴ ።

ባሩዱ በከምሱር ይነሳል ፡ አንበሳ በዱር ያገሳል ።

ባስር ጣቱ ፡ በሰፌው ደረቱ ።

ባስተጋባ ፡ ከባህር ሄዶ ገባ ።

ባቄላ ሳይሰበር ፡ መነኩሴ ሳይቀበር ።

ባቄላ አለቀ ቢለው ፡ ፈስ ቀለለ ።

ባትዋጋ እንኳን ትሰለፍ ።

ባንዱ ታዘብ ፡ ባንዱ ተለዘብ ።

ባንድ ሁለት ፡ በጥሬ ዱቄት ።

ባንድ ራስ ፡ ሁለት መላስ ።

ባንድ እልጋ ፡ ሁለት አራስ ።

ባንድ አይን ጉድፍ ።

ባንድ አገራ ፡ ሁለት አውራ ።

ባንድ አፍ ተናጋሪ ፡ ባንድ በቅሎ ሰጋሪ ።

ባንድ ከፈጩ የለም እመቤት ።

ባንድ ዙፋን ሁለት ንጉስ ።

ባንድ ደብር ፡ ሁለት መምህር ።

ባእድ ስር የለወ ም ።

ባእድ ከሳመው ፡ ዘመድ የነከሰው ።

ባዋቂ ፊት መናገር ፡ መታገም ።

ባይሰጡት ፡ ፈግጡት ።

ባይብ እንጂ በቅቤ አያወፍሩም ።

ባይቸኩል እንቁላል ይሄዳል በግሩ ።

ባይኔ መጣህብኝ ።

ባይኔ አልቅሼ ፡ በጄ አብሼ ።

ባዳና ጨለማ አንድ ነው ።

ባድላዊ ያድላበት ፡ ባመጠኛ ሰይፍ ይዘዝበት ።

ባግባቡ ፡ በደጃፉ ይግቡ ።

ባኀረስኩ እጄን ተነከስኩ ።

ባጡፋ ወታደር ፡ ይከሳል ባላገር ።

ባፈሳ ይታፈሳል ፡ በነጠር ይመለሳል ።

ባሬ ማን በላበት አለ እርኩም ።

ባፍ ይጠፉ ፣ በለፈለፉ ።

ቤት ሰሪ በኋላ ይመጣል ።

ቤተክርስቲያን ለማላጅ ፣ ገበያ ላርፋጅ ።

ቤተ ክርስቲያን አቃጥል ቢሉት ፣ ደጀ ሰላም አቃጠለ ።

ቤተ ክርስቲያን የገባ ውሻ ።

ቤታቸውን እየከፈቱ ሰው ሌባ ይላሉ አለች ውሻ ።

ቤት ያለመወጫ ፣ ፊት ያለ አፍንጫ ፤ ያ መፈንጫ ፣ ያ ማጌጫ ።

ቤት ሲሰፋ ፣ የሰው ሁሉ ተስፋ ።

ቤት በማገር ፣ ንጉስ በባላገር ።

ቤት ቢሰፋ ፣ ደልሰ ተስፋ ።

ቤት አለ ክዳን ፣ ከምንም አያድን ።

ቤት ከነጉልላቱ ፣ ምድጃ ከነማዘንቱ ።

ቤት ዘግተው የደበደቡት ውሻ ባለቤቱን ይነክሳል ።

ቤት ያለ ሴት ፣ ክብት ያለበረት ።

ቤት ያለ ቁልፍ ፣ አልጋ ያለምንጣፍ ።

ቤት ያለ አጥር ፣ ሬሳ ያለ መቃብር ።

ቤት ያለ አጥር ፣ ሰው ያለ ልብስ ።

ቤትን መመስረት ፣ በባላገር እንጀት ።

ብላ ቢለኝ ፣ እንደ አባቱ በቆመጠኝ ።

ብልህ ያመቱን ፣ ሞኝ የለቱን ።

ብልህና ቅባት ፣ ብርሃንና መብራት ።

ብልህን ማሞኘት ፡ ቂምን ማቆየት ።

ብልጥ ለብልጥ ፤ አይን ብልጥጥ ።

ብልጥ ሰው ይታወቅበት አይመስለውም

ብልጥ አይን አስቀድሞ ያለቅሳል ።

ብልጥ አይጥ ከባለቤት እኩል ስትበላ ትኖራለች ።

ብሎ ብሎ ፡ የዶሮ አንገት ከማሰሮ ።

ብመታው ሰደበኝ ።

ብረት ለብረት ሲፋጭ ስለት ይወጣል ።

ብረት በብረት ይሰራል ፡ እውር በሰው ይመራል ።

ብረት ካልፈላ ፤ አይላላ ።

ብርሌ ከነቃ ፡ አይሆንም እቃ ።

ብርቅና ድንቅ ፡ ያለ አንድ ቀን አይደምቅ ።

ብርና ወርቅ ያምራሉ ፡ ግን ሰውን ያጣላሉ ።

ብርድ ቆላ ወረደ ፡ ልጅ አባቱን ወደደ ።

ብርድ ከማንቀጥቀጥ በቀር ምን ያመጣል ።

ብቅ ብቅ ፡ እንደ ስንዴ ምርቅ ።

ብቻኩል ያንቺንም የኔንም በላሁት ።

ብቻውን የሚሮጥ የሚቀድመው የለም ።

ብቻውን የሚሟገት የሚረታው የለም ።

ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል ።

ብነጨው ፊቴን ፡ ብመታው ደረቴን ።

ብንከባለል መንገዴ ፡ ጣለኝ ከወንበዴ ።

ብዙ ሃብት ፣ ያመጣል ብዙ ጠላት ።

ብዙ መሳም ፣ ልብ አይነካም ።

ብዙ ሰው ሊበላ ፣ አንድ ሰው ይጠላ ።

ብዙ ስንቅ የሚሸከም ሳይበላ ይወድቃል ።

ብዙ ቢተቹ ፣ ይሰለቹ ።

ብዙ ቢያወጉ ፣ ይዘነጉ ።

ብዙ ቧልት ፣ ያፈርሳል ንብረት ።

ብዙ እውር አየሁ ፣ እንዳንቺስ ፈረስ የለም ።

ብዙ ከብት ለማርባት ፣ አልቅትን ጠብቆ ውሃ ማጠጣት ።

ብዙዎች ለብዙ ሲያውቁ ፣ የራሳቸውን አይጠነቀቁ ።

ብጤ ከብጤው ።

ብጥለው ገለበጠኝ ።

ቧልትና ቅዘን ቤት ያጠፋል ።

ቧልተኛ ሰው አንቱ ሳይባል ያረጃል ።

## - ተ -

ተሁለት ዛፍ የወደቀ ።

ተሁሉም ያው ወንድም ፣ ቢከፋም ቢበጅም ።

ተለማማጭ ፣ አልማጭ ።

ተለማበት የተጋባበት ።

ተለጣጭ ፣ የጎረቤቷን ድልህ ሟጣጭ ።

ተላም የዋለ በሬ ፣ ተሴት የዋለ ገበሬ ።

ብዙ ሃብት ፣ ያመጣል ብዙ ጠላት ።

ብዙ መሳም ፣ ልብ አይነካም ።

ብዙ ሰው ሊበላ ፣ አንድ ሰው ይጠላ ።

ብዙ ስንቅ የሚሸከም ሳይበላ ይወድቃል ።

ብዙ ቢተቹ ፣ ይሰለቹ ።

ብዙ ቢያወጉ ፣ ይዘነጉ ።

ብዙ ቧልት ፣ ያፈርሳል ንብረት ።

ብዙ እውር አየሁ ፣ እንዳንቺስ ፈረስ የለም ።

ብዙ ከብት ለማርባት ፣ አልቅትን ጠብቆ ውሃ ማጠጣት ።

ብዙዎች ለብዙ ሲያውቁ ፣ የራሳቸውን አይጠነቀቁ ።

ብጤ ከብጤው ።

ብጥለው ገለበጠኝ ።

ቧልትና ቅዘን ቤት ያጠፋል ።

ቧልተኛ ሰው አንቱ ሳይባል ያረጃል ።

## - ተ -

ተሁለት ዛፍ የወደቀ ።

ተሁሉም ያው ወንድም ፣ ቢከፋም ቢበጅም ።

ተለማማጭ ፣ አልማጭ ።

ተለማበት የተጋባበት ።

ተለጣጭ ፣ የጎረቤቷን ድልህ ሚጣጭ ።

ተላም የዋለ በሬ ፣ ተሴት የዋለ ገበሬ ።

ተሌባ ሌባ ቢሰርቀው ፥ ምን ይደንቀው ።

ተልባ መስሎሽ ሰናፍጭ ትቀምሽ ።

ተልባ በጥባጭ ሳለች ፥ ጎመን ቀንጣሽን ምች መታት ።

ተልባ ቢንጫጫ ፥ በአንድ ሙቀጫ ።

ተመልከት አላማህን ፥ ተከተል አለቃህን ።

ተመልከኛ ዳኛ ፥ መልካም ፈራጅ ።

ተመመረመር ፥ ይገኛል ነገር ።

ተመረቅሁ ብለህ ተተረገመ ጋር አትዋል ።

ተመሮጥ ፥ ማንጋጠጥ ።

ተመንግስት አመልጣለሁ ፥ ከሞት እድናለሁ ማለት ዘበት ።

ተመከሮ ልብ ፥ ተሸምቶ ድልብ አይሆንም ።

ተመዋረድ ፥ ጌታን መውደድ ።

ተማሪ ፥ ውሻ ቀባሪ ።

ተማሪና ዶሮ በሞቱ ክብሩ ነው ፥ በቁመናው እራቱ ጥሬ ነው ።

ተማከሮ የፈሱት ፈስ አይገማም ።

ተምሮ የማይፅፍ ፥ አክፍሎ የማይገድፍ ።

ተምሮ ያላስተማረ ፥ ዘርቶ ያላጠረ ።

ተሞተች ሚስቴ ፥ ምን አለኝ ካማቴ ።

ተሚጋች እኔ እረታ ይመስለኛል ፥ ሰውም ይመለከተኛል ።

ተራስ በላይ ነፋስ ።

ተራጋሚ ፥ ራሱን ደርጋሚ ።

ተርጅናና ተሞት ፥ ቢሸሹ አያመልጡ ።

ተሰብሮ ቢጠገን ፣ እንደነበረ አይሆን ።

ተሰው አለሁ ብዬ ፣ ተጅብ ተዳብዬ ።

ተስግዳዳ ቦታ ፣ ታዳጊ ጌታ ።

ተሴትን ትብሱ ፣ ትመለሱ ።

ተስስታም አንድ ያንቀው ፣ አንድ ይወድቀው ።

ተስፋ መስጠት ፣ እዳ መግባት ።

ተሽፋፍኖ ቢቶኙ ፣ ገልጦ የሚወጋ ጌታ አለ ።

ተሹም ከመታለል ፣ ጥሎ መኮብለል ።

ተቀመጥ በወንበሬ ፣ ተናገር በከንፈሬ ።

ተቀማጭ ፣ አፉ ምላጭ ።

ተቀማጭ የሌለው ተሚጋች ፣ ስልቻ የሌለው ቢጋች ።

ተቀምጦ ከመላክ ተነስቶ መስራት ።

ተቀምጦ የሰቀሉት ቆሞ ለማውረድ ያስቸግራል ።

ተቀባሪ ወዲያ ማን ያርዳ ።

ተቁመቱ ማጠር ፣ የልቡ መጠጠር ።

ተቁም ዶሮ ፣ ከሽከላ ማሰሮ ።

ተቂል አትጫወት ፣ አይንህን ያወጣል በእንጨት ።

ተቅበላ ጥጋብ ፣ የስቅለት ጠም ማደር ይሻላል

ተቆብ ላይ ሚዶ ።

ተበድሮ ቅቤ ፣ ታርዞ ጎፈሬ ።

ተባለቀትር ፣ አትቀታተር ።

ተተሳለ የማይበርድ ፣ ተታዘለ የማይወርድ ።

ተተናገረ አያባራ አፋቸው ፤ ከያዘ አይለቅ ምንቾታቸው ።

ተተናገረ አያባራ አፋቸው ፤ ከያዘ አይለቅ እጃቸው ።

ተተያዙ ፤ ብዙ ነው መዘዙ ።

ተተያዙ ወዲያ ቂስ ጥሩልኝ ማለት ፤ ላያደላድሉ በሺ ብር ጭነት ።

ተታመሙ መክሳት ፤ ካጡ መንጣት ።

ተናት ቀን ይሻላል ።

ተናካሽ ውሻ ፤ የጅብ መቋደሻ ።

ተናዞ ይሞቷል ፤ አምኖ ይሟገቷል ።

ተናግሮ አናገረኝ ይወደኝ ይመስል ፤ ሄዶ ተናገረ የላኩት ይመስል ።

ተናግሮ ከማሰብ ፤ ተከንፈር መሰብሰብ ።

ተናግሮ ያጣ ሰው ፤ ሶስት ጊዜ ሞቱ ነው ።

ተንከትክተሽ ስትስቂ የጥርስሽ ወገብ እንዳይቀጭ ።

ተንኮለኛ መበለት ፤ በጦም ዶሮ በፋሲካ እልበት ።

ተንኮለኛ ፤ ተሰባብሮ ተኛ ።

ተንኮለኛ ገደል ፤ ዝንጀሮ ይጥላል ፤ በሬ ያሳልፋል ።

ተንጋሎ ቢተፉ ፤ ተመልሶ ባፉ ።

ተኛ ወዲያ ጎራሽ ፤ እህል አበላሽ ።

ተከበሩ ፤ ሰው አይፈሩ ።

ተከብሮ ፤ ያደርጋል ደንቆሮ ።

ተከብት እንስት ፤ ተሃብት ርስት ።

ተከፈት ያለው ጉሮሮ ጦም አያድርም ።

ተኩላ እንደ አንበሳ እጮሀ ብላ ተተረተረች ።

ተኩላ ፥ ፍየል በላ ።

ተክፉ ተወልጄ ስፈጭ አደርኩ ።

ተክፉ ጎረቤት ፥ አይሰሩም ደህና ቤት ።

ተኮሰ ጣለ ፥ ወጋ ነቀለ ።

ተወደዱ ወዲያ ገደሉ ሜዳ ።

ተወገብ በላይ ታቦት ፥ ከወገብ በታች ጣኦት ።

ተወገብ በላይ ጥጋብ ፥ ተወገብ በታች ራብ ።

ተወጭት አፍ ፥ የወንጭት አፋፍ ።

ተዋቅሶ ወዳጅነት ፥ የቂም ጠባሳ ባንገት ።

ተዋጊ በሬ ተጭድ ይጣላል ።

ተዋጊ በሬህን ፥ ተናካሽ ውሻህን ያዝ ።

ተው አትርሳ ፥ ተሰርቶልሃል የሳት ገሳ ።

ተው ፈረሴን ለጉም ፥ አይዘነጉም ለሴትና ለጉም ።

ተዝካር ያየ ተማሪ ፥ ሽቀጥ ያየ አጣሪ አይን የለውም ።

ተይዛ ትዘፍን ጠጣ ።

ተይዞ ከመለማመጥ ፥ አርፎ መቀመጥ ።

ተደርቦ መጣላት ፥ ሰራ ማጣት ።

ተደብቃ ትፀንሳለች ፥ ሰው ሰብስባ ትወልዳለች ።

ተድረው ቢመለሱ ፥ የውሃ መንገድ ረሱ ።

ተጀመሩ መጨረስ ፥ ካረገዱ ማልቀስ ።

ተጂ ፥ በጉንጩ ።

ተገዳዩ ሟቹ ይጣደፋል ።

ተጋበዙና ብሉ ፤ ሃይ በሉ ፡ ክልክሉ ።

ተጋፊ ውሃ ሽቅብ ይሄዳል ።

ተግደርዳሪ ፡ በለጠብ ሽሮ ተበዳሪ ።

ተግደርዳሪ ፡ ጦም አዳሪ ።

ተነሽ እበት ፡ ተንጨት ሽበት ።

ተጎንብሶ የሚበላን ፡ ተኝተህ ቀላውጠው ።

ተጠማኝ ቢሰነብት ፡ ባለርስት ይሆናል ።

ተጥዶ የማይፈላ ፡ ተሹሞ የማይበላ ።

ተጦረኛ ስንቅ አይደባልቁ ።

ተጠጣ የዋለ ጉሬዛ ፡ እህል ፈጅቶ ገባ ።

ተጨንቆ ኩራት ፡ ተንጠራርቶ ራት ።

ተጫውቶ መማረር ፡ አለ ጉዳይ መብረር ።

ተፈጣሪ ፡ ሙርጥ ጫሪ ።

ተፈጣሪ ፡ ይበልጣል ቂጥ ጫሪ ።

ተፈጥሮ ሞት ፡ ተሾሞ ሽረት ።

ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም ።

ታለቀ መቆጠብ ፡ ተሞተ መንጠብጠብ ።

ታላረፉ ፡ መከራ ነው ትርፉ ።

ታላወቀ ዘዴ ፡ በለው በጎራዴ ።

ታልተናገሩ ፡ አይከፈት በሩ ።

ታሞ የተነሳ ፡ እግዜርን ረሳ ።

ታረጁ ወዲያ ጎፈሬ ፡ አዝመራ የሳተው ገበሬ ።

ታርቄ ተመርቄ ፣ ታጥቤ ተለቃልቄ ።

ታርቆ ሙግት ፣ በልቶ ስስት ።

ታሳጭ ማራኪ ይሻላል ።

ታቀበት በረዶ ፣ ተቁልቁለት ዘንዶ ።

ታባ ቁፍር እሸት ተበልቶለት ።

ታባቱ የተረፈ ፣ ተጠለፈ ።

ታቡት ክፉ አፀደ መልካም ።

ታቦት በራሱ ፣ ቃጭል በጥርሱ ።

ታከረሩት ይበጠሳል ።

ታየው ትመለከተው ፣ ትታነቀው ትሞተው ።

ታዳጊ ያለው በግ ላቱን በውጭ ያሳድራል ።

ታጉል ጉልበት ፣ እዩልኝ ስሙልኝ ማለት ።

ታጉል ጥንቆላ ፣ የጨዋ ልጅ መላ ።

ታጥቦ ጭቃ ።

ትለብሰው የላት ፣ ትከናነበው አማራት ።

ትላንት ልጄን ፣ ዛሬ እናቴን ፣ ምን ይበጃል ዘንድሮ ፣ አለ አውራ ዶሮ ።

ትልቅ ብልሃት ፣ ለንጉስ መገዛት ።

ትልቅ ጥቃት ፣ ለምኖ ማጣት ።

ትልና መጋዝ ፣ በሽተኛና ጓዝ ።

ትምህርት በልጅነት ፣ አበባ በጥቅምት ።

ትምህርት ፣ የማያልቅ ምርት ።

ትሻልን ትቼ ትብስን አገባሁ ።

ትተውት የማይሄዱትን ባልንጀራ አይቀድሙትም ።

ትናንሽ ልጆች ፣ ትናንሽ ሀብቶች ።

ትንሳኤ ትንሳኤ ቢሉኝ ፣ ፀሎተ ሃሙስ መሰሎኝ ።

ትንሽ ሰው ፣ ትንሽ ነው ።

ትንሽ ቆሎ ይዞ ካሻሮ ተጠጋ ።

ትንሽ ፣ አበላሽ ።

ትንሽ ጎልማሳ ፣ ትቢያ ታነሳ ።

ትንኝም ለሆዱ ፣ ዝሆንም ለሆዱ ፣ ወደ ወንዝ ወረዱ ።

ትኩስ ሬሳ ፣ ደረቁን አስነሳ ።

ትፀድቅ ? ትኮነን ? ቢለው ፣ ቆይ መከሬ አስታውቀሃለሁ አለ ።

ትፈጭ የነበረች ማንጓለል አቃታት ።

ቶሎ ቶሎ ቢቆጡ ፣ አብረው አይቀመጡ ።

ቶፋ ፣ በማን ምድር ትለፋ ።

## - ቸ -

ቸር ተመኝ ፣ ቸር እንድታገኝ ።

ቸርን ቢያጠቁት ቢስ ይሆናል ።

ቸኩለው ያፈሱታል ፣ ተቀምጠው ይለቅሙታል ።

ቸኩሎ ከተጠቀመ ፣ ዝግ ብሎ የተጎዳ ይሻላል ።

ቻቻታ የለመደ ፣ ሰው አባይ ዳር ቅበሩኝ ይላል ።

ችኩል ሰው ጠንቋይ ይጠይቃል ።

ችኩል ቅቤ ያንቀዋል ።

ችኩል አደንጓሬ ሳይበሉት ሆድ ያማል ።

ችኩል አፍ ሞትን ይጠራል ።

ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል ።

ችኮ የጠም ስጋ ።

ችግር ለወዳጅ ሲያዋዩት ይቀላል ።

ችግር ነው ጌትነት ።

## - ነ -

ነበርንበት ፣ አትኩሩበት ።

ነቢይ ቢኖር ፣ በከበረ ነበር ።

ነቢይ ባገሩ አይከበርም ።

ነብር ቢያንቀላፋ ፣ ዝንጀሮ ጎበኘው ።

ነብር ባየለበት ዘመን ፣ ድመት ይኮርታል ።

ነብር አየኝ በል ።

ነብር አይኑን ታመመ ፣ ፍየል መሪ ሆነ ።

ነብር የሞተለት ፍየል ልጅዋን ትድራለች ።

ነዋሪ ለዘላለም ፣ አለ አምላክ የለም ።

ነውር ለባለቤቱ እንግዳ ነው ።

ነገረኛ ሰው ከቤቱ አይሞትም ።

ነገረኛ ናቸው ፣ አርቃችሁ ቅበሯቸው ።

ነገረኛ ዝንጀሮ ውሻ ታረባለች ።

ነገሩ ነገር ነው ፣ ውስጡ ጥቅንጥቅ ነው ።

ነገር ሲበዛ ፣ ይሆናል ዋዛ ።

ነገር ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም ።

ነገር ሲጀምር ፣ እህል ሲከመር ።

ነገር ሳያውቁ ሙግት ፣ ሳይጎለብቱ ትእቢት ።

ነገር ስንት ነው ? ሁለት ፣ ምን ያበዛዋል ? ውሸት ።

ነገር በሆዱ ፣ መንገድ በአመዱ ።

ነገር በሆዴ እየተመኘሁ ፣ ቢከፍቱት ተልባ ሆኘ ተገኘሁ ።

ነገር በለዛው ፣ ጥሬ በለዛዛው ።

ነገር በልክ ፣ ሙያ በልብ ።

ነገር በመልከኛ ፣ ጠላ በመክደኛ ።

ነገር በምሳሌ ፣ ጠጅ በብርሌ ።

ነገር በቀጠሮ ፣ ዘፈን በከበሮ ።

ነገር በትኩሱ ፣ ጨዋታ በወዙ ።

ነገር በነገር ይጠቀሳል ፤ እሾህ በእሾህ ይነቀሳል ።

ነገር በእርቅ ፣ መንገድ በድረቅ ።

ነገር በዋስ ፣ እህል በነፋስ ።

ነገር በዋና ፣ ዘፈን በገና ።

ነገር በዳኛ ፣ ሚዶ በእረኛ ።

ነገር ቢሳሳት ከጥንቱ ፣ ሰይፍ ቢመዘዝ ካፎቱ ።

ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንም ።

ነገር ባዋቂ ፣ ብረት በጠራቂ ።

ነገር አለኝ ከማለት ፣ ስራ አለኝ ማለት ።

ነገር አለዳኛ ፥ ነዶ አለመጫኛ ።

ነገር እንዳገቡት ፥ ሙከት እንዳሰቡት ።

ነገር እንዳፋ ፥ ዛፍ እንደ ቅርንጫፉ ።

ነገር ከመጀመሪያው ፥ ወሃ ከመሻገሪያው ።

ነገር ከሰነበተ ፥ ቅራሪ ከሆመጠጠ ።

ነገር ከስሩ ፥ ውሃ ከጥሩ ።

ነገር ከእብድ ይገኛል ።

ነገር ከዋስ ፥ ምላስ ከጥርስ አያልፍም ።

ነገር ከውሉ ፥ ጋሻ ከንግቡ ።

ነገር ከግቡ ፥ ጋሻ ከንግቡ ።

ነገር ካንኙ ፥ ስጋ ከጠባኙ ።

ነገር ወዳድ ሰው ከመንገድ ዳር ቅበሩኝ ይላል ።

ነገር ወዳጅ ከቤቱ አይሞትም ።

ነገር ወዴት ትሄዳለህ ፤ ጎንደር ፤ መጨረሻህ ፤ ታገር ።

ነገር የሚከረው ፥ ጎንጓኙን ሲያገኝ ነው ።

ነገር የፈራ ይቃጠራል ፥ አውሬ የፈራ ያጥራል ።

ነገር ፈጣሪውን ፥ እሾህ አጣሪውን ።

ነገርህና ነገሬ ልክ ነው ፤ ሰው መስማቱ ትርፍ ነው ።

ነገርህን በጠጂ ፥ ርስትህን በልጂ ።

ነገርም ይበረከታል ፤ ባለጋራም ይታከታል ።

ነገርና መጫኛ ፥ እንዳሳጠሩት ወይም እንዳስረዘሙት ነው ።

ነገርን በእርቅ ፥ ወይፈንን በድርቅ ።

ነገርን አዳምጦ ፣ እህልን አላምጦ ።

ነጋሪ የሌለው ይታማ አይመስለው ።

ነጋዴ ወረቱን ፣ ዘላን ከብቱን ፣ ገበሬ ምርቱን ።

ነጋዴን ተዘማች ምን አቀላቀለው ።

ነጭ ድሃ ፣ ነጭ ማር ይከፍላል ።

ነፋስ በተነሳበት ጊዜ እሳት አይጭሩም ።

ነፍስ በፈጣሪዋ ፣ ሴት ባሳዳሪዋ ።

ኑ ባይ ከባሪ ፣ እንቢ ባይ ቀላይ ።

ኑሮ በዘዴ ፣ አቶ ዘወልዴ ።

ኑሮ በደጋ ፣ መተኛት ባልጋ ።

ኑሮ ቢያምርህ ችላ ፣ ጥጋብ ቢያምርህ ባቄላ ።

ኑሮ ከማናደድ ፣ ሄዶ መመስገን ።

ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል ።

ና ብላ ሳይሉት ፣ ከወጡ አውጡልኝ ።

ና ያሉት እንግዳ ፣ እራቱ ፍሪዳ ።

ናዳ መጣልህ ቢሉት ፣ ተከናንቤአለሁ አለ ።

ንቡን አባሮ ማሩን ።

ንብ ላጥር ሳያረዳ አይሄድም ።

ንብ ቢሄድ ካጥር ፣ ሰው ቢሄድ ካገር ።

ንብ ባውራው ፣ ገበሬ ባዝመራው ።

ንብን አይተህ ተገዛ ብሏል እግዜር ።

ንካ ያለው አይቀርም ።

ንዳማ ቢአጭዱት ክምር አይሞላም ።

ንገስ ቢሉት ሳልዋጋ አልነግስ አለ ።

ንጉስ በመንግሥቱ ፣ እግዜር በመለኮቱ ፣ ጎልማሳ በሚስቱ ።

ንጉስ በማንቡ ይታማል ።

ንጉስ ቢቆጣ ፣ ቀስ ብለህ ውጣ ።

ንጉስ ቢያርፍ ፣ ሁሉ ይተርፍ ።

ንጉስ አንጋሹን ፣ ቤተ ክርስቲያን ቀዳሹን ።

ንጉስ አይከሰስ ፣ ሰማይ አይታረስ ።

ንጉስ ከተነፈሰ ፣ አይን ከፈሰሰ ።

ንጉስ የቆረጠው እጅ ካለ ይቆጠራል ።

ንጋትን ዶሮ ያውቃል ፣ ወፍ ያረጋግጣል ።

ንፋግ ለግሶ ቢሰጥ ፣ እጁ ይንቀጠቀጥ ።

ኖር ካንገት ፣ ወገብ ስራ አለበት ።

ኖሮ ኖሮ ከሞት ፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት ።

## - አ -

አሁን ሊደርቅ ውሃ ፣ አደረገኝ ድሃ ።

አሁን የሚያልፍ ውሃ ፣ አደረገኝ ድሃ ።

አህያ ለማኝን አህያ ለማኝ ቀደመው ።

አህያ ለሰርዶ ፣ ባላገር ለመርዶ ።

አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር ።

አህያ ሰባ ፣ ምን ረባ ።

አህያ ሰባ ፥ አልታረደም ምን ረባ ።

አህያ ሲጠግብ አምቦ ፥ ልጅ ሲጠግብ ሸንጎ ።

አህያ ሲጭኑ ሶስት ሆኖ ፥ መንገድ ሲሄዱ ሁለት ሆኖ ።

አህያ ቀንድ ቢያወጣ ፥ ቁራ እንዴት በነጣ ።

አህያ በሞተች ባመቷ ኩርኩር ።

አህያ ቢሞት ጉዞ አይቀሩም ፥ ገኸር ቢጠፋ ተገኸር አይጠፋም ።

አህያውን ቢፈሩ መደላድሉን ሰበሩ ።

አህያ ተማሎ ጅብን አወረደ ።

አህያ እንኳን በወለደች ታርፋለች ።

አህያ እጅብ ለቅሶ ሄደች ።

አህያ ወደ ሚዳ ፥ ጅብ ወደ ጓዳ ።

አህያ የሌለው በቅሎ ያንኳስሳል ።

አህያ የተጫነችውን አትበላም ።

አህያም እንዳባቱ ይፈርጥጥ ፤ ጅብም እንዳባቱ ይዘርጥጥ ።

አህያና ጓያ ፥ ባምሳያ ።

አህያን በመንገድ ፥ ካህንን በመርገድ ።

አህያን ባመድ ፥ ካህንን በማእድ ።

አህያውን ቢፈሩ ዳውላውን መቱ ።

አህያውን አመሰግን ብሎ ፈረሱን አዋረደ ።

አለማረፌ ፥ አንተን ማንከርፈፌ ።

አለማረፍ የተርብ ቤት መቆስቆስ ።

አለማወቂ ፥ በላሁ ተጨንቄ ።

አለማወቁ ፥ ከዘመድ መራቁ ።

አለም ሃላፊ ፥ መልከ ረጋፊ ።

አለም ተልባ ነው ይሸተብሃል ።

አለም አታላይ ፥ እንደ በቅሎ ኮብላይ ።

አለስራ አይበላ እንጀራ ፥ አለባል ቆሞ አይሰራ ።

አለቃ ፥ ለራሱ አይበቃ ።

አለቃ ቢለቅ ለሻለቃ ፥ ምንዝር ቢለቅ ላለቃ ።

አለቃ የሌለው ህዝብ ፥ አውራ የሌለው ንብ ።

አለቃ የሰጠው ፥ አጣሪ የሸጠው ።

አለቃ ያውቃል ፥ ድሃ ይጠይቃል ።

አለ በል ቀለቤን ፥ ሞተ በል ከፈኔን ።

አለባለቤቱ ፥ አይነድም እሳቱ ።

አለባል ሴት ወይዘሮ ፥ አለማንገቻ ከበሮ ።

አለባብሰው ቢያርሱ ፥ ባረም ይመለሱ ።

አለብልሃት ገደል መግባት ፥ አለ ጉልበት ውሃ መግባት ።

አለአሽከር በቅሎ ፥ አለወንድማማች አምባጓሮ ።

አለኩያ ጋብቻ ፥ ቆይ ብቻ ።

አለንጋ እስቲገዙ ፥ በክርን ይተክዙ ።

አለንጋ እስኪመጣ ፥ በክርን ያዝግሙብኝ ።

አለኝ ብሎ ከማፈር ፥ የለኝም ብሎ መድፈር ።

አለኝ እንጂ ነበረኝ አይጠቅምም ።

አለ አቡን ቁስ ፥ አለዘውድ ንጉስ ።

አለ እህል አቁማዳውን ይሞላሉ ፥ አለ ዘር ይቀራሉ ።

አለ ወንድም ጋሻ ፥ አለ ድግር እርሻ ።

አለዋንጫ አይስማት ፥ አለቀንጠፋ አይስባት ።

አለዋዛው ዋዛ ፥ ቅቤም አያወዛ ።

አለዋዛው ዋዛ ማቄን ትቀጃለሽ ።

አለው አለወ ና ሳይመታው ቀረ ።

አለዳኛ ሙግት ፥ አለገመድ እክት ።

አለዳኛ ቀጠሮ ፥ አለቅቤ ዶሮ ።

አለዳኛ አይካሱ ፥ አለጥርስ አይነክሱ ።

አለድሃ ዘውድ ፥ አለ ገበሬ ማእድ ።

አለፈ በዋዛ ፥ ልብ ሳልገዛ ።

አለፊቱ አይቆርሱ ፥ አለረጃቱ አይወርሱ ።

አሉ ብለህ ካላሉህ አትገኝ ።

አሉን ያህል ነገር ፥ ማሉን ያህል ምስክር ።

አላህንም አምናለሁ ፥ አህያየንም አስራለሁ ።

አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ መጣች ።

አላሽከር በቅሎ ፥ አለወንድም አምባጓሮ ።

አላቁማዳ መጫኛ ፥ አለከብት እረኛ ።

አላቅሙ ፥ ጥሬ መቃሙ ።

አላባት ነገር ፥ ዝንጀሮን ከባህር ፤ አሳን ከገደል ።

አላባት ቢዛቁን ፥ ይባክን ።

አላባት ጃሮ በጡጫ ።

አላባት ፣ ኀመን ባኀት ።

አላቻ ጋብቻ ፣ ቆይ ብቻ! ቆይ! ብቻ ።

አላንኮበር ሾላ ሜዳ አይገኝም ።

አላንድ የላት ጥርስ ፤ በዘነዘና ትነቀስ ።

አላዋቂ ለባሽ ፣ ልብስ አበላሽ ።

አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል ።

አላዋቂ አጉራሽ ፣ አፍ ያበላሻል ።

አላዋቂ ካረደው ፣ አዋቂ ያወራረደው ።

አላውቅም ፣ አስገድሎ አያውቅም ።

አላጋጭ ፣ አልማጭ ።

አላጋጭ ገበሬ ፣ ይሞታል በሰኔ ።

አሌ ብሎ የተረታ ፣ መሃል አገዳውን የተመታ ።

አልሞት ባይ ተጋዳይ ።

አልሰሜ የናቱን ተዝካር ይበላል ።

አልቀባም ብትል ትመሰክር ።

አልቅትና ድሃ ፣ ውሃ ለውሃ ።

አልጋው ሲገኝ ፣ ባሉ አይገኝ ።

አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል ።

አመሌ ፣ አወጣኝ ከማህበሬ ።

አመል ቤት አይጠብቅ ።

አመል ፣ ያስወጣል ከማህል ።

አመልህ ፣ በጥፊ ይበልህ ።

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

አመልህን በጉያ ፣ ስንቅህን ባህያ ።

አመልና ጅራት በስተሁዋላ ይበቅላል ።

አመስጋኝ ፣ አማሳኝ ።

አመት አርሶ አያጎርስ ፣ አመት ፈትላ አትለብስ ።

አመት አስቦ ለልደት

አመት ዘመን ፣ ሙክሳት መሙንሙን ።

አመንዝራ ስታረጅ ፣ አቃጣሪ ትሆናለች ።

አመንዝራ ካሏት ፣ ብትቆርብም አያምኑዋት ።

አመካከት ፣ ዝንጀሮን ተመልከት ።

አመድ በዱቄት ይስቃል ።

አመድ ባለበት በስመአብ ማለት ፣ የተኛ ጋኔን መቀስቀስ ነው ።

አመድ ያጠለቀው ፣ ጉልቻ የላቀው ።

አመፀኛ ሎሌህን በሰው ፊት አትዘዘው ።

አሙኝ ብለህ ካሙህ አትገኝ ።

አማቱን ምታ ቢለው ፣ ሚስቱን በየት አልፌ ።

አማትና ምራት ፣ እሳትና እራት ፣ ሳይስማሙ መሬት ።

አማቻችን አፈኛ ፣ ቢመለስ ወደኛ ፣ ወይ እኛ እንሁን አሳረኛ ።

አማች የበላው ፣ እሳት የበላው ።

አማችና ቂጥ ትርፍ ነው ።

አማችና ጋሻ ካልሰጎዱት አይወድም ።

አማጭ ለልማዱ የበቅሎ ክበድ ፣ የሣር ገመድ አለኝ ይላል ።

አማጭ ፣ ረማጭ ።

አምላክ የተቆጣው በረዶ ፣ ከድንጋይ ላይ ወርዶ ።

አምራለሁ ብላ ተኩላ ፣ አይንዋን አጠፋች ቸኩላ ።

አምሳ ሆነው አምሳ በግ ፈጁ ።

አምሳ ሎሚ ላምሳ ሰው ጌጡ ነው ፣ ላንድ ሰው ሸክሙ ነው ።

አምሳ ሰማ ፣ ጀሮ ገማ ።

አምሳ ዳቦ ከመላስ ፣ አንዱን መጉረስ ።

አምና ከላሞቹ ፣ ዘንድሮ ከጥጆቹ ።

አሞሌ ሲወፍር ፣ እወንዝ አውርዳችሁ እጠቡኝ ይላል ።

አሞራ ሲበሉ ፣ ስሙን ጅግራ ይሉ ።

አሞራና ቅል ተጋቡ ፣ አሞራው በረረ ቅሉም ተሰበረ ።

አረምን መንቀል ስር ሳይሰድ ነው ።

አረረም መረረም ማበሬን ከፈልኩ ።

አረጉን ሲስቡት ዛፍ ይወዛወዛል ።

አራስ የጅዋን ፣ ድመት የልጅዋን ።

አራት ቁና አጃ ቢጠፋት ፣ ሁለት ቁና ስንዴ ይዛ ከጠንቋይ ቤት ።

አርሶ ያልበላ ፣ ሆነ ነሁላላ ።

አርሶ ያልጠገበ ነግዶ ።

አርጂ ጥኑ ነው ።

አሮጌ መጥረጊያ ቤት አያጠራም ።

አሮጌ ማሳ ያረሰ ፣ ለእንጀራ ልጅ ያጎረሰ ።

አሮጌ ውሻ በከንቱ አይጮህም ።

አሰሩት ተበተቡት ፣ በሁዋላ ሊፈቱት ።

አሰተኛ ሲናገር ይታወቃል ፣ በሶ ሲበሉት ያንቃል ።

አሰት ሲናገሩ ውቃቢ ይርቃል ።

አሰት አያድንም ፣ መራቆት መልክ አያሳምርም ።

አሰትና እውነት ፣ የቱ ይረታ ጧት ።

አሰድ ፣ ያየውን አይሰድ ።

አሳ ለወጋሪ ፣ ነገር ለጀማሪ ።

አሳ መብላት ፣ በብልሃት ።

አሳ በልቶ ውሃ መጠጣት ፣ መልሶ ከነበረው ማግባት ።

አሳ በወንዙ ይታረዳል ፣ የጨዋ ልጅ በቤቱ ይፈረዳል ።

አሳ ብለምነው ዘንዶ ፣ ዝናም ብለምነው በረዶ ።

አሳሳች ፣ ከላይ ሲሉት ከታች ።

አሳውም እንዳያልቅ ፣ ውሃውም እንዳይደርቅ ።

አሳይቶ መሳሳት ፣ የሰጭ ቅሌት ።

አሳዳጊ የበደለው ፣ ለከፋት ያደለው ።

አስቀድሞ ማመስገን ለሃሜት ያስቸግራል ።

አስተካክሎ ይቀዷል ፣ ለእግዚአብሔር ብሎ ይፈርዷል ።

አስጨነቀኝ ገንፎ ፣ ከራቱ ተርፎ ።

አስፍቶ ከማረስ ፣ ከተቀባዩ ማሳነስ ።

አሽከሩን አይዳኝ ፣ በገናውን አይቃኝ ።

አሽከር ባንደበቱ ፣ ውሻ በጅራቱ ።

አሾከሻኪ ፣ አንካኪ ።

አቀማመጥ ያላወቀ ፣ ከባልና ሚስት መካከል ይቀመጣል ።

አቀበት ያደክማል ፡ እርሻ ያዳግማል ።

አቀፈ ፡ አዘለ ለባለቤቱ ያው ሸክም ነው ።

አቃቢ በተልባ በበላች ፡ ገበዙን ተጋረፈው ።

አቃቢ ኮሶ ቢጠጡ ፡ ቄስ-ገበዙን አሻራቸው ።

አቅሙን አያውቅ ፡ ቶሎ አይታረቅ ።

አበልጂ ፡ አትቁም ከደጂ ።

አበባ ፡ እያገርህ ግባ ።

አበድረኝ ፡ አይማረኝ ፡ ተዋሰኝ ፡ ግዝት ነኝ ።

አቡን ቄስ ናቸው ወይ ? ቢሉት ተርሷቸው ይናኛሉ አለ ።

አቡኩቶ አሳብ ።

አባ ላዩ ዳባ ፡ ውስጡ ደባ ።

አባ በሌሉበት ተዝካር ተበላ ።

አባ ቢዘሉ እስከ ንፍሮ ።

አባ ከበሉ እመን አነሳቸው ።

አባም ሰው ሆኑና ጋላ ገደላቸው ።

አባሪ ፡ ተነባባሪ ።

አባቱ ሲላጨው ፡ እናቱም ስታቅፈው ።

አባቱ ያልበላው ኑግ ፡ ልጁ አማረው ቅባ ኑግ ።

አባቱ ዳኛ ፡ ልጁ ቀማኛ ።

አባቱን ሳይመስል የተወለደ ልጅ ፡ ጎረቤት ያሳማል ።

አባቱን አያቅ ፡ አያቱን ናፈቀ ።

አባቱን የጠላ ፡ የሰው አባት ይሰድባል ።

አባቱን ገድሎ ላማቱ ይነጭ ፣ እማቱን ገድሎ እናቱን ያስፈጭ ።

አባቴ ትንሽ ነው ፣ ብልቴ ትልቅ ነው የሚል የለም ።

አባት ሲታማ ፣ ልጅ አይስማ ።

አባት ሳለ አጊጥ ፣ ጀንበር ሳለ ሩጥ ።

አባት አይከሰስ ፣ ሰማይ አይታረስ ፣ ውሃ አይጠበስ ።

አባት ካነሰው ፣ ምግባር ያነሰው ።

አባት የሌለው ልጅ ፣ መዝጊያ የሌለው ደጅ ።

አባት ያበጀው ፣ ለልጅ ይበጀው ።

አባት ያጠፋው ፣ ልጁን ያለፋው ።

አባትና ጋሻ ፣ ምስክር አያሻ ።

አባትና ጋሻ በወጭ ያስታውቃል ።

አባትና ጋሻ አይሸሸግም ።

አባያ ቢቀና ፣ ቤት ያቀና ።

አባያ ከሰው ሁሉ ፊት ይተኛል ።

አባይ ለሉቱ ፣ ደስ ማሰኘቱ ።

አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል ።

አባይ በቃሉ ያስታውቃል ፣ በጁ ሲበላ ይታነቃል ።

አባይ ቢሞላ ፣ ተሻገር በመላ ።

አባይ ፣ ነፍስ አስገዳይ ።

አባይ ፣ አንተ አየህኝ ከደረት ፣ እኔም አየሁህ ከጉልበት ።

አባይ ጠንቋይ ቤት ያስፈታል ።

አባይና ስንቅ እያደር ይቀላል ።

አባይን በጭልፋ ፡፡

አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል ፡፡

አብ ሲነካ ፤ ወልድ ይነካ ፡፡

አብሎ መብላት ፤ በእሳት ፡፡

አብሮ መብላት ያናንቃል ፡፡

አብሮ ማደግ ያናንቃል ፡፡

አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሃንስ አይሽረው ም ፡፡

አብን ያየ ፤ ወልድን አየ ፡፡

አቦን አይጠምቅ ፤ ወር አይፀድቅ የለም ፡፡

አቦን አይጠምቅ ፤ ፍልሰታን አይጥድ የለም ፡፡

አተር ቢጎድል ፤ ሽምብራ ይበረክትልናል ፡፡

አተርፍ ባይ ፤ አጉዳይ ፡፡

አታላይ ለጊዜው ያመልጣል ፤ በሁዋላ ይሰምጣል ፡፡

አታላይ ባለሟል ፤ ባቄላ አሽቶ ይበላል ፡፡

አታላይ እታች ሲሉት እላይ ፡፡

አታማርጭው ፤ አንዱን አምጭው ፡፡

አታርፍ አትሰራ ፤ አትፆም አትበላ ፡፡

አታስለምዳቸው ፤ አትክልክላቸው ፡፡

አታግባና የሰው አጥር ዝለል ፡፡

አታበድር ፤ እንዳትቸገር ፡፡

አታበድር ፤ ካበደርክም አታስቸግር ፡፡

አታንቀላፋ ነቅተህ ተኛ ፤ ይህ ሁሉ መንገደኛ ፡፡

አታወላውል ፣ እንዳትቀር ከመሃል ።

አትማታ በበትር ፣ ተከራከር ባጤ ስር ።

አትረፍ ያለው በሬ ቆዳው ከበሮ ይሆናል ።

አትቁም ያሉት ለማኝ ከሰጡት አንድ ነው ።

አትትረፊ ያላት ወፍ በጥቅምት ትሞታለች ።

አትናገረው ፣ ምስህ ቅበረው ።

አትኩራ ገብስ ፣ ጎመን ባወጣው ነፍስ ።

አትክልት በውሃ ይለመልማል ፣ እህል ከፈጩት ይልማል ።

አትዋል ይዋሉብህ ፣ አትምከር ይምከሩብህ ።

አትግደርደሪ ፣ ጠምሽን እንዳታድሪ ።

አትፍራ ጋብዘኝ ፣ አትናገር ሸኘኝ ።

አነሰ ሲሉት ተቀነሰ ።

አነከስ ብዬ በቅሎ ገዛሁ ፣ አይኔ ይጠፋ ብዬ መሪ አበጀሁ፣ያላሰብሁት ጀርዬ ደነቀረ።

አነጋገሩ ባህታዊ ፣ አወሳሰዱ እንደነአባይ ።

አነጋገራችን ፣ እንደጠባያችን ።

አነጋገር ቢያምር አሚሚት ይከፋል ።

አነጋገር አያውቅ ምርቃት ያበዛል ።

አንቃ ፣ ለራሱ አይበቃ ።

አንበሳ ላንበሳ ቢያገሳ ፣ ሞቱ ለከሳሳ ።

አንበሳ ምን ይበላል ? ተበድሮ ፤ ምን ይከፍላል ? ማን ተናግሮ ።

አንበሳ ሰባሪ ፣ አሞራ በራሪ ።

አንበሳ ሲያረጅ ከሳሳ ፣ ምስጢር ሲያረጅ አፈሳ ።

አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል ።

አንበሳ ሳይገድሉ ቆዳውን ያስማማሉ ።

አንበሳ የሰበረው ፣ ለጅብ ይተርፋል ።

አንበጣና ፌንጣ ፣ ሰንጠረዥና ገበታ ።

አንተ ሰው ፣ ና ግንቡን ጣሰው ።

አንተ ቀውላላ ፣ መኖህ ባቁላ ።

አንተ አስበሃል ፣ ስላሴ ያውቁልሃል ።

አንተ አብጀው ፣ አስቤም አልፈጀው ።

አንተ ውለታ ቆጣሪ ቢለው ፣ አንተ ውለታ አስቆጣሪ አለው ።

አንተ ግፋኝ ከላይ ፣ እኔ እወድቃለሁ ከስጋ ላይ ።

አንተም ሌባ እኔም ሌባ ፣ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ ።

አንተን ብዬ መጣሁ ፣ አንተን አጣሁ ።

አንቱ ትተረጉሙ ፣ አንቱ ትደረግሙ ።

አንቺ ምን አለብሽ ሁለት አባት አለሽ ፣ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ ።

አንቺ ታመጭው ፣ አንቺው ታሮጭው ።

አንቺ ክምር አለሁ ብለሻል ፣ ተበልተሽ አልቀሻል ።

አንቺማ ታቦኪያለሽ ፣ ውሻ ይደፋብሻል ።

አንቺው ሲሳይ ፣ የተጫነሽው ሲሳይ አለ ጅብ ።

አንካሳ በልቡ ፣ ኢየሩሳሌም አሳቡ ።

አንካሳን ማገም ፣ ድንጋይ መቆርጠም ።

አንደኛው ልብ አብርድ ፣ ሁለተኛው ልብ አንድድ ፣ ሶስተኛው ነገር ቀስቅስ ፣ አራተኛው ጎራዴ ምዘዝ ።

አንዱ ሲበላ አንዱ ያገበግባል ።

አንዱ ልብ መካሪ ፣ አንዱ ቃል ተናጋሪ ።

አንዱ ሲሻር አንዱ ይሾማል ።

አንዱ ሲናገር ያፈዝ ፣ አንዱ ሲናገር ያደነግዝ ።

አንዱ ባንዱ ሲስቅ ፣ ጀንበር ጥልቅ ።

አንዱን ሳይዘው ፣ ደረሰ ጊዜው ።

አንዱን ጥላ ፣ አንዱን አንጠልጥላ ።

አንዳንድ ጊዜም በዋልድባ ይዘፈናል ።

አንድ ሎሌ ለሁለት ጌታ አይገዛም ።

አንድ ምስክር አያስደነግጥ ፣ አንድ አይን አያስረግጥ ።

አንድ ሰኔ የተከለው ፣ ካመት አተረፈው ።

አንድ ሰኔ የገደለውን ፣ ሶስት ሰኔ አያድነውም ።

አንድ ሲናገር ሁሉ ይሰማል ፣ ሁሉ ሲናገር ማን ይሰማል ?

አንድ ቀን ቢሳሳቱ ፣ አመት ይፀፀቱ ።

አንድ በሬ ስቦ ፣ አንድ ሰው አስቦ ።

አንድ አመት ሰርተት ፣ አንድ አመት ከርተት ።

አንድ አመት በደመወዝ ፣ አንድ አመት በወዝ ።

አንድ አይነድ ፣ አንድ አይፈርድ ።

አንድ አይና ሰው ባፈር አይጫወትም ።

አንድ አይና በግ ሄደች ፣ በአንድ አይኗ እንቅልፉን ትፈጀለች ፣ በአንድ አይኗ ጊዜን ትጠብቃለች ።

አንድ እግረኛ ያወራውን ፣ አንድ ፈረሰኛ አይመልሰውም ።

አንድ ወናፍ ፣ ሁለት አፍ ።

አንድ ጣት በቆማጣ ቤት ብርቅ ናት ።

አንድ ፋሲል ነበረ ፣ እሱም ተመተረ ።

አንገት ለምን ተሰራ ፣ ዞሮ ለማየት ።

አንጋጣጭ ፣ ዱላ ዋጭ ።

አንጣሪያ ላንጣሪያ ቢደጋገፍ ፣ ተያይዞ ዘፍ ።

እኝከህ ፣ እኝከህ ወደ ዘመድህ ዋጥ ።

አካሄዱን አይተህ ፣ ጭብጦውን ቀማው ።

አካል የወለደው ፣ ዘመድ የወደደው ።

አካልና ከብት ፣ ሚስትና ቁርበት ።

አከንባሎና እዳ ተሽራርፎ ያልቃል ።

አወላለድ ያለው ፣ አከፋፈል አይቸግረው ።

አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት ፣ መፅሃፍ አጠበች ።

አወይ ብልሃት ፣ ለንጉስ መገዛት ።

አዋቂ ሲበዛ እስታራቂ ይሞታል ።

አዋቂ ፣ አስታራቂ ።

አዋጅ ቢነግሩ ፣ ልዩ ነው ምክሩ ።

አውሬ ከዋሻ ፣ በሬ ከርሻ ።

አውቆ መተው ፣ ነገሬን ከተተው ።

አውድማ እንደ ነፋስ ፣ አገር እንደ ንጉስ ።

አዎን ማለት መረታት ፣ አለመመከት መመታት ።

አዎን ባይ እዳ ከፋይ ፣ አሌ ባይ ሞት ተቀባይ ።

አዎን ብለህ ተሟገት ፥ ከጠገበ ሽምት ።

አዎን ብሎ የተረታ ፥ መሃል አገዳውን የተመታ ።

አዎን ያለች ምላስ ፥ እናት የሌላት አራስ ።

አዎን ያለን አያሟግቱ ፥ እሺ ያለን አይመቱ ።

አዘኑ ሳይለቅህ ፥ ድግሱ አያምልጥህ ።

አዘንጊ ወጥ ከእንጀራ ይተርፋል ።

አዘዞ አንድም ተናዞ ፥ አንድም ስንቅ ይዞ ።

አዛኝ ቅቤ አንጓች ።

አዛዩን ነካሽ ።

አዝመራ በቁንጫ ፥ ሰማይ በጡጫ ።

አያ ተዋሰኝ ፥ ስትሄድ አሳንሰኝ ።

አያ ጅቦ ሳታመኽኝ ብላኝ ።

አያርም አራሽ ፥ አያጥብ ለባሽ ፥ አይረታ ከሳሽ ።

አያርስ አይነግድ ፥ አይተች አይፈርድ ።

አያስብ ቀበኛ ፥ ተንኮለኛ ።

አያስገሳ ኮሶ ፥ የት ደርሶ ።

አያውቅ ቢዳኝ ፥ ከቤቱ ይናኝ ።

አያውቅ እንደኛ ፥ የበግ እረኛ ።

አያድርስ የባል ቢስ ፥ አያቅፍ አያንተርስ ።

አያድን አግሬ ጎድን ያሰብር ።

አያድን ጋሻ ቂጥ ያስወጋ ።

አያገባት ገብታ ፥ አያወዛት ተቀብታ ።

አያጥብ ለባሽ ፣ አይረታ ከሳሽ ።

አዬ ሌላ ፣ ወዬ ሌላ ።

አዬ ጉድን አታበላሽ ፣ ለባለ ቀን ይሆናል ።

አዬና ወዬን ምን አገናኘው ።

አይሆንም እንጂ ከሆነማ ፣ ከመጋዞ ይሻላል ጉልማ ።

አይመረው አይተኩሰው ፣ ውጦ ወጦ ጨረሰው ።

አይመጣምን ትተሽ ፣ ይመጣልን በያዝሽ ።

አይሰጥ አዛኝ ከነፍሰ ገዳይ አንድ ነው ።

አይበላ የለ ፣ አይጠጣ ይባስ ።

አይበላ ዳኛ በእግት ይመረር ።

አይቡ ዳኛ ፣ ቅቤው መልከኛ ።

አይቡን ሲያዩ ፣ አጓቱን ጨለጡት ።

አይብ ሲያድር አጥንት ይሆናል ።

አይብ ከአጓቱ ፣ ልጅ ከእናቱ ።

አይብ የጠላ ፣ ጎመን ይበላ ።

አይተህ ቁረስ ፣ ከጥርስህ እንዲደርስ ።

አይተፉሽ ማር ነሽ ፣ አይውጡሽ ምርቅ ነሽ ።

አይታ የማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሳ ፣ ተመለሺ ቢሏት ወዴት ተመልሳ ።

አይታፈሩበት ቤት ገላጋይ አይሆንም ።

አይቶ አጣ ቤት ጎመን የተቀቀለ ለት ሲጨበጨብ ያድራል ።

አይቶ ያጣ ፣ ጠምዶ የፈታ ።

አይችሉት ድንጋይ ቢሸከሙት ከፍ ብሎ ያረት ይመታል፣ዝቅ ብሎ እግር ይቆርጣል።

አይችል ዳኛ በቤቱ ይናኝ ።

አይነ ደረቅ ሌባ ፤ ከነ ቃጭሉ ይገባ

አይነ ደረቅ ፤ መልሶ ልብ ያደርቅ ።

አይነጋ መስሏት እቋት አራች ።

አይኔን ሲያመው ፤ ጥርሴን አታስቆጣው ።

አይን ህመም ልግም ይወዳል ።

አይን ህመም ክሱት ነው ፤ የሆድ ህመም ስውር ነው ።

አይን ሲያይ ብረቱ ፤ ጆሮ ሲሰማ መስኮቱ ።

አይን አይቶ ልብ ይፈርዳል ።

አይን አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች ።

አይን አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ትወልድ ።

አይን ካላዩበት ግንባር ነው ።

አይኗን ቢያጠፋት ፤ ቅንድቡን አደራ ።

አይዋስ ቢዋሰኝ ፤ ከባለዳው ባሰኝ ።

አይዋጋ ብላቴና ፤ አይዘንብ ደመና ።

አይዋጥ አይተፋ ፤ መላው የጠፋ ።

አይዞህ አይዞህ ማለት ከመውደቅ ያድናል ።

አይጠቅም ጠላ ፤ ባልና ሚስት ያጣላ ።

አይጠቅም ጠላ ፤ ከጎረቤት ያጣላ ።

አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች ።

አይጥ በበላ ፤ ዳዋ ተመታ ።

አይጥ በድመት አፍንጫ ወርዶ ፤ አህያ ታስሮ በሰርዶ ።

አይጥ በጉድጓዱ ፤ ሰው በዘመዱ ።

አይጥ ነሽ እዩት ከንፈን ፤ ወፍ ነሽ እዩት ጥርሴን ።

አይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ሲቀር ሲጥ ።

አይጥ ጣረ ሞት ይዟት ፤ ትጫወታለች ድመት ።

አይጥና ዝሆን ቢዋደዱ ፤ አሳ ወለዱ ።

አይጥና ድመት ታገሉ ፤ ማናቸው ጣሉ ።

አይጥና ፍልፈል ፤ ሽከላና ገል ።

አይፅፍ ደብተራ ፤ ክንፍ የሌለው አሞራ ።

አደራ ቢሏቸው ፤ ይብሳሉ እሳቸው ።

አደራ ጥብቅ ፤ ሰማይ ሩቅ ።

አደባባይ ፤ አይውል አባይ ።

አደናግር ፤ እንደ ነብር ።

አደንጓሬ ፤ የእህል አውሬ ።

አዲስ ወጠ ሰሪ ዝንጅብል ታበዛለች ።

አዳኝ ውሻ ጭገር ባፏ ፤ በትር ትርፏ ።

አድላዊ ዳኛ ፤ አምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ ።

አድረው ሲለዩ ፤ አመል ያሳዩ ።

አገሩ ሩቅ ፤ ስንቁ ደረቅ ።

አገሬ ሩቅ ፤ ጭብጦዬ ደረቅ ።

አገር ላጣ ሰሜን ፤ ምግብ ላጣ ጎመን ።

አገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል ።

አገር በጤና ፤ ለማኝ በጭራ ።

አገር ቢጠላህ አልፌህ አልፌህ ታረቅ ።

አገር ቢያብር ፡ ለንጉስ ያስቸግር ።

አገር አላት ይበሉኝ ፡ ማህደረ ማርያም ቅበሩኝ ።

አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ ፡ ማጭድ የሌለው መስክ ሰፋሪ ።

አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ ፡ ማጭድ የሌለው ወራሪ ።

አገር ያለምክር ፡ ቤት ያለማገር ።

አገር ያደረው ፡ ዘንዶ የወደረው ።

አገር ጥሎ ፡ ቁርበት ጠቅሎ ።

አገርህ ወዴት ነው ? ማርያም ውሃ ፡ እንግዲያው ዘመዴ ነሃ ።

አገባሻለሁ ያለ ላያገባሽ ፡ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ ።

አገኘሁ ብልሃት ፡ እርሶ መብላት ።

አገኝ ባይ ፡ ልብ የለህም ወይ ።

አጉል መጋባት ፡ መጋማት ።

አጉል ፍቅር ፡ ያመናቅር ።

አጋም ተደግፎ ይዋጋል እንባጮ ።

አጋሰስ በጭነት ፡ ወገብ በመቀነት ።

አጋዘን ሲጠግብ ፡ የነፍጠኛ ጎጆ ይታከካል ።

አጋጨው ፡ እንደ ነጋዴ ጨው ።

አግኝቶ ከመዋረድ ፡ አጥቶ መኩራት ።

አጎንብሶ በላን ተኝተህ ቀላውጠው ።

አጓት ጠጥቶ የሰከረ ፡ ካሳ በልቶ የከበረ የለም ።

አጣሪ እንደ ለጋስ ከመንገድ ዳር ትቀመጣለች ።

አጤ ከሞቱ ፣ በማን ይሟገቱ ።

አጤን መደብ ፣ እቴጌን ገደብ ።

አጤን ያሻል ቀላጤ ።

አጥልቆ የሚያርስ ፣ ከብሮ የማይጨርስ ።

አጥልቆ የማያርስ ፣ ጀምሮ የማይጨርስ ።

አጥር ጥሶ ፣ ቅጥር አፍርሶ ።

አጥባቂ ፣ ደን ጠላቂ ።

አጥባቂ ፈረስ ፣ ከገደል ያደርስ ።

አጥብቀህ ጎርስህ ወደ ዘመድህ ዙር ።

አጥብቆ ያሰረ ዘቅዝቆ ይሸከማል ።

አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል ።

አጥንትና ጅማት ፣ በአካላት ።

አጥፊና ጠፊ ፣ ወናፍና አናፊ ።

አጥፊው አልሚ መስሎ ይታየዋል ለሰው ።

አጥፍቶ ይርቃል ፣ አልምቶ ይሞቃል ።

አጭር አህያ ሁልጊዜ ውርንጭላ ።

አጮላቂ ፣ ሰራቂ ።

አፈረች ፣ ድብኝት አከለች ።

አፈር ማሽ ፣ በአንድ እጁ አፈር መላሽ ።

አፈር ብለው አያፈሱህ ፣ እህል ብለው አያፍሱህ ።

አፈኛ ባፉ ፣ ሃይለኛ በመዳፉ ።

አፉ ከኛ ፣ ልቡ ከነኛ ።

አፉ ከኛው ፣ ልቡ ከወሬኛው ።

አፉን የረቱ ፣ እጁን የመቱ ።

አፉን ጠቅሞ ፣ ወርቁን ቅሞ ።

አፍ ሲነድ ፣ ሆድ ይንደድ ።

አፍ ሲናገር ልብ ይንቃል ።

አፍ ሲናገር አፍንጫ ያሽሟጥጣል ።

አፍ ሲከዳ ከሎሌ ይብሳል ።

አፍ ሲዋሽ ሆድ ይታዘባል ።

አፍ ሲያርፍ ወዳጁን ያማል ።

አፍ ሲያብል ልብ ዳኛ ነው ።

አፍ ነገር ፣ አይን አገር አያጣም ።

አፍ እኩል ፣ ጉልበት ስንኩል ።

አፍ ካልተናገሩበት እዳሪ ነው ።

አፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥነዋል ።

አፍ ያለው ? ያግባሽ ከብት ያለው ?

አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል ።

አፍ ያበዛ ፣ ጥበቡ ዋዛ ።

አፍ ዳገት አይፈራም ።

አፍላ ፣ ያለወጉ ፈላ ።

አፍና ቅብቅብ ሁል ጊዜ አያበላም ።

አፍና እጅ አይን የላቸው ፣ ምነው አለመሳሳታቸው ።

አፍና እጅ ፣ እጅና ፍንጅ ።

አፍንጫን ሲመቱት አይን ያለቅሳል ።

አፍጣኝና አቅጣኝ ፤ እመዳሮው እንገናኝ ።

እህል ለቀጠና ፣ ወርቅ ለዝና ።

እህል ላበደረ አፈር ፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር ።

እህል ሲያጡ ፤ የናት ልጅ ያጡ ።

እህል ሲገኝ ወፍጮ ይሟልጣል ።

እህል ሲጠፋ ወፍጮ ይሰላል ፣ እህል ሲገኝ ወፍጮ ይደንዛል ።

እህል ሲጠፋ ወፍጮው ይቀራል ።

እህል በቀርበቦ ፤ እንቁላል በወታቦ ።

እህል ከበዩ ፤ ሰው ከገዳዩ ።

እህል ከባዶ ፣ ልጅ ካጎዶ ።

እህል ከውድማ ብቻውን ዋለ ፣ አያሌ ሰዎችን እንዳልገደለ ።

እህል ከዱር ፣ ልጅ ካጉል ።

እህል የበቀለበት ያስታውቃል ።

እህል የያዘ ፈርዛዛ ፡ ወርቅ የያዘ ቀበዝባዛ ።

እህል ያለውሃ ፣ ንጉስ ያለድሃ ።

እለት ፣ ቆይቶ ላመት

እልልታ ፤ ደስታ ።

እልከኛ መኸርገር ከላም ጡት ተጣብቆ ይገኛል ።

እልክ ምላጭ ያስውጣል ።

እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል ።

እማኝ ሲገዙ ፣ ነገር አያበዙ ።

እምብዛም ብልሃት ፥ ያደርሳል ከሞት ።

እምድር የወደቀ ስጋ አፈር ሳይዝ አይነሳም ።

እረኛ ቢያኮርፍ ራቱ ምሳው ይሆናል ።

እሬት ለቀመሰው እንጂ ፥ ላልቀመሰው አይመርም ።

እርም ለትህትና ።

እርሟን ብታፈላ ፥ አንድ ቁና አተላ ።

እርሟን ብታፈላ ፥ ጋን ሙሉ አተላ ።

እርሟን ጠምቃ ፥ ፈጀችው ጠልቃ ።

እርስ በርሱ ፥ ስጋን በኩበት ጠበሱ ።

እርሻ ሲሉ ሞፈር ቆረጣ ።

እርሻ ቢያለሰልሱት እህል ያሳምራል ፤ ገንዘብ ቢያከማቹት ያኮራል ።

እርሻ ቢያርሱ ፤ እንደልብ ያጎርሱ ።

እርሻ ያውቋል ፥ ያጠብቋል ።

እርሻ ደጉ ፥ ሳያደገድጉ ።

እርሻ ጋራ ዞሮ ፥ የጎረቤት ዶሮ ።

እርቅ ቢፈርስ ፥ ካስታራቂው ድረስ ።

እርቅ አይፈርስ ፥ አይን አይፈስ ።

እርቅ ከወርቅ ፥ ዛላ ከምርቅ ።

እርቅ ፥ የሰው ደም ያደርቅ ።

እርቅ የፈለገ ንጉስን ገበሬ ያስታርቀዋል ፥ እርቅ ያልፈለገ ገበሬን ንጉስ አያስታርቀውም ።

እርኩም ይሆን እስከበላ እድሜ ስጠኝ ይላል ።

እርኩም ጉድ ባይ ፥ ጦጣ አታላይ ።

እርያ በሬ አይደለም ።

እርጅና ፥ ብቻህን ና ።

እርጉዝ ላም ያለው ፥ ደረቅ አያንቀው ።

እርጉዝ ሲያርዱ ፥ በወዳጅ ሲፈርዱ ፥ ሆድ መርበድበዱ ።

እርጉዝን ያቅፉ ፤ ይደግፉ ።

እሰራለሁ ብላ ሄዳ ፥ ተላጭታ መጣች ።

እሰር በፍንጅ ፥ ጣል በደጅ ።

እሱ አይወደኝ ፥ መከራው አይለቀኝ ።

እሳት ለፈጀው ፥ ምን ይበጀው ።

እሳት መጣብህ ቢሉት ፥ እሳር ውስጥ ገብቻለሁ አለ ።

እሳት ቢያንቀላፉ ገለባ ጎበኘው ።

እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል ፥ ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል ።

እሳት ቢፈጃት ወደ ልጅዋ ጣለች ።

እሳት አለ እንጨት አይለማ ፥ ጆሮ እዳውን አይሰማ ።

እሳት አመድ ይወልዳል ።

እሳት ከበላው ፥ ወራሪ የዘረፈው ።

እሳት ከበረበረው ፥ ሴት የመከረው ።

እሳት ካልነደደ አያበራም ።

እሳት ካየው ፥ ምን ለየው ።

እሳት የገባ ቅቤ ።

እሳት ጭሮ ከነፋስ ላይ ።

እሳትና ነገር ቢያጋንኑት ይጋነናል ።

እሳትና ነፋስ ፡ ማርና መላስ ።

እሳትና ድሃ ሲነካኩት አይወድም ።

እስላም ሲከብር ሴት ፡ ክርስቲያን ሲከብር መሬት ያበዛል ።

እስኪያልፍ ፡ ያለፋል ።

እሷ ሰንፋ ራቷን ገንፎ አድርጋ ፡ ቢያጎርሷት ተኮሳት ።

እሷ ነፍጋ ራቷን ገንፎ አድርጋ ፡ ቢያጎርሷት ተኮሳት ።

እሷ በፈሳችው ፡ በኔ ላከከችው ።

እሷ ጣፋጭ ፡ ልጅቷ ቆንጣጭ ።

እሷው ሙታ ፡ እሷው መርዶ ጠርታ ።

እሷው ወልዳ አልመሰለም ፡ እሷው ጋግራ አልበሰለም ።

እሼ ባይ አክባሪ ፡ እምቢ ባይ አቅላይ ።

እሺ ፡ ይበልጣል ከሺ ።

እሺና ገለባ አይከብድም ።

እሾህ በሾህ ይነቀሳል ፡ ገንዘብ በገንዘብ ይመለሳል ።

እሾህ አጣሪውን ፡ ነገር ፈጣሪውን ።

እሸት በወረት ፡ እህል መውቃት በክብት ።

እሸት አድርገህ ቅዳው ፡ እንዳይጎሽ ጠላው ።

እቃ እንደመጣ ፡ ይውጣ ።

እበላ ብዬ ተበላሁ ፡ ምነው ሳልበላ በቀረሁ ።

እበላ ያለ ዳኛ ፡ እገድል ያለ መጋኛ ።

እበት ትል ይወልዳል ።

እበት ትል ይወልዳል ፥ ድሃ እብለት ይወዳል ።

እበትና ኩበት ፥ ወገንና ከብት ።

እባብ ለባብ ፥ ይተያያል ካብ ለካብ ።

እባብ ላይበላው ፥ አብላላው ።

እባብ ሲያዩት ይለሰልሳል ፥ ጌታ ቢጫወት ባልንጀራ ይመስላል ።

እባብ ቀጭን ነው ተብሎ ራሱ አይረገጥም ።

እባብ በራሱ ላይ የጠመጠመ ፥ ከሰይፍ ላይ እግሩ የቆመ ።

እባብ በእግርህ ፥ በትር በእጅህ ።

እባብ አፈር ያልቅብኛል ብሎ ሲሰስት ይኖራል ።

እባብ እንደ መለስለስሽ ፥ ቅናት የሃንስ በሆንሽ ።

እባብ ከምድር ተጋድሞ ፥ ሰው በትር ይዞ ቆሞ ።

እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው ።

እባብ ያየ ፥ በልጥ በረየ ።

እባብ ጉድጓዱን አይስት ።

እባብ ጉድጓዱን ፥ ውሻ ጌታውን ።

እባብ ግደል ፥ ከነበትሩ ገደል ።

እባብ ጥበስልኝ ፥ ይብረድልኝ ።

እባብና ጓጉንቸር ባንድ ይኖራሉ ።

እባብን ሞት ብሎ እራሱን መርገጥ ፥ መቅበጥ ።

እባክህ አታጋልጠኝ ፥ ለጠላት አትስጠኝ ።

እባክሽ ያሏት ጎረቤት ፥ ትሆን እመቤት ።

እቤት ሆኖ ካሰበ ፥ ሄዶ ያልሰጠ በለጠ ።

እቤት ዶሮ ሲታረድ ፣ እዱር ቆቅ ይያዛል ።

እብድ ቢጨምት እስከ እኩለ ቀን ነው ።

እብድ ከወፈፍተኛ ቤት ያድራል ።

እብድ የያዘው መልክ አይበረክትም ።

እብድና ብርድ ፣ ያስቃል በግድ ።

እብድና ዘመናይ የልቡን ይናገራል ።

እብድና ገር ፣ የታየውን ይናገር ።

እታከል ተግመል ።

እቴ ከሆንሽ ካለስሜ አታልቅሽ ።

እናቱ የሞተችበትና ውሃ የወረደችበት እኩል ያለቅሳሉ ።

እናቲቱ ዶሮ ፣ ልጅዋን ይዛ ጓሮ ለጓሮ ።

እናቲቱን አይተህ ልጅቷን አግባ ።

እናቴን ላህል ዘጠኝ ወር ቀረኝ አለች ።

እናት ለልጅዋ ነቢይ ናት ።

እናት ትረገጣለች እንደ መሬት ።

እናቷ ዘንድ ሄዳ ከመጣች ፣ ከንብላው በቀር ስራ አጣች ።

እኔ ልብላ አንተ ጦም እደር ።

እኔ ሙቼ ፣ እኔው ቄስ ጠርቼ ።

እኔ በልጇ ሳዝን ፣ ልጇ በልጁ ያዝን ።

እኔ ባልኩ ፣ ይልኩና ይላኩ ።

እኔ አለኝ ቁስል ፣ ያንቱን የሚመስል ።

እኔ እውነት እናገራለሁ ፣ ሌላውን አስኮንናለሁ ።

እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ ።

እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ ፣ ገብስ የሚደርሰው ለፍልሰታ ።

እኔን ሲፈጀኝ ልጄን ያቃጥለው ።

እንስራዋን ረስታ ውሃ ወረደች ።

እንስራዋን ጥላ ወንዝ ወረደች ።

እንቁራሪት ዝሆን አክል ብላ ተሰንጥቃ ሞተች ።

እንቅልፍ ታበኸር ፣ ከነብር ትፋዘኸር ።

እንቅልፍና ሞት ፣ እሬትና ሃሞት ።

እንበለ ገንዘብ መዝናናት ፣ ያመጣል ውርደት ።

እንባ ሲሻኝ ፣ አይኔን ጢስ ወጋኝ ።

እንኳን ለሀቴ ፣ ለሌላም ይዘፍናል አንገቴ ።

እንኳን ለራሱ ፣ ለሰው ይተርፋል እሱ ።

እንኳን ለቤቱ ፣ ይተርፋል ለጎረቤቱ ።

እንኳን ለገንፎ ፣ ለሙቅም አልደነግጥ ።

እንኳን ሊያበሉኝ ፣ ገርፈው ሰደዱኝ ።

እንኳን ተልባ ሽቶሽ ፣ እንዲያውም ዘጠኝ ቂጣ ትፈጃለሽ ።

እንኳን እመነኩስ አልከናነብም ።

እንኳን እናቴ ሙታ እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል ።

እንኳን ከፎከረ ፣ ያድናል አምላክ ከወረወረ ።

እንኳን ዘንቦብሽ ፣ እንዲያውም ጤዛ ነሽ ።

እንደ ልጅ በቀለበት ፣ እንደ ድመት በወተት ።

እንደ መረብ ሽፍኖ ፣ እንደ እንቁላል ደፎኖ ።

እንደ ሰው ትመጪ ፤ እንደ አውሬ ትሮጪ ።

እንደ ሽመላ ፤ በሁለት ይበላ ።

እንደ ቆጫት ተነስታ የሰው ለቅሶ አጠፋች ።

እንደ በሶ አንቆ ፤ እንደ እርጉዝ አስጨንቆ ።

እንደ ንብ ቀስሞ ፤ እንደ ወፍ ቀምሞ ።

እንደ ንጉሱ ፤ አጎንብሱ ።

እንደ አንድ ልብ መካሪ ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ።

እንደ አገሩ ይኖሩ ፤ እንደ ወንዙ ይሻገሩ ።

እንደ አጤ ስርአት ፤ እንደ አብርሃም እራት ።

እንደ እንግዳ ደራሽ ፤ እንደውሃ ፈሳሽ ።

እንዳትበላ ለጎሚት ፤ እንዳትሄድ ቀየዷት ።

እንዳየን ፤ ጤፍ አጋየን ።

እንዳዩ መብላት ሆድ ያስፋል ።

እንዳያማህ ጥራው ፤ እንዳይበላ ግፋው ።

እንዳገሩ ይናገሩ ።

እንዳገሩ ይኖሩ ፤ እንደወንዙ ይሻገሩ ።

እንዶድ በገርነቱ ውሃ ወሰደው ።

እንጀራ ለራብ ፤ ድንጋይ ለካብ ።

እንጀራ ለባእድ ፤ መከራ ለዘመድ ።

እንጀራ በማየት አያጠግብም ።

እንጀራ በሰፌድ ፤ አሞሌ በገመድ ።

እንጀራ የለም እንጂ በወተት አምገህ ትበላ ነበር ።

እንጀራ ያለወጥ ፣ ቤት ያለሴት ፣ ከብት ያለበረት ።

እንጀራ ይጋግሯል እማድ ቤት ፣ መላ ያማክሯል ለሴት ።

እንጀራን ምን ይጨርሰዋል ? መጉረስ ።

እንጀራው ሳይኖር ከወጡ አስነኩልኝ ።

እንግዲህ ነገሬን በከንፈሬ ።

እንግዳ ሲወደስ ፣ ባለቤቱን ያጎርስ ።

እንግዳ ሲያዘወትር ፣ ቤተሰብ ይሆናል ።

እንግዳ ሲያፍር ፣ ባለቤት ይጋብዛል ።

እንግዳ ደራሽ ፣ ውሃ ፈሳሽ ።

እንግዳ ፊት ወርቅ ፣ ሁዋላ ብር ፣ ሁዋላ ብረት ።

እንግዳና ሞት ፣ በድንገት ።

እንጎቻ የበላ ፣ ከራት ይታገሳል ።

እንጣጥ እንደ ፌቆ ፣ ሙልጭ እንደሰብቆ ።

እንጥስ ቢሉ ቅንጥስ ።

እንጨት ሞልቶ ዛቢያ አይገኝበት ።

እንጨት ቢያነዱት አመድ ፣ ቃጫ ቢፈትሉት ገመድ ።

እንጨት አይሸከሙ ላመድ ፣ እርጊት አያገቡም ላትወልድ ።

እንጨት ካልነሱት እሳት አይጠፋም ።

እኖር ባይ ፣ ተጋዳይ ።

እኛ በአገራችን ፣ ዳቦ ፍሪዳችን ።

እከክ የሰጠ ጌታ ፣ ጥፍሩን አይነሳም ።

እኩሉ በዶሮ ፣ እኩሉ በሽሮ ።

እካስ ያለ ታግሶ ፣ እፀድቅ ያለ መንኩሶ ።

እወቁኝ ፣ ደብቁኝ ።

እወቅ ያለው ባርባ ቀኑ ፣ አትወቅ ያለው ባርባ ዘመኑ ።

እወደዋለሁ እንጂ ይወደኛል አትበል ።

እውር ምን አይቶ ፣ ደንቆሮ ምን ሰምቶ ።

እውር ሲቀናጣ ምርኩዙን ወርውሮ ይፈልጋል ።

እውር ሲወበራ ፣ በሽማው ላይ አራ ።

እውር ሲጠግብ ከመሪው ጋር ይጣላል ።

እውር በዘንጉ ፣ ነጋዴ በወርቁ ።

እውር ቢጠግብ ዘንጉን ይወረውር ።

እውር ተመሪው ፣ ሞኝ ተመካሪው ።

እውር እውርን ቢከተል ፣ ተያይዘው ገደል ።

እውር ይወልዱ ፣ እውር ቢፈርዱ ።

እውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም ።

እውነቱን ተናግሮ እመሸበት ያድራል ።

እውነት የተናገረ ፣ በመርከብ የተሻገረ ።

እውነትና ንጋት እያደር ይታያል ።

እዚያው ሞላ ፣ እዚያው ፈላ ።

እየቆሉ ጥሬ ።

እየቀረጣችሁ ፣ አንበሳውም ሄደ ፤ ነብሩም ሞተላችሁ ።

እየቤትህ ግባ ፤ እየራስህ ተቀባ ።

እየተፈጨ እየተቦካ ፣ እየሞተ እየተተካ ።

እየታጠቡት ያድፋል ፤ እየመከሩት ያጠፋል ።

እየወገንህ ቢሉት ፥ የሙቶ አመት ቆዳ ከብት ተራ ቆመ ።

እየፈለገው እወቀኝ እወቀኝ ብሎ መጣ ።

እያለው የማይከፍል ፥ ጭና የማያደላድል ።

እያየህ ተናገር ፤ እየዋኘህ ተሻገር ።

እያየኋት የምታስቅ ሚስት አገባሁ ።

እዩዩ ሲደላ ነው ።

እዳ ሰርጉ ፥ ነውር ማእረጉ ።

እዳ ቢያምርህ ዋስትና ፥ ኩነኔ ቢያምርህ ግብዝና ።

እዳ ከሜዳ ሲለኝ አደረ ።

እዳሪ ሳያወጣ የበላ ፥ እዳውን ሳይከፍል ጎታውን የሞላ ።

እዳሪ ያረሰ ፥ ለልጁ አጎረሰ ።

እዳው ዶሮ ፥ መጋቢያው ዳወሮ ።

እድለቢስ ሲዳር ፥ ውሃ ይሞላል በጥር ።

እድለቢስ አሞራ ፥ አንበጣ ሲመጣ አይኑ ይጠፋል ።

እድላም እሞሌ በቅሎ ይለውጣል ።

እድል የሌለው ፥ የሚለፋው ለሰው ።

እድል ፈንታ ፥ ጥዋ ተርታ ።

እድሜ ለንስሃ ፥ ዘመን ለፍስሃ ።

እድሜ ያልመከረው ሽማግሌ ፥ ከውሃ የገባ አሞሌ ።

እድሜና መስተዋት አይጠገብም ።

እድሜና ቁረንጮ ተበጣጥሶ ያልቃል ።

እድሜና ጨርቅ ፣ ሲበጣጠስ ያልቅ ።

እድሜና ጨርቅ ፣ በደህና አያልቅ ።

እድር ፣ እስከ በጌምድር ።

እጁ ተበትር ፣ አፉ ከነገር ።

እጁን በሰንሰለት ፣ እግሩን በግር ብረት ።

እጇን በጇ ቆረጥኩት ።

እጅ ላፍ ሚዛኑ ነው ፣ ባፍ የገባ ለእጅ ሃይሉ ነው ።

እጅ ሲነድ ፣ ልብ ይነድ ።

እጅ እሾህን ይነቅሰዋል ፣ ጥጋብ ሞትን ያስረሳዋል ።

እጅ ከልብስ ፣ ምላስ ከጥርስ ።

እጅ ይዘው ያስገቡት እጅ ይዞ ያስወጣል ።

እጅና አፍ አይተጣጡም ።

እጅና ጭራ ፣ አፍና እንጀራ ።

እጅግ ማግኘት ፣ ያመጣል ትእቢት ።

እጅግ ስለት ፣ ይቀዳል አፎት ።

እጅግ ብልሃት ፣ ያደርሳል ከሞት ።

እገሌ የዋለበት ሸንጎ ፣ አይጥ የገባበት እርጎ ፤ እርጎውንም ለውሻ ፣ እርሱንም ለውርሻ ።

እግረ ቀጭን እንደ ሰሳ ፣ ልበ ሙሉ እንደ አንበሳ ።

እግረ ቀጭን ይሞታል ሲሉት ፣ እግረ ወፍራም ይሞታል ።

እግሩን ለጠጠር ፣ ግንባሩን ለጦር ።

እግር ሄዶ ፣ ሄዶ ካር ጉድጓድ ይገባል ።

እግር ሲደርስ ፣ እግት ይመለስ ።

እግር ቢሳሳት ከአንጋዳ ፣ አፍ ቢሳሳት ከእዳ ።

እግር ተርካብ ፣ እጅ ተዛብ ።

እግር ከሸሸ ፣ ልብ ሸሸ ።

እግር የላት ፣ ክንፍ አማራት ።

እግር ዜጋ ነው ።

እግርና እራስ ፣ እኔ እለብስ ፣ እኔ እለብስ ይጣላሉ ።

እግርን ለጠጠር ፣ ደረትን ለጦር ።

እግዜር ሲሰጥ ፣ እንጀራ በወጥ ።

እግዜር ሲቆጣ ፣ በዝናብ አር ያመጣ ።

እግዜር ሲጥል እናት አታነሳም ።

እግዜር ባወቀ ፣ ሰማይን አራቀ ።

እግዜርን ሳይጨምር የቆጠረ ፣ ሁልጊዜ ሲቆጥር ይኖራል ።

እጠጣ ሲል ይዋኛል ፣ እበላ ሲል ይዳኛል ።

እጭን ያለ ኮርቻውን ፣ እለምን ያለ ስልቻውን ።

እፍረት ያከሳል ፣ ያመነምናል ።

ኧረ በከንቱ ፣ ማን ሊሰማ ነው ጩኸቱ ።

ኧረ ጉዴ ፣ ባሌ ገደለ በጎራዴ ።

## - ከ -

ከሀብታም ተወለድ ወይ ካለው ተጠጋ ።

ከሁለት አይነ ፍርቅርቅ ፣ አንድ አይነ ምሩቅ ።

እግር ሲደርስ ፣ እግት ይመለስ ።

እግር ቢሳሳት ከአንጋዳ ፣ አፍ ቢሳሳት ከእዳ ።

እግር ተርካብ ፣ እጅ ተዛብ ።

እግር ከሸሸ ፣ ልብ ሸሸ ።

እግር የላት ፣ ክንፍ አማራት ።

እግር ዜጋ ነው ።

እግርና እራስ ፣ እኔ እለብስ ፣ እኔ እለብስ ይጣላሉ ።

እግርን ለጠጠር ፣ ደረትን ለጦር ።

እግዜር ሲሰጥ ፣ እንጀራ በወጥ ።

እግዜር ሲቆጣ ፣ በዝናብ አር ያመጣ ።

እግዜር ሲጥል እናት አታነሳም ።

እግዜር ባወቀ ፣ ሰማይን አራቀ ።

እግዜርን ሳይጨምር የቆጠረ ፣ ሁልጊዜ ሲቆጥር ይኖራል ።

እጠጣ ሲል ይዋኛል ፣ እበላ ሲል ይዳኛል ።

እጭን ያለ ኮርቻውን ፣ እለምን ያለ ስልቻውን ።

እፍረት ያከሳል ፣ ያመነምናል ።

ኧረ በከንቱ ፣ ማን ሊሰማ ነው ጩኸቱ ።

ኧረ ጉዴ ፣ ባሌ ገደለ በጎራዴ ።

## - ከ -

ከሀብታም ተወለድ ወይ ካለው ተጠጋ ።

ከሁለት አይነ ፍርቅርቅ ፣ አንድ አይነ ምኑቅ ።

ከሁለት ዛፍ ያረፈች ወፍ ፣ ሁለት ክንፏን ትነደፍ ።

ከሁለት ያጣ ጎመን ።

ከሁሉ ልብ ይበርድ ፣ ከሁሉ ልብ ይነድ ።

ከሁሉ መጣላት ፣ ቀባሪ ማጣት ።

ከሁሉ ክፉ የመበለት አራስ ።

ከሆነ ወዲያ ንዴት ፣ ለሽበት ።

ከሆድ የመጣን ትፋት ፣ የጥርስ መግጠም አያድነውም ።

ከሆድ ያኖሩት ያድናል ፣ የተናገሩት ያስገድላል ።

ከሁዋላ ፀፀት ፊት መጠንቀቅ ።

ከለማኝ ለማኝ ፣ ቁረንጮዩን ቀማኝ ።

ከላይ እንዳያፈስ ፣ ከታች እንዳይተነፍስ ።

ከላይ ከደፈረስ ፣ ከታች አይጠራም ።

ከሌለ ባለቤት ፣ አይረዳም ጎረቤት ።

ከሌለ ባካፋ ፣ የለኝም ተስፋ ።

ከልጅ ልጅ ቢለዩ ፣ አመትም አይቆዩ ።

ከልጅ አትጫወት ፣ ይወጋሃል በንጨት ።

ከመሃል አይደርስ ፣ ከዳር አይመለስ ።

ከመሃይም ጎረምሳ ፣ የተማረ አሮጌ ።

ከመሆን ፋቂ ፣ ይሻላል ነጣቂ ።

ከመልካም ሽቱ ፣ መልካም ስም ይበልጣል ።

ከመልካም ጠላ ክፉ ጠጅ ፣ ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ ።

ከመመላለስ ፣ ይሻላል ማረስ ።

ከመመስከር ፣ ማስመስከር ።

ከመምህሩ ፣ ደቀ መዝሙሩ ።

ከመሞት ፣ መሰንበት ።

ከመረቁ አውጡልኝ ፣ ከስጋው ጠመኛ ነኝ ።

ከመሬት የወደቀ ስጋ ፣ አፈር ሳይዝ አይነሳም ።

ከመቃለል ፣ ማጠቃለል ።

ከመቅረት ማዘግም ይሻላል ።

ከመቅናት መፍታት ፣ ከመፍታት አለማግባት ።

ከመቆም መቀመጥ ፣ ከመቀመጥ ማላመጥ ።

ከመታማት ፣ ይሻላል መስራት ።

ከመታገል ፣ መታደል ።

ከመቶ ቅል ፣ አንድ እርኮት ።

ከመቶ አምሳ ዳዊት ፣ የልብ ቅንነት ።

ከመቶ ውሸት ፣ አንድ እውነት ።

ከመቸገር ፣ ለእግዜር መንገር ።

ከመቸገር ፣ ሰርቶ ማደር ።

ከመነኩሴ ቤት ስስት ፣ ከሸማኔ ቤት ቁጢት ።

ከመነኮሰች ባሰች ፣ ከቆረበች አፈረሰች ።

ከመነኮሰች ባሰች ፣ ከተተኮሰች አነከሰች ።

ከመናገር ማዳመጥ ፣ ከመዋጥ ማላመጥ ።

ከመናፍቅ ትርጓሜ ፣ ከትምባሆ ልምላሜ ።

ከመንታ የተንጠለጠለች ወፍ ፣ ሁለት ክንፉን ትነደፍ ።

ከመንቻካ ተሰናባች ፡ ደሀና ከዳተኛ ይሻላል ።

ከመንደር አደባባይ ፡ ከነጋሪት ደባይ ።

ከመውደቅ በፊት ተጠንቀቅ ፡ ከሞት በፊት ዕድቅ ።

ከመደብደብ ፡ ይሻላል ማደብ ።

ከመግፋት ፡ ይሻላል መገፋት ።

ከመጠምጠም ፡ መማር ይቅደም ።

ከመጣህ ፡ አዘን ልንገርህ ።

ከመጣሽ ፡ ማርያም ታምጣሽ ።

ከመጥፎ የተጋባ ፡ ገደል ገባ ።

ከመጫን ከመተብተብ ምናለኝ መሸከም ።

ከሚስቱ ጋር የቀረበ ፡ ከእግዜር የተማከረ ።

ከሚያስፈልገው በላይ የሚለማመጥህ ፡ ሊያታልልህ ፡ ወይም ሊገድልህ ።

ከማርከኝ ፡ ሞቴን አታሳየኝ ።

ከማሽላ ቢያስወጧት ፡ ከዘንጋዳ ገባች ።

ከማያውቁት መንፈስ ቅዱስ ፡ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል ።

ከማይረባ ሎሌ ፡ ወደል ውሻ ይሻላል ።

ከማይናገር ከብቱን ፡ ከማይራገጥ ወተቱን ።

ከማይጠቅም ኑሮ ፡ መቃብር ይሻላል ።

ከምሳ የተለየ ደብተራ ፡ ያደርጋል ሴራ ።

ከምን ላይ ቁመሽ ፡ እግዜርን ታሚያለሽ ።

ከምክር የለዩት ደብተራ ፡ ነገር ይሰራ ።

ከምድር አደላድሎ ከአህያ ፡ ከቡላድ አደላድሎ ከቋያ ።

ከሞተ በሁዋላ ማልቀስ ፣ ድንጋይ መንከስ ።

ከሞተ ንጉስ ፣ የቆመ አምባራስ ።

ከሞተ አንበሳ ፣ ያለ እንስሳ ።

ከሞቶች አቴቴ ፣ ምን አለኝ ካማቴ ።

ከሞቱ በሁዋላ መድሃኒት ፣ ካረጁ በሁዋላ አቤት አቤት ።

ከሞኝ ሽክም ሞፈር ቀንበር ይቆረጥበታል ።

ከሞኝ ክብረት የብልህ ድህነት ።

ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል ።

ከሩቁ በቅርቡ ፣ ከደረቁ በርጥቡ ።

ከሩቅ ዘመድ ፣ የቅርብ ጎረቤት ።

ከራስ በላይ ንፋስ ።

ከራስ ወዲያ መስካሪ ፣ ካምላክ ወዲያ ፈጣሪ ፣ ከጠጅ ወዲያ አስካሪ ።

ከራስ ጠጉር ፣ እስከ እግር ጥፍር ።

ከርቀም ነገ ነው ።

ከርዛት ክፉ ሱሪ ማጣት ፣ ከአካላት ክፉ የሆድ ጂማት ።

ከሮጠ ፣ ያንጋጠጠ ።

ከሰልስተኛ ይሻላል ትናንትና ።

ከሰማይ የወረደ ለምድር አይከብደውም ።

ከሰሪው ፣ አሰሪው ።

ከሰቀላ ፣ ወደ ጥላ ።

ከሰው መልካም ገበሬ ፣ ከእህል መልካም ፍሬ ።

ከሰው መርጦ ለሹመት ፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት ።

ከሰው ምቀኛ ፡ ይሻላል የባብ መርዘኛ ።

ከሰው ስህተት ፡ ከብረት ዝገት ።

ከሰው ቀለብላባ ፡ ከመሬት ገብጋባ ።

ከሰው አድር ብየ ፡ ቀረሁ ተታልየ ።

ከሰው አገር መልከኛ ፡ ያገር ምንደኛ ።

ከሰው እንደ ቡዳ ፡ ከከብት እንደ ጎዳ ።

ከሰው ክፉ የሚያማ ፡ ከእንጨት ክፉ ጠማማ ።

ከሰው ክፉ ደባል ፡ ከእንጨት ክፉ ደራል ።

ከሰው ክፉ ደባል ፡ ከጭነት ክፉ አላል ።

ከሰው ክፉ ደብተራ ፡ ካውሬ ክፉ ዳሞትራ ።

ከሰው ፊት አይበሉ ፡ ስጋን አይበድሉ ።

ከሰው ፊት ፡ ውሃ በወንፊት ።

ከሰጡህ አትለፍ ፡ በሰጡህ አትስነፍ ።

ከሰጭው ፡ አሳጭው ።

ከሱሪ የተሸሸገ ብልት ፡ እንቅልፍ የሌለበት ሌሊት ።

ከሳሽ የተከሳሽን ልብ ቢያውቀው ፡ ከቤቱ አይነሳም ነበር ።

ከሳሽና ተከሳሽ ፡ የመረጠን ያሽ ።

ከሴት ሆዳም ፡ ያንድ አመት በረዶ ይሻላል ።

ከሴት መምከር ፡ ደግሶ መስከር ።

ከሴት ነገር ፡ ከበቅሎ መንበር አይታጣም ።

ከሴት ነገር ፡ ከበቅሎ መደምበር ።

ከስስታም አፈር ይጠግባል ።

ከስብ ስም ይሸታል ።

ከስቼ ቢያዩኝ ፣ ቁማ ለመኑኝ ።

ከስድብ ከፉ አቅሙን አያውቅ ።

ከስጋ ብስና ፣ ጎመን በጤና ።

ከሶ ነገር ያጣ ፣ ቀብቅቦ ዘር ያጣ ።

ከሸንጎ ቢረታ ፣ ሚስቱን ከቤት መታ ።

ከሹመት ግብዝና ፣ ከህመም ቁምጥና ።

ከሹም ፊትና ከመጥረቢያ ፊት አይቆሙም ።

ከሺ ሎሌ ፣ አንድ በሬ ።

ከሺ ሎሌ ፣ አንድ ወሬ ።

ከሺ መካሪ ፣ አንድ ቋጣሪ ።

ከሺ ምስክር ፣ የታቦት እግር ።

ከሺ በቅሎኛ ፣ አንድ ፈረሰኛ ።

ከሺ ነፍጠኛ ፣ አንድ መልከኛ ።

ከሺ አባራሪ ፣ አንድ አምራሪ ።

ከሺ እብለት ፣ አንድ እውነት ።

ከሺ ወሬኛ ፣ አንድ ልበኛ ።

ከሺ ዋቢ ፣ ራሱ ቀራቢ ።

ከሺ ደብተራ ፣ አንድ ቄስ መንጓሳ ።

ከሺ ደብተራ ፣ የቄስ ደንካራ ።

ከሺ ገበና ፣ አንድ ቀጣፊ ልበኛ ።

ከሸማግሌ ምክር ከሸበታም ፣ ከጎበዝ ውረር ከጉልበታም ።

ከቀበጡ ሞት አይቀርም ።

ከቀኑ ያለፈ ስጋ መግማቱ አይቀርም ።

ከቀናተኛ ሰው ሽሽ ፣ እንዳትበላሽ ።

ከቀዳዳ ፣ ይሻላል ጨምዳዳ ።

ከቀጥቃጭ ያረፈደ ፣ ቀጥቃጭነት ለመደ ።

ከቁርባን ወጪ ክርስትና ።

ከቁንጫ ሌጦ ያወጣል ።

ከቁንጫ ፣ መላላጫ ።

ከቂጡ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም ።

ከቃጫ ወዲያ ገመድ ፣ ከእናት ወዲያ ዘመድ ።

ከቅርቡ የወደቀ ፣ መሰበሩ አልታወቀ ።

ከቅርብ የወደቀ ፣ ከስብራት ይድናል ።

ከቅርብ የወደቀ ፣ ከቁስል ይድናል ።

ከቆረሰ ፣ የጎረሰ ።

ከቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡ አይቀሩም ።

ከቋት የሚዘግንለት ፣ ከምርት የሚነፈግለት አለ ።

ከበላ ብላ ፣ ከሰው አትጣላ ።

ከበሬ ፊት መቆፈር ።

ከበሬ ፊት የምትገኝ ጥጃ የሳር በሽታ ይገላታል ።

ከበሮ በሰው እጅ ያምር ፣ ሲይዙት ያደናግር ።

ከበሽታ ላይ ችግር ፣ መሬ የሌለው እውር ።

ከበቀለ ፣ ያልተነቀለ ።

ከቡቃያየ ሲገባ አፈላማ ።

ከባህር አይቀዳ ፣ ለንጉስ አይረዳ የለም ።

ከባህር ወጥታ ጨዛ ላሰች ።

ከባለቤቱ የዋለ እንቁላል አይሰበርም ።

ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው ።

ከባለጌ ጡጫ ፣ ከዳገት ሩጫ ያድናችሁ

ከባላገር ንብ ፡ የከተማ ዝንብ ትበልጣለች ።

ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሽሮ አበድሪኝ ።

ከባልሽ ታረቂ ቢሏት ፣ ልመና መሰላት ።

ከባልንጀሮቿ ከፍ ያለች ማሽላ ፣ ወይ ለወፍ ወይ ለወንጭፍ ።

ከባቄላ ፣ አይጠፋም ዲቃላ ።

ከባእድ እየጎረስክ ወደ ዘመድ ዋጥ ።

ከባእድ ወደ ዘመድ ፣ ከጫካ ወደ መንገድ ።

ከባእድ ጋር የበሉት በሶ ፣ ይወጣል ደም ጎርሶ ።

ከቤተ ቀሊል ፡ ቤት ቆማጣ ይሻላል ።

ከቤት ዶሮ ሲገኝ ፣ ከውጪ ቆቅ ይያዛል ።

ከብልህ የሚወጣ ስህተት ተራራ ያህላል ።

ከብልህ ያለ ሞኝነት ተራራ ያህላል ።

ከብልህ ጠበቃ ሞኝ ራሱ ያውቃል ።

ከብቱ በእግት ፣ እጁን በሰንሰለት ።

ከብት ቢወፍር ለልደት ፣ ሰው ቢወፍር ለመሬት ።

ከብት አይቶ ከፉ ማግባት ፣ ከብቱ ቢያልቅ ሁለት ጥፋት ።

ከብት አይወድም ገደል ፣ ሰው አይወድም በደል ።

ከብት ያለረኛ ፣ ህዝብ ያለዳኛ ።

ከብዙ ጉልበት ፣ ትንሽ ብልሃት ።

ከብዙ ጉልበት ፣ ጥቂት ብልሃት ።

ከብዙ ፀሎት ፣ የልብ ቅንነት ።

ከተመቱ መጠርጠር ፣ ጅብ ከወሰደ አጥር ማጠር ።

ከተማረ ፣ የተመራመረ ።

ከተራበ ፣ አዝናለሁ ለጠገበ ።

ከተቆረበ ይበላዋል ፣ ሳይወድቅ ይታገለዋል ።

ከተባሉ ብየኛ ፣ ከታገሉት ደመኛ ።

ከተናጋሪ ሰሚ ፣ ከሰሚ ተርጓሚ ።

ከተናጋሪ ዝምተኛ ያስቆጣል ።

ከተዘጋ ቤቴ ፣ ከተዳፈነ እሳቴ ።

ከተዛመደ ፣ የተዋደደ ።

ከተዛመዱ ፣ የተዋለዱ

ከተያዙ ወዲያ ቄስ ጥሩልኝ ማለት ።

ከተጋደሉ ደመኛ ፣ ከተማማሉ ማለኛ ።

ከታዳጊ ጌታ ፣ ሰግደድ ያለ ቦታ ።

ከታገልህ ፣ አባትህ አይጣልህ ።

ከትንሽ በላተኛ ፣ ይሻላል ጠመኛ ።

ከነጂው የተጣላ በሬ ቀንዱ ቁርፍርፌ ።

ከነገረኛ ሰው ስንቅ አይደባልቁም ።

ከነገሩ ፣ ጠም እደሩ ።

ከነገሩት አያኅርስ ።

ከነገር ተው ባይ ፣ ከጦር አግባ ባይ ።

ከነገር እንጃ ፣ ከእህል አጃ ።

ከነገር ክፉ ቁጭት ፣ ከወፍ እስደንጋጭ ድርጭት ።

ከኑግ የተገኘን ሰሊጥ ፣ አብረሀ ወ ቀጥ ።

ከናበሳሽ ፣ ማን ይግዛሽ ።

ከናት ልጅ አያበልጡ ፣ ከሞት አያመልጡ ።

ከናት ትሻል ሞግዚት ።

ከናትዋ ልጅዋ ትብስ ፣ ባቄላ አርባት እጅዋን ትልስ ።

ከኔ ከወሰድሽው ፣ ተቀምጠሽ ልበሽው ።

ከንጉስ በላይ ሰው አይፈርድ ፣ ከባህር ላይ እሳት አይነድ ።

ከንፋግ አንድ ያንቀው ፣ አንድ ይወድቀው ።

ከአርባ አመት አትመክት ፣ ከሃምሳ አመት አትሟገት ፣ ከስልሳ አመት አትዶልት ።

ከአርብ ሮብ በፊት ይህን ይፁም ፣ ክፉ ነገር ካፍ አያወጡም ።

ከአባቱ ፊት የሚናገር ፣ አፍ ለምፅ ይሆናል ።

ከአውሬ ክፉ ዘንዶ   ከዝናብ ክፉ በረዶ ።

ከአይን ማየት ፣ የልብ እውቀት ።

ከአይን የራቀ ከልብ ይርቃል ።

ከአፍሽ ይለቡልሽ ፣ አይግባ ከሆድሽ ።

ከእህል ክፉ አጃ ፣ ከሳር ክፉ ሙጃ ፣ ከነገር ክፉ እንጃ ።

ከእንጨት አጥር ፥ የሰው አጥር ።

ከእውር ቤት አንድ አይና ብርቅ ነው ።

ከእጅ አይሻል ዶማ ።

ከኩትት እስከ ሽበት ፥ ከልጅነት እስከ እውቀት ።

ከካህን ይዋደዷል ፥ ከላም ይሳደዷል ።

ከክፉ ሎሌ ጌታው ኮበለለ ።

ከክፉ ባለዳ ጎመን ዘር ተቀበል ።

ከወረወረ ፥ የመከረ ።

ከወሰን ቢያልፉ ፥ ይቀስፉ ።

ከወደቁ ወዲያ መፈራገጥ ፥ ለመመለጥ ።

ከወደቁ ወዲያ መፈራገጥ ፥ ወገብን መምለጥ ።

ከወዳጅ መሰንበት ፥ አንጡ አለማለት ።

ከወገኑ የተለየ አንበጣ ፥ ይሆናል ፌንጣ ።

ከወገብ በላይ ታቦት ፥ ከወገብ በታች ጣእት ።

ከወፈሩ ፥ ሰው አይፈሩ ።

ከዋለች አደረች ፥ ካደረች ለመደች ።

ከውትር ውትር ፥ ይነሳል በትር ።

ከዘር የሚሰጡ ፥ ከአውድማ የሚነፍጉ ።

ከዘፈን ፥ ይሻላል ማዘን ።

ከዚሁ ብሶ ፥ አጎንብሶ ።

ከዚህ የወደቀን ሬሳ ፥ ማን ያንሳ ።

ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል ።

ከዝንጀሮ ጋሜ ፡ ያንበሳ መላጣ ።

ከይሉኝ አይል አይብ አትብላ ።

ከደሀና ቢደርሱ ፡ ያደርጋል እንደርሱ ።

ከደስ ደስ ፡ ይሻላል ማረስ ።

ከደባል ሆድ ቁርጠት ይሻላል ።

ከደግ ተወለድ ፡ ወይንም ከደግ ተጠጋ ።

ከዲዳ ፡ ላም ንዳ ።

ከዳቦ የተገኘን ወጥ ፡ አብረህ ግመጥ ።

ከዳኛ ፊት አይተነፍሱ ፡ እምዛ ከሰው ፊት አይቆርሱ ።

ከዳኛ ፊት አይናገሩም ዋዛ ፡ ከልጅ ፊት አይቆርሱም እምዛ ።

ከድሃ ቤት ሰርግ ፡ የባለጠጋ ቤት ሃዘን ይደምቃል ።

ከድሃ ከመበደር ፡ ከባለጠጋ መለመን ።

ከድስት እፍላል ፡ ከቅመም ድንብላል ።

ከጀርባ ሆድ ይቀርባል ።

ከጅብ ዋሻ ሲሸሹ ፡ እጅብ ዋሻ ።

ከጅብ የተጠጋ ፈረስ ሁዋላውን አያይም ።

ከጅብ ጎሬ ሸሽቶ ፡ ጅብ ዋሻ ።

ከጅብ ጎፈሬያም ያንበሳ መላጣ ።

ከገቢያ ሂዶ ማንቀላፋት ፡ ባፋፍ ላይ ሆኖ መንጠራራት ።

ከጌታህ አትፎካከር ፡ ከውሻህ አትሽቀዳደም ።

ከግቡ የተጎዳ ፡ ከጥንስሱ የተቀዳ ።

ከጠላት መሳም የወዳጅ መንከስ ።

ከጠጅ ወዲያ አስካሪ ፣ ከባለቤት ወዲያ መስካሪ ።

ከጢስ የተቀመጠን ልጅ አትንካው ።

ከጥላ ያረፉ ፣ ከሞት የተረፉ ።

ከጥቅምት ማለዳ ፣ የጊደር እዳ ።

ከጥንት ፣ እስከ አጥንት ።

ከጠጣ የዋለ ጉሬዛ ።

ከጨለመ ዱር ፣ ከጎደጎደ ምድር ።

ከጨርቅ ነጩ ፣ ከቡሃ ልጩ ።

ከጭቅጭቁ ከንዝንዙ ፣ የሌባ ገንዘብ ምነው ባይገዙ ።

ከጮማ ብስና ፣ የጎመን ጤና ።

ከፈታሁዋት ሚስቴ የተወለዱ ሁሉም የኔ ናቸው ።

ከፊት ተወጣ ጆሮ ፣ በሁዋላ የወጣ ቀንድ በለጠው ።

ከፍላት እጅ ጥልቅ ፣ ሙልቅቅ ።

ከፍታቱ ፣ መሻማቱ ።

ከፍትፍቱ ፣ ፊቱ ።

ከፍትፍቱ ፊቱ ፣ ከጠላው ማቶቱ ።

ከፎከረ ፣ የጠረጠረ ይሻላል ።

ኩላሊት ያጨሰውን ፣ ልብ ያመላለሰውን ፣ መርምሮ የሚያውቅ የለም ።

ኩሩ ሰው አይሸሽም ፣ አይዋሽም ፣ ቢሸሽም አያመልጥም ።

ኩራት እራት ነው ።

ኩበት ፣ ሰማይ ይከፍት ።

ካሀን ቢመኑን ፣ ክርስቱ ይለምን ።

ካሀንና ሽመላ ፡ ያልዘራውን ይበላ ።

ካሀያ ባልንት ፡ የፈረስ ውሽማነት ።

ካሀያ አፍለኛ ፡ የጅብ አሮጌ ይበልጣል ።

ካሀያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ መጣች ።

ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል ።

ካለስንቅ መንገድ ፡ ካለገንዘብ ንግድ ።

ካለፈ ወዲያ ነገር ይቆጫል ።

ካለፈቱ አይቀርሱ ፡ ካለርስት አይወርሱ ።

ካላረፉ ፡ መከራ ነው ትርፉ ።

ካላስተዋሉ ፡ አይገኝ ሁሉ ።

ካላበበ አያፈራ ፡ ካልሰማ አያወራ ።

ካላባት ፡ ዶሮ ባንት ።

ካላወቁት መንፈስ ቅዱስ ፡ ያወቁት ሰይጣን ።

ካላዋቂ ቤት እንግዳ ይዋኝበታል ።

ካላዩ ፡ አያሳዩ ።

ካላዩ አይቆጩ ፡ ካልሰሙ አይበሳጩ ።

ካላዩም አይነድ ፡ ካልሰሙም አይቆጭ ።

ካልረባ አዝማሪ ፡ ዋሬ ቃሚ ይሻላል ።

ካልረባ ጉልበት ፡ እዩልኝ ስሙልኝ ማለት ።

ካልረባ ግብር ፡ ይሻላል ጦም አዳር ።

ካልረባ ጎበዝ ይሻላል ቀበሮ ፡ ግልገል ያመጣል ተራራ ዞሮ ።

ካልሰሩ ፡ አይገኝ መከሩ ።

ካልሰሩ ፡ አይገኝ ብሩ ።

ካልሰጡ አይፀድቁ ፡ ካልተማሩ አያውቁ ፡

ካልቀመሰ ፡ የደገመ ባሰ ።

ካልታረደ አይታይ ስባቱ ፡ ካልተናገሩ አይገኝ ብልሃቱ ።

ካልታጣ ገበያ ጓያ ሸመታ ።

ካልቻኮሉ ፡ እንቁላል ይሄዳል በግሩ ።

ካልወደቀ አይሰበር ፡ ካልሞተ አይቀበር ።

ካልደፈረሰ አይጠራም ፡ ካልጠራ አይጠጣም ።

ካልጠበቁ ፡ አይጠይቁ ።

ካልጠገቡ አይዘሉ ፡ ካልዘለሉ አይሰበሩ ።

ካመት ልፋት ፡ ያንድ ቀን ጥፋት ።

ካመት በሽታ ያንድ ቀን ድንጋጤ ።

ካማራሪ ፡ አባራሪ ይሻላል ።

ካምና ይሻላል ዘንድሮ ።

ካሚጋች ፡ አስታራቂ ፡ ካጣቢ አድራቂ ።

ካረጁ መንገድ ፡ ከመነኮሱ መውለድ ።

ካረጁ አንባር ይዋጁ ።

ካረጁ ፡ አይበጁ ።

ካረገዘች ክታብ ያዘች ፡ ፈቷን ፈስታ ቂጧን ያዘች ።

ካስር ቡልኮ ግማሽ እንጀራ ።

ካሰብሽው ፡ አልተውሽው ።

ካስታዋይ ይልቅ አብድ በጤናው ይኖራል ።

ካበደው ያገረገረው ይበዛል ።

ካባት ልጅ አይበልጡ ፤ ከሞት አያመልጡ ።

ካብ አይገባ ድንጋይ ።

ካብሮ አደግህ አትስደድ ።

ካብታምና ካብታም አንተ ለኔ ፤ አንተ ለኔ ፤ ይባባላሉ ምን ነው ?

ካብነት ሁሉ ከሰ ፤ ለቤት መቋሚያ ምሰሶ ።

ካነጋገር ይፈረዳል ፤ ካያያዝ ይቀደዳል ።

ካንበሳ መንጋጋ ፤ ማን ያወጣል ስጋ ።

ካንተ አፍ ወሬ ፤ ከዝንጀሮ አፍ ጥሬ ።

ካንድ ልጃገረድ ፤ ይገኛል ሁለት ዘመድ ።

ካንድ ብርቱ ፤ ሁለት መድሀኒቱ ።

ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም ።

ካዋቂ ጠራቂ ፤ ከሂያጅ አጥባቂ ፤

ካዋቂ ጠራቂ ፤ ካጣቢ አድራቂ ፤ ከሂያጅ ጠያቂ ።

ካዋቂ ፤ ጠያቂ ።

ካይን የራቀ ፤ ከልብ ራቀ ፤

ካይን የፈጠነ ፤ ከውሃ የቀጠነ ።

ካይጥ ሽሽቶ ከባብ ፤ ከቤት ወጥቶ ከጠብ ።

ካይጥ ቤት ብቅል ፤ ከውሻ ቤት ጠፍር ።

ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ፤ ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ ።

ካገር ሆድ ይሰፋል ።

ካገር ደጋ ፣ ከመኻታ አልጋ ።

ካጉል ብልሃት ፣ አርሶ መብላት ።

ካጉል ጥንቆላ ፣ የሰው ልጅ መላ ፣

ካጋም የተጠጋ ቁልቋል እንዳለቀሰ ይኖራል ።

ካጣቢ ሳሙና ፣ ከምግባር ትህትና ።

ካጣቢ አድራቂ ፣ ከተሟጋች ታራቂ ።

ካጤ ቃል በላይ ፣ ዋና አታላይ ።

ካጪደ የሰበሰበ ።

ካጭር ምክር ፣ ከረጂም ውረር ።

ካፈር በላይ ተንጋለው ፣ ይህን ማን ተቀብለው ።

ካፍ ከወጣ አፋፍ ።

ካፍ ወለምታ የእግር ወለምታ ይሻላል ።

ካፍ የወጣ ቃል ፣ ከእጅ የወደቀ እንቁላል ።

ካፍ የወጣ ፣ ከጥርስ የነጣ ።

ከረምት ከጭቃ ፣ ከበጋ ከግጫ ፣

ከረምትና በጋ ፣ ቆላና ደጋ ።

ከረምትና ኮሶ ፣ ቤት በምሰሶ ፣ ።

ከረምትና ወላድ ሲጠሉት ያከብራል ።

ከረምትን የፈጀ በጋ ፣ እዳውን የፈጀ ዜጋ ።

ከርና መርፌ ፣ ስንደዶና ወስፌ ።

ከርና ነገር ባጭር ።

ከርስትናም እነሳለሁ ፣ ፋጡማንም እወዳለሁ ።

ከንፉ የተሰበረ አሞራ ፣ ከስሩ የተነቀለ ወይራ ።

ከጾ ከመሟገት ፣ አምኖ መረታት ።

ከፉ ለመናገር ፣ ቂጣ ለመጋገር ።

ከፉ ሎሌ ከሰው ፊት ያሳፍራል ።

ከፉ መልስ ፣ ይሰብራል ራስ ።

ከፉ ሰው ለከፉ ቀን ይሆናል ።

ከፉ ሰው በከንፈሩ ያለቅሳል ።

ከፉ ሰውን ከመሬት ፣ በግን ከበረት ።

ከፉ ሴት ጧት ወተት ፣ ማታ ሬት ።

ከፉ በሬ ያስቸግራል ለገበሬ ፣ ከፉ ገበሬ ያስቸግራል ለበሬ ።

ከፉ ፣ በትር ነው ትርፉ ።

ከፉ ነገር ከከርስ ፣ ከፉ ስጋ ከቁርስ ፣

ከፉ አሽከር እሰው ቤት ሲደርስ ወደ ሁዋላ ይቀራል ።

ከፉ አውሬ አይልመድ ፣ ከለመደም አይውለድ ።

ከፉ የከፋለት ፣ ቢስ የባሰለት ።

ከፉ ፣ ይነካል በከንፉ ።

ከፉ ጌታ ከዳገት ያሰግራል ።

ከፉ ጎረቤት ዶሮና ፍየል ያረባል ።

ከፉን አይረሱም ፣ አይነሱም ።

ከፉት እሌለበት ፣ የለም ሃጢአት ።

ኮሶ ላልቀመሰው ፣ ይመር አይመስለው ፣

ኮሶ ላፍ ይመራል ፣ በሁዋላ ጠላት ይገድላል ።

ኮሶ ሲጠጣ ስቅጥጥ ፣ ወተት ሲጠጣ ሽምጥጥ ፣

ኮሶ ሳይመር ፣ አያሽር ።

ኮሶ በኮሶ ይሞታል ።

ኳደሬ በንጉስ ፣ መበለት በቄስ መቅናት አይችልም ።

## - ወ -

ወለባ ፣ ለሹርባ ።

ወልደው ሳይጨርሱ ፣ በሰው ልጅ አይስቁ ፣

ወልደውት ያላሳረፈ ፣ ነግዶ ያላተረፈ ።

ወልዶ አይሳምለት ፣ ተናግሮ አይሳቅለት ።

ወልዶ አይስም ፣ ዘርቶ አይቅም (የለም) ።

ወልዶ አይስም ፣ ዘርቶ አይከምር (የለም) ።

ወልጂ አላከሁ ፣ መንኩሼ አልፀደቅሁ ።

ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ፣ ዋግ የመታው ስንዴ ፣

ወራሽ የሌለው ባለፀጋ ፣ ፍራሽ የሌለው አልጋ ፣

ወራት ይገፋል ባቄላ ፣ ጠላት ያጠፋል ዲቃላ ።

ወራጅ ውሃ አይውሰድህ ፣ ሟች ሽማግሌ አይርገምህ ።

ወሬ ለጠያቂ ፣ ገበጣ ላዋቂ ።

ወሬ ቢነግሩህ መላ ጨምር ።

ወሬ ቢያምርህ በየሎሌህ ።

ወሬ ብነግርህ በሚስጥር ፣ መላ ጨምር ።

ወሬ ታሽቶ አይቆረጠም ፣ ነገር ተዘግኖ አይቃም ።

ወሬን ከባላገር ፣ ጦርነትን ከወታደር ።

ወሬኛ ሚስት ፣ ዘርዛራ ወንፊት ።

ወርቁ ቢጠፉ ፣ ሚዛኑ አይጠፋ ።

ወርቁ ከዳኛ ፊት ይቅረብ ፣ መፃፉ ከቄስ ፊት ይነበብ ።

ወርቅ ሳንጣሪ ፣ በቅሎ ሳስጋሪ ።

ወርቅ በእሳት ፣ መሬት በጣት ።

ወርቅ የያዘ ሳጥን በወርቅ አልተለበጠም ፣

ወርቅ ያለው ቀበዝባዛ ፣ እህል ያለው ፈርዛዛ ።

ወርቅና ሰም ፣ ፈትልና ቀለም ።

ወርቅና ጨዋ አስታራቂ ነው ።

ወርቹ አሳልፎ ገራፊ ፣ ዳኛ ካለ ዘራፊ ።

ወርቹ የረገጠው ፣ እግር አይስተው ።

ወርውረው ቢስቱት ያልወጉት ይመስለዋል ።

ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም ።

ወተት ለእንቦሳ ፣ ስጋ ለአንበሳ ።

ወተት ተበድሮ ለእንግዳ ፣ ቅቤ ተበድሮ ላቁማዳ ፣

ወተት ተበድሮ ለእንግዳ ፣ ፈረስ ተውሶ ለሜዳ ።

ወተት ጠጥቶ ጠላ ፣ እግዚሄር ሲጠላ ፤ ጠላ ጠጥቶ ወተት ፣ የእግዚሄር ስጦታ ።

ወተቷንም አለቀ ፣ ጥጃዋም አይከሳ ።

ወታደር ሲያረጅ አቃቢ ይሆናል ።

ወታደር ሲደኸይ ጃኖ ያዘወትራል ።

ወታደር ቢበድል ፣ ባላገር ይካስ ።

ወታደር ባለቃው ፤ ባላገር በጭቃው ።

ወታደር ፤ ዋቶ አደር ።

ወንዝ ለወንዝ መቀደስ ፤ ያረፈ ሰይጣን መቀስቀስ ።

ወንዝ ለወንዝ ሩዋጭ ፤ የሰው በግ አራጅ ።

ወንድ ሊበላ ፤ የሴት ሌባ ።

ወንድ ልጅ ለፈረስ ፤ ሴት ልጅ ለበርኖስ ።

ወንድ ልጅ በበላበት ፤ አንበሳ በሰበረበት ።

ወንድ ልጅ በተሾመበት ፤ ሴት ልጅ ባገባችበት ።

ወንድ ልጅ አንድ ቀን እንደአባቱ ፤ አንድ ቀን እንደእናቱ ።

ወንድ ባለ በእለት ፤ ሴት ባለች በአመት ።

ወንድ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ ፤ አመልማሎ ይስጡት ይፍተል እንደእናቱ ።

ወንድ የሞተበት ፤ ወንድ አይሻገርበት ።

ወንድም ለግርግርታ ፤ ጋሻ ለመከታ ።

ወንድም ወንድሙን አይበልጠው ፤ ምላጭ ምላጭን አይቆርጠው ።

ወንድምና ወጥ ማስፈራሪያ ነው ።

ወንድምን አስቀይሞ ከመፆም ፤ ይሻላል ስጋን መኮምኮም ።

ወንጭፉ ባልነበረ ፤ የማሽላ እሸት ደግ ነበረ አለች ወፍ ።

ወዛም ይገማል ቢለው ፤ የንጭ ወሬ ነው አለ ።

ወዩው ጉድ አይገርምም ፤ ጂል ሰው አያሳዝንም ።

ወየው ጉድ ፤ ያሰቡት አይገድ ።

ወይ ልጅ ፤ በማን እጅ ፤

ወይ መሮጫ ሜዳ ፤ ወይ መውጫ ቀዳዳ ።

ወይ ባልዘፈንሽ ፥ ከዘፈንሽም ባላሳፈረሽ ።

ወይ ባይ እንደ ጠሪው ነው ።

ወይ አለማወቅሽ ፥ መራቁ አገርሽ ።

ወይ አገርሽ መራቁ ፥ ልቤን አለማወቁ ።

ወይ አጥብቆ ይርቃል ፥ ወይ አንድዶ ይሞቃል ።

ወይ የምድር ሰው ፥ እኔ ዘንድ ሆነህ ባየኸው ።

ወይ ጉዱ ፥ ላግባሽ አለኝ ነጋዴ ።

ወይ ጋሻ ፥ ቀድሞ ቀረሻ ።

ወይ ጣጣ ፥ ምን ነገር መጣ ።

ወይ ጣጣ ፥ በዚህም አያስወጣ ።

ወይ ጣጣ ፥ ዞሮ መጣ ።

ወይም አጥፍቶ ይርቃል ፥ ወይም አንድዶ ይሞቃል ።

ወይኖ አረሰው ፥ ወይኖ ጎረሰው ።

ወይኖን ግረፈው ፥ ለቡሉ እንዲሰማው ።

ወይዘሮና ሚዶ ፥ ገበሬና ምሳር ።

ወይፈን ለገራፊ ፥ አሳ ለጠላፊ ።

ወይፈን ካረሰው ፥ በሬ ያንከላወሰው ።

ወይፈን ካሳመረው ፥ በሬ ያበላሸው ይሻላል ።

ወደ ጎሬ መሄድ ፥ መጥፎ አካሄድ ።

ወደሽ ከተደፋሽ ፥ ቢረግጡሽ አይከፋሽ ።

ወደቀ ሲሉ ተሰበረ ።

ወዲያ አጥፍቶ ይርቃል ፥ አልምቶ ይሞቃል ።

ወዳጁን የሚበድል ለወንድሙ አይሳሳም ።

ወዳጄ ስለው በለጠኝ ፣ ስለቴ ስለው ቆረጠኝ ።

ወዳጄ ቢጠላኝ ፣ ሸክሙ ቀለለኝ ።

ወዳጅ ሲበዛ ፣ ጠላት ይቀንሳል ።

ወዳጅ ሲከዳ ፣ ይቀላል እዳ ።

ወዳጅ ባንደበቱ ፣ ውሻ በጅራቱ ።

ወዳጅ ወዳጁን አይከዳም ፣ ከጅብ ወዲያ ሆዳም ።

ወዳጅህ ሲታማ ፣ ለኔ ብለህ ስማ ።

ወዳጅህ ቢሰክር ይስምሃል ፣ ጠላትህ ቢሰክር ይነክስሃል ።

ወዳጅና ስእል በሩቅ ያምራል ።

ወዳጅና ጠላት አንድነት ይስሙሃል ፣ አንድነት ይጠይቁሃል ።

ወድቆ ይነሷል በእጅ ፣ ዘግይቶ ይከብሯል በልጅ ።

ወዶ የዋጡት ቅልጥም ፣ ከብርንዶ ይጥም ።

ወዶ ገባ ፣ ልብሱ ዳባ ።

ወዶ ገባ ውሻ ፣ ባለቤቱን አትግባ ይላል ።

ወገኑ ብዙ ፣ ሀዘኑ ብዙ ።

ወገን ያለው ፣ ማንም አይታገለው ።

ወገን ያለው ያግባሽ ።

ወግ ነውና ሲዳሩ ማልቀስ ።

ወግ አድራሽ ገበሬ ፣ ይሞታል በሰኔ ።

ወጠጤ ለወጠጤ ቢማከሩ ፣ እንዳይታረዱ ።

ወጡ ሳይወጠወጥ ፣ ወስከንባዩ ቂጥ ።

ወጥ ለኛ በርበሬ አይደቅልንም እንጂ ።

ወጥ ማን ያውቃል ? ቀላዋጭ ።

ወጥ ሲታጣ ይበላል በዱባ ።

ወጥ ቢጣፍጥ ፥ እጅ ያስመጥጥ ፤

ወጥ ያጣ ዱባ ፥ ልብስ ያጣ ዳባ ።

ወጥ ያጣ ጎመን ፥ አገር ያጣ ሰሜን ።

ወጥ ይሉሻል በርበሬ ነው ።

ወጥን የሚጨርስ መጎራረስ ፥ ሴትን የሚያስመታት መመላለስ ።

ወጭትና ሴት ሲከናነቡ ይሻላል ።

ወፍ እንዳገሯ ትጮሃለች ።

ወፍ ከድንጋይ ላይ አርፋ ፥ ፍሊጋዋ ጠፋ ።

ወፍ የሚፈራ ዘንጋዳ አይዘራም ።

ወፍ ጠባቂ ቢያደርጓት ፥ ድንጋይ ለቃሚ ቀጠረች ።

ወፍ ጠባቂ ቢያደርጓት ፥ ድንጋይ ለቃሚ አገባች ።

ወፍራም ቢከሳ ይቀጥናል ፥ ቀጭን ቢከሳ ይመነምናል ።

ወፍጮና ሴት ፥ መቼም አይሞላላት ።

ዋሱን የሚያወጣ ፥ ጢም አያወጣ ።

ዋስ አይሞግት ፥ ቆማጣ አይፈትፍት ።

ዋስ አይወሳወስ ፥ በግ አይናከስ ።

ዋስ ካለህ ዱቄትክን ለነፋስ አበድረው ።

ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ ፥ ነፋስ በወጥመድ እይዛለሁ ።

ዋቢ ተሸሸ ፡ ጠላ ከጎሸ ።

ዋቢ ያለው ባጤ በቅሉ ይቀመጣል ።

ዋቢ ያለው ያመልጣል ፡ ዋቢ የሌለው ይሰምጣል ።

ዋቢ ያለው ይወጣል ፡ ዋቢ የሌለው ይቀጣል ።

ዋና ከቤት ፡ ጠባቃ ከዱለት ።

ዋንዛ በልታ ብሳና መረቀች ።

ዋንጫ በገበታ ፡ ሹመት በተርታ ።

ዋጨው ብላት ትጎርስበት ፡ ተይው ብላት ትጨምርበት ።

ውሃ ለሚወስደው ሰው ፡ በትርህን እንጂ እጅህን አትስጠው ።

ውሃ ለቀደመ ፡ ግዳይ ለፈለመ ።

ውሃ ለወሰደው ፍለጋ የለውም ።

ውሃ ሊያንስ ሲል ይገማል ፡ ሰው ሊያንስ ሲል ይኮራል ።

ውሃ ላነቀው ፡ ባለቤቱ ላላወቀው ፡ መድሃኒት የለውም ።

ውሃ ልትቀዳ ሂዳ እንስራዋን ረስታ መጣች ።

ውሃ መልስ ፡ ውሃ ቀልስ ።

ውሃ ምን ያገሳ ፡ ድሃ ምን ያወሳ ።

ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው ።

ውሃ ሲደርቅ ይሸታል ፡ ሰው ሲከዳ ይወሸከታል ።

ውሃ ሲጎድል ተሻገር ፡ ዳኛ ሲገኝ ተናገር ።

ውሃ በለዘብታ ድንጋይ ይፈነቅላል ።

ውሃ በብልሃት ፡ ይቆላል በእሳት ።

ውሃ በእሳት ፡ ሰላ በዳገት ።

ውሃ ቢወግጡት እንቦጭ ።

ውሃ ቢደርቅ ፣ አሳ ያልቅ ።

ውሃ አያንቅ ፣ አገር አያልቅ ።

ውሃ እድፍን ያጠራል ፣ ትምህርት ልብን ያበራል ።

ውሃ ከነቁ ፣ አበባ ከአፀቁ ።

ውሃ የሚወስደው ሰው አረፋ ይጨብጣል ።

ውሃ የጥቅምት ነበርሽ ፣ ማን በጠማሽ ።

ውሃ ፣ ጭስ ፣ ክፉ ሴት ፣ ሰውን ያበራሉ ከቤት ።

ውሃና ገደል እያሳሳቀ ይወስዳል ።

ውሃና ጠጅ እኩል ይጠጣሉ ።

ውሃን መመለስ ፣ ወደ ሌላ ማፍሰስ ።

ውሃን ምን ያስጮኸዋል? ድንጋይ ።

ውሃውም እንዳይደርቅ ፣ አሳውም እንዳያልቅ ።

ውሃውም እንዳይደርቅ ፣ አሳውም እንዳያልቅ ፣ አድርገ ነው እርቅ ።

ውላ ከመጣች ፣ ነገር አመጣች ።

ውላ ውላ ፣ ባሏ ሲመጣ ትበላ ።

ውል አያወላውል ፣ ምላት አያሻግር ።

ውል አይፈርስ ፣ አይን አይፈስ ።

ውል ያዋለ ፣ ሰንበት ያከበረ ።

ውል ያዋውላል ።

ውል ያዋውላል ፣ ታንኳ ያሻግራል ።

ውል ያዋውላል ፣ ታንኳ ያሻግራል ፣ አቧራ ያስላል ።

ውል ያዋውላል ፡ ትምባሆ ያስላል ።

ውሎ ውሎ አህያ ለጅብ ።

ውሎ ውሎ ከቤት ፡ ኖሮ ኖሮ ከመሬት ።

ውረድ ከማማ ፡ ውጣ ከጫማ ።

ውርርድ ፡ ቁም ነገር ይጋርድ ።

ውርርድ እንደጫፉ ፡ ዛፍ እንደቅርንጫፉ ።

ውርርድ ከጫፉ ፡ አሞራ ከክንፉ ።

ውርርድ ከጫፉ ፡ አሞራ ከዛፉ ።

ውርደት ካር ይገማል ።

ውሸት ተናግረህ እውነትን አግኝ ።

ውሸት ደግ ነበር ፡ ጣጣው ባል ነበር ።

ውሸትና ቅራሪን ሽምጥጥ ነው ።

ውሻ ምሳ በማጣት ያረጃል ።

ውሻ ምን ትበያለሽ ? አለች ጌኛ ፤ ቢበልግም እሌቴን ባይበልግም አንችን ።

ውሻ ሳይችግረው ገበያ ወጥቶ ይደበደባል ።

ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል ።

ውሻ በቀደደው ፡ ጅብ ገብቶ ለመደው ።

ውሻ በበላበት ይጮሃል ።

ውሻ ቢመላለስ ፡ የልቡን አያደርስ ።

ውሻ ቢጠሩ ፡ ቀን ቢቆጥሩ ፡ ደረሰ በእግሩ ።

ውሻ አጥንትን የሚቆረጥመው ፡ መዋጥ ቢያቅተው ።

ውሻ ከሊጥ ፡ ጠጣ ከጥጥ ።

ውሻ ከሸሹለት ፥ ልጅ ከሳቁለት ፥ ያ አይመለስ ፥ ያ አይታገስ ።

ውሻ ካልቀበጠ ጅብ አይበላውም ።

ውሻ የሚበላውን እንጂ የተቃጣበትን ዱላ አያይም ።

ውሻ ጌታዋን በለጠች ።

ውሻ ጌታዋን እንጂ የጌታዋን ጌታ አታውቅም ።

ውሻም በላው አንቺም በላሽው ፥ ካልከደንሽው ።

ውሻና ውሻ ባጥንት ይጣላል ፥ በአውሬ ይስማማል ።

ውሻን በእግር መምታት ፥ እንካ ብሎ ስጋን መስጠት ።

ውሽማ ሲቆይ ባል ይሆናል ።

ውሽማዋን ብታይ ባልዋን ጠላች ።

ውሾች ምንጊዜ ነው የሚናከሱ ? ጅብ አባረው ሲመለሱ ።

ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ።

ውትር ውትር ፥ ያነሳል ብትር ።

ውዝፍ ለሹም ፥ ጥንብ ለጅብ ።

ውድሽና ውዴ ፥ የለቀሙት ስንዴ ።

ውጣ ከቤት ፥ ተነቀል ተመሬት ።

ውጣ ውጣ ከሚሉት በሬ ዶማ ይሻላል ።

ውጦ ውጦ ጨረሰው ፥ አይመረው አይተኩሰው ።

ዋ ፥ ቅል ካንተ በሁዋላ ገደል ።

# - ዘ -

ዘመነ ግልምቢጥ ፣ ውሻ ወደ ሰርዶ አህያ ወደ ሊጥ ።

ዘመን የሰጠው ቅል ፣ ድንጋይ ይሰብራል ።

ዘመን የወለደው ፣ ንጉስ የወደደው ።

ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው ።

ዘመዱን ያማ ፣ ገማ ።

ዘመድ ሲጣላ ያረክሳል

ዘመድ በዘመዱ ፣ አይጨክንም ሆዱ ።

ዘመድ ቢረዳዳ ፣ ችግርም አይጎዳ ።

ዘመድ ከዘመዱ ፣ አህያ ካመዱ ፣።

ዘመድ ያረጀ ፣ በልቶ ያፈጀ ።

ዘመድና መድሃኒት ፣ የተቸገሩ ለት ።

ዘመድና ሚዛን ከወገብ ይይዛል ።

ዘመድና እሳት ሩቅ በሩቅ ።

ዘመድና ዋንጫ እያለቀሰ ይመጣ ።

ዘመድና ገንዘብ ሳያስቡት ይገኛል ።

ዘመድና ፍየል ቤት አጥፊ ነው ።

ዘመድን ከዘመድ ጋር ማማት ፣ ዳቦ መግመጥ ነው ።

ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጅንፎው አይለቀቅም ።

ዘምቶ ተወረሰ ።

ዘምቶ ያረጀ ፣ በልቶ ያፈጀ ።

ዘረፋና ቀን ካልተሻሙበት ያልቃል ።

ዘሩ የጣቴ ፣ ምድሩ ያባቴ ።

ዘር ልትበድር ሂዳ ፣ እህል ሲሸት መጣች ።

ዘር ከልጓም ይስባል ።

ዘር ከልጓም ይጠቅሳል ።

ዘርቶ መቃም ፣ ወልዶ መሳም ።

ዘርቶ ያልበላ ፣ አምላክን ጠላ ።

ዘንጋዳ ተቆረጡት አገዳ ፣ ሚስት ከፈቷት ባዳ ።

ዘንጋዳ ተቆረጡት አገዳ ፣ እደኛ ከደረሱ እዳ ።

ዘንጋዳ የገለበጠ ፣ አባቱን የገላመጠ ።

ዘንጋዳና ወታደር ፣ በመከር ጊዜ ይታይ ነበር ።

ዘንዶ ፣ የዳገት በረዶ ።

ዘንግ ከተተከለ ልብ ተከፈለ ።

ዘኬውን ሲቋጥር ፣ እነቀው ነብር ።

ዘጠኝ ሞት መጣ ቢለው ፣ እንዱን ግባ በለው አለው ።

ዘጠኝ ጠጥቶ አስረኛውን የወደደ ፣ በሙሉ ነደደ ።

ዘጠኝ ጠጥቶ አስር የወደደ ፣ ዘጠኙ ተናደ ።

ዘፈን በበገና ፣ ነገር በዋና ።

ዘፈን በከበሮ ፣ አዋጅ በደበሎ ።

ዘፈን አለ በገና ፣ ነገር አለ በዋና ።

ዘፍኖ አያምር ፣ እንኳን አልቅሶ ።

ዘጥ ዘጥ ፣ አቁማዳ ቂጥ ።

ዛር ልመና ፣ ሳይያዙ ገና ፤ ከተያዙ ብዙ ነው መዘዙ ።

ዛብ የሌለው ፈረሰኛ ፣ ምሳ የሌለው ኮሶኛ ።

ዛፍ ሲወድቅ ከግንዱ ፣ ሰው ሲቸገር ከዘመዱ ።

ዛፍ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል ።

ዛፍ ዝናብ ያስጥላል ፣ ትልቅ ሰው ከጸ ያስጥላል ።

ዛፍ ያለቅርንጫፍ አይደምቅም ፣ ሰው ያለሰው አይከበርም ።

ዛፎች ቢጠፉ ፣ ቁጥቋጦች ተሰለፉ ።

ዜማ በሃሌ ፣ ነገር በምሳሌ ።

ዝሆኑ ሳለ ዱካውን ።

ዝሆን ለቀንድ ፣ ባላባት ለትውልድ ።

ዝሆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል ።

ዝሆን እንሆት ፣ ፍለጋው ወዬት ።

ዝሆን ጥርሱን ፣ አዝመራ ገብሱን ።

ዝም ማለት ከሞኝ ያስቆጥራል ።

ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም ።

ዝም ፣ አይነቅዝም ።

ዝም ያለ ተንኮለኛ ይመስላል ፣ እንብላ ያለ ስስታም ይመስላል ።

ዝምታ ለበግም አልበጃት ፣ አስራ ሁለት ሆና አንድ ነብር ፈጃት ።

ዝምታ ወርቅ ነው ፤ መናገር ብር ነው ።

ዝቅ ቢል ከገብርዬ ፣ ከፍ ቢል ከዚያ ሰውዬ ።

ዝባድን ከውሻ ፣ እምነትን ከባለጌ አትሻ ።

ዝናር የሌለው ነፍጠኛ ፣ አለንጋ የሌለው ፈረሰኛ ።

ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር ።

ዝናብ ሊጥል ሲል ይነፍሳል ።

ዝናብ ሲያባራ ከዋሻ ፥ ምን ሊሻ ።

ዝናብ ሳይመጣ ገና ፥ የውሃ መንገድ መጥረግ ደህና ።

ዝናብ ባይመጣ ሁሉ ቤት ፥ እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት ።

ዝናብ ከደመና ፥ ነገር ከዋና

ዝናብ ዘነበ ቢለው ፥ ከደጅህ እየው ።

ዝናብና ልጅ ሲጠሉት ያከብር ።

ዝንብ ሩቅ አይበር ፥ የሚዳ ልጅ ዱር አይደፍር ።

ዝንብ ሳይቅሙ ፥ ዝግን አይቅሙ ።

ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍት ።

ዝንብ ቢሰበሰብ ጋን አይከፍትም ።

ዝንብ ካይን ፥ ጭራ ከዘባን ።

ዝንጀሮ መቀመጫዬ ይብሳል አለች ።

ዝንጀሮ ፥ ሰው ነበር ይላሉ ዱሮ ።

ዝንጀሮ ቢሰበሰብ ውሻን አይመክትም ።

ዝንጀሮ እንሳሳቅ ካልሽ ፥ ነዶዬን መልሽ ።

ዝንጀሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ ፥ በባልንጀራዋ ትስቃለች ።

ዝንጀሮና ጥዋ ከፋ ነው የሚይዝ ።

ዝንጀሮን በበግ ለውጠኝ ቢለው ፥ ጣፋጩን ትቼ አልማጩን ።

ዝንጅብል ማን? ቢሉህ ማነኝ ትል ።

ዞር አሉ አልሸሹም ።

ዞሮ ዞሮ ፣ መዝጊያው ጭራሮ ።

ዞሮ ዞሮ ፣ የዶሮ አንገት በማሰሮ ።

## - የ -

የሀምሌ ብራ ፣ የባልቴት ወበራ ።

የሀምሌን ወሃ ጥም ፣ የሀዳርን ራብ የሚያውቅ ያውቀዋል ።

የሃር ገመድ ፣ የበቅሎ ክበድ ።

የሀብታም ልጅ ሲጫወት ፣ የድሃ ልጅ ይሞታል ።

የሀጢአት ክፉ ጉቦ ፣ የበሽታ ክፉ ተስቦ ።

የሀጥኡ ዳፋ ፣ ፃድቁን ያዳፋ ።

የሁለት ሴቶች ባል ፣ ይሞታል ይበላል ሲባል ።

የሁለት አገር ሰደተኛ ።

የሁለት እዳ ከፋይ ።

የሀልም ሩጫ ፣ የጨለማ ፍጥጫ ።

የሆነ አይመለስ ፣ እሳት አይጎረስ ።

የሆድ ማበድ ፣ ያስቃል በግድ ።

የሆድ ምቀኛ አፍ ነው ።

የሆድ ብልሃት ፣ የጋን መብራት ።

የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ።

የሁዋላ ሁዋላ ፣ አይቀርም ዱላ ።

የለመነ ፣ መነመነ

የለመነ ያገኛል ፣ የነገደ ያተርፋል ።

የለመኑትን የማይነሳ ፣ የነገሩትን የማይረሳ ።

የለመደ ልማድ ፣ ያሰርቃል ከማእድ ።

የለመደ እጅ ፣ ጆሮ ግንድ ያስመታል ።

የለመደ ፈረሰኛ ዛብ አይጨብጥ ፣ እርካብ አይረግጥ ።

የለመደች ጦጣ ፣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ ።

የለማኝ ስልቻ ሲንከባለል ፣ ከለማኝ ደጅ ይወድቃል ።

የለም ቀሪ ፣ ካለ ፈጣሪ ።

የለበሰ ፣ የማንንም ጎረሰ ።

የለበሱት ያልቃል ፣ የሰጡት ያፀድቃል ።

የሊጋስ ምስክሩ መስጠቱ ።

የላሜ ልጅ ፣ ያውራዬ ውላጅ ።

የላም መንጃ ፣ የሽማ መከንጃ ፣ የማር መቅጃ ።

የላም ወተቱን ፣ የጌታ ከብቱን ።

የላከ እንደ አፉ ፣ ያከከ እንደ እጁ ፣ አይሆንለትም ።

የላይ ለምጡን ፣ የውስጥ እብጡን ፣ ባለቤቱ ያውቀዋል ።

የላይ እልጋ ፣ የውስጥ ቀጋ ።

የላይኛው ከንፈር ለክርክር ፣ የታችኛው ከንፈር ለምስክር ።

የላጭን ልጅ ቅማል በላው ፤ ያናጢን ልጅ ጅብ በላው ።

የሌለው ልብ የለው ፣ ወዳጅ የለው ።

የሌለው ሚስት የለው ፣ ወዳጅ የለው ።

የሌሊት ግስገሳ ፣ የቀን ዘለሳ ።

የሌላት እራት ፣ ደግሞ ምሳ አማራት

የሌባ ምኝታው ካመድ ፣ መታሰሪያው ገመድ ።

የሌባ ሞኝ ፣ ከጎተራ ስር ይገኝ ።

የሌባ አይነ ደረቅ ፣ መልሶ ልብ ያድርቅ ።

የሌባ እጁን ፣ የፍየል ልጁን ።

የሌባን ጠባቃ ፣ አደባልቀህ ውቃ ።

የልመና በሬ ትክክል አይሄድም ።

የልመና እንጀራ ምንጊዜም ከልመና አያወጣም ።

የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል ።

የልብ ሳይደርስ ፣ እድሜ ይደርስ ።

የልብህን ቢያናግሩህ ፣ አለ እዳ ቢለቁህ ።

የልብስ ቀላል ፣ ባለቤቱን ያቀላል ።

የልጅ ልጅ እህል ፈጅ ፣ ሁዋላም ጅብ ያስፈጅ ።

የልጅ ልጅ ፣ ጅብ አስፈጅ ።

የልጅ ሞት ፣ የእግር እሳት ።

የልጅ ቀላቢ ፣ የአህያ ጋላቢ ።

የልጅ ብልጥ ፣ እየቀደመ ይውጥ ።

የልጅ ተሚጋች ፣ በፊት ሰማይ ያያል ፣ ሁዋላ መሬት ።

የልጅ ተሚጋች ጪት ሰማይ ሰማይ ፣ ማታ ምድር ምድር ያይ ።

የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ ፣ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ ፣ ።

የልጅ ነገር ፣ ጥሬ በገል ።

የልጅ ክፉ ዲቃላ ፣ የቤት ክፉ ሰቃላ ፣ የልብስ ክፉ ነጠላ ።

የልጅ ክፋቱ ፣ አለመከማቸቱ ።

የልጅ ጥፉ ፣ በስም ይደግፉ ።

የልጅ ፍቅር ፣ የቤት ከንፈር ፣ እናትን ኦያስቀብር ።

የልጅቷን ስጋ በእናቷ ቅቤ ።

የሎሌ አልቃሽ ፣ የቤት ቀዳሽ ።

የመልኳን ሲኋት የጠባይዋን ።

የመሬት ሴሰኛ ፣ ከመንገድ ዳር ይተኛ ።

የመሬት እርጥብ እሸቱን ፣ ደረቅ ምርቱን ።

የመስከረም ውስጡ በጋ ፣ ያረመኔ ልቡ ቀጋ ።

የመቀናጆ በሬ ሲመሽ ወደ ቤቱ ይስባል ።

የመበደሪያ አፍ መክፈያ አይሆንም ።

የመታሰር ምልክቱ መያዝ ፣ የመሻር ምልክቱ መጋዝ ።

የመታሰር ምልክቱ መጋዝ ፣ የመዳኘት ምልክቱ መያዝ ።

የመነነ ከዱር ፣ የሞተ ከመቃብር አይወጣም ።

የመነኩሴ ሎሌ ፣ የክረምት አሞሌ ።

የመነኩሴ ፈራጅ ።

የመንማና ፣ የለው ገናና ።

የመንታ እናት ፣ ተንጋላ ትሞት ።

የመንገድ ዳር እሸት ፣ ባል የሌላት ሴት ለማንም ናት ።

የመከሩበት ሞተ ፣ የወረወሩበት ተሳተ ።

የመከራ ልጅ ሁል ጊዜ መከራ መስሎ ይታያል ።

የመከራ ሎሌ መከራ መስሎ ይታያል ።

የመከራ ውዝፍ ያለበት ነጋዴ ከሚወረር አገር ይደርሳል ።

የመከራን ጉድጓድ ፣ ሚዳቋ አትዘለውም ።

የመኮንን ልጅ በከተማ ፣ የድሃ ልጅ በውድማ ።

የመኮንን ልጅ አዘን ቢነግሩት አደን ።

የመዝሙር መጀመሪያ ሃሌታ ፣ የዘፈን መጀመሪያ እስከስታ ።

የመጠጡት ቅልጥም ፣ ከብርንዶ ይጥም ።

የመጣ ቢመጣ ፣ ከቤቴም አልወጣ ።

የመጥረቢያ ልጅ መዘለፊያ ።

የሙሽራ እድሜ ቢያጥር ፣ የሰርጉ ድግስ ሆነ ለተዝካር ።

የሙት ቀናተኛ ፣ ሚስቴን አደራ ይላል ።

የሙት አልቃሹ ፣ የቂም ወራሹ ።

የሙት ፣ የለውም መብት ።

የሚሆን ቢሆን ፣ ዝሆን ይበላ ቢሆን ።

የሚሉሽን በሰማሽ ፣ ገበያም ባልወጣሽ ።

የሚመከተው ጋሻ ፣ የሚጠጋበት ዋሻ የለውም ።

የሚመጣውን እንድታውቅ ፣ ያለፈውን እወቅ ።

የሚሮጡበት ሜዳ ፣ የሚወጡበት ቀዳዳ ።

የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ፣ ሰላማዊ መስሎ ይገባል ።

የሚሰርቅ ሰው አደራ ቢያስቀምጡት እጅ ይነሳል ።

የሚስት መናኝ ፣ የእናት አገር ለማኝ ።

የሚስት አምባሻ ፣ የጎረቤት ውሻ ፣ የደጅ እርሻ ።

የሚስት ወይዘሮ ፣ እርሻው ጋራ ዞሮ ።

የሚሸሹበት አምባ ፣ ሲሸሽ ተገኘ ።

የሚበላው ካጣ ፣ ይበላበት ያጣ ፤

የሚበጀውን ባለቤት ያውቃል ።

የሚከርምም የማይከርምም አንድነት ዝናም ይለምናል ።

የሚካኤል ስለት ለገብርኤል ምኑ ነው ።

የሚወዱትን አቅፎ ፣ የሚጠሉትን ነቅፎ ።

የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል ።

የሚዛንን አባይ ለእሳት ፣ የዳኛን አባይ ለሰንሰለት ።

የሚያልቅ እህል ከማያልቅ ዘመድ ያጣላል ።

የሚያልፍ ቀን ፣ የማያልፈውን ስም ያወርሳል ።

የሚያልፍ ነገር ፣ የማያልፍ ስም ይሰጣል ።

የሚያልፍ ውሃ ፣ አይረገኝ ድሃ አለች ልጅዋን ጎርፍ የወሰደባት ።

የሚያልፍ ዝናም አይምታህ ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ ።

የሚያልፍ ዝናም አይምታህ ፣ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ ።

የሚያማ ጠበኛ ፣ ዘወር ይበል ከኛ ።

የሚያስፈራውን ለሚነግርህ ፣ የሚያስ ቀዝነውን ንገረው ።

የሚያድግ ልጅ ፣ በእናቱ እጅ ።

የሚያድግ ልጅ አትበድል ፣ የሚሞት ሽማግሌን አታቃልል ።

የሚያድግ ልጅ አይጥላህ ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ

የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል ።

የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ ፣ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ ።

የሚያፈስ ቤት ፣ ጨቅጫቃ ሚስት ።

የሚዳቋ ብዛት ፣ ለውሻ ሰርግ ነው ።

የሚጸድቅ ግርግርታ ፡ ለውሻ ሰርግ ነው ።

የሚጣፍጥ ምግብ ምንድ ነው ? ቢሉት ሲርብ የበሉት ።

የሚፈልግ ያገኛል ፡ የሚተኛ ያልማል ።

የሚፈርስ ከተማ ፡ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ ።

የሚፈታ ከተማ ፡ አዋጅ ቢነግሩበት አይሰማ ።

የማህበር አሽከር በልቶም አይጠገን ፡ ታሞም አይድን ።

የማሽላ ዘር ፡ ከነአገዳው ቸር ።

የማታ ማታ ፡ እውነት ይረታ ።

የማታ ማታ ፡ ጭምት ይረታ ።

የማታ ምግብ ለእንግዳ ፡ የጧት ምግብ ለአገዳ ፡ የጧት መጠጥ ለእዳ ።

የማታ ሩጫ እንቅፋት ትርፉ ።

የማታድግ ውርንጫ እናትዋን ትመራለች ።

የማታድግ ጥጃ እናቷን ትመራለች ።

የማትሄድ መበለት ፡ ዞራ ዞራ ትሰናበት ።

የማትረባ ፍየል አምስት ትወልዳለች ፡ ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች ፡

የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል ።

የማነው እህል ? ያሰኘሃል ክምር ፡ የማነው ቤት ? ያሰኘሃል አጥር ።

የማን እርሻ ብለህ እረስ ፡ የማን ሚስት ብለህ ውረስ ።

የማን ገበሬ ሹርባ ይሰራል ።

የማያመሽ ባል ፡ ቅንድብ ይስማል ።

የማያምኑበት ተዘግቶ ፡ ይተውታል ተከፍቶ ።

የማያስተኛ ነግረውህ ፡ ተኝተው ያድራሉ ።

የማያበላ ቢገላምጥ ፣ አያስደነግጥ ።

የማያበድር ደመኛ ፣ የማይመልስ ቀማኛ ።

የማያበድር ገዳይ ፣ የማይመልስ አባይ ።

የማያዋጣ ባል ፣ ቅንድብ ይስማል ።

የማያውቁት አገር አይናፍቅም ።

የማያውቅ ፣ ምን ያውቅ ።

የማያድግ ልጅ ባራስ ቤቱ ዳንኪራ ይመታል ።

የማይገዙ በከፊር ፣ ያግዛሉ በከንፈር ።

የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል ።

የማያፍር እንግዳ ባለቤቱን ይጋብዛል ።

የማይሆን ነገር የተገላቢጦሽ ፣ ያችን ላንቺ ማናለሽ ።

የማይመለስ ማር ፣ ሹመኛ ይበደረዋል ።

የማይመስል ነገር ፣ ለሚስትህ አትንገር ።

የማይመቱት ልጅ ፣ ቢቆጡት ያለቅሳል ።

የማይሰማ ሰው ፣ ልቤን አፈረሰው ።

የማይሰራ አይብላ ፣ የማይረዳ አይጥላ ።

የማይስማሙ ዝንቦች ጥምብ ይልሳሉ ፣ የሚስማሙ ንቦች ማር ይጎርሳሉ ።

የማይቀና ባይወልድ ፣ የማያስብ ባይነግድ ይሻላል ።

የማይበሉት እህል ፣ ከአፈር እኩል ነው ።

የማይበላ የለም ፣ የማይጠግብ ባሰ ።

የማይተማመኑ ባልንጀሮች ፣ በየወንዙ ይማማላሉ ።

የማይተች አይፍረድ ፣ የማያተርፍ አይነግድ ።

የማይቻል ጠላት ፣ ከወዳጅ ይቆጠራል ።

የማይችሉት ድንጋይ ሲያወጡት ደረት ፣ ሲያወርዱት ጉልበት ይመታል ።

የማይከፍል ባለ እዳ ፣ የሰጡትን ይቀበላል ።

የማይዘልቅ ማህበር ፣ በጠጅ ይጀመራል ።

የማያዘልቅ ፀሎት ለቅስፈት ።

የማይደርሱበትን አያኩም ።

የማይድን በሽተኛ በጥር እሸት አምጡ ይላል ።

የማይድን በሽተኛ የበጋ እሸት አምጡልኝ ይላል ።

የማይድን በሽተኛ ፣ የማይመለስ ሃጢአተኛ ።

የማይድን ባህታዊ ወተት አምጡ ፣ የማይድን ቆቅራ ጠላ ስጡ ።

የማይገባ ሱሪ ፣ የማይበቅል ዘሪ ።

የማይጠረጥር ፣ ቤቱን አያጥር ።

የማይጣሉ መላእክት ፣ የማይታረቁ አጋንንት ።

የማይፅፍ ደብተራ ፣ ክንፍ የሌለው አሞራ ።

የማይፈወስ ደዌ ይ ፣ የማይመለስ ጊጉይ ።

የሜዳ ንስንሱን ፣ የቤት ጉስጉሱን ።

የምመክተው ጋሻ ፣ የምጠጋበት ዋሻ ።

የምሮጥበት ሜዳ ፣ የምወጣበት ቀዳዳ የለም ።

የምስራች በቃሏ መላች ።

የምታሸንፈውን ምታ ቢሉት ፣ ወደ ሚስቱ ሮጠ ።

የምትመክተው ጋሻ ፣ የምትሰወርበት ዋሻ ።

የምትሮጥበት ሜዳ ፣ የምትገባበት ቀዳዳ ።

የምትበላው እህል ፥ ከማታየው መሬት ይበቅላል ።

የምትታጠቀው የሌላት ፥ የምትከናነበው አማራት ።

የምትነቃነቅ ግንድና የምትስቅ ሴት ልብ ሩቅ ነው ።

የምትኩነን ነፍስ ጎረቤት ያውቃታል ።

የምትጠላው ሰው ፊቱ እሆዱ ውስጥ ሳለ ይሸታል ።

የምትጠላውን የምትወደውን ስጥተህ ሸኘው ።

የምትጠባ ጥጃ አትጮህም ።

የምድሩን በአፍ ፥ የሰማዩን በመጣፍ ።

የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ ።

የምጥ መድሀኒቱ አንድ እግር ማስቀደም ነው ።

የሞተ ልጅ አንገቱ ረጅም ነው ።

የሞተ ቢሞት ፥ ያለን እንጫወት ።

የሞተ አይከሰስ ፥ የፈሰሰ አይታፈስ ።

የሞተ ያልነበረ ይመስላል ፤ ያለ የማይሞት ይመስላል ።

የሞተን አትርሳ ፥ የወደቀን አንሳ ።

የሞተው ወንድምሽ ፥ የገደለው ባልሽ ፤ አዘንሽ ቅጥ አጣ ፥ ከቤትሽም አልወጣ ።

የሞተውን አያ ይለዋል ።

የሞት በደለኛ ፥ አይያዘ በዳኛ ።

የሞኝ ልቅሶ ፥ መልሶ መልሶ ።

የሞኝ ሚስት ፥ በምልክት ።

የሞኝ ምስጋና ፥ የማንበት ደመና ።

የሞኝ በትር ፥ ሆድ ይቀትር ።

የሞኝ እጁን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው ፤ አንድ ጊዜ ሳያይ ፣ ሁለተኛው ሲያሳይ ።

የሞኝ ዘመድ ያፍራል ።

የሞኝ ጠላ ፣ በለው ባንከላ ።

የሞኝን ጥርስ ብርድ ፈጀው ።

የረዘመን በጠፍር ፣ ያጠረውን በድግር ።

የረዘመውን በጦር ፣ ያጠረውን በድግር ።

የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ፤ የረጋ ሰው ማለፊያ ይሆናል ።

የሩቁን የሚመለከት ፣ የፊቱን ያፈሳል ።

የራሱን እንዳይበላ ገንዘብ የለው ፣ የሰው እንዳይበላ አመል የለው ።

የራሱን ጥሎ ፣ የሰው አንጠልጥሎ ።

የራስ ጌጥ ስለጨርቅ ፣ የሌላው ያስጨንቅ ።

የራስዋ ቢያርባት ፣ የሰው ታማስላለች ።

የራስዋ ጊዜ አለቀሰች ፤ የሰው ጊዜ ሳቀች ።

የራበው ፣ ይጠግብ አይመስለው ።

የራበውን ገበያ አታውጣው ።

የሬሳ ጎረቤት እሳት አያጫጭር ፣ ቢሞቱ አይቀብር ።

የሮጠ አመለጠኝ ፣ የበላ በለጠኝ ።

የሰለጠነ ፣ ሰየጠነ ።

የሰማ ይስማ ፣ ያልሰማ ይግማማ ።

ሰማዩ ንጉስ እስኪረዳ ፣ የመሬቱ ንጉስ ይጎዳ ።

የሰማዩን ያህል እንጀራ ይስጥህ ቢለው ፣ የኮከቡን ያህል በላተኛ አለበት አለ ።

የሰራው ቢረሳ ፣ የተሰራው አይረሳ ።

የሰባን አርዶ ፣ የጠራን አውርዶ ።

የሰነፍ መላሰኛ ፣ የበሽተኛ በላተኛ ።

የሰነፍ አበላል ይብረድልኝ ፣ የሰነፍ ምስክር ይማልልኝ ።

የሰከረ ሲተፋ ፣ የገደለ ሲደነፋ ።

የሰከረ አወዳደቁ አያምር ።

የሰከረ ይተፋል ፣ የገደለ ይደነፋል ።

የሰው ሆዱን ፣ የወፍ ወንዱን የሚያውቅ የለም ።

የሰው ልጅ መከራው እንጀራው ያልቅና ፣ ወጡ ይተርፍና ።

የሰው ልጅ በምን ይታፈራል? በወንበር ፤ አይደለም በወንበር ፣ በከንፈር ።

የሰው ልጅ ቢወልድ ሎሌውን ፣ ባለጌ ቢወልድ ጌታውን ።

የሰው ልጅ ከማሳደግ ፣ የውሻ ልጅ ማሳደግ ።

የሰው ልጅ ካለ አገሩ ፣ ጎራዴ ካለ ሰፈሩ ።

የሰው መሰረቱ ፣ አባትና እናቱ ።

የሰው መዋደዱ ፣ መዋለዱ ።

የሰው መዋደጃው ፣ በየምድጃው ።

የሰው ሞኝ ፣ አንድ እንጨት ያስራል ።

የሰው ስጋ ቢጠብሱት ያራል ፣ ቢበሉት ይመራል ።

የሰው ቀላል ለራሱ ይቀላል ፤ የልብስ ቀላል ባለቤቱን ያቀላል ።

የሰው ቀላል ራሱ ይቀላል ፤ የልብስ ቀላል ለባሹን ያቀላል ።

የሰው ቃሪያ እስቲሞት ድረስ አይበስልም ።

የሰው በልቶ ፣ አያድሩም ተኝቶ ።

የሰው ባህርይ ሳይደርሱ ፣ የድንጋይ ስር ሳይምሱ ።

የሰው ቤት ሲቃጠል ቋያ ይመስላል ።

የሰው ብልሃቱ ፤ ለፈጣሪ መንገር ነው መድሃኒቱ ።

የሰው ብድር ፤ አይቀር በምድር ።

የሰው ታናሽ ፤ ይገዛል በማማሽ ።

የሰው ታናሽ ፤ ይጥላል ጭራሽ ።

የሰው ነገር ፤ አለመናገር ።

የሰው አመሉ ዳውላ ሙሉ ፤ መች ያስታውቃል አብረው ታልኖሩ ።

የሰው አባቱ ሽማ ፤ የሽማ አባቱ ጥለቱ ።

የሰው አባት የሚሰድብ አባቱን የጠላ ነው ።

የሰው አባት የሚሰድብ ፤ አባቱን ያሰድብ ።

የሰው አትበይ ምግባር የለሽ ፤ የራስሽን አትበይ ገንዘብ የለሽ ።

የሰው አገሩ ፤ ምግባሩ ።

የሰው አገር ዝናምና የእንጀራ አባት አይምታህ ።

የሰው እንግዳ ፤ ያገር ባዳ ።

የሰው እጅ ፤ የእግዜር ደጅ ።

የሰው ከማየት ፤ የራስን መብላት ።

የሰው ከርፋፋ ሲሰድቡት አይከፋው ።

የሰው ኩራቱ ፤ በናትና ባባቱ ።

የሰው ክብረቱ ፤ ያሰኘዋል አንቱ ።

የሰው ክፉ ዋሾ ፤ የእፅ ክፉ አብሾ ።

የሰው ክፉ ፤ ጠማማ ነው አፉ ።

የሰው ወርቅ ፤ አያደምቅ ።

የሰው ግብሩ ፡ አይለየው እስከ መቃብሩ ።

የሰው ግብር ቢመለከቱ ፡ ድሃ ይሆኗል ባመቱ ።

የሰው ግብር ፡ እስከ መቃብር ።

የሰው ጠላቱ ፡ ይወጣል ከቤቱ ።

የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል ፤ አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል ።

የሰው ፊት አይቆረስ ፡ የሰው ገንዘብ አይወረስ ።

የሰው ፊት የማያፍር በቅሎ አይቀመጥ ።

የሰው ፊት ደግነቱ ፡ አለመፋጀቱ ።

የሰውን ባህያ ፡ የራስን በጉያ ።

የሰውን ነገር ፡ ስንቱን ልናገር ።

የሰይጣን ክፋቱ ፡ ያለ መታየቱ ።

የሰይጣን ገንዘብ የተበደረ ፡ ሳይበላው ተቀበረ ።

የሰይጣንን አመጣጥ የማያወቅ አይጡንኩስ ።

የሰዳጅ ፡ ለወዳጅ ።

የሰጋ ቤቱን ዘጋ ፡ የዘነጋ ተወጋ ።

የሰጠ ቢነሳ ፡ የለበት ወቀሳ ።

የሰጠኸኝ ሸማ ፡ ከደጅህ ተቀማ ።

የሰጠውን አላህ ማን አልችል ይላል ።

የሰጡህን ተቀበል ፡ ያደረጉልህን ቸል አትበል ።

የሰጡህን አትንሳ ፡ ያደረጉልህን አትርሳ ።

የሰጡን ይሰጧል ፡ የገዙን ይነዷል ።

የሰጡን ይሰጧል ፡ ያጠቡን ያስጧል ።

የሳር ክምር ፣ የጭሰኛ ክብር ።

የሳተ ይምከርህ ፣ የዋለ ይንገርህ ።

የሴት ልቧ እንጂ ፣ ሆዷ አይመርጥም ።

የሴት መልኳ ምንድር ነው ? እጅዋን ታጥባ እንኩ ስትል ነው ።

የሴት መጠጥ ደፋር ፣ የወንድ አይን አፋር ።

የሴት ምክር ፣ የሾህ አጥር ።

የሴት ሞቷ ፣ በማጀቷ ።

የሴት ረኸም ፣ የማቅ ውኸምኸም ፣ እምብዛም አያስጎመጂም ።

የሴት ረኸም ፣ የማቅ ውኸምኸም አያስጎመጂም ።

የሴት ስካር ፣ ያጭር ሰው ኩራት አይታይም ።

የሴት ቀበጥ የበቅሎ መድን ለመሆን ገበያ ትወጣለች ።

የሴት በሬ ፣ የበቅሎ ቦሬ ።

የሴት በሬ ፣ የበቅሎ ደንባሬ ።

የሴት ብቻዋን ሂያጅ ፣ የቄስ አርፋጅ ፣ ሁለቱም ነገር ወዳጅ ።

የሴት አመዳም ፣ የአሮጌ ሆዳም ።

የሴት አመዳም ፣ ያህያ ሆዳም ።

የሴት አገሯ ፣ ባሏ ።

የሴት አገሯ ባሏ ፣ ማደሪያዋ አመሏ ።

የሴት አጭር ወይዘሮ ፣ የወንድ አጭር አውራ ዶሮ ።

የሴት እንግዳ ፣ የመርፌ ጎዳ ።

የሴት ከርፋፋ ዕቃውን በእቃ ደጋግፋ ፣ አንዱን ስታነሳ ሁሉም ይደፋ ።

የሴት ክፉ ምላሰኛ ፣ የበሽታ ክፉ መጋኛ ።

የሴት ክፉ አፈኛ ፣ የጎረቤት ክፉ ምቀኛ ።

የሴት ዘበናይ ፣ የፊቷን እንጂ የሁዋላዋን አታይ ።

የሴት ዘንገኛ ፣ የናት ምቀኛ ።

የሴት ዶሮ ኩኩሉ ፣ ለባለጌ ኩሩ ።

የሴት ጉልበቷ ፣ ምላስዋ ።

የሴት ጠጪ ፣ የግመል ፈንጪ ።

የስራት መቋሚያው ፈጠም ፣ የስጋ መቋሚያው ቅልጥም ።

የሰሱ ልጅ ስሱ ፣ መደቆሻ ሲልስ ተሰበረ ጥርሱ ።

የስንዴ ንፍሮ ያተር ድብልቅ ፣ ከዚያችው ወጥተው እዚያችው ጥልቅ ።

የስንዴ አራራ ፣ የሴት መራራ ።

የስንዴ አራራ ፣ የቆንጆ መራራ ።

የስድብ አበጥ የለው ።

የስድብ ክፉ አባት ፣ የብትር ክፉ እናት ።

የስጋ ልል ጭቅና ፣ ያመትባል ትልቅ ገና ።

የስጋ መድሃኒት ላም ፣ የነፍስ መድሃኒት ማርያም ።

የስጋ መጨረሻ አጥንት ፣ የነፍስ መጨረሻ ግዝት ።

የስጋ ቁራጭ ፣ የብርሌ ጭላጭ ።

የስጋ ትል ፣ የዘመድ ጥል ።

የስጋዬ ቁራጭ ፣ የአጥንቴ ፍላጭ ።

የሸማ ጥቅል ፣ የወርቅ እንክብል ።

የሸንጎ አይን ጉልበትን ይሰብራል ።

የሹም ሰነፍ ፣ አንዱን ሳይጨርስ አንዱን ይወዝፍ ።

የሹም ሰነፍ ፣ ይለፈልፍ ።

የሹም ከርፋፋ ፣ አገር ያጠፋል ፣ ያሀያ ጅላፋ መስከ ያጠፋል ።

የሹም ጠሩ ፣ እቅፍ ሙሉ ።

የሹክሹክታ ግቢ ለፍች ያስቸግራል ፣ ገርጋሪ በቅሎ ይደነብራል ።

የሺ ሞት ሰርግ ነው ፣ ያንድ ሞት ጉዳት ነው ።

የሺ ቃል ንቁፍ ፣ የዋና ቃል ፅሁፍ ።

የሺ አካላት መሰብሰቢያው አናት ።

የሺ ገንዘብ ብላ ፣ ከሺ ወንድም አትጣላ ።

የሺ ገንዘብ ተቀበል ፣ የሺ ወንድም አትግደል ።

የሺ ፍልጥ ፣ ማሰሪያው ልጥ ።

የሺን ገንዘቡን ብላ ፣ ወንድሙን አትንካ ።

የሽሮ ፋከራ ፣ ከምጣዱ እስኪወጣ እንጀራ ።

የሸንኩርት ሴባ አታላይነቱ ፣ ልሽተት ማለቱ ።

የሽኮኮ ዳቦ ለመስበኪያ ፣ ቀጭን ሽማ ለማረግረጊያ ።

የሽኮኮ ፀሎት ።

የቀማኛ የለው እጅ ፣ የበቅሎ የለው ልጅ ።

የቀበሮ ባህታዊ ከበግ መሃል ይፀልያል ።

የቀበጡ ለት አይገኝም ሞት ።

የቀበጡ ለት ሞት አይገኝም ።

የቀባጣሪ አፉ ጠማማ ነው ።

የቀና ሲታጣ ፣ ይመለመላል ጎባጣ ።

የቀን ጨዋታ ፣ አይገኝም ማታ ።

የቀደመው ያገሳታል ፣ ደግሞ ደግሞ ያጎርሳታል ።

የቀድሞ አርበኛ ፣ የቅምጥ ይዋጋል ።

የቀጇ ልጅ ጠጪ ።

የቂል ብትር ፣ ሆድ ይቀትር ።

የቂል ፣ ጓደኛው ቂል ።

የቂጣ እንደሁ ይጠፋል ፣ የማርገዝ እንደሁ ይገፋል ።

የቄስ ልጅ ባገባ ፣ በሜሮን ፈትፍቼ እበላ ነበር አለ ።

የቄስ ምንደኛ ፣ የቤት በትረኛ ።

የቄስ ሞገደኛ ፣ የቤት በትረኛ ፣ አያድርስ ከኛ ።

የቄስ ቀማኛ ፣ የጻኛ ምቀኛ ።

የቄስ ቃል ፣ አንድ ይበቃል ።

የቄስ ነጋዴ ፣ ይሆናል ወንበዴ ።

የቄስ ነጋዴ ፣ ይመስላል ወንበዴ ።

የቄስ አባይ ፣ የደበሎ ተባይ ።

የቅማል ስደት ፣ ከራስ ወርዶ አንገት ።

የቅርቡን በደጅ ፣ የሩቁን ባዋጅ ።

የቅርብ አራሽ ፣ በእንቅብ አፋሽ ።

የቅርብ አዝመራ ፣ ለጤና ።

የቅርብ ጠበል ፣ የልጥ መንከሪያ ይሆናል ።

የቆለኛ ምስክር ከጥይት ይፈጥናል ።

የቆመ ሌባ ፣ የተቀመጠውን ይቀማ ።

የቆመው እግር ቢሆን አሳቢው ራስ ነው ።

የቆረጠ ፡ አመለጠ ።

የቆቅ ለማዳ ፡ የካይላ እንግዳ ፡ ከቤት ሲሉት ወደ ሜዳ ።

የቆቅ አውራ ፡ ይወ ላል ተራራ ።

የቆዳ ጓንታ ለወ ሻ ሰርጉ ነው ።

የቆጡን ስታይ የብብቷን ጣለች ።

የቆጡን አወርድ ብላ ፡ የብብቷን ጣለች ።

የበላ በለጠኝ ፡ የሮጠ አመለጠኝ ።

የበላ ቢሮጥ ፡ አያመልጥ ።

የበላ ቢያብል ፡ ገላው ይናገር ።

የበላ ዳኛ ፡ የወጋ መጋኛ ።

የበላች ብትዘፍን ፡ ያልበላች ታዝን ።

የበላን ሆድ ፡ የወጋን ክንድ ያውቃል ።

የበላው ፡ አብላላው ።

የበላውን ያብላላዋል ፡ የለበሰውን ይበርደዋል ።

የበላይ ፡ አዳባይ ።

የበረታ ከራሱ ፡ የሰነፈ ከዋሱ ።

የበረደውን አሙቆ ፡ የረጠበውን አድርቆ ።

የበሬ ሆዳም ፡ ቢሞት አይጎዳም ።

የበሬ ሻኛማ ፡ የላም ግታማ ።

የበሬ ቀንዱን ፡ የወይራ ግንዱን ።

የበሬ እቃ ፡ እየራሱ አለቃ ።

የበሬ ዳተኛ ፡ በ ሣል ይተኛ ።

የበሬ ዳተኛ ፣ የሴት ምላሰኛ ፣ አታምጣ ወደኛ ።

የበሬ ዶሰኛ ፣ የሴት ምላሰኛ ፣ አያድርስ ወደኛ ።

የበሬም ዋይ ይውላል ገበያ ፣ ስጋው ለመብል ቆዳው ለጠፍር ።

የበሬን ምስጋና አህያ ወሰደችው ።

የበሰለ ይበላል ፣ ጥሬ በምጣድ ይቆላል ።

የበሶ አቅማዳ ተፈቶ ፣ የሌባ አፍ ነጥቶ ።

የበሶ አቅማዳ ተፈቶ ፣ የተሸካሚው አፍ ነጥቶ ፣ ይመስላል ?

የበሽታ ክፉ ቁርጥማት ፣ የሃጢአት ክፉ ቅናት ።

የበሽታ ክፉ እህል ያስወድዳል ።

የበቅሎ እቃ ፣ እየራሱ አለቃ ።

የበደለ ይከሳል ፣ የቀማ ይመልሳል ።

የቡና ስባቱ ፣ መፋጀቱ ።

የቡና ቀዝቃዛ ፣ የሹም ፈዛዛ ።

የባህር ዳር ሲታረስ ፣ ጓጉንቸር ሆድ ይብሳታል ።

የባለስር ፣ ምላሱ አስር ።

የባለቤት ሰነፍ ቤቱን ያዋርዳል ።

የባለቤት አዳይ ጦም ያሳድራል ።

የባለቤት እውር እቃውን ያነሳል ።

የባለጌ ሀይለ ቃል ፣ እንደ ሽመል ይወቃል ።

የባለጌ ሃይማኖት ከጅማት ይከራል ።

የባለጌ ልጅ መብል ያፍር ፣ ነገር ይደፍር ።

የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጅ ፣ ነገር አይፈጅ ።

የባለጌ ልጅ እያደር ይጋሻል ፤ የጨዋ ልጅ እያደር ይበጃል ።

የባለጌ ባለሟል ፣ ቂጥ ገልቦ ያያል ።

የባለጌ ባለሟል ካፍ አታውጡኝ ይላል ።

ባለጌ ተለጣጭ ፣ ከድንጋይ ላይ ተቀማጭ ።

የባለጌ ኩራቱ ፣ እንዲያው በከንቱ ።

የባላባት ልጅ ቤት ሊሰራልህ ነው ያሉት እንደሆን ከስቶ ያድራል ።

የባላገር ስልጡን እሰው ፊት ይቆርሳል ።

የባላገር ስልጡን እጅ ይዞ ያጫውታል ።

የባላገር እንግዳ ሞት ፣ የባልቴት ሳዱላ መሬት ።

የባላገር ዱለት ፣ ይፈታል በኩበት ።

የባል ዘመድ ፣ ባይኑ አመድ ።

የባል ደግነቱ ፣ ባትናገር ሚስቱ ።

የባልቴት ወበራ ፣ የክረምት ብራ ።

የባሰ አለ ሚስትህን አትፍታ ።

የባብ ለማዳ ፣ ያህያ ፍሪዳ የለውም ።

የባብ ልጅ በቅንብቻ ።

የባብ ልጅ በቅንብቻ ፣ ስንቅ በስልቻ ።

የባብና የቤት ፍለጋ ፣ ማነው የሚያወጋ ።

የባእድ ሞኝ ከዘመድህ እኩል አርገኝ ፣ የዘመድ ሞኝ ከልጅህ እኩል አርገኝ ።

የባእድ ፍቅር ፣ የውሃ ጌጥ አንድ ነው ።

የባዳ ሞኝ ፣ ከልጅህ እኩል አድርገኝ ይላል ።

የቤቴ መቃጠል ለትሁዋኑ በጀኝ ።

የቤት ቀጋ ፣ የሚዳ አልጋ ።

የቤት ቀጋ ፣ የውጭ አልጋ ።

የቤት ቀጋ ፣ የዱር አልጋ ።

የቤት ቤት አለው ማጀት ፣ የሆድ ሆድ አለው አንጀት ።

የቤት አመል ገበያ ይወጣል ።

የቤት ጥጋብ አለስንቅ ያዘምታል ።

የብልጥ አይን ፣ ቶሎ ያለቅሳል ።

የብረት ቆሎ ፣ የደንጋይ ንፍሮ ።

የብትር ትህትና ያስመታል ፤ የነገር ትህትና ያስረታል ።

የብዙ ህዋሳት ፣ መሰብሰቢያው እናት ።

የብድር ሽሮ ፣ ምን ሲል ተጀምሮ ።

የቧልተኛ ሎሌ ሳይሰለፍ ያረጃል ።

የተለፋን ቆዳ ላልተለፋ ፣ መለወጥ ለዘጥ ዘጥ ።

የተላከ ፣ አፉን ለከከ ።

የተላጠ እንጨት ዳግም አይላጥም ፣ ሰው አለ አንድ ጊዜ አይበለጥም ።

የተልባ ስፍር የሀልም እንጀራ ።

የተመረረ ድሃ ፣ ይገባል ከውሃ ።

የተመረጠ እንጨት ለታቦት ፣ የተመረጠ ሰው ለሹመት ።

የተመሰከረ ይፈረዳል ፣ የሰባ ይታረዳል ።

የተመታ ዳኝ ፤ ደም የተፈናጠቀበት ሞት ።

የተመቸው ገንፎ ያላምጣል ።

የተመኘነውን አገኘነው ።

የተማማሉት ማለኛ ፣ የተጋደሉት ጠበኛ ።

የተማረ መልካም ፣ ጥቃት አያስነካም ።

የተማረ ፣ ነፍሱን የመረመረ ።

የተማረ ፣ ክብሩን መረመረ ።

የተማረ ፣ የተሟረ ።

የተማሪ ጋፍ ፣ መልክ ያጋፍፍ ።

የተማከሩት ዳኛ ያግዛል ፣ የመተሩበት እጅ ይወዛል ።

የተሚጋች ፣ ሚስቱ ቧጋች ።

የተረገዘ በሆድ ፣ የታዘለ በለምድ ።

የተራበ አይዘፍንም ፣ የጠገበ አያርፍም ።

የተራበ ከባቄላ ፣ የተበደለ ከሰቀላ ።

የተሳለ ብረት ፣ አንገትን ከደረት ፣ ስጋን ከጅማት ይለያያል ።

የተሸሸገ ምግብ ሆድ አይጠፋለትም ።

የተሸሸገ ምግብ ፣ የተሸሸገ ሆድ አያጣም ።

የተሸከመው ክብዶታል ፣ እንደገና ይጨምርበታል ።

የተሾመ ወደ ግምጃ ፣ የተሻረ ወደ ሙጃ ።

የተሾመን ይሟገቱበታል ፤ የተሻረን ይመሳከሩበታል ።

የተቀመጠ ማርና ልጃገረድ የሚሆኑት አያጡም ።

የተቀማጭ ፣ ምላሱ ምላጭ ።

የተቀማጭ ፣ አፉ ምላጭ ።

የተቆለፈ ወርቅ ፣ ያልተቆለፈ ጨርቅ ።

የተበደለ ከነጋሽ ፣ የተጠማ ከፈሳሽ ።

የተታታ ገመዱ ፣ የተቆፈረ ጉድጓዱ ።

የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አያርፍም ።

የተናቀ መንደር ባህያ ይወረራል ።

የተናገሩት ከሚጠፋ ፣ የወለዱት ይጥፋ ።

የተኛን አንበሳ ፣ አስነሳችው ላም ልሳ ።

የተኛቸው ሳለች ፣ ያዳመጠችው አረገዘች ።

የተከፋ ፣ ተደፋ ።

የተከፋ ፣ ጨርሶ ተደፋ ።

የተወለዱት ይራባሉ ፣ እንደገና ይወልዳሉ ።

የተዘጋ ተጠበቀ ፣ ያልተዘጋ ተሰረቀ ።

የተደረገ ተደርጎ ፣ እንዳለ መስማት በጎ የለም ።

የተደፋ ሬሳ ፣ የተጠበሰ አሳ ።

የተገኘ ጥበብ ፣ ከዶሮና ከንብ ።

የተገዘተች ነፍስ ፣ የተለጎመች ፈረስ ።

የተጠማ ከፈሳሽ ፣ የተጠቃ ከነጋሽ ።

የተጠረጠሩበት ፣ ድንጋይ ይጥሉበት ።

የተጠገነ እጅ እንደቀድሞው አይሆንም ።

የተጣደፈን ቅቤ ይንቀዋል ።

የተፃፈ ይወረሳል ፣ በቃል ያለ ይረሳል ።

የተፈተለ ይለበሳል ፣ የተጀመረ ይጨረሳል ።

የተፈጠመ አይናገር ፣ እንካሳ አይሻገር ።

የተፈጠመ ያርፋል ፣ የተኛ ያኮርፋል ።

የተፋትን ነገር መልሰው ቢውጡት ፣ ተራራ ያህላል ።

የታለህ ያላሉት ፣ እዚህ አለሁ ይላል ።

የታመመውን ሙት ጠየቀው ።

የታመነ ሎሌ ፣ ጠጅ የመላበት ብርሌ ።

የታቀፈችው እናቷቱ ፣ የሚላጨው አባቱ ።

የታነቀ የልቡን ይናገራል ፣ ግን የሚያምነው የለም ።

የታናሽ ልጅ አሳናሽ ፣ የዘንጋዳ ወጥ እህል አበላሽ ።

የታደለ ፣ ተደላደለ ።

የታደለች ሴት ፣ በፊት ትወልዳለች ሴት ።

የታደለች ቤት አሮጊ ታያለች ።

የት ላይ ተቀምጠሽ ፣ እግዜርን ታሚያለሽ ።

የት ትሄዳለህ? እሁዳዳቸው ፤ ምን ያሮጥሃል? ውቃቢያቸው ።

የት አውቅሽ ብሎ ፣ አጥብቆ ሳመኝ ።

የትም ተከሰስ ፣ አለቃህ ድረስ ።

የትም ተወለድ ፣ አንኮበር እደግ ።

የትም ፍጪው ፣ዱቄቱን አምጪው ።

የትምህርት ሙግት ፣ አንድ ተናግሮ ጉልት ።

የትንሽ ሰው ፍቅር ፣ በመቀምቀሚያው ጥቁር ።

የትእቢት ፣ መድሃኒቱ ጭንቀት ።

የትውልድ ጉልበቱ ፣ ህብረቱ ፤ የህዝብ ሀብቱ ፣ አንድነቱ ።

የቸኮለ አፍሶ ለቀመ ።

የቸገረው እርጉዝ ያገባል ።

የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል ።

የችግር ከፉ እህል ማጣት ፣ የሃጢአት ከፉ ነፍስ ማጥፋት ።

የነሃሴ ውሃ ጥሩ ነው፣የሚጠጣው የለም ፤ የድሀ ነገር ፍሬ ነው፣የሚሰማው የለም ።

የነ ቂሉ ቤት ፣ ግድግዳው ሰንበሌጥ ።

የነበረ ይናገር ፣ ያየ ይመስክር ።

የነበረ ፣ ገብርኤል ተወገረ ።

የነብር ልጅ አይታቀፍ ፣ የጨዋ ልጅ አይነቀፍ ።

የነብር አይን ከፍየል ፣ የፍየል አይን ከቅጠል ።

የነብርን ጅራት አይዙም ፣ ከያዙም አይለቁም ።

የነብርን ጅራት አይጨብጡም ፣ ከጨበጡም አይለቁም ።

የነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ ።

የነገሩ ሁነኛ ፣ የጠሩ አርበኛ ።

የነገሩትን የማይረሳ ፣ የለመኑትን የማይነሳ ፣ እግዜርን አትርሳ ።

የነገር ትህትና ያስረታል ፣ የብትር ትህትና ያስመታል ።

የነገር ወጡ ፣ ማዳመጡ ።

የነገር ጠማማ በሽማግሌ ይታረቃል ።

የነገር ጣእሙ ዝግታ ፣ ያዋቂ ጣእሙ ዝምታ ።

የነገደ አተረፈ ፣ ያለፈ ተራገፈ ።

የነጋሪት በቅሎ ፣ ከላይሽ ማን ወርዶ ።

የነፍስ ገዳይ ምልክቱ ፣ ደም በጣቱ ።

የነፍስ ትቶ የገባስ ።

የኑሮ ከፉ ደባል ፣ የመንገድ ከፉ ገደል ።

የኑግ ገለባ ፥ እያገርሀ ግባ ።

የናት ሆድ ዝንጉርጉር ነው ።

የናት ሆድ ዝንጉርጉር ፥ ወላጅ ቀይና ጥቁር ።

የናት ልመና ፊት አያስመልስ ፥ አንገት አያስቀልስ ፤ ሲሆን በውድ ፥ አለዚያ በግድ ።

የናት ልጅ ቢጣላ እውነት ይመስላል ።

የናት ልጅ የሌለው አይበላ ፥ ጀርባ የሌለው ምንቸት አይፈላ ።

የናት ልጅ ፥ የጎን እጅ ።

የናት ሞትና የእግር እሳት እያደር ያንገበግባል ።

የናት ሞትና የደንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል ።

የናትን ክፋት ፥ የደመናን ውሃ ጥማት ፥ ባለቤት ያውቃል ።

የኔ ነህ በለኝ ፥ ደስ እንዲለኝ ።

የኔን ችግር ፥ ለማን ልንገር ።

የኔን ወጥ በቀመስሽው ፥ ያንቺን በደፋሽው ።

የንጉሥ ምንቸት ራሱ አይድን ፥ ሰው አያድን ።

የንጉሥ ወልጋዳ ፥ የመንገድ አንጋዳ ።

የንጉሥ ክፉ አባሎ ፥ የዳኛ ክፉ መድሎ ።

የንፉግ ለጋስ ፥ የሰጠውን ይወርስ ።

የንፉግ ገንዘብ በለጋስ እጅ ይገኛል ፤ የጠላት ገንዘብ በወዳጅ እጅ ይገኛል ።

የንፍጣም ነገሩ አይጥም ።

የአህያ ባል ፥ ከጅብ አያስጥል ።

የአህያ ፍሪዳ ፥ የእባብ ለማዳ የለውም ።

የአልኮል ፍቅር ፥ እስከመቃብር ።

የአመል ታናሽ ፣ ይጥላል ጭራሽ ።

የአምላክ ነገር ፣ አይመረመር ።

የአረፋውን ሲሏት የጀጀባውን ።

የአርበኛ ልጅ ይዋጋል ፣ የአርጌ ልጅ ያወጋል ።

የአስር እናት ፣ ጅብ በላት ።

የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ፣ ሲወጋ እንጂ አይታይም ሲወረወር ።

የአተር ክምር ፣ የጢሰኛ ክብር ።

የአንበሳ ልጅ ሲሞት ቅበር ፣ አንበሳ ሲሞት እቤትህ ዋል ።

የአንበሳ ገራም ፣ ይውላል ከላም ።

የአዋጁን በጆሮ ።

የአይን ህመም ከሱት ነው ፤ የሆድ ህመም ልማም ነው ።

የአይን ጨንቋራ ሰው ያየዋል ፣ የልብን ጨንቋራ እግዜር ያየዋል ።

የአይጥ እርጉዟ ፣ የድመት ወዟ ።

የአይጥ ሞትዋ ፣ የድመት ጨዋታዋ ።

የአዳኝ ውሻ መነፅሩ ከአፍንጫው ነው ።

የአገር ጠላት ሽፍታ ፣ የገንዘብ ጠላት መሸታ ።

የአፍ ብልሀት ጌትነት ፣ የእጅ ብልሃት ባርነት ።

የአፍ ዘመድ ፣ ከገበያም አይገድ ።

የእህል ጌታ ፈርዛዛ ፣ የወርቅ ጌታ ቀበዝባዛ ።

የእህል ጣእም በጉሮሮ ፣ የነገር ጣእም በጆሮ ።

የእህት ልጅ ፣ ባይወልዱትም ልጅ ።

የእረኛ ፣ ፈሱ መርዘኛ ።

የእሬትን ምሬት ያልቀመሰ ፣ የማርን ጣእም አያውቅም ።

የእሳት ልጅ አመድ ።

የእቡይ ልጅ ወዳቂ ፣ የዘማ ልጅ ሳቂ ።

የእብድ ቅል ፣ ማንጠልጠያው ክር ።

የእብድ አሞራ ፣ ሲላ ደንገጡሯ ።

የእብድ አጫዋች ሙር ነው ።

የእብድ ዘመድ ሳያማስን አይሰድ ።

የእብድ ገላጋይ ፣ ሾተል አቀባይ ።

የእናት ልጅ ፣ የጎን አሳጅ ።

የእንቢተኛ መድሀኒቱ ዳኛ ።

የእንቧይ ካብ ።

የእንጀራ ቀንጣቢ ፣ የድመት አላቢ ።

የእንጀራ እናት ፣ ምን አጠናሽ እንደ ጅማት ።

የእንግዳ ቅብጠ ፤ ባለቤት ያጎርሳል ።

የእንግዳ ችኩል ፣ ባለቤቱን ያጎርሳል ።

የእንጦጦ መምር ቢናገር ባመት ፣ ያውም ሬት ።

የእከክ መድሀኒቱ ፣ አለመቅረብ አለመቀራረብ ነው ።

የእውር ልቡ ፣ ኢየሩሳሌም ነው አሳቡ ።

የእውር ሞቱ ፣ የጨረቃ ንጋቱ ።

የእውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል ።

የእውር ነፍጠኛ ፣ የወንበር ፈረሰኛ ።

የእውር አስተናባሪ ፣ የድውይ አጋፋሪ ።

የእውር አዝማሪ ፣ የደንቆር ተጣሪ ።

የእውር አፍጣጭ ፣ የንጉስ ቀላዋጭ ።

የእውር ግልምጫ ፣ ያንካሳ ሩጫ ።

የእውነት በትር ትቀጥናለች እንጂ አትሰበርም ።

የእውነት ዘንግ ትመነምናለች እንጂ አትሰበርም ።

የእጅ ብልሃቱ ባርነቱ ፣ የአፍ ብልሃቱ ጌትነቱ ።

የከረረ ይበጠሳል ፣ የበደለ ይወቀሳል ።

የከረረ ይበጠሳል ፣ የተበደለ ይካሳል ።

የከሳ እሪያ ይገራል ።

የከብት አገሩ ባለቤቱ ፣ የሰው አገሩ ምግባሩ ።

የከተማ ዳንዴ ፣ የበረሃ ወንበዴ ።

የከተማን ወሬ መስማት ፣ ትልቅ አዳራሽ መስራት ።

የከፋ እውነት ፣ የተፈጠረ ነው ከውሸት ።

የካህን አፉሩ ፣ ያህያ እውሩ ።

የካህን አፉር ፣ ያህያ እውር ፣ የሴት ደፋር አይረባም ።

የክረምት ጥማትና የመከር ጊዜ ራብ ፣ አለባለቤቱ የሚያውቀው የለም ።

የክፉ ልጅ እናት ሁል ጊዜ ታለቅስ ።

የክፉ ልጅ እናት ሁለት ጊዜ ታዝናለች ።

የክፉ ሰው ተዝካሩ ያቅራል ።

የክፉ ሰው ተዝካር ፣ ውሃ ያስወስዳል በሀዳር ።

የኮራ ተጎዳ ፣ አይዋጋም የበሬ ቆዳ ።

የኮሶ ማግስት ፣ እናት በሆነች አራት አምስት ።

የወለደ ይልሳል ፣ የበደለ ይከሳል ።

የወለደውን ሲስሙለት ፣ የደገሰውን ሲበሉለት ደስ ይለዋል ።

የወለደውን ቢስሙለት ፣ ያቀረበውን ቢበሉለት ።

የወለዱት ሁሉ ካደገ ፣ የዘሩት ሁሉ ከፀደቀ ።

የወለፈንድ ስልቻ ፣ ጤፍ ይቋጥራል ፣ ባቄላ ያፈሳል ።

የወለፈንድ ኑሮ ፣ በሁዳዴ ቋንጣ በፋሲካ ሽሮ ።

የወላጅ ሆድ ቀጥቀጥ ፣ የልጅ ሆድ ቀጥ ።

የወረት ኮሶ ይጣፍጣል ።

የወረት ውሻ ፣ ስሟ ወለተ ጴጥሮስ ።

የወረወርኩት አንካሴ ፣ ተመልሶ ለራሴ ።

የወረደ መአቱን ፣ የመጣ ምጣቱን ።

የወሬ ቆርፋዳ ፣ ዋንጫ ቅቤ አያርሰውም ።

የወርካ ልጅ ሳንቃ ፣ ያለቃ ልጅ አለቃ ።

የወሰን ላይ ሰዎች ፣ ሌቦች ወይም ሽፍቶች ።

የወታደር ፈዛዛ ፣ የናት ነዝናዛ የለውም ።

የወንድ ልጅ ሞት ፣ ያደረገውን የዘነጋ ለት ።

የወንድ አልጫ ፣ የእንዶድ ሙቀጫ ።

የወንድ አጭር ዝንጀሮ ፣ የሴት አጭር ወይዘሮ ።

የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ ።

የወንድምህ ጢም ሲላጭ ፣ ጢምህን ውሃ አርስ ።

የወንዶች ባል ፣ አይተህ ማር ።

የወንጭፍ ድንጋይ ባልነበር ፣ የማሽላ እሸት መልካም ነበር አለች ወፍ ።

የወይን ዘለላ ፣ ጋን ይሞላ ፤ የስንዴ ዛላ ፣ እፍኝ ይሞላ ።

የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል ።

የወደቀን አንሳ ፣ የሞተን አትርሳ ።

የወደደ ሰው አይንም የለው ።

የወደደውን አቅፎ ፣ የጠላውን ነቅፎ ።

የወደዱትን ቢያጡ ፣ የጠሉትን ይቀላውጡ ።

የወደድሽው ቂጣ ፣ ሰተት ብሎ ወጣ ።

የወዳጅ ስልቻው ፣ እየብቻው ።

የወዳጅ ተጋፊ ፣ የጠላት ደጋፊ ።

የወዳጅ ከዳተኛ ፣ አዱኛ ።

የወዳጅና የኮርቻ ፣ አለመንካቱ ብቻ ።

የወጋ መጋኛ ፣ መቅቡጥ የለመደ ዳኛ ።

የወጋ ቢረሳ ፣ የተወጋ አይረሳ ።

የወጣ ሰው አንዱን ጥሎ ፣ አንዱን አንጠልጥሎ ።

የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል ።

የወፍ ወንዱን ፣ የሰው ሆዱን ፣ የሚያውቅ የለም ።

የወፍ ዘላ ፣ ከቤት ይውላል አሽን ሲፈላ ።

የወፍጮ እንጉርጉሮ አይሆንም ለሰርግ ።

የዋህ ፊቱን ቢመልስ ፣ ማጅራቱ ጋራ ይመስለዋል ።

የዋለች ውላ ፣ ባልዋ ሲመጣ ትበላ ።

የዋልንበትን አረም በላው ።

የዋስ ተሚጋች ፣ የቆማጣ ፈትፋች ።

የዋስ ተሟጋች ፤ የድውይ ፈትፋች ።

የዋስ ወንድም አይታገት ፤ የአበያ ወንድም አይነተት ።

የዋኘ ይሻገራል ፤ የሰራ ይከብራል ።

የዋጋ ብልጥ ፤ ልብ ይግጥ ።

የዋጋ ብልጥ ልብ ይግጥ ፤ የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ ።

የወሃ ሽታ ፤ የባብ ፍለጋ የለውም ።

የወሃ ወሃ ፤ ምን አለኝ ቅሃ ።

የወሃ ጡር በድፍ ያስታጥባል ።

የውስጥ አንጀቴን ፤ የላይ ቁርበቴን ።

የውሻ ትህትና ፤ የካህን እብድና ፤ መቼ ይጋጠምና ።

የውሻን ጥርስ ባጥንት ይፈሯል ።

የውሽማ ሞት ፤ ፊት አይነጭለት ።

የውድማ ዘንዶ ፤ ይቀጠቀጣል እንደ በረዶ ።

የዘላን ቤት ሁልጊዜ ስደት ።

የዘላን ጠመኛ ፤ ከጥጃ ጓዳ አታስገቡኝ ይላል ።

የዘመተ ይመለስ ፤ የገደለ ይንገስ ።

የዘመኑ ሰው ምላሱ መንታ ፤ አንዱ ለፍቅር አንዱ ላሜታ ።

የዘመኑ ሰው ሲያቀርቡት ይርቃል ፤ ሲወዱት ይጠላል ።

የዘመኑ ወሬ ፤ ይቀዳል ባቦሬ ።

የዘመኑ ጫጩት ፤ ከአውራ እኩል ልዋጥ ይላል ።

የዘመድ ለማኝ ፤ ከዝምድናው ወጥቶ ፤ የለመነውንም አጥቶ ።

የዘመድ ሎሌ ፤ የፈረስ ሙሌ ፤ ሲወጣ ወጥቶ ነው ።

የዘመድ ቂስ ፣ እየፈታ ያለቅስ ።

የዘመድ አዳይ ጦም ያሳድራል ።

የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል ።

የዘመድ ጥል ፣ የስጋ ትል ።

የዘማ ልጅ ሳቂ ፣ ያባያ ልጅ ወዳቂ ።

የዘሬን ብትው ያንዘርዝረኝ ።

የዘነጋ በሩን ዘጋ ።

የዘነጋ ቤቱን ዘጋ ።

የዘነጋ ፣ ተወጋ ።

የዘነገነ አዘነ ፣ ያልዘገነም አዘነ ።

የዘገዩ ፣ ተለዩ ።

የዘፈን መጀመሪያው እስክስታ ነው ።

የዚህ አለም ፍቅር ሰኞ አዲስ ፣ ማክሰኞ ልብስ ፣ ረቡእ ብጥስጥስ ።

የዝሆን ክሳት ፣ የባለፀጋ ድህነት አይታወቅም ።

የዝንብ ሽውታ ፣ የነገር ስልት ይበጥሳል ።

የዝንብ ተላላ ካንድ በሬ ደም ይቀርባታል ።

የዝንብ ተባቱ ፣ የ—ጭምቱ ፣ ሳይታወቁ ሞቱ ።

የዝንጀሪትዮ ዝንጀሪት ፣ ባሌ ገደለ በነጋሪት ።

የዝንጀሮ ልጅ ከዛፍ ፣ የመምህር ልጅ ከመፅሃፍ ።

የዝንጀሮ መነኩሴ ፣ የስንበሌጥ አንካሴ ።

የዝንጀሮ መንገድ ፣ ከገደል ያደርሳል ።

የዝንጀሮ ንጉስ ፣ እሱው ይከምር እሱው ያፈርስ ።

የዝንጀሮ ጎልማሳ የውሻ ራት ይሆናል ።

የዞረ ምን ያመጣ? ፌራና ፈንጣጣ ።

የዞረ ምን ያመጣል? ፈንጣጣ ።

የየጁ ቄስ ቅኔው ቢጎድልበት ፡ ቀረርቶ ሞላበት ።

የያዘውን ከወረወረ ፡ ፈሪ አይባልም ።

የደላው ሙቅ ያኘካል ።

የደላው ውሻ ማር ይቀላውጣል ።

የደመና ውሃ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም ።

የደበሎ ተባይ ፡ የዳኛ አባይ ፡ ቢገልጡት አይታይም ።

የደባ ገበያ ፡ በሬው ባስር ፡ ቆዳው በሃያ ።

የደንቆሮ ለቅሶ ፡ መልሶ መልሶ ።

የደንቆሮ ተጣሪ ፡ የእውር አዝማሪ ፡ ዙዋሪ ።

የደንቆሮ ዘፈኑ ፡ ያው አንድ ብቻ ነው ።

የደገመ ፡ ተረገመ ።

የደፋት ሬሳ ፡ የጠበሱት አሳ ።

የዱሮ አርበኛ የቅምጥ ይዋጋል ።

የዳቦ ልብ ልቡ ፡ የዳገት ጥግ ጥጉ ።

የዳኛ ልል ያማታል ፡ የአባል ልል ያፋታል ።

የዳኛ ጅሉ ያማታል ፡ ያመል ክፉ ያፋታል ።

የዳኛ ጅል ፡ ያማታል አባይ ምስክር ያስረታል ።

የዳገት ሩጫ ፡ የባለጌ ጡጫ ።

የዳገት በረዶ ፡ የቆላ ዘንዶ ።

የዳጉሳ እንጀራ በትኩሱ ፥ የባእድ ፍቅር በአዲሱ ።

የድሃ ማጀት ቃጢ ማር ለማስቀመጥ አይችልም ።

የድሃ ቁምነገሩ ፥ ገብስ ከናሰሩ ።

የድሃ ብድር ፥ አይውል አያድር ።

የድሃ ተዝካር ፥ የጎባጣ ስካር ።

የድሃ ነገር ማንገቻ የለውም ።

የድሃ ጉልበት በገለባ ያልቃል ።

የድሃ ጉልበት ፥ በገበያ ያልቃል ።

የድሃ ጠላ ፥ ጢት አልፈላ ፥ ማታ አትላ ።

የድመት ማንቀላፋት ፥ አይጦችን ለማጥፋት ።

የድንጋይ ልብ ፥ የኩበት ማምብ ።

የድንጋይ መቀመጥና የባእድ ፍቅር ፥ እያደር ይቀረቀር ።

የድንጋይ ንፍሮ ፥ የብረት ቆሎ ።

የድንጋይን ጠርነት ፥ የሸሮን ቀለብነት ፥ የሚስትን ባርነት ።

የድፍድፍ ኩራት ፥ ውሃ እስኪገባበት ።

የዶሮ አንገት ፥ ከምንቸት ።

የጀመሩትን መጨረስ ፥ የቀረሱትን መጉረስ ።

የጅብ ሁለት ስብሩ ፥ የባለጌ ወታደሩ አስቸጋሪ ነው ።

የጅብ ለማዳ ፥ ያህያ ፍሪዳ የለውም

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ።

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ፤ ያይጥ ችኩል የድመትን አፍንጫ ይልሳል ።

የጅብ እንግዳ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ።

የጅብ ገበሬ ፣ የአህያ በሬ ፣ የጠጣ ዘር አቀባይ ፣ የዝንጀሮ ጎልጓይ ፣ ሁሉም እበላ ባይ ።

የጅብ ጓደኛ ከጥንብ ያደርሳል ።

የጅብ ፈሪ ፣ የሞት ቀሪ ።

የገማ ሰው ሰውን አይሸሽም ፣ ሰው እርሱን ይሸሻል እንጂ ።

የገበያ ሽብር ፣ ለሌባ ሰርጉ ነው ።

የገበያ ሽብር ፣ ለቀጣፊ በጀው ።

የገበያ ወንድና የታሰረ አንበሳ ፣ በብላሽ ያገሳ ።

የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል ።

የገብስ ብዙ ነዶ ፣ የጤፍ ስሱ ነዶ ።

የገንዘብ እርጊ ፣ ያባት ባለጌ የለውም ።

የገዛ ጌታ ፣ እግር ይዞ ይመታል ።

የገደለ ባልሽ ፣ የሞተ ወንድምሽ ፤ አዘንሽ ቅጥአጣ ፣ ተቤትሽ አልወጣ ።

የገደል ማሚቶ ፣ ዳቢ ልስጥሽ ድፎ ።

የጉልበት ገሚሱ ምላስ ነው ።

የጉልበት ግማሽ አፍ ነው ።

የጉም ሌባ ፣ ጉሙ ሲጠፋ ወዴት ትገባ ።

የጉሮሮን መታነቅ ፣ ያይን መደንቆል ያስጥለዋል ።

የጋራ ፣ ወንጋራ ።

የጌታ ሆድ ፣ ጥዋት ከባድ ማታ ወላድ ።

የጌታውን አመካከት ፣ ሎሌው ይመልከት ።

የግመል መጫኛ ፣ ቢበጠስ ላህያ ይበቃል ።

የግፍ ግፍ ፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ።

የጎረቤት ሌባ ቢያውቁት ይስቃል ፣ ባያውቁት ያሰጋል ።

የጎረቤት ሌባ ቢያዩት ይስቃል ፣ ባያዩት ይሰርቃል ።

የጎረቤት አሳብ ከገበያ አይወጣም ።

የጎበዝ ልቡ ከደረቱ ፣ የፈሪ ልቡ ከፊቱ ።

የጎበዝ ሹም ፣ የሀዳር ጉም ፣ አገር ይደረግም ።

የጎበዝ ሹም ፣ የጎንደር ጉም ፣ አገር ይደረግም ።

የጎበዝ አሰሳ ፣ የወሬ አፈሳ ፣ ይደርሳል እግር ሳይነሳ ።

የጎበዝ ክምር ፣ እያደር ይጨምር ።

የጎበዝ ዱዳ ፣ ባመቱ ምድረ በዳ ።

የጎበዝ ጉልበቱ ፣ ከደረቱ ።

የጎደለው ሊሞላ ፣ የተረፈው ሊከላ ።

የጎጃም አዝመራ ሽምብራ ነው አሉ ፣ እኛም እንዳንበላ ተነቀለ አሉ ።

የጓጉንቸር ልጅ መሄድ ሳትማር መዝለል ተማረች ።

የጠላ ክፋቱ ፣ አለመገኘቱ ።

የጠላ ክፋቱ አለመገኘቱ ፣ የልጅ ክፋቱ አለመስማቱ ።

የጠመመውን አቅንቶ ፣ የጎደለውን ሞልቶ ።

የጠረጠረ ስንቁን ቋጠረ ።

የጠረጠረ ፣ ቤቱን አጠረ ።

የጠሩት እንግዳ ፣ እራቱ ፍሪዳ ።

የጠበቀ ከራራ ፣ ባጥና ጣራ ።

የጠብ መነሻ ፣ የስብስቱ እርሻ ።

የጠብ መነሾ ፣ አበድሪኝ እርሾ ።

የጠንቀኛ ፌስ ፣ አይን ያፌስ ።

የጠይብ ጂል ፣ ትበላለች በገል ።

የጠጅ ቤት አዛዥ ፣ አተላ አጋዥ ።

የጠጅ ቤት አዛዥ ፣ አተላ አፋሽ ።

የጠገበ ሰው ራሱን አያስብም ።

የጠገበ ሰው ራብን አያስብም ።

የጠገበ ሰው የተራበ ያለ አይመስለውም ።

የጠገበ አበደ ።

የጠገበ እንግዳ ፣ ሳይተኛ አይወጣም ።

የጠገበ እውር ዘንጉን ይወረውራል ።

የጠገበች ዶሮ ከነጭልፊት ማህበር ትገባ ።

የጠጉር ጥቁሩ ፣ የነገር አጭሩ ።

የጢስና የልጅ መውጫው አይታወቅም ።

የጣመው ፣ ቀለጠመው ።

የጣታ በሬ ፣ ለነገ ብሎ ይጠጣል ዛሬ ።

የጣውንት ደግ ፣ የእንቧጮ ዘንግ የለውም ።

የጥር በልግ ፣ የብር ዘንግ ።

የጥርስን እድፍ ፣ የራስን ጉድፍ

የጥቁር ሴት ንቅሳት የምንድነው ገ ቢለው ፣ የእግዜር ቁጣ ነው አለው ።

የጥቅምት በረዶ ፣ የጫካ ላይ ዘንዶ ።

የጥቅምት እርሻ ፣ የናት ጉርሻ ።

የጥቅምት እርሻ ፣ ያባት ውርሻ ።

የጥጋብ ለት ሁሉ አንበሳ ፣ የራብ ለት ሁሉ ሬሳ ።

የጠመኛ ፣ ምቀኛ ።

የጠም ቆሎ ፣ የቁልቁለት በቅሎ ።

የጠም ቆሎ ፣ የበአል ዶሮ ።

የጦር ስለቱ ፣ መዋጋቱ ።

የጦርነትን ነገር ፣ ከፈሪ ጋራ አትምከር ።

የጠጣ ልጅ በዛፍ ፣ የመናፍቅ ልጅ በመፃፍ አይቻሉም ።

የጠጣ ብልጣ ብልጥ ፣ የዝንጀር ቅልጣ ቅልጥ ።

የጠጣ ዘር አቀባይ ፣ የዝንጀሮ ጎልጓይ ።

የጠጣን ልጅ በዛፍ ፣ የፀጋን ልጅ በመፅሀፍ ማን ይችላል ።

የጢት ለማኝ ለማታ ።

የጢት መጠጥ ለእዳ ፣ የጢት ምግብ ለአገዳ ፣ የማታ ምግብ ለእንግዳ ።

የጨለማ አፍጣጭ ፣ የእውር ገልማጭ ።

የጨለማ ገልማጭ ፣ የእውር አፍጣጭ አይረባም ።

የጨረቃ ሂያጅ ፣ የምስከር ፈራጅ ።

የጨረቃ ንጋትና የእውር ሞት አይታወቅም ።

የጨርቅ ነጩ ፣ የበሬ ልጩ ።

የጨነቀው ይዋጋል ፣ ያልደረሰበት ያወጋል ።

የጨዋ ልጅ ሁሉ ፣ አርግዟል በሆዱ ።

የጨዋ ልጅ ሲያዝን ፣ እሳ በወንዝ ይመክን ።

የጨዋ ልጅ ሲፋታ ፣ ይጋባ ይመስላል ።

የጨዋ ልጅ ከከተማ ፣ የድሀ ልጅ ከውድማ ።

የጨዋ ልጅና ቅል ተሰባሪ ነው ።

የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል ፣ ብልህ ያለቅሳል ።

የጨው ገደል ሲናድ ብልህ ያለቅሳል ፣ ሞኝ ይልሳል ።

የጨውን ባለዳ በጨው ቢያባብሉት ጨዌን ማለቱ አይቀርም ።

የጨጌ ከብት ፣ በየወገኑ ይከተት ።

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ ፣ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም ።

የጫማ ጠጠርና የእንጀራ እናት ፣ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም ።

የፈላ ጠጅ ፣ የደረሰ ልጅ ።

የፈረሰኛ ማቅ ለባሽ ፣ የቤት ትንባሆ ጎራሽ ።

የፈረሰኛ ጥለት ለባሽ ፣ የቤት ትምባሆ ጎራሽ ።

የፈረሰ አልጋ ፣ የተሸበረ ዜጋ ።

የፈረንጅ አሽከር ፣ ነጭ ለባሽ ፣ ሳህን አመላላሽ ።

የፈሩት ይደርሳል ፣ የጠሉት ይወርሳል ።

የፈሰሰ ፣ አልታፈሰ ።

የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ ።

የፈሲታ ፣ ተቆጢታ ።

የፈስ ማደናገሪያው ዳባ ።

የፈቷት ሚስት ፣ ያጠቡት ወጥት ፣ የወጡበት ቤት አንድ ነው ።

የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል ።

የፊተኛውን አሳረርሽ ቢሏት ፣ የሁዋለኛውን ጥሬ አወጣች ።

የፊት መሪ ፣ የሁዋላ ቀሪ ።

የፊት ምስጋና ፣ ለሁዋላ ሃሜት ያስቸግራል ።

የፊት እድፍ በመስታወት ፣ የሃጢአት እድፍ በካህናት ።

የፊት ክብት ፣ የእጅ ወረት ።

የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ ፤ የሁዋለኛው እንዳይሸሽ ።

የፊት የፊቱን አለ ጓያ ነቃይ ።

የፋቂ ልጅ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ ፣ አንዱን ይዘፍቅ ።

የፋቂ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ ፣ አንዱን ይዘፍቅ ።

የፋቂ ቆንጆ ቡድንነት አይተወውም ።

የፌጦ ብቅል ፣ የብሳና ጌሾ ፣ የትልባ አሻሮ ፣ ይህን ጠምቆ ለማን የሰው ነገር ለማይ
ሰማ ።

የፍቅር ጣእሙ ፣ በመሳለሙ ።

የፍየል ልጇን ፣ የሌባ እጇን ።

የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ፣ ብልት አይከድን ።

የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ፣ እፍረት አይከድን ።

የፍየል ጭራና የሰው ሀሳብ ፣ ሁልጊዜ ወደ ላይ ነው ።

የፍጅት ወራት ፣ እሳት በወንፊት ።

ያ በሬ ባላገደደ ፣ ያ በሬ ገደል ባልገባ ።

ያ በሬ ባገደደ ፣ ያ በሬ ገደል ገባ ።

ያህያ ልጅ ጥሎ ይረግጣል ፣ የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል ።

ያህያ ስጋ ፣ ካልጋ ሲሉት ካመድ ።

ያህያ ስጋ ውርደተኛ ፣ አልጋ ላይ ቢያኖሩት እመሬት ይተኛ ።

ያህያ ቀበጥ ፣ ከጅብ ጡት ይጣባል ።

ያህያ ባል ፥ ከጅብ አያስጥል ።

ያህያ እንግዳ ፥ የጅብ ራት ነው ።

ያህያ ውሀ ጠጭ ፥ ሳይታወቅ መጣጭ ።

ያህያ ፍሊጋና የጥሬ ራት በግዜ ነው ።

ያለ የሚኖር ይመስላል ፥ የሞተ ያልነበረ ይመስላል ።

ያለ ይበዛል (አለወፍሮ)።

ያለህ ምዘዝ ፥ የሌለህ ፍዘዝ ።

ያለመከራ ፥ አይገኝም እንጀራ ።

ያለመከራ ፀጋ ፥ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝም ።

ያለመጥረቢያ እንጨት ሰባሪ ፥ የቆማጣ ዘንግ ወርዋሪ ።

ያለሴት ምን ያደርጋል ቤት ።

ያለሴት ቤት ፥ ያለበሬ መሬት ።

ያለስራ መብል ፥ ያለ ዳኛ ውል ።

ያለስራ አይበላ እንጀራ ።

ያለስፍራው የተሰበረ ፥ ሲጠግኑት ያስቸግራል ።

ያለበሬ ፥ ምን ያደርጋል ገበሬ ።

ያለበት ይብላላበት ።

ያለበት ይጉላላበት ።

ያለባለቤቱ ፥ አይነድም እሳቱ ።

ያለአቻ ጋብቻ ፥ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ ።

ያለእዳው ዘማች ፥ ዋ ብሎ መቅረት ።

ያለክንፍ መብረር ፥ ያለ ስራ መክበር ።

ያለው ይምዘዝ ፥ የሌለው ይፍዘዝ ።

ያለው ይበላል ፥ የሌለው ያፈጣል ።

ያለውን ካልሰጡ ፥ በስም አይበሉ ።

ያለዘዴ ጋሻ ፥ እንቅብ ነው ።

ያለዝናብ ነጎዳ ፥ ያለብድር እዳ ።

ያለጊዜው የተወለደ ልጅ ፥ አባቱን ጥሎ እያቱን ያስረጅ ።

ያለጎረቤት ቡና ፥ ያለ ሙያ ዝና ።

ያለጎታ ደረባ ፥ ያለልብስ ካባ ።

ያለጎታ ደረባ ምንድነው ?

ያለጥርስ ቆሎ ፥ ያለ ጓድ አምባጓሮ ።

ያለጨው በርበሬ ፥ ያለጭፈር በሬ ።

ያለፈቱ አይቆርስ ፥ ያለቤቱ አይወርስ ።

ያለፍርድ ማሰር ፥ በፈጣሪ ማማረር ።

ያለፍቅር ሰላም ፥ ያለ ደመና ዝናብ ።

ያለፍቅር ፀሎት ፥ ያለ እንጨት እሳት ።

ያሉሽን በሰማሽ ፥ ገበያ ባልወጣሽ ።

ያላረፈች ምላስ ፥ ሾማ ትልስ ።

ያላረፈች እግር ፥ ከዘንዶ ጉድጓድ ትገባለች ።

ያላሰብከውን አግኝ ፥ መረገምም ምርቃንም አይደል ።

ያላሳደጉት ውሻ ቤት ዘግተው ቢመቱት ዞሮ ይናከሳል ።

ያላባቱ ቢዛቁን ፥ አባክና ያባክን ።

ያላወቁ ፥ አለቁ ።

ያላዋቂ ቆራሽ ፣ ማእድ አበላሽ ።

ያላየ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው ።

ያላዩት አገር አይናፍቅም ።

ያሌሟል ፣ ይተረጉሟል ።

ያሌሞላ ተርፎ አይፈስም ።

ያሌሞተና ያልተኛ ብዙ ይሰማል ።

ያልሰማ ጆሮ ፣ ከጎረቤት ያጣላል ።

ያልሰማ ጥኑ ነው ፣ ባልሽ ወዳጄ ነው ።

ያልሰጡት ተቀባይ ፣ ያልጠሩት አቤት ባይ ።

ያልሳሉት አይላጭ ፣ ያላዩት አይቆጭ ።

ያልቆረጠ እግብ አይደርስም ።

ያልበሉት እዳ ፣ ያልጠሩት እንግዳ ።

ያልበላ ሬሳ ፣ ያልለበሰ እንሰሳ ።

ያልበላ ዳኛ አያሟግት ፣ ያልጠጣ እንግዳ አያጫውት ።

ያልበላኝን ቢያከኝ ፣ አይገባኝ ።

ያልተማረ አይፀድቅ ፣ ያልተወቀረ አያደቅ ።

ያልተማረ ዋናተኛ ፣ ከዳኛ ፊት እንቢተኛ ።

ያልተረታ አይረታ ፣ ያልጠገበ አይማታ ።

ያልተሾመ አያዝ ፣ ያልቀሰሰ አያናዝዝ ።

ያልተቀጣ ልጅ ቢቆጡት ያለቅሳል ።

ያልተቀጣ ልጅ ፣ ያልታጠበ እጅ ።

ያልተነካ ግልግል ያውቃል ።

ያልተገላበጠ ያራል ።

ያልተገራ ፈረስ ፣ ይጥላል በደንደስ ።

ያልተፈተነ ወዳጅ ያልተተኮሰ ሽከላ ።

ያልታየ እንጂ ያልተሰማ ፣ ያልተደረገ እንጂ ያልተባለ ነገር የለም ።

ያልታደለ በሪዶ ከድንጋይ ላይ ያርፋል ።

ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል ።

ያልታደለች ወፍ አይንዋ በጥቅምት ይጠፋል ።

ያልነበረ ያፈርሳል ፣ ቀዳዳ ያፈሳል ።

ያልወለደ አንጀት ጨካኝ ነው ።

ያልወለደ አይነሳ ፣ የሽምብራ ማሳ ።

ያልወለደ ፣ አጋድሞ አረደ ።

ያልወለዱ ሁሉ ፣ ጊደሮች ይባላሉ ።

ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ ፣ አፈን ዳባ ዳባ አለኝ ።

ያልዘሩት አይበቅልም ።

ያልዘራሁት በቀለብኝ ፣ ዱባ ያልኩት ቅል ሆነብኝ ።

ያልዘራውን የሚበላ ዝንጀሮ ነው ።

ያልገደለ ዘማች ፣ ያልወለደ አማች ።

ያልጋ ሴሰኛ ፣ ሶስት ያስተኛ ።

ያልጠረጠረ ፣ ተመነጠረ ።

ያልጠሩት መካሪ ፣ ያልሾሙት ፈታውራሪ ።

ያልጠሩት ሰርገኛ ፣ በትረኛ ።

ያልጫ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ።

ያልፋል ፣ እስኪያልፍ ያለፋል ።

ያመል ትንሽ ፣ ይጥላል በጭራሽ ።

ያመነታ ፣ ተመታ ።

ያመኑት ሲከዳ ፣ ይቀላል እዳ ።

ያመኑት ፈረስ ፣ ጣለ በደንደስ ።

ያመጣሁት ውሻ ነከሰኝ ፣ ያነደደኩት እሳት ጠበሰኝ ።

ያመጣል አንበሴ ፣ ይበላል ኮሳሴ ።

ያማከሩት ዳኛ ያግዛል ፣ የመተሩበት እጅ ይወዛል ።

ያምራል ብለው ሰነብር ልጅ አይድሩም ።

ያምራል ብለው ከተናገሩት ፣ ይከፋል ብለው ያስቀሩት ።

ያምራል ብለው ከመናገር ፣ ይከፋል ብሎ መተው ።

ያምራል ብሎ ይሽልሟል ፣ ያውቃል ብሎ ይሾሟል ።

ያምሯል ፣ ይታደሏል ።

ያምና ጥኝ ፣ ዘንድሮም ድገመኝ ።

ያምናውን ዘንድሮ ፣ የአዋጁን በጆሮ ።

ያሞላቀቁት ልጅ ፣ አይሆንም ወዳጅ ።

ያሞሌ ጥጃ ፣ በወንዟ ትነፋ ።

ያረሮ ልጅ ጠለፋ ።

ያረሰ ፣ እንደልቡ ጎረሰ ።

ያረጀን ሹም ገባር ይከሰዋል ፣ ያረጀን ጅብ አህያ ይልሰዋል ።

ያራስ ከፉ መበለት ፣ ያዶጋ ከፉ እሳት ።

ያራሷን በርጉዟ ።

ያራሷን ገንፎ እርጉዟ ውጣ ሞተች ።

ያርጋጅ ፣ አናጋጅ ።

ያሰረ ይፈታል ፣ የሰጠ ይረታል ።

ያሰቡት አይገድም ፣ ጎኔን ላርገው ጋደም ።

ያሳደግሁዋት ጥጃ ፣ አለችኝ በርግጫ ።

ያስታርቀኛል ሙተራ ፣ እያንዳንዱ እየኮራ ።

ያሽላል ያሉት ፣ ኩል አይን ያጠፋል ።

ያቀረቡልህን ጉረስ ፣ የተረፈህን መልስ ።

ያበደ ለኑሮው ፣ የፈረደ ለጉሮሮው ።

ያበደች ጋለሞታ ፣ እናቷን ትመታ ።

ያበጠው ይፈንዳ ።

ያባሆይ መቋሚያ ፣ ላዩ ባላ ታቹ ዱላ ።

ያባ ጎፍናኔ ቤቱ በሪድ ።

ያባቱን ቢሰጡት ህይወቱ ፣ ያባቱን ቢነሱት ሞቱ ።

ያባት ልጅ የደንደስ ስጋ ።

ያባት ምርቃት ፣ አያስገባም ጥቃት ።

ያባቷ ሞቱን አይወዱ ፣ ረጃቱን አይሰዱ ።

ያባት ሲቀር ፣ ምሰህ ቅበር ።

ያባት አገር ከሞት አያስጥልም ።

ያባት እርግማን ሲዳሩ ማልቀስ ።

ያባት እዳ ለልጅ ፣ ያፍንጫ እድፍ ለጅ ፣ የወፍጮ እዳ ለመጅ ።

ያባት ወርቅ ባለዝና ፣ እህል ለቀጠና ።

ያባት ያምራል ፣ የባእድ ያናግራል ።

ያባት ደግ ይደልላል ፣ ያባት ክፉ ለእንጀራ ልጅ ያደላል ።

ያባትህ ቤት ሲበዘበዝ አብረህ ዝረፍ ።

ያባትህና የናትህ ወገኖች ሲጣሉ ጥግህን ያዝ ።

ያባያ ልጅ ወዳቂ ፣ ያራኝ ልጅ አጥባቂ ።

ያባያ እናት አትታረድም ።

ያባያ ወንድሙ አይታረድም ።

ያባይ ምልክቱ አንደበቱ ፣ የገዳይ ምልክቱ ሽልማቱ ።

ያባይ እንባ አይታገድም ።

ያባይ ውሃ ተለያየ ሲሉት ተገናኘ ።

ያባይን እናት ፣ ውሃ ጠማት ።

ያብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፈራል ።

ያብዬን እከክ ፣ ወደ እምዬ ልከክ ።

ያናጢን ልጅ ጅብ በላው ፣ የላጭን ልጅ ቅማል ፈጀው ።

ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ነው ።

ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ፣ የቄስ ልመና እናዞ ።

ያንበሳ ማላጅ ጋማ ይዞ ፣ ጅብን መውጋት አህያን ተነዝንዞ ።

ያንበሳ ኮርዳዳና የጨዋ ልጅ ሞግዚት ከመሆን ይሰውርህ ።

ያንተን የሚመስል ፣ የኔም አለኝ ቁስል ።

ያንችን አትበይ ገንዘብ የለሽ ፣ የሰው አትበይ ምግባር የለሽ ።

ያንካሳ ልቡ ኢየሩሳሌም ።

ያንዱ በሬ ሲሞት ላንዱ አጋዘኑ ፣ ላንዱ ፍስሃው ላንዱ ሀዘኑ ።

ያንዱ ቤት ሲቃጠል ፣ ላንዱ ቋያው ነው ።

ያንዱ ቤት ሳይጠፋ ፣ ያንዱ ቤት አይለማ ።

ያንዱ ነገር ላንዱ የእንጀራ ልጁ ነው ።

ያንዱ አገር መልከኛ ላንዱ አገር ገባር ነው ።

ያንድ ላም ወተት ፣ ያንድ እርሻ እሸት ።

ያንድ ሚስቱን ፣ የሺ ከብቱን ።

ያንድ ሰው ፍቅር ባንድ እጅ እንደማጨብጨብ ያለ ነው ።

ያንድ በሬ እሸት ፣ ያንድ ላም ወተት ።

ያንድ ቀን ስህተት ፣ የዘላለም ፀፀት ነው ።

ያንድዋ እለት ፣ አንድዋ ባልቴት ።

ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል ።

ያኩራራ ምላ እራት ይሆነዋል ።

ያኮረፈ ፣ ልብሱን አራገፈ ።

ያኮረፈ ምሳው ራቱ ነው ።

ያወረደ መአቱን ፣ ያመጣ ምህረቱን ።

ያወቀ ተጠነቀቀ ፣ የዘነጋ ተነጠቀ ።

ያወቀ ተጠነቀቀ ፣ የዘነጋ ተወጋ ።

ያወቀ ተጠነቀቀ ፣ ያላወቀ ተነጠቀ ።

ያወቀ ፣ ናቀ ።

ያወቀ ዘለቀ ፣ ያላወቀ አለቀ ።

ያዋቂ ሴት ቤት ፣ አለው ውበት ።

ያዋቂ አጥሬ ፣ የእስራኤል ጣሬ ።

የአዋቂ አጥፊ ፣ የያመኛ ገዳፊ ።

ያዋጇን በጆሮ ፣ የእለቱን በቀጠሮ ።

ያውሬ ስጋ ለወሬ ።

ያውቃል ብሎ ይሾሟል ፣ ያምራል ብሎ ይሸልሟል ።

ያዛኸ ቤት ክርስቲያን ሳሚ ፣ ያጋፋሪ ራስጌ ቋሚ ።

ያየ ልናገር ቢል ፣ የሰማ ላውራ አለ ።

ያየ ቢሄድ ፣ የሰማ ይመጣል ።

ያየ ቢሄድ ፣ ያልሰማ ይመጣል ።

ያየ ይናገራል ፣ የተወለደ ይወርሳል ።

ያዩትን ቢያጡ ፣ ያላዩትን ይቀላውጡ ።

ያይን ጨንቋራ ሁሉ ያየዋል ።

ያይጥ ምስክሯ ፣ ድንቢጥ ።

ያይጥ ሞት ፣ የድመት ሰርግ ።

ያይጥ እርዳታ በጭራንፎ ያልቃል ።

ያይጥ ፋከራ ለመከራ ፣ ድመት ምን ሊበላ ።

ያይጦች ዝላይ ፣ ለነአቶ ውሮ ሲሳይ ።

ያደረገችውን ታስታውቅ ፣ ከደረቷ ትታጠቅ ።

ያደፈ በእንዶድ ፣ የጎለደፈ በሞረድ ።

ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም ።

ያዳኘ ውሻ ጠጉር ባፉ ፣ ብትር ትርፉ ።

ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ ።

ያገሩን ሰርዶ ያገሩ በሬ ይወጣዋል ።

ያገር ልማት ፣ የገበሬ ሀብት ።

ያገር ልጅ በምን ይመታል? በኩበት ፤ ያም እንዳይሄድ ፣ ያም እንዳይሞት ።

ያገር ልጅ ፣ የማር እጅ ።

ያገር እድር ፣ ለንጉስ ያስቸግር ።

ያገር እድር ፣ ጠም ያሳድር ።

ያገርህ ልጅ ብታገባት ሚስትህ ፣ ብትፈታት እህትህ ።

ያገርህ ዱር ፍራትን ያስወግድል እንጂ ከሞት አያድንም ።

ያገባሽ ይፈታሻል ፣ ይብላኝ ለወለደሽ ።

ያገኘ ከራሱ ፣ ያጣ ከዋሱ ።

ያጓኑት ድንጋይ ተመልሶ ራስን ።

ያጣ ሰው ያገኘ አይመስለውም ።

ያጥንት ፍላጭ ፣ የስጋ ቁራጭ ።

ያፍ አማኝ አደረገኝ ለማኝ ።

ያፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም ።

ያፍ ዘመድ ፣ በመንገድም አይገድ ።

ያፍላ የለው ቀርፋፋ ።

ይህ ሁሉ ከርከሬሻ ፣ ባንቺ የተነሳ ።

ይህ ሁሉ ጠባሳ ፣ ባንቺ የተነሳ ።

ይህ አንበሳ ፣ ደምደም አገሳ ።

ይህ ከርከሬሻ ፣ ዳቦዬን ለማንሻ ።

ይህን ብሰጥ ፣ ምን እውጥ ።

ይህን ፈርቼ ፣ ደጄን በቀን ዘግቼ ።

ይሆናል ብዬ ጎሽ ጠመድኩ ፣ የማይሆን ቢሆን ፈትቼ ሰደድኩ ።

ይሆን ቢሆን ፣ ዝሆን ይበላ ቢሆን ።

ይሉ አይሉ ፣ የት አለ ቅሉ ።

ይሉኝን ብትሰሚ ፣ ጎንደር ላይ ከረሚ ።

ይሉኝ አይል ውሽማ ፣ ዶሮ ሲጮህ ይማለላል ።

ይሉኝ አይል ፣ የሁዋላውን አያይ ።

ይሉኝ አይል ፀሀፊ ከሙሴ ይገድፋል ።

ይሉኝታ ፣ የራስ አሊን ቤት የፈታ ።

ይሉኝታና መጠቀም ፣ አንድ ላይ አይገኝም ።

ይመሰክረዋል ለነፍሱ ፣ ይፈተፍተዋል ለከርሱ ።

ይመታሉ የሚጠሉ ይመስል ፣ ይስማሉ የሚወዱ ይመስል ።

ይሙት የገደለ ፣ ይካስ የበደለ ።

ይማሩኝ እያልክ ከምትታማበት አትገኝ ።

ይምሰል አይምሰል ፣ የጠይብ እጁ ተከሰል ።

ይስጡኝ ብሎ ከሰጠ ፣ ቆጥቦ የበላ በለጠ ።

ይሰጣል መስሎ ይሸጣል ።

ይሰበረኝ ይሰንጥረኝ የሚሉ ፣ የሰውን ልብ ሊሰብሩ ።

ይቅር ለእግዜር ፣ ወድቆ እማይሰበር ።

ይቅር ለእግዜር ፣ ወድቆ አይሰበር ፣ ሞቶ አይቀር ።

ይቅደም ደግነት ፣ ይከተል ቸርነት ።

ይበላ እንደቤቱ ፣ ይሰራ እንደ ጉልበቱ ።

ይበላ እንደ ቤቱ ፣ ይሰራ እንደ ጎረቤቱ ።

ይበላው ካጣ ፥ ይበላበት ያጣ ።

ይበጃል ያሉት መድሀኒት አይን አጠፋ ።

ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ ።

ይብራና ይብራ ፥ ተጣሉ በሰው ሽንብራ ።

ይታደጿል እንጂ ይታገሷል ?

ይች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም ።

## - ደ -

ደህና ሲታጣ ፥ ይመለመላል ጎባጣ ።

ደህና ወገን ያጣ ፥ ወየው ያለበት ጣጣ ።

ደህና ጦር ያለው ፥ ለግምብ ይሞክረው ።

ደመና ለዝናብ ፥ ድግስ ለሆዳም ።

ደመና በሰማይ ፥ የጨዋ ልጅ በአደባባይ ።

ደመና የጨበጠ ፥ ሰማይ የቧጠጠ የለም ።

ደም ቢያለቅሱ ፥ ድንጋይ ቢነክሱ ።

ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም ።

ደም ተበክለህ ዝንብን አትጥላ ።

ደሞዙ ስንዴ ፥ ስራው የምን ግዴ ።

ደሞዝ ያጣ ሎሌ ፥ ይኮበልላል በሃምሌ ።

ደሞዝተኛ ፥ አርፈህ አትተኛ ።

ደረሰሁ ልጅ ፥ ፈላሁ ጠጅ ።

ደረቅ ይቀመጠላል ፥ እርጥብ ይነብጣል ።

ይበላው ካጣ ፣ ይበላበት ያጣ ።

ይበጃል ያሉት መድሀኒት አይን አጠፋ ።

ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ ።

ይብራና ይብራ ፣ ተጣሉ በሰው ሽንብራ ።

ይታደሷል እንጂ ይታገሷል ?

ይች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም ።

## - ደ -

ደህና ሲታጣ ፣ ይመለመላል ጎባጣ ።

ደህና ወገን ያጣ ፣ ወየው ያለበት ጣጣ ።

ደህና ጦር ያለው ፣ ለግምብ ይሞክረው ።

ደመና ለዝናብ ፣ ድግስ ለሆዳም ።

ደመና በሰማይ ፣ የጨዋ ልጅ በአደባባይ ።

ደመና የጨበጠ ፣ ሰማይ የቧጠጠ የለም ።

ደም ቢያለቅሱ ፣ ድንጋይ ቢነክሱ ።

ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም ።

ደም ተበክለህ ዝንብን አትጥላ ።

ደሞዙ ስንዴ ፣ ስራው የምን ግዴ ።

ደሞዝ ያጣ ሎሌ ፣ ይኮበልላል በሃምሌ ።

ደሞዝተኛ ፣ አርፈህ አትተኛ ።

ደረስሁ ልጅ ፣ ፈላሁ ጠጅ ።

ደረቅ ይቀመጠላል ፣ እርጥብ ይጎብጣል ።

ደረቴን ቢያመኝ ፣ እግሬን አገመኝ ።

ደረጃ ለፍቶ መሄጃ ።

ደስታ ፣ በሽታ ።

ደስታና መከራ ፣ ቀኝና ግራ ።

ደባ ራሱን ፣ ስለት ድጉሱን ።

ደባል ሲሰነብት ፣ ይሆናል ባለቤት ።

ደባልና ሹመት ፣ ያለሰበብ አይሄድ ።

ደብር ለላስታ ፣ ድግድግታ ለጌታ ።

ደብተራ ሲኮራ ፣ እቤተ ክርስቲያን ገብቶ ጭራ ይይዛል ።

ደብተራ ፣ የዘኬ ጎተራ ።

ደብተራ የዘኬ ጎተራ ፣ ዘኬውን ሲቋጥር አነቀው ነብር ።

ደብተራና ተማሪ ፣ ሰናፊልና ሱሪ ።

ደንቆሮ ከሚያጫውተኝ ፣ የሚሰማ ያውጋኝ ።

ደንቆሮ የሰማ ለት ያብዳል ።

ደወል ላንበሳ ባማረለት ፣ ታድያ ማን ይሰርለት ።

ደጃቸውን አይዘጉ ሰውን ሌባ ይላሉ ።

ደጃፉን ጥሎ በጓሮ ይመጣል ።

ደገኛ ሲያርስ ፣ ቆለኛ ያነፍስ ።

ደጉ ነገር ሳያልቅ ፣ ክፉ መናገር ።

ደግ ጌታ ሲለግስ ፣ እንደ ፏፏቴ ያርስ ።

ደግ ጎረቤት ውሻና ድሙት ያሳድጋል ።

ደግና ማለፊያ ፣ ትግልና ልፊያ ።

ደፋር ሴት ጉልቻ ረግጣ ትወጣለች ።

ደፋር ወጥ ያውቃል ።

ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም ።

ዱላ ለባለጌ ፣ ምርኩዝ ለአሮጌ ።

ዱላን ይዞ ሌባን መጠየቅ ።

ዱብ ባገሩ ፣ ጋን ያህላል አሉ ።

ዱባና ቅል ፣ አበቃቀሉ አንድ ይመስላል ፤ አበላሉ ፣ ለየቅሉ ።

ዱባና ቅል አብሮ ይበቅል ፣ አበላሉ ፣ እየቅል ።

ዱባና ቅል ፣ አበቃቀሉ እየቅል ።

ዲያቆን ሲጠግብ በጧፍ ይማታል ፣ ወይፈን ሲቦርቅ ድንበር ያፈርሳል ።

ዲያቆን ከዘፈነ ፣ ፍየል ከቀዘነ ።

ዳር ሲፈታ ፣ መሀል ዳር ይሆናል ።

ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ፣ ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን ።

ዳቦ በገና ፣ ቡና በጀበና ።

ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ፣ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ ።

ዳቦ ያለ ቅርፊት ፣ ጠላ ያለ ምርጊት ።

ዳቦውን ጎርሶ ፣ ደሙን አብሶ ።

ዳተኛ በሬ ሀብታም ነው ።

ዳኛ ለዳኛ ያወርሳል ፣ ጉም ተራራ ያለብሳል ።

ዳኛ ምን ያደላ ፣ ከተረታ ሊበላ ።

ዳኛ ሲመረምር ፣ ከራስ ይዞ እስከ እግር ።

ዳኛ ሲቆጣ ማር ይዞ ከደጃ ።

ዳኛ ሲያዳላ በዳኛ ፤ እሀያ ሲያጋድል በመጫኛ ።

ዳኛ ሲገኝ ተናገር ፤ ውሃ ሲጠራ ተሻገር ።

ዳኛ ስበር ፤ በእጅ ክበር ።

ዳኛ ቢንቁ ፤ የተያዘ እሀልን ይወቁ ።

ዳኛ ቢያዳላ በዳኛ ፤ እሀያ ቢያጋድል በመጨኛ ።

ዳኛ ቢያጋድል በዳኛ ፤ እሀያ ቢያጋድል በመጫኛ ።

ዳኛ አውጥቼ ፤ ዘንግ አቅንቼ ።

ዳኛ አይነቀፍ ፤ እሳት አይታቀፍ ።

ዳኛ ካዳላ ጭነት ቀላል ።

ዳኛ የወል ፤ ምሰሶ የመካከል ።

ዳኛ የፈረደበት ፤ መርከብ የተሰበረበት ።

ዳኛ የፈረደው ፤ ስለት የቀደደው ።

ዳኛ ያዳላበት ፤ እሳት የበላበት ።

ዳኛ ያፈሰሱለት ፤ ፈረስ ያከሰከሱለት ።

ዳኛ ይመረምራል ፤ ጣዝማ ይሰረስራል ።

ዳኛ ፍርድ አይከላ ፤ እሀል ጎታ ይሞላ ።

ዳኞች ከመረመሩ ፤ ይናገራል ምድሩ ፤ ይገኛል ነገሩ ።

ዳኞች ከመረመሩ ፤ ይገኛል ነገሩ ።

ዳዊትን ያሀል መዝሙር ፤ ጨለማን ያሀል ጥቁር የለም ።

ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን ፤ ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ።

ዳገት እርሙ ፤ ሜዳ ወንድሙ ።

ድሃ ለወዳጁ አይሰንፍ ፤ ሀብታም ካለወዳጁ አይተርፍ ።

ድሃ ሲቀልጥ ፣ አመድ አመድ ይሸታል ።

ድሃ ሲቀመጥ እጁን ይዘህ አወዛውዘው ።

ድሀ ሲቀማጠል ፣ ከወገቡ ቀምጠል ።

ድሃ ሲቆጣ እግሩ ይፈናጠራል ።

ድሃ ሲቆጣ ከንፈሩ ያብጣል ፣ መንገዱን ያሰልጣል ።

ድሃ ሲንቀባረር ፣ ያለቀሰ ይመስላል ።

ድሃ ቅቤ ወዶ ፣ ማን ሊሸከም ነዶ ።

ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ፣ እከክ ይጨርሰው ነበር ።

ድሃ በጉልበቱ ፣ ባለፀጋ በሀብቱ ።

ድሃ ባይ አይኔን አመመኝ ።

ድሃ ተበድሎ ፣ ማሩኝ ይላል ቶሎ ።

ድሃ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል ፣ ሀብታም በድሎ ተመልሶ ይስቃል ።

ድሃ ከንቡ ይዳላ ።

ድሃ ካለቀሰ ፣ ቀኑ መች አነሰ ።

ድሃ ካልሰራ ፣ ዶሮ ካልጫረ ።

ድሃ ካልዘራ ዶሮ ካልጫረ ፣ ማን ያበላው ነበረ ።

ድሃ ውሃውን ጠጥቶ እሳቱን ይሞቃል ፣ ሃብታም ስለ ገንዘቡ ይጨነቃል ።

ድሃ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም ።

ድሃ በጉልበቱ ፣ ባለፀጋ በከብቱ ።

ድሃ ያልፍልኛል ይላል ፣ ጌታ ቀኑን ይቆጥራል ።

ድሃ ያመልክት ፣ ዳኛ ያሟግት ።

ድሃ ያመልክት ፣ ዳኛ ያሟግት ።

ድሃና ሹም ተማግቶ ፥ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ፤ የማይሆን ነው ከቶ ።

ድሃና እመቤት ፥ እልፍኝና ማድቤት ።

ድሃና ጌታ ተሟግቶ ፥ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ።

ድሃና ጌታ ተሟግቶ ፥ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ፥ የማይሆን ነው ከቶ ።

ድሃን ምን ትሰራለህ እንጂ ፥ ምን ትበላለህ የሚለው የለም ።

ድሃን ሲያስለቅሱ ፥ ከሰላሴ ይወቀሱ ፥ መንግስተ ሰማያትን አይወርሱ ።

ድሃን ካስለቀሱ ፥ በስላሴ ዘንድ ይወቀሱ ።

ድህነት ፥ ከአምላክ መሰማማት ።

ድል በመታደል ፥ ሙያ በመጋደል ።

ድል እድል ፥ በአንድ ድልድል ።

ድመት መንኩሳ ፥ አመሏን አትረሳ ።

ድመት በታች ከሆነች ፥ ውሻ ታሸንፋለች ።

ድመትና አይጥ ፥ እሳትና ጭድ ።

ድመትን በቆሎ መጠርጠር ።

ድመትን አይጥ ገደለቻት ፥ ወይ ጥቃት ወይ ጥቃት ።

ድምቢጥ እንደ አቅሟ በብር ትታገማለች ።

ድምፅና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል ።

ድራቶ ከነቅማሉ ፥ መጥፎ ሰው ከነአመሉ ፥ ወዲያ በሉ ።

ድሪያ የዝሙት ቀዘማ ።

ድር ቢያብር ፥ አንበሳ ያስር ።

ድርብርብ ፥ እንደ ደጋ ንብ ።

ድርና ማግ ፥ ለሀጭና ልጋግ ።

ድርጎ ራቱ ፥ ድርጎ ቢቀር ሞቱ ።

ድርጎ የለመደች መበለት ፥ ወተት ያየች ድመት ።

ድርጭት ፈንጠር ፥ ምዝግዝግ ጎንደር ።

ድሮ ካያታችን ፥ ካጤ ነው ትውልዳችን ።

ድበላ ፥ አንዳንድ ጊዜ ይበላ ።

ድንቁርና ከልብህ መካከል ተራራ ያህል ።

ድንኳን ያየ ባለጌ ።

ድንኳን ገልጦ ፥ ዙፋን ረግጦ ።

ድንኳን ገልጦ ፥ ዙፋን አጊጦ ።

ድንጉተኛ ስህተት ፥ የቁልቁለት ውድቀት ።

ድንጋይ ላይ ተቀማጭ ፥ የባለጌ ተለጣጭ ።

ድንጋይ በድንጋይ ላይ ትልቅ ቤት ይሆናል ።

ድንጋይ ወርዶ እዘብጥ ያርፋል ፥ ያገኘው ይተርፋል ።

ድንጋይን ለረገጠ ፍለጋ የለው ፥ ውሃን ለጠጣ ሽታ የለው ።

ድግርና ገባር ፥ ሲተካከል ያምር ።

ድግስ የሌለው ዋዜማ ፥ ምልክት የሌለው ዜማ ።

ድጥ ማንሸራተቱን ፥ ባለጌ ማሽሟጠጡን አይተውም ።

ዶማ ለመማሻ ፥ ማረሻ ለመፈለሻ ።

ዶሮ ላትበላው ታፈስ ።

ዶሮ ፥ ልጆቿን ይዛ ጓሮ ለጓሮ ።

ዶሮ ሲሉ ስምታ ፥ ሞተች ከጢስ ገብታ ።

ዶሮ በልቶ ከብስና ፥ ጎመን በልቶ በጤና ።

ዶሮ በልጅዋ እንጀት ትጫወታለች ።

ዶሮ በማሰር ፥ ገደል ለዝንጀሮ ።

ዶሮ በጋን ።

ዶሮ ቢጠፋ ከቤቱ ፥ መነከሰች እናቱ ።

ዶሮ ብትታመም በግ አረዱላት ።

ዶሮ አንዱን እንቁላል በወለደችበት ወታቦ ትሞላለች ።

ዶሮ እኔ ባልበላ ጭሬ አላፈስም ወይ አለች ።

ዶሮ ከቆጥ ፥ በሬ ከጋጥ ።

ዶሮ ከቤት ውላ ዝናብ ይመታታል ።

ዶሮ ከጋጥ ፥ በሬ ከቆጥ ።

ዶሮ ከጮኸ ሌሊት ፥ ከደብረታቦር ወዲያ ክረምት የለም ።

ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ፥ ከቡሄ ወዲያ የለም ክረምት ።

ዶሮ ካልበሏት ፥ አሞራ ናት ።

ዶሮ ጭራ ማረጃዋን አወጣች ።

ዶሮ ጭራ የምታወጣው ምስጢር ።

ዶሮ ጭራ ጭራ ፥ አወጣች ማረጃዋን ካራ ።

ዶሮና ቀበሮ ፥ ተገናኝቶ ጓሮ ።

ዶሮን ሲቀጣጠብዋት ፥ በመጫኛ ጣሏት ።

ዶሮን ሲደልሏት ፥ በመጫኛ ጣሏት ።

ዶሮን ቢያማት ፥ በሬ ተሳሉላት ።

## - ጀ -

ጀማሪ ይጥፉ ፣ ሰካራም ይትፉ ።

ጀምሮ የማይፈፅም ፣ ፈጭቶ የማያልም ።

ጀምሮ ይጨርሳል ፣ ለጉም ይተኩሳል ።

ጀምበር ሳለ ሩጥ ፣ አባት ሳለ አጊጥ ።

ጀርባ ለባለቤቱ ባእድ ነው ።

ጀርባዬን አሳከከኝ ፣ ተንጠራርቼ ማከክ ተሳነኝ ።

ጀርባዬን እከከኝ ለኔ ራቀኝ ።

ጀግና የሚታወሰው ወይም ከሞተ ወይም ከተለየ በሁዋላ ነው ።

ጃርት ያስደነገጠው ዱባ ይመስላል ።

ጅምር ይጨረሳል ፣ ልጉም ይተኮሳል ።

ጅምርን ለነገ አያሳዩም ።

ጅራትና ሀሜት በስተሁዋላ ነው ።

ጅራቷ ፣ ታደርሳለች ከናቷ ።

ጅራፍ መትቶ ያለቅሳል ፣ ባለፀጋ በድሎ ተመልሶ ይወቅሳል ።

ጅራፍ እሱው ይገርፍ ፣ እሱው ይለፍ ።

ጅብ ምን ይመስላል ? እግሩ ያነክሳል ፣ አፉ ይነክሳል ።

ጅብ ሲበላህ በልተኸው ተቀደስ ።

ጅብ ባጥንት የተገደገደ ፣ በጅማት የተማገረ ቤት አለ ቢሉት ፣ ወዴት ነው ሳይል
ገደል ገብቶ ሞተ ።

ጅብ አያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ።

ጅብ እስኪነክስ ፣ ያነክስ ።

ጅብ እንኳን ጓደኛውን ይጣራል ።

ጅብ እንደ ቁመቱ ልብ የለውም ።

ጅብ እንደ አባቱ ይዘርጥጥ ።

ጅብ እንደ አባቱ ይዘርጥጥ ፣ አህያ እንደአባቱ ይፈርጥጥ ።

ጅብ እንደ አገሩ ይጮሃል ።

ጅብ እንደ ጉልበቱ ልብ የለውም ።

ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ።

ጅብ ከላይ ውሃ ሲጠጣ ፣ ታች ያለችውን አህያ አታደፍርሽብኝ አለ ።

ጅብ የኔ ነው ስለው ወናፌን ቀማኝ ።

ጅብና ሸማኔ ከጉድጓድ አይወጡም ።

ጅብና እህል ሳይተዋወቁ ይኖራሉ ።

ጅብን ሊወጉ ፣ ባህያ ይጠጉ ።

ጅብን ፈርቼ ከዛፍ ብወጣ ነብር ቆየኝ ።

ጀሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው ።

ጀሮ በላ ፣ ሆድ ጠሙን አደረ ።

ጀሮ ባይጠም ፣ ይመስላል ሆዳም ።

ጀሮ አይጠምም ፣ አይን አይጠግብም ።

ጀሮ እዳውን አይሰማም ።

ጀሮ ካያት ያረጃል ።

ጀሮ የሰማውን ፣ ለማየት ይሄዳል አይን ።

ጀሮ የሰማውን ፣ ልብ ያውቀዋል ።

ጀሮ የቀድሞዎቹ እኩያ ነው ።

ጀሮውን ቢቆርጡት ፣ መስሚያው ይቀራል ።

## - ገ -

ገላጋይ አጥቼ ግልገሌን በላሁዋት ።

ገለፈንት ፣ የቤት ጋለሞታ ።

ገመድን ሲበጠስ መቀጠል ፣ አባይ መስካሪን ገደል ።

ገራገሩን ተጫውቶ ፣ ይኖሯል ተስማምቶ ።

ገር ገሩን ተጫውቶ ፣ ይበሏል ተስማምቶ ።

ገርነት ፣ የእግዜር ቸርነት ።

ገርነት ፣ ያገባል ገነት ።

ገርና ልል ፣ ሙዳይና አገልግል ።

ገርን ልጅ እናቱ አትወደውም ።

ገበሬ አቆጣጠረኝ ፣ ወታደር አወራወረኝ ።

ገበሬ አከባሪውን ፣ ባለጌ መካሪውን ይጠላል ።

ገበሬ አከባሪውን ይጠላል ።

ገበያ ቢመቻት ፣ ልጅዋን ሸጠቻት ።

ገበያ ነሽ ብለው ይሻሻጠብሻል ።

ገበያ እንደሰጠህ እንጂ ፣ እናትህ እንደላከችህ አይሆንም ።

ገበያ እንዴት ዋለ? ቢለው ፣ አንዱ ባንዱ ሲስቅ ።

ገበያ የሚሰጥን እናት አትሰጥም ።

ገበጣ ላዋቂ ፣ ወሬ ለጠያቂ ።

ገበጣ ላዋቂ ፣ ወሬ ለጠያቂ ፣ ዋዛ ፈዛዛ ለሳቂ ።

ገቢ ያፈርሳል ፣ ቀዳዳ ያፈሳል ።

ገቢውን ባለቤት ያውቃል ።

ገባ ወጣ ፣ ነገር ያመጣ ።

ገባር ያህያ ግምባር ።

ገብሬል ያየው ምስጢር ።

ገብስ ሲበስል ፣ አባቱን ይመስል ።

ገብስና ሽንኩርት ቂጡ ሲበስል ነው ።

ገብስና ገብስ አብሮ ይነፈስ ።

ገና ዘንቦ ባርቶ ።

ገናም በሙክቱ ፣ ሁዳዴም በእልበቱ ይታወቃል ።

ገናና ጥምቀት ፣ እኩል አውዳመት ።

ገንዘቡ የሰው ቢሆን ፣ አዳዩ የኔ ይሁን ።

ገንዘቤ አትውጪ ከቤቴ ፣ ታጣይኛለሽ ከጎረቤቴ ።

ገንዘብ ከጁ ፣ ዘመድ ከደጁ ።

ገንዘብ ከጅ ከወጣ ፣ ያመጣል ጣጣ ።

ገንዘብ ከጅ ከወጣ ፣ ይመጣል ይዞ ጣጣ ።

ገንዘብ ከጅ ፣ ዘመድ ከደጅ ።

ገንዘብ ካለ ፣ በሰማይ መንገድ አለ ።

ገንዘብ የልብ ስር ነው ።

ገንዘብ የጠፋበት ፣ ብዙ ሀጢአት አለበት ።

ገንዘብ ያልያዘ መንገደኛ ፣ አይፈራም ቀማኛ ።

ገንፎ ለጉንፋን ይበጃል ፣ ወዲህም ለሆድ ይበጃል ።

ገንፎ ለጉንፋን ደግ ነው ፣ እግረ መንገዱንም ለሆድ ይበጃል ።

ገንፎ ማላመጥ ፣ በእግዜር ማልመጥ ።

ገንፎ ስርታ ለራት ፣ ቢያጎርሳት ተኮሳት ።

ገንፎ ሲበሉ ልጅ አስወግዶ ፣ ጠላ ሲጠጡ እሳት አንድዶ ።

ገንፎ በድስት ፣ ጎመን በምንቸት ።

ገንፎ እፍ እፍ ቢሉሽ ፣ ሊውጡሽ ነው እውነት አይምሰልሽ ።

ገዝቶ የማይቆጣ ፣ አጥቦ የማያነጣ ።

ገደል ለዝንጀሮ ፣ ጉድጓድ ለቀበሮ ።

ገዳም የገባ አይወጣ ፣ ከል የገባ አይነጣ ።

ገዳይ ቢያረፍድ ፣ ሟች ይገሰግሳል ።

ገዴ ገድሽ ለኔ ፣ ስጋሽ ለአረመኔ ።

ገድለው ካላመለጡ ፣ ምንድነው ጌጡ ።

ገድሎ ነበር ሞተ ።

ገድሎ ባለቃዬ ፣ ከሶ ከጠበቃዬ ።

ገጣባ አህያ ትሰለቻለች ፣ ጭና ታበላለች ።

ገጣጣ ሲሞት የሳቀ ይመስላል ።

ጉልበት አለኝ የበላ ፣ ምላስ አለኝ ፣ የሰላ ።

ጉልበት አለኝ የዝሆን ፣ አፍ አለኝ ላንተ የሚሆን ።

ጉልበት አለኝ የዝሆን ፣ አፍ አለኝ የመስፍን ።

ጉልበት አለኝ የዝሆን ፣ አፍ አለኝ የመኮንን ።

ጉልበት የሌለው ወንበዴ ፣ ትርፍ የሌለው ነጋዴ ።

ጉልበት የሌላት ወይዘሮ ፣ ገደል የሌለው ዝንጀሮ ።

ጉልቻ የላቀው ፣ አመድ ያጠለቀው ።

ጉልቻ የላቀኝ ፣ አመድ ያጠለቀኝ ፣ አለ አማኑኤል ማን ጠየቀኝ ።

ጉም ሲለቅ ፣ የታባትህ ትገባ አንተ ሌባ ።

ጉም መጣመጥ ፣ ውሃ መጣመጥ ።

ጉም ተራራን ያለብሳል ፣ ሹም ለሹም ያወርሳል ።

ጉሬዛ ቢውል ከጠጣ ፣ ጥፋት ለምዶ መጣ ።

ጉሮሮ የሚውጠውን ፣ እጅ ይመጥነዋል ።

ጉብ የለመደ ዳኛ ፣ አህያ የለመደ ጅብ አንድ ነው ።

ጉቦና ሌባ በር አይወድም ።

ጉትቻ ለጆሮ ትንሽ ትመስላለች ፣ ዛፍ ጎበዝ ትቆጥራለች ።

ጉትቻ ለጆሮ ፣ እልፍኝ ለወይዘሮ ።

ጉትቻ ለጆሮ ፣ ጥሬ ለዶሮ ።

ጉንዳን ባልንጀራው ሲሞት ፣ ብቻውን ተሸክሞ ይዞራል ።

ጉንዳን ፣ ቤቱን ይመራል ።

ጉንዳን የባልንጀራውን ሬሳ ፣ ብቻውን ያነሳ ።

ጉንፋን የተያዘና ፍየል ይዞ የተደበቀ ፣ ሳይጋለጥ አይቀርም ።

ጉደኛ ውሻ ፣ ስጋ ተቀምጦ ቆሎ ትሻ ።

ጉዳት ከመጣ ፣ መከር አይታጣ ።

ጉዳይ ሳይኖርህ ገበያ አትውረድ ፣ ያንዱን ነገር ሰምተህ አትፍረድ ።

ጉዳይ አሳልፍ እንድትታማ ፣ አሮጌ ሁን ልትፎክር ፣ ሙት ልትመሰገን ።

ጉዳይ የሌለህ ገበያ አትውረድ ፣ ያንዱን ሰው ነገር ሰምተህ አትፍረድ ።

ጉድ ለባለቤቱ ልግም በገላ ነው ።

ጉድ ለባለቤቱ ያንገት ልብስ ነው ።

ጉድ እንግዳ ነገር ፣ አሳድሮ መቸገር ።

ጉድ ያለው ገንፎ አድሮ ይፋጃል ።

ጉድ ይገርማል ፣ አህያ ከጅብ ይከርማል ።

ጉድ ይገርማል ፣ ጅብ ከአህያ ጋር እንዴት ይከርማል ።

ጉድሽ ድንቅሽ ፣ ና ብለሽ ወዴት ሄድሽ ።

ጉድነሽ ያንኮበር ቅጠል እያደር ትለበለቢያለሽ ።

ጉድና ብርቅ ፣ እስከ ሶስት ቀን ያስጨንቅ ።

ጉድና ድንቅ ፣ አለ አንድ ጊዜም አይደምቅ ።

ጉድና ድንቅ አንድ ሰሞን ነው ።

ጉድና ጅራት በስተሁዋላ ነው ።

ጉድጓድ በራሱ አፈር አይሞላም ።

ጉጉት ብትጠቃ ፣ እርኩም ሆነ ጠበቃ ።

ጉፋያ ሲነዱ ፣ ይሸከሙ ።

ጉፋያ ከመብላት ፣ ስብ መሸከም ይሻላል ።

ጉፋያ ከመብላት ፣ ጮማ መሸከም ።

ጉፋያ ከሚያርዱ ፣ ስብ ይቀላውጡ ።

ጉፋያን ሲበሉ ፣ ስብ ይቀላውጡ ።

ጊዜ ሲከዳ ፣ መሬቱ ያድጣል ።

ጊዜ ወርቅ ነው ፤ ግን ሃላፊ ነው ።

ጊዜ የሌለው የለም ፤ ግን ከእድሉ የሚያልፍ የለም ።

ጊዜ የሰጠው ቅል ፣ ድንጋይ ይሰብራል ።

ጊዜ የሰጣት አይጥ ከፈረሰኛ እኩል ትሮጣለች ።

ጊዜ ያለው ፣ ጊዜ አይጠብቅ ።

ጋለሞታና ጌታ ፣ ደጅ የጠኑለታ ።

ጋራና ጉባ ፣ ቅልና ዱባ ።

ጋሻ ለማንባር ፣ ጫማ ለጠጠር ።

ጋሻ እሰጥ ጋሻ እሰጥ ሲሉ ጦር አገባ ።

ጋሻ ፣ ዱሮ ቀረሻ ።

ጋሻና ውጊያ እንዴት ነው፣ ቢለው ፣ ጋሻ ወርውሮ ጦር መመከት ነው አለ ።

ጋሻና ማንባር አይሸሸግም ።

ጋን ሰሪ ፣ ምጣድ አይዋጣለትም ።

ጋን ሲለቀለቅ ፣ ማድጋን ይሞላል ።

ጋን ሲያሟጥጡት ፣ ምንቸት ይሞላል ።

ጋን ቢያንጫልጡት ፣ ማሰሮ ይሞላል ።

ጋኖች አለቁና ፣ ምንቸቶች ጋን ሆኑ ።

ጋይ የለ እሸት ፣ ስጡኝ አለ ።

ጋጋሪ ያበስላል ፣ ተናጋሪ ያስመስላል ።

ጌታ ሁን ፣ እንዳሻህ ሁን ።

ጌታ ሁን ፣ እንደፈቀደህ ሁን ።

ጌታ ለሎሌው ፣ ነጋዴ ላሞሌው ያስባል ።

ጌታ ሲሰጥ ፣ ማን ይከለክላል ።

ጌታ ሲወድ ማን ይጠላል ፣ ጌታ ሲሰጥ ማን ይከለክላል ።

ጌታ ቢጫወት ፣ ያልኮራ ይመስላል ።

ጌታ ባወቀው ይፈርዳል ፤ ሰው ባላወቀው ይጎዳል ።

ጌታ የለቁን ፣ አባት የመሰረቱን ።

ጌታ ያዛል ፥ ውሻ ይለዛል ።

ጌታ ያዛል ፥ ውሻ ያንዘዛል ።

ጌታና ሎሌ ተጣልተው ፥ ዱባና ቅል ተማተው ፥ ኧረ አይመስልም ተው!!

ጌታና ሎሌ ተጣልቶ ፥ ቅልና ድንጋይ ተማቶ ።

ጌታና ገቢታ አቅራቢ ነው ፥ ሰጭው እግዜር ነው ።

ጌታና ጋለሞታ ፥ ደጅ የጠኑ ለታ ።

ጌታዋን የምታምን ውሻ ፥ ፍሪዳ ሲታረድ እወንዝ ወረደች ።

ጌታዋን የምትወድ ላም በመስከረም ትወልዳለች ።

ጌታዬ ምን አልኩህ ? ጠጅ አጠጥተህ ውሻ ።

ጌታዬ ካሉበት እገሙኝ ።

ግልግልና ገንፎ ትኩሱን አያስገባም ።

ግመል ምን ተጭነሃል? ሽመል ፤ ምን ያወዛውዝሃል? አመል ።

ግመል ሰርቆ አጎንብሶ ሄደ ።

ግማሹን ተላጭታ ፥ ግማሹን ተቀብታ ።

ግማሽ ልጩ ፥ ግማሽ ጎፈሬ ።

ግም ለግም ፥ አብረህ አዝግም ።

ግረፍ ፥ ከባት አትለፍ ።

ግራ መብል ፥ ቀን ገንፎ ፥ ሌሊት ድፎ ።

ግራ መብል ፥ ቀን ገንፎ ሌሊት ዶሮ ።

ግራ ነገር ፥ ከወንዝ ማዶ ፍቅር ፥ ከጎረቤት ጥል ።

ግርግርታ ፥ የሌባ ደስታ ።

ግባ ያላለው ገንዘብ ፥ አጥር ቀዶ ይወጣል ።

ግብ እንደግቡ ፥ሙከት እንደ ስቡ ።

ግብር እስከ መቃብር ።

ግብር ይውጣ ።

ግብር ይውጣ ፥ የማይቀር እዳ ።

ግብዝና ፥ መቼ እንደ ጲቁና ።

ግብዝን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው ።

ግንብና ድንጋይ ፥ ጌታና አባይ ።

ግንቦት ቢዳምን የሚዘንብ ይመስላል ፤ አሮጌ ቢፎክር የሚዋጋ ይመስላል ።

ግንቦት ቢዳምን ይዘንብ ይመስላል ፤ ሃምሌ ቢባራ በጋ ይመስላል ።

ግንድ ለሺ አይከብድም ።

ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ ።

ግዳይ ለከንፈሬ ፥ ጥምጥም ለምምሬ ።

ግዳይ አምሯቸው ዘመቱ ፥ እሳቸውም ሞቱ ።

ግፈኛ ፥ የሰይጣን መላከተኛ ።

ግፍ ሲቆም ፥ ፀሎት አያሻም ።

ግፍ ሲናኝ ኩበት ፥ ሲጠልቅ ድንጋይ ይዋኝ ።

ግፍ ባገር ሲሞላ ፥ ርስ በርስ ያባላ ።

ግፍ ባገር ሲናኝ ኩበት ፥ ጠልቆ ድንጋይ ይዋኝ ።

ግፍ አይፈሬ መሬት ፥ እንክርዳድ ያበቅላል ።

ግፍ የተሰራ በኛ ፥ ካሱ ይሉናል በዳኛ ።

ግፍስ በባህር ይመላል ፥ እሳ አሳውን ይበላል ።

ኀልማሳ ሲታጠቅ ከደረቱ ፣ ሲሮጥ ከጉልበቱ ።

ኀልማሳ እበቀለበት ላም አይማረክም ፤ ሽማግሌ እበቀለበት ነገር አይሳሳትም ።

ኀልማሳ ካለበት ከብት አይሰረቅ ፣ ሽማግሌ ካለበት ነገር አይነጠቅ ።

ኀልማሳ ካለበት ከብት አይነጠቅ ፣ ሽማግሌ ከዋለበት ነገር አይወድቅ ።

ኀመን በጤና ።

ኀመን ባወጣው ነፍስ ፣ አትኩራ ገብስ ።

ኀረምሳ ፣ እንደበላህ አንሳ ።

ኀረቤት አያውቀው ነገር ፣ ወንጠፍት አያጠራው አሰር ።

ኀረቤት ፣ ይሆናል ጠላት ።

ኀረቤት ይሆናል ጠላት ፣ ያችን ሴት አትዝጊ በሏት ።

ኀራዴ ለወንበዴ ፣ ሱቅ ለነጋዴ ።

ኀራዴህ ኀመዳም ፣ ሚስትህ አመዳም ።

ኀራዴና ምስጥ ፣ ውስጥ ለውስጥ ።

ኀርፍ ሲወስድ እያሳሳቀ ፣ ተንኮለኛ ሰው ሲጎዳ እየተራቀቀ ነው ።

ኀሽ ለልጅዋ ብላ ትወጋ ።

ኀሽ ጠመድኩ ይሆናል ብዬ ፣ ፈትቼ ሰደድኩ አይሆንም ብዬ ።

ኀበዝ ፊት ሰማይ ሰማይ ያያል ፣ ሁዋላ ምድር ምድር ያያል ።

ኀባጣን ሲቀብሩ እንደ አመሉ ።

ኀባጣን ቀንና ቅምዝምዝምን አጎንብሰህ አሳልፈው ።

ኀባጣን ይቀብሩ ፣ እንደምግባሩ ።

ኀኑ የኔ ፣ ቀኑ ሰኔ ።

ኀንደር ወጣ ፣ ምን ይዞ መጣ ።

ጎንደር ወጣህ ፣ ምን አመጣህ ?

ጎንደር ወጣሽ ፣ ምን አመጣሽ ?

ጎጳ ከብት ከቀንጳም ይብሳል ።

ጎዳናና መንገድ ፣ ጉንጉንና ገመድ ።

ጎጳው ፍየል ፣ ቀንጳሙን ወጋው ።

ጎድሎ ነበር ሞላ ፣ ሞልቶ ነበር ፈላ ።

ጎጃም በዘነበ ፣ ሳይንት እህል ሆነ ።

ጎጆ ወጭ ሙሽራ ፣ በገፍ ወጥ ትሰራ ።

ጓሳና ድንግል ፣ ያላንድ ጊዜ አይበቅል ።

## - ጠ -

ጠላ በማቶቱ ፣ እንጀራ በሌማቱ ።

ጠላ ባለቤቱን አያውቅም ።

ጠላ ካስር ፣ ነገር ካገር ።

ጠላ ካሰከረው ፣ ውትት ያሰከረው ።

ጠላ ያለ አተላ ፣ ጠጅ ያለ አንቡላ ።

ጠላት በጥርስ ሲገኝ ።

ጠላት ቢያባብሉት ፣ ወዳጅ አይሆንም ።

ጠላት የሌለው ወዳጅ አያሻውም ።

ጠላት ፣ ይቀበል ጥላት ።

ጠላትህን ውሃ ሲወስደው ፣ እንትፍ ብለህ ጨምርበት ።

ጠላትን ለማግኘት ሲጎረጉሩ ፣ በወዳጅ ይጀምሩ ።

ጠላትን በጦር ፣ አባትን መጦር ።

ጠላና ጉተና እለቱን አይደርስም ።

ጠላኝ ማለት ያስጠላል ፣ ልግደል ማለት ያስገድላል ።

ጠላው ሳይገባ ማቶቱ ፣ ቀንዱ ሳይገባ ጅራቱ ።

ጠላው የባእድ ፣ አሳላፊው ዘመድ ።

ጠልቶ ለጠላት ፣ አስሮ ለእስራት ።

ጠመንጃ ያለ ጥይት ዱላ ፤ ወንድ ያለ ሴት ቀውላላ ።

ጠመንጃ ያለ ጥይት ዱላ ፤ ወንድ ያለ ሴት ድሃ ።

ጠመደና በሬና ዝሆን ፣ መቸም እንዳይሆን ።

ጠርቦ ለደጁ ፣ ፈርዶ ለልጁ ።

ጠርጥር ፣ ከምግቡ ውስጥ አለ ስንጥር ።

ጠቃሚ ከናሪያ ይመጣል ፣ አጥፊ ከጉልበት ይወጣል ።

ጠቋሚ ፣ ጠቃሚ ።

ጠበቃ ታፈጀ ፣ በርበሬ ታረጀ ።

ጠበቃና ቅል ባጠገብ ይውላል ።

ጠባ ለኪዳን ፣ መሸ ለቁርባን ።

ጠባቂ ያላት በግ ፣ ላቷ እደጅ ያድራል ።

ጠባብ አልጋ የግድ ያስተቃቅፋል ።

ጠብ ባለበት ቤት ፣ ዶሮ ትሞት ።

ጠብ ተጀመረ ፤ አንበሳ ላምን ሰበረ ።

ጠብ ተጀመረ ፤ ያ ልጅሽ አለ ልጄ ሲል የነበረ ።

ጠብ ካለበት ቤት ፣ ዶሮ ከጋጥ ትሞት ።

ጠብ የሻ መኮንን ፡ የዶሮ ሻጡኛ አም ይላል ።

ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ።

ጠንቋይ ባያሳምን ፡ ያጠራጥር ።

ጠንቋይ አባይ ቤት ያስፈታል ።

ጠያቂ የለም እንጂ ከድሃ ምክር ይገኛል ።

ጠይብ በገል ይበላል ።

ጠጅ ለወረት ፡ ወጻጅ ለችግር ለት ።

ጠጅ ለጨዋ ልጅ መጫወቻው ፡ ለባለጌ ልጅ መማቻው ።

ጠጅ በብርሌ ፡ ነገር በምሳሌ ።

ጠጅ የሌለበት   አበጋዝነት ።

ጠጅ ፡ የወረት ወጻጅ ።

ጠጅ ይሻላል በመጠኑ ፡ የጨዋ ልጅ ይበልጣል በቀጭኑ ።

ጠጅና መኮንን ፡ ድሃና ጎመን ።

ጠገብሁ ያለውን ብላ አትብለው ፡ ፈራሁ ያለውን ድፈር አትበለው ።

ጠጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል ።

ጠፍር በሊታ ብትሄድ ፡ ልጓም በሊታ መጣች ።

ጠፍር መጫኛ ፡ ቁርበት መገኛ ።

ጡት መጥባት ፡ የናት ።

ጢም የሌለው መምህር ፡ አፀድ የሌለው ደብር ።

ጢም የሌለው መምህር ፡ አፀድ የሌለው ደብር ፡ አምሮም አያምር ።

ጢምህን እጠላለሁ ፡ መሳምህን እወዳለሁ ።

ጢሰኛ ሲቆይ ባለርስት ይሆናል ።

ጣል በደጅ ፣ እስር በፍንጅ ።

ጣመኝ ፣ ድገመኝ ።

ጣት ገማ ብሎ ፣ ቆርጦ አይጣልም ።

ጣዝማ ሰርሳሪ ፣ ዳኛ መርማሪ ።

ጣይ ያየውን ፣ ሰው ሳያየው አይቀርም ።

ጣጣ ፣ ፈንጣጣ ።

ጣጣ ፈንጣጣ ፣ ድንጋይ ፈለጣ ።

ጤና ከሀብት ፣ ወፍጮ ከከብት አይቆጠርም ።

ጤፍ መፍሰስሽን ቢያይ ፣ ገበሬ ባልዘራሽ ።

ጤፍ ቢሰኩ ፣ ሰማይን ቢያኩ ፣ አይገኝም ልኩ ።

ጤፍ አይቆላ ፣ የጭቃ ልጅ አይጠላ ።

ጤፍ አጎደለ ቢለው ፣ ገብስ እንዳይሰማ አለው ።

ጤፍ ከዘመዷ ፣ ጎታ ትሞላለች ።

ጤፍ ካላረሙ አይለማ ፤ ስጋ ካልሰነበተ አይገማ ።

ጥለውት የመጡትን ጓደኛ ዙረው አያዩትም ።

ጥላና ሸኝ ቤት አይገቡም ።

ጥል ያለሽ በዳቦ ።

ጥል ያጠላላ ፣ ኩስ ላፍ ይጠላ ።

ጥልቅ ብዬን ውሃ ወሰዳት ።

ጥምብ ባለበት ቁራ ይዞራል ።

ጥምድ እንደበሬ ፣ ቅንት እንደገበሬ ።

ጥምጥም የሌለው መምህር ፣ አፀድ የሌለው ደብር ።

ጥሩ መስሎ አተላ ፣ ፍሬ መስሎ ገለባ ።

ጥሩ እንደ ብርሌ ፣ ቀይ እንደ በርበሬ ።

ጥሩ ድህነት ጥሩ ነፃነት ፣ ጥሩ ሀብት መልካም ርስት ።

ጥሩ ጠላት ጥኑ ወዳጅ ይሆናል ።

ጥሬ ለዶሮ ፣ ግልግል ለቀበሮ ።

ጥሬና ክፉ ንግግር ፣ ሆድ ያሻክራል ።

ጥርስና ከናፍር ፣ ቢደጋገፍ ያምር ።

ጥርስና ከንፈር አብሮ ይደማል ።

ጥቂት ሀመም ታመህ ፣ ወዳጅ ጠላትህን እየው ።

ጥቂት ስጋ ፣ እንደ መርፌ ትወጋ ።

ጥቂት ሽሮ ፣ ማታ ዶሮ ።

ጥቂት ያላት ፣ እረፍት የላት ።

ጥቂት ያላት ፣ እንቅልፍ የላት ።

ጥቂት ጥቂት ኤሊም ትሄዳለች ፤ ካሰበችበት ትደርሳለች ።

ጥቃት ከጥንብ ይገማል ።

ጥቅልል ያለን ጠጉር ዘርዘር ያለ ሚዶ ያስነሳዋል ።

ጥቅልል ላለ ጠጉር ፣ ዘርዘር ያለ ሚዶ ።

ጥበብ ያስከብራል ፣ ሀብት ያስጨፍራል ።

ጥኑ ወዳጅ ጥኑ ጠላት ይሆናል ።

ጥኑ ወዳጅ ጥኑ ጠላት ፣ ጥኑ ጠላት ጥኑ ወዳጅ ይሆናል ።

ጥንቱን ሲሉህ ቡዳ ፣ ቆዳ ይዘህ ሚዳ ።

ጥንቱንም ባልዘፈንሽ ፣ ከዘፈንሽም ባላሳፈርሽ ።

ጥንቱንም የተውሶ ፥ ጠፋ ተመልሶ ።

ጥንቱንም የተውሶ ፥ ጠፋ ጨርሶ ።

ጥንቸል እንደ ዝሆን እሞሻለሁ ብላ ተስነጥቃ ሞተች ።

ጥንቸል እንዳትቅሟ ታግታለች ።

ጥንቸልም ለሆዷ ፥ ዝሆንም ለሆዱ ፥ አብረው ውሃ ወረዱ ።

ጥዋት ጀርሮ ማታ ጀርሮ ።

ጥዋፍ ያበራል ፥ ከሳሽ ይመራል ።

ጥይት አይር ፥ ፈትል ድውር ።

ጥጃ ሳር ይበላል ፥ ቤቱ እዳ ይሞላል ።

ጥጃ ቢሳሳት ከናቱ ፥ ነገር ቢሳሳት ከጧቱ ።

ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ ፥ ውሃ ቢሮጥ በጎድጓዳ ።

ጥጃ ጠባ ፥ ከሆድ ገባ ።

ጥጋበኛንና ውሃ ሙላትን ቁመህ አሳልፈው ።

ጥጋብ ቢሻህ ባቄላ ፥ ኑሮ ቢሻህ ችላ ።

ጥጋብ ቢያምርህ ጠላ ፥ መግዛት ቢያምርህ ችላ ።

ጥጋብን ወደኛ በል ፥ ጥጋበኛን ወዲያ በል ።

ጥጋብን የማይችል አህያ ነው ።

ጥጥ ለፈታይ ፥ ሽልማት ላገሊጋይ ።

ጥጥና ሹም እያደር ይከዳል ።

ጦም ከማደር ዳቦ ቀርቅር ።

ጦር ለወረወረ ፥ መሬት ለገበረ ።

ጦር መጣ ሲባል ፥ ሶማያ ቀረጣ ።

ጦር ሲመጣ ፥ ዛቢያ ቆረጣ ።

ጦር እንደ ወረወሩት ፥ ጎራዴ እንደሰነዘሩት ።

ጦር ከወጋው ፥ ምላስ የወጋው ።

ጦር ከፈታው ፥ ወሬ የፈታው ።

ጦርና ጭሬ ፥ አራሽና ገበሬ ።

ጠጣ ምን ትወጃለሽ ? ቢሏት ፥ ከዛፍ ላይ ትግል ።

ጠጣ ፥ ባለቤቱን ታስወጣ ።

ጠጣ ተይዛ ትዘፍን ።

ጠጣና ዝንጀሮ ፥ ተኩላና ቀበሮ ።

ጢሪ ፥ በፈጣሪ ።

ጢት ከበላተኛ ፥ ማታ ከአድመኛ ።

ጢት ከበላተኛው ፥ ማታ ከጠመኛው ፥ እንደሸመላ ፥ በሁለት ይበላ ።

ጢት ከጀንበር ፥ ማታ ከጨንገር ።

## - ጨ -

ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል ።

ጨረቃ ብትደምቅ ፥ አትሞቅ ።

ጨረቃና ሴት ፥ ዛሬ ብርሃን ነገ ፅልመት ።

ጨቅጫቃ ሚስትና የሚያፈስ ቤት አንድ ናቸው ።

ጨካኝ ሰይጣን መሳይ ።

ጨካኝና ጨስ መውጫ አያጣም ።

ጨዋታ ለአዋቂ ፥ ወሬ ለጠያቂ ።

ጨዋታን አዳምጦ ፣ እህልን አላምጦ ።

ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ፣ አለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል ።

ጨው ሻጭ በገበያ ፣ ጦር በሰማያ ።

ጨው ቢያልጥ በምን ይጣፍጣል ? ዳኛ ቢያዳላ በምን ይሟገቷል ?

ጨው የሌለው ምግብና ሰው የሌለው ሰው አንድ ነው ።

ጨውና በርበሬ ፣ ጀሮና ወሬ ።

ጩኸት ለሲላ ፣ መብል ላሞራ ።

ጩኸት ለቁራ ፣ መብል ላሞራ ።

ጫማ ምንም ወርቅ ቢሆን ከእግር በታች ነው ።

ጫን ካለ ጫን ይፈጃል ።

ጫን ያለው ኮርቻውን ፣ ለምን ያለው ስልቻውን አያጣውም ።

ጫንቃዬን ተገርፌ ፣ ጨርቄን ተገፍፌ ።

ጭልፊትና ሲላ ተጋብተው ጉጉት ወለዱ ።

ጭምት ያበደ እንደሆን የጤፍ ቆረን ደኑ ።

ጭንቅ አልጋ ያስተቃቅፋል ።

ጭድና ጭቃ ፣ ቡሃና በቃ ።

ጮኸ የማታውቅ ወፍ አንድ ቀን ብትጮህ እለቁ እለቁ አለች ።

ጮሌ ሲያረጅ መጋኛ ይሆናል ።

## - ጳ -

ጳጉሜ ሲወልስ ፣ ጎተራህን አብስ ።

ጳጉሜን ሲወልስ ፣ ገበሬ ጎተራህን አብስ ።

ጳጉሜ ቢለግስ ጎታህን አብስ ።

ፀሃይ ሳለ ሩጥ ፣ አባት ሳለ አጊጥ ።

ፀሃይ ብልጭ ፣ ወፍ ጭጭ ሲል ።

ፀሃይ ካልወጣ ፣ ከሰፈረበት አይነሳ አንበጣ ፣ ሴት ምክንያት አታጣ ።

ፀሃይ የጧት ፣ አዱኛ የሽበት ።

ፀሃይ ያየውን ሰው ሳያየው አይቀርም ።

ፀሃይና ንጉስ ሳለ ፣ ሁሉም አለ ።

ፀሎት በፅሞና ፣ ነገር በደመና ።

ፀሎት በፍቅር ፣ ሃይማኖት በምግባር ።

ፀሎት ከፍቅር ፣ ሃይማኖት ከምግባር ይበጃል ።

ፀሎት ያለ ፍቅር ፣ ሃይማኖት ያለ ግብር አይረባም ።

ፀፀት ፣ እያደር ይመሰረት ።

ፃድቃን ካልተቃጠሩበት ስፍራ ይገናኛሉ ፤ ሆዋእን ግን ከተቃጠሩበት ይተጣጣሉ ።

ፅዋ በተርታ ፣ ስጋ በገበታ ።

ፅድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ ።

ፅድቅ ለመንኳሽ ፣ ቀኝ ለከሳሽ ።

ፆም ገዳፊና ሰው ጠባቂ ለጥቂት ይሳሳታል ።

ፆማ ፆማ ለፀሎት ሀሙስ ፣ እርጎ ትልስ ።

ፈላ ገነፈለ ፤ ተሞላ ጎደለ ።

ፈረሰኛ ሲሮጥ ፤ እግረኛን ምን አቆመው ?

ፈረሰኛ የወሰደውን ፤ እግረኛ አይመልሰውም ።

ፈረሱም ይኸው ፤ ሜዳውም ይኸው ።

ፈረስ ሲያጠብቅ ፤ ልጓም አይለቀቅ ።

ፈረስ በራሪ ፤ በቅሎ ሰጋሪ ።

ፈረስ ቢያነክስ ፤ አህያ ታጉዝ ።

ፈረስ ቢጠፋው ፤ ኮርቻውን ገልቦ አየ ።

ፈረስ አውቃለሁ ፤ ስገታ እወድቃለሁ ።

ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም ።

ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል ፤ በቅሎ ጥሎ ይረግጣል ።

ፈረንጆች እንደመርፌ ይገቡ ፤ እንደዋርካ ይሰፉ ።

ፈሩ ፈሩ ፤ ማጀት አሩ ።

ፈሪ ለእናቱ ይገባል ።

ፈሪ ለእናቱ ፤ ጀግና ለጀግንነቱ ፤

ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል ።

ፈሪ እንዳይሉኝ አንድ ገደልሁ ፤ ጀግናም እንዳይሉኝ አልደገምሁ ።

ፈሪ ካልጋ ላይ ይወድቃል ።

ፈሪ የሚያባርረው ሳይኖር ይሸሻል ።

ፈሪ የናቱ ልጅ ነው ።

ፈሪ ፈራና እጉድባ ቢገኝ ፤ ጀሮውን በላው ያይጥ ቀበኛ ።

ፈሪና ንፉግ እያደር ይቆጨዋል ።

ፈሪን በውሃ ውስጥ ያልበዋል ።

ፈርተው ድንጋይ ቢጥሉ ፣ ጅብ ወጣ ከዱሩ ።

ፈስ ያለበት ቂጥ ዝላይ አይችልም ።

ፈትል ሲረዳዳ ፣ አንበሳ ያስቀራል ።

ፈጅቶ ከሚያጠግበኝ ፣ አስቲበርድ ይራበኝ ።

ፈጣሪን የሚያህል ጌታ ፣ ርስትን ያህል ቦታ ።

ፈጥነው የገመዱት ፣ ፈጥኖ ይበጠሳል ።

ፈጥኖ መስጠት ፣ ሁዋላ ለመፀፀት ።

ፈጭታ የነበረች ፣ ላመልማሎ ኮራች ።

ፉት ቢሉት ጭልጥ ።

ፊተኛው ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ ፤ ምነው? ሁዋለኛው እንዳይሸሽ ።

ፊት የተናገረን ሰው ይጠላው ፣ ፊት የደረሰን ወፍ ይበላው ።

ፊት የወጣን ጆሮ ፣ ሁዋላ የበቀለ ቀንድ በለጠው ።

ፊት ያሞጠሙጧል ፣ ሁዋላ ይስሟል ።

ፊት ያሞጠሙጧል ፣ ሁዋላ ያፏጯል ።

ፊት ጆሮ ይፈጠራል ፣ ሁዋላ ቀንድ ይብቅላል ።

ፋሲል ሲፈርስ ፣ ጎንደር ይታረስ ።

ፋሲካ የሌለው ጠም ፣ ደስታ የሌለው አለም ።

ፋሲካን ሊያገኙ ፣ ሁዳዴን ይመኙ ።

ፋቂ ቁርበቱን ፣ አናጢ እንጨቱን ።

ፌቆ ስትዘል ፣ አትፈራ ገደል ።

ፊንጣ ብትቆጣ ፥ አንድ እግሯን ታጣ ።

ፊንጣ ብትቆጣ ፥ እግሯን ጥላ ሄደች ።

ፍረድ ለነፍስህ ፥ ብላ ለከርስህ ።

ፍሬ ለመብል ፥ ስንቅ ባገልግል ።

ፍርዱ ገምዳይ ፥ እውነት አጉዳይ ።

ፍርድ ለልጅ ፥ ጥራቢ ለደጅ ።

ፍርድ ለተቀማጭ ፥ ወጥ ለቀላዋጭ ።

ፍርድ አያውቅ ዳኛ ፥ ተገን አያውቅ እረኛ ።

ፍርድ እንደ አሉላ ፥ ፅድቅ እንደ ላሊበላ ።

ፍርድ ጎደለ ፥ ድሃ ተበደለ የሚል ንጉስ አይታጣ ።

ፍርድና ፍትፍት ፥ በየፊት ።

ፍርድና ፍትፍት ፥ ወደፊት ።

ፍቅር ሲጠና ቀሎ ያጓርሳል ።

ፍቅር ያሰራል ፥ እውቀት ያስከብራል ፥ ጥበብ ያኮራል ።

ፍቅርህን የፈለገ ፥ ልጅህን ፤ ጥልህን የፈለገ ፥ የላም ልጅህን ።

ፍትፍት ለልጅ ፥ ጥራጊ ለደጅ ።

ፍንክች ፥ ያባ ቢላዋ ልጅ ።

ፍንጥር ፍንጥር እንደ ሽምብራ ፥ ያባ ምንይዋብ ፉከራ ።

ፍየል ሁለት ወልዳ አንዱ ለመፅሃፍ ፥ አንዱ ለወናፍ ።

ፍየል ሳምስት ፥ ዶሮ ለባልና ሚስት ።

ፍየል መንታ ትወልድና አንዱ ለወናፍ ፥ አንዱ ለመፅሃፍ ።

ፍየል በልታ ፥ በበግ አበሰች ።

ፍየል ከመድረኳ ፣ ቅጠል መበጠሷ ።

ፍየል ወዲህ ፣ ቅምዝምዝ ወዲያ ።

ፍየል የለኝ ፣ ከነብር ምን አጣላኝ ።

ፍየልና ቀበሮ ፣ ምጥማጥና ዶሮ ።

ፍየሏን እንደ በግ ።

ፍዳ ለሀጥአን ፣ እሴት ለፃድቃን ።

ፍጥም አያናግር ፣ የጎርፍ ሙላት አያሻግር ።

ፍጥም አፍራሽ ፣ ቤተክርስቲያን ተኳሽ ።

ፍጥም ያቆማል ፣ እርቅ ይጠቀልላል ።

ፍጥም ያውላል ፣ አቧራ ያስላል ።

ፎክሮ መሸሽ ፣ ታሪክ ያበላሽ ።

# የቃላት መፍቻ

(ቃሉ የሚገኝበት ገፅ እጎኑ ይገኛል)

ሁዳድ 24,196 — ሰፊ እርሻ

ላዋይ 27 — በእንስት ፆታ የምትጠራ የቤት ውስጥ ቆሌ

ላዳን 76 — ከቁና የሚበልጥ የእህል መስፈሪያ

ልቅ 82 — ልቃቂት

ልበ ሳንባ 36 — በደረቱ አካባቢ ቀይ የሆነ

ልባልባ 36,52 — ጌጠኛ የሴቶች ሱሪ

ለኮ 30 — የፈረስ ፣ የበቅሎ መሳቢያ ጠፍር

መልከኛ 39,102,121,144
145,221 — በዱሮ ጊዜ ንጉስ ርስት እየሰጠ የተከለውና
ከቀን ብዛት እንደ ባላባት የተቆጠረ

መቀናጆ 39,175 — በወንፈል የመጣ በሬ

መቃን 41, — በቤት በር ግራና ቀኝ ያለ አራት ማእዘን እን
ጨት

መቋደሻ 96 — ቁርስ

መበለት 41,96,140,158,178
218,231 — መነኩሲት ፣ እማሆይ ፣ አሮጊት

መናጆ 42 — ተከታይ

መናፍቅ 141,211 — ተጠራጣሪ (ለሃይማኖት)

መን 69 — ሸማ መስሪያ እቃ

መንጓላ 145 — ንፍጣም

መዘለፊያ 176 — ጥልቆ ፣ እነስተኛ መጥረቢያ

መዳሮ 127 — ድር ማድሪያ

መጋዞ 121 — የምርቱን ውጤት ከባለ መሬቱ ጋር ለመካፈል
አራሹ የሚያደርገው ስምምነት

መጋገር 251 — የጭነት ፈረስ

መግላሊት 171 — የማሰሮ መክደኛ

መጭ 40 — ኑግ የሚመስል አረም ።

ሙሬ 56 — የወፍጮ መጥረጊያ

| | | |
|---|---|---|
| ሙር 200 | — | በእውቀት ብዛት እንደ እብድ የተቆጠረ |
| ሙተራ 219 | — | በጎጃም ውስጥ ያለ ተራራ |
| ሙሴ 224 | — | የማህበር አለቃ |
| ማህሌት 68 | — | በክብሮና በፅናፅል እየታጀበ የሚቀርብ መንፈሳዊ መዝሙር |
| ማህደረ ማርያም 124 | — | በጎንደር ያለ ደብር |
| ማርያም ውሃ 124 | — | በጎንደር ያለ ቀበሌ |
| ማቅ 45,108,212 | — | ከበግ ፀጉር እንደ ብርድ ልብስ ሆኖ የሚሰራ |
| ማቶት 152,245 | — | ከሳር ከልጥ የሚሰራ የእንስራ ወይም የጋን ማስቀመጫ |
| ማዘንት 91 | — | በምድጃ ዙሪያ በጭቃና በድንጋይ የሚሰራ የወጥ እቃ ማስቀመጫ |
| ሜሮን 189 | — | ቅብአ ቅዱስ |
| ምርቅ 47,92,121,128 | — | እንደ ገብስና ስንዴ ባሉ እህሎች ላይ ያለ ሻካራ ቀጫጭን እሾህ |
| ምስለኔ 34,47 | — | በፊውዳሉ ስርአት የነበረ ሹም |
| ምንደኛ 189 | — | በሰው ቤት ተቀጥሮ የሚሰራ እረኛ |
| ምዝግዝግ 231 | — | የተወረወረ ፡ የተምዘገዘገ ዱላ ፡ ዘንግ |
| ሞረት 44 | — | በመርሃ ቤቴ የሚገኝ የሃገር ስም |
| ረጃት 108,219 | — | ከዘር ለልጅ ያለፈ ገንዘብ ወይም ቅርስ |
| ረጋ 34 | — | ከትውልድ ያገኘው ሳይሆን ከሽክላ ሰሪዎች በመማር ሸክላን ወይም ብረትን የሚሰራ |
| ርቦ 66,78 | — | አንድ አራተኛ |
| ሮቃ 53 | — | የብርብራ አይነት ዛፍ ፍሬው ሲበሉት የሚሆመጥጥ |
| ሰርተት 118 | — | ጎተት |
| ሰሳ 138,164 | — | ፍየል የሚመስል የዱር አውሬ |
| ሰናፊል 226 | — | የድሮ ዘመን ሱሪ ፡ ቦላሌ ፡ ተነፋነፍ |
| ሰግዳጻ 95,148 | — | ሰዋራ ድብቅ ስፍራ |
| ሱፋጭ 46 | — | ስለታም ድንጋይ |
| ሲላ 200,251 | — | ያሞራ ስም |

ሲቀጣጠብዋት 232 — ሲያላግጡባት ፤ ሲያታልሏት

ሳታት 62 — የሌሊት ፀሎት

ስሉስ 36 — ሶስት ምስክር

ስማርድ 83 — የነብር ወጥመድ

ስንቆ 41 — በክረምት የሚበቅል የጎመን አይነት ቅጠል

ስብቆ 135 — የእጅ አጥሚት

ሶማያ 249,251 — የጦር እጀታ

ሾላ ሚዳ 109 — ባይፋት ክፍል ያለ ቀበሌ

ሾተል 37,38,71,200 — በሁለት ወገን ስለት ያለው ቀጪን ሰይፍ

ቀርቀሬ 71 — ቆላማ የሆነ ቦታ

ቀርበቦ 127 — ከበሬ ግንባር ቆዳ በጋን ቂጥ የተበጀ ሚዛን ፤ ቁና

ቀብቅቦ 145 — የእርሻ መሬትን አለስልሶ

ቀነቀነ 30 — ዘፈነ

ቀንጠፋ 108 — ልብስ የሚቀድ በጫካ ውስጥ የሚገኝ እሾህ

ቀየዷት 134 — የበቅሎን ፊት እግርና ሁዋላ እግር ወይም ፊት እግርና አንገት ማሰር

ቀጠነኝ 86 — ፍርድ ተዛባብኝ

ቀጠና 127,219 — ረሃብ ችግር

ቁልቢጥ 73 — ትንሽ ቁና

ቁረንጮ 137,140 — የቆዳ ብጫቂ

ቁርፍርፌ 148 — ስንጥቅጥቅ

ቁግ 145 — ከጅማትና ኪቃጫ የሚሰራ የጅራፍ ጫፍ

ቃጢ 207 — በጣም ትንሽ የሆነች ቁና

ቅሃ 204 — በጎንደር ያለ ወንዝ ስም

ቅንብቢት 44 — በቡልጋ አጠገብ ያለ ቀበሌ

ቅንብቻ 192 — የተረሳና ትርፍ እቃ ማስቀመጫ ፤ ከቆዳ የተሰፋ መናኛ ኮርጆ ፤ አፈ ክፍት ስፌት

ቆረን 251 — አዝመራ የታጨደበት ማሳ

ቆርቶ 66 — በጥቶ ፩ ፈንክቶ

ቋያ 142,184,221 — የበረሃ ሳር ሳይታጨድ ቆይቶ የደረቀ

በለጠብ 98 — በትንሽ መስፈሪያ (የቅቤ ቅል መክደኛ)

በመረገድ 106 — በማህሌት

ቡላድ 142 — ሲፋጭ እሳት የሚወጣው ብርጭቆ መሳይ ድንጋይ

ቡሌ 161 — ዳላቻ መልክ ያለው የከብት ስም

ቢዛቁን 108,215 — ድቁና ቢቀበል ፣ ቢለፋ ፣ ቢደክም

ቢያረምም 59 — ዝም ቢል

ባጥ 209 — ጣራ

ብር 210,230 — የገብስ ወይም የስንዴ አገዳ

ብርብሬ 73 — ፍሬው እሳ የሚያስከር የዛፍ አይነት

ብሳና 44,164,213 — በወይና ደጋ የሚበቅል ነቀዛም እንጨት

ብስና 145,152,231 — መጥፎ ጠረን ያለው ግሳት

ብየኛ 148 — በካሳ የሌላውን ገንዘብ የበላ

ቦራ 186 — ቢጫነት ያለው በሬ

ቦና 41 — ድርቅ

ቦቃ 251 — ግንባረ ነጭ በሬ

ቦዝ 34,38 — ዝንጉ የተናቀ

ቧጋች 95,194 — ውድማ ለውድማ እየዞረ የሚለምን

ተሟረ 194 — ሲያውቅ አበድ

ተታታ 195 — ተጎነጎነ

ተጠማኝ 98 — የሰው መሬት አራሽ

ታርጣጣ 37 — ሰነፍ ውዝፍ ሴት ከተቀመጠችበት የማትነሳ

ትፋዘዥ 133 — ትፋጠጪ

ቶፋ 100 — ወኪል ፣ ገባሪ

ነቁ 165 — የውሃ ጉድጓድ

ነዳይ 27 — ድሃ (ምስኪን)

ነጠር 90 — ነፍስ ወከፍ

ንዳማ 105 — ቁጭት

አለብላቢት 62 — ሲነኩት የሚያቃጥል ቅጠል

አላል 144 — የጭነት ማስተካከያ ፣ ተጨማሪ ጭነት፣መጣያ

አሜኬላ 31 — የእሾህ አይነት

አምበራስ 143 — ያምባ ሹም ዋና ግንባር ቀደም

አምዛ 151 — ወፍራም የጤፍ እንጀራ

አራድማ 48 — በመንዝ ውስጥ ያለ አገር

አሰድ 112 — የኮከብ ስም በእሳት የሚመሰል

አሳጅ 200 — የጎን ስጋ

አሸን 203 — ክረምት አግቢ

አሸከት 32 — ሻካራ ፣ ቁርንድድ

አቃቢት 54,113 — ግብር የምትፈጭ መነኩሲት

አቃቤ 159 — ዘበኛ ፣ ጠባቂ

አቢላማ 26,85 — ላም ጠባቂ እረኛ

አባሎ 198 — ለጠላና ለወተት እቃ ማጠኛ የሚሆን የዛፍ አይነት

አባ ምንይዋብ 255 — በአጤ ምኒሊክ ጊዜ የነበሩ ጨዋታ አዋቂ ሰው

አብርጣም 80 — ሹርባ

አብሾ 184 — ወፈፍ የሚያደርግ አብሽ መሳይ ፍሬ

አብቼ 44 — በምእራብ ሸዋ ያለ ቀበሌ

አትቀታተር 95 — አትጩካኰር

አንቃ 116 — ሙጫው እንደ እጣን የሚሸት የዛፍ አይነት

አንጋዳ 139,198 — ጠመዝማዛ

አንጣሪያ 119 — መሬት ለመሬት እያደገ የሚዘምት ቅጠል

አዘዞ 120 — በጎንደር ውስጥ ያለ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም

አጉራ 90 — የበረት መዝጊያ

አግሬ 120 — ትልቅ ጋሻ

አጎዶ 127 — የከሰል ጉድጓድ

አጣሪ 97,107,124 — ቸርቻሪ ነጋዴ

አፅቅ 165 — የአበባ አንጓ

አፈላማ 147 — ከብት አዝመራ ሲበላ የሚከፈል እዳ

አፍላል 151 — ከሸክላ የሚሰራ ማሰሮ መሳይ ድስት

አፎት 37,71,102,138 — የሰይፍ የጎራዴ መከተቻ ፣ ቤት ፣ ሰገባ

እመ 113 — እማሆይ

እርከፍከፎ 75 — ካፊያ

እርኮት 141 — ከቆዳ የተሰራ የውሃ መያዣ

እርያ 129,201 — በዱር የሚኖር ያሳማ አይነት አውሬ

እቡይ 200 — ትእቢተኛ

እናርያ 245 — የቀድሞው የኢትዮጵያ ደቡብ ምእራብ ግዛት መጠሪያ ስም ፣ በወላይታ ፣ በሲዳሞ ፣ በኩሎ ፣ በኮንታ የሚኖር ነገድ

እንበለ (ግእዝ) 133 — ያለ

እንባሮ 124,170,210 — የእንጨት አይነት

እከት 108 — ቅራቅንበ እቃ

እይር 249 — ቅልቅል

ከርከሬሻ 223 — ፍጅት ፤ ጠብ

ከፈር 179 — እንቅብ

ኩርዲዳ 220 — ብርቱ አራዊት ገሪ

ኩተት 150 — ቁንጮ

ካምሱር 89 — በጦር መሳሪያ ውስጥ ክብሪታዊ ባህርይ ያለ ውና ቃታው ሲወጋው ጥይቱን የሚያቀጣ ጥል አካል ።

ካይላ 190 — በጎንደር የሚገኝ ነገድ

ኮሸሽላ 75 — በወይና ደጋ የሚበቅል እሾህማ እንጨት

ኳደሬ 65,158 — ገባርን እያዘዘ ስራ የሚያሰራ ሹም

ወለባ 29,36,52,158 — በወይዛዝርና በመኳንንት ፀጉር ላይ የሚሰካ የራስ ጌጥ

ወለፈንድ 202 — ጠማማ

ወሶ 34 — ጎሽ ፣ እሰይ

ወቄራ 37 — ጩቤ

ወባራ 136,172,192 — ቀበጠ

ወታቦ 127,232 — ከእበትና ካመድ የተሰራ ጎድጓዳ እቃ

ወንጋራ 208 — ወልጋዳ

ወንጠፍት 243 — የጠላ የቅቤና የዘይት ማጥለያ ወንፊት

ወንጭት 97 — በደራና በመርሃቤቴ መሃከል ያለ ጅረት

ወዘት 41,74 — እሳት አጠገብ መቀመጥ

ወይኖ 161 — የወይንማ በሬ ስም

ወደረ 124 — ጥርቅም አርጎ ያዘ

ወጀድ 70 — የአትክልት ስፍራ፣ባጥር በቅጥር የተከበበ ቦታ

ወጋሪ 112 — አሳን ወርውሮ በድንጋይ ላይ የሚከሰከስ

ወጭት 97,163,212 — ጣባ

ዋልድባ 118 — በጎንደር ውስጥ ያለ ታላቅ ገዳም

ዋቢ 164 — ሰጪ ፣ አቀባይ

ዋንዛ 164 — ፍሬው የሚበላ እንጨቱ የማይነቅዝ ዛፍ

ዋግ 67,158 — የሰብል በሽታ

ውኸርምኸርም 186 — ረኸርም ፣ ጎታታ

ውኸርሞ 80 — ውስጠ ክፍት እንጨት ወይም መቃ ለጋያ መጠጫ የሚሆን

ዘለሳ 173 — ቁጥቋጠ ምልመላ

ዘማ 200,205 — አመንዝራ

ዘባን 171 — ጀርባ

ዘባጣ 37,231 — ረባዳ ቦታ

ዛብ 170,173 — ለፈረስ ለበቅሎ እንደ ልጓም ሆኖ የሚገታ

ዝማሚ 30 — በመቋሚያ እየተወዛወዙ የሚዘመር መንፈሳዊ መዝሙር

ዝባድ 170 — ጥሪኝ ከምትባል አውሬ የሚገኝ የሽቱ ቅባት

| | | |
|---|---|---|
| ዞላ 203 | — | ሰነፍ |
| ይብራ 225 | — | ውሃ ውስጥ ጠልቃ የምትወጣ እግረ ቀይ መልከ ብዙ የውሃ ዶሮ |
| ይቶት 31 | — | መነኩሲት ፤ እማሆይ |
| ይክርታል 101 | — | ይጎራል |
| ይዋጁ 61,89,154 | — | ይገዙ |
| ይጋጃል 192 | — | ይበላሻል |
| ደለማ 63 | — | ጨለማ ፤ ሰዋራ |
| ደልሰ 91 | — | በለፀገ |
| ደረባ 215 | — | የጎተራ ጣራ |
| ደረጣ 34 | — | ሁከት |
| ደራል 144 | — | የእንጨት አይነት |
| ደባይ 142 | — | ሰፊ ነጋሪት |
| ደንካራ 145 | — | ደካማ ፤ አላዋቂ |
| ዳሞትራ 144 | — | የሚናደፍ ጥቁር መርዘኛ ሸረሪት |
| ዳንዴ 201 | — | ቀማኛ |
| ዳወሮ 137 | — | የቀድሞ ሃረርጌ ስም |
| ዳፋ 172 | — | ጠንቅ |
| ድርጎ 231 | — | ጉርሻ |
| ድርጭት 149,231 | — | ከርግብ የሚያንስ ወፍ |
| ድበላ 231 | — | ባቄላ ፤ አተር ፤ ምስር ፤ ከገብስና ስንዴ ቅል ቅል የሚጋገር እንጀራ |
| ድጉስ 66,226 | — | ማህደር ፤ አፎት |
| ዶሰኛ 191 | — | ሃይለኛ |
| ዶባ 68 | — | የበረሃ ቀንደ ረዥም በሬ |
| ዶጮ 74 | — | ከገንቦ የሚያንስ የሸክላ እቃ ፡ የጠጅ የጠላ ፡ የውሃ ማኖሪያ |
| ጀላፋ 188 | — | ሰነፍ |
| ጀንፎ 168 | — | በዘንግ ጫፍ ላይ የሚሰካ ጥምጥም ብረት |

ጀጀባ 199 — በወንዝ ዳር የሚበቅል ፍሬው የሚበላ ዛፍ

ጀኖ 159 — በስፌ ቀይ ጥለት የተሰራ ዝቅዝቅ ልብስ

ገለፈንት 235 — በሆነው ባልሆነው የምትስቅ

ጉልላት 37,91 — በዘውድና በአክሊል ምሳሌ የተሰራ ሸክላ ፣ በድንኳን በቤተክርስቲያን ጫፍ የሚሰካ

ጉልማ 121 — ላሽከር፣ለሎሌ፣ለዘመድ፣ለወዳጅ ተከፍሎ የተ ሰጠ ማሳ

ጉጣ 62 — የማረሻ እላቂ

ጊጉይ 180 — አመፀኛ ወንጀለኛ

ጋት 68 — ውስጥ እጅ ፣ መዳፍ

ጋይ 240 — አፈሩን በማቃጠል የሚደረግ ባህላዊ የእርሻ ማዳበሪያ

ጋፍ 194 — ሞኝ

ጌኛ 44,166 — መጋዣ ፈረስ

ግልምቢጥ 168 — የተገላቢጦሽ

ግጫ 156 — የሳር አይነት

ጎታ 215,228,247 — ከመቃ ወይም ከቀርከሀ እንደ ቅርጫት የተጎነጎነ የእህል ማስቀመጫ

ጎዳ 73,144,186,244 — የተጎዳ ፣ ቀላሳ ከብት ፣ ዱልዱም

ጎንጅ 36 — በጎጃም የሚገኝ የታወቀ የቅኔ ትምህርት ቤት

ጎፍላ 35 — መርገፍ ፤ ጌጥ

ጠራቂ 102,155 — በያጅ ፤ ብረት አልባሽ

ጠገራ 72 — በራሳም እንጨት ቀዳዳ የተዋደደ መፍለጫ

ጥቅንጥቅ 101 — ውስብስብ

ጥንቅል 22 — ቁንጣሪ

ጨንቋራ ,199,222 — ሸውራራ

ጩንገር 250 — የዛር ስም

ጭራንጮ 222 — የጭራሮ ጫፍ

ጭሬ 250 — ቅጠሉ ጠባብ ጦር

ጭቃ 34,85, — ቀደም ሲል የነበረ የሹመት አይነት የቀበሌ ሹም

ፈርዛዛ 127,159,199 — ደስተኛ

ፈግጡት 90 — ተዉት

ፈጠም 187,195,256 — የነገር መግቻ

ፈፋ 31 — የውሃ መውረጃ

ፋቅራ 180 — የእስላም ቃልቻ

ፈራ 206 — ወረርሽኝ ፥ ተላላፊ የተስቦ በሽታ

ፈቆ 135,254 — የሰስና የሚዳቋ አይነት የዱር ፍየል

ፍንጅ 126,129,247 — እንደ ካቴና ያለ የእጅ ማሰሪያ

ፎገራ 26 — በጎንደር ያለ ቀበሌ